# ምዕራፍ ሃያ ሶስት

# በኢሊባቡርና በከፋ የተካሄደው ትግል

በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ የተመራው የኢትዮጵያ ሠራዊት ከሽሬ ጦርነት በኋላ በጐንደርና በጐጃም አድርጐ ዓባይን በመሻገር በወለጋ በኩል ኢሊባቡር፣ ጐሬ ገባ። ጦሩ ይህንን ያደረገው መንግሥቱ ወደ ጐሬ ተዛውሮ ጦርነቱ በመንግሥት ደረጃ እንዲቀጥል ታቅዶ የነበረውን ሐሳብ በመከተል ነበር። ነገር ግን ንጉሠ ነገሥቱ ባልታሰበ ሁኔታ ትተው ወደ አውሮፓ በመሄዳቸው ይህ ዕቅድ ወደቀ።[1]

በራስ እምሩ የሚመራው ቡድን ከአድካሚ ጉዞ በኋላ ጐሬ ሲገባ፣ ጉስታፍ ሮዘን የተባሉት ኢትዮጵያን የሚወዱ የስዊድን መሥፍንም በአይሮፕላን ጎሬ ገቡ። ነገር ግን በአዛዥ ወልደ ፃድቅ መሪነት ወደ ጎሬ ተዛውሮ ጦርነቱ እንዲቀጥል የተሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ማድረግ ስለአልተቻለ፣ ሌላ አዲስ መመሪያ ከንጉሠ ነገሥቱ፣ ከለንደን ተጠበቀ። የተላለፈው መመሪያ የተፃፈው ሐምሌ 12 ቀን 1928 ዓ.ም ሲሆን፣ የተላከውም በእነ ልጅ ፈቃደ ሥላሴ ኅሩይና በእነ ብንያም ነበር። እሱውም የእንደራሴ ሥልጣን የሚሠጥ፣ ቢትወደድ ወልደ ፃድቅን ጠቅላይ ሚኒስትር የሚያደርግና 12 ሚኒስትሮች እንዲሾሙ የሚፈቅድ ነበር።[2]

ሁኔታው በዚህ ዓይነት በእንጥልጥል እንደአለ የራስ እምሩን ጎሬ መግባት የሰማው የጥቁር አንበሳ ጦር ገስግሶ በጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም ጎሬ ደረሰ። በነባሩ የራስ እምሩ ጦር ላይ ይህ አዲስ የተማሩ ወጣቶችን ያቀፈ ቡድን ሲቀላቀል ጦሩ፣ አዲስ ስሜት አደረበት። አዲስ አበባን ለማጥቃት አሰበ። ጦሩ ከጐሬ ተነስቶ በወለጋ በኩል ወደ አዲስ አበባ አመራ። ራስ እምሩም በጉስታ ቮን ሮዛን አይሮፕላን ወደ ሱዳን ለመሄድ ሲችሉ የሠራዊቱን ጥያቄ ተቀብለው በመሪነት ቆሙ። ምክር ተደርጐ አዲስ የጦር ዕቅድ ተሠራ። እቅዱም፡- 1ኛ/ ራስ እምሩ በነበራቸው ጦር ላይ የጥቁር አንበሳን ሠራዊት ጨምረው እየመሩ በወለጋ በኩል ወደ አምቦ ሊጓዙ። 2ኛ/ በወቅቱ በጎሬ ከተማ የነበሩት ቢትወደድ ወልደፃድቅ በዚያ የነበረውን ሠራዊት ይዘው በጂማ በኩል እስከ ወሊሶ ድረስ ሊመጡ ሲሆን፤ ዓላማው አዲስ አበባን ከብቦ ጠላትን መድረሻ ማሳጣት ነበር። ሻለቃ በልሁ በስደት ሔደውበት ከነበረው ከካርቱም ተመልሰው በጋምቤላ በኩል በመግባት ከዚህ ጦር ጋር ተሰልፈው ነበር።

ነገር ግን የራስ እምሩን ጦር አመጣጥ የጠላት ጦር አስቀድሞ ሰምቶ ኖሮ፣ ጉዴ ከተባለው ቦታ ጦርነት ገጠማቸው። የኢትዮጵያ ጦር በልቡ እየተሳበ፣ በጉምብስ እየከበበ ከምሽጉ ከተጠጋ በኋላ፣ በሕብረት ከምሽጉ ዘልሎ በመግባት የጠላትን ወታደር በጠመንጃ፣ በሳንጃ፣ በጩቤ፣ በጐራዴ፤ ባጭሩ



በያዘው ሁሉ መሣሪያ ወጋው። የአንድ ቀን እረፍት ከተደረገ በኋላም ምክር ተጀመረ። አንዱ ክፍል በቀድሞው ሐሳባችን ፀንተን ወደ አምቦ እንቀጥል ሲል፣ ሌላው ቡድን መንገዳችንን ለውጠን ወደ ጂማ እንሂድ አለ። አዲስ አበባን ለማጥቃትና መልሶ ለመያዝ የታሰበው ሕልም መሆኑ ስለ ታመነበት፣ ወደ ጂማ እንሂድ የሚለው ሀሳብ የድምፅ ብልጫ ስላገኘ ወደ ጂማ ለመሄድ ተወሰነ።

ጦሩ በውሣኔው መሠረት ከወለጋ ወደ ጂማ ተሻግሮ በደሌ ገባ። ከዚያም በጉማይ በኩል አድርጐ አጋሮ ደረሰ። ጦሩ አጋሮ ሲገባ ጠላቱን ለማጥቃት የሚችል፣ ማጥቃት ባይችል ደግሞ ለመከላከል ምቹ ቦታ የሚያገኝ መስሎት ነበር። ነገር ግን እንደዚህ አልሆነም። ሦስት ጣምራ ችግሮች አጋጠሙት። ከእነዚህም አንዱ የጂማ ከተማ በጠላት መያዝ ሲሆን፣ ሁለተኛው በአካባቢው የነበረው የአማራ ሕዝብ ነፍሱን ለማዳን በዙሪያው ተሰብስቦ ሰፈረ። ሦስተኛው ደግሞ ለጠላት አይሮፕላን መጋለጡ ሆነ። እነዚህ ሁኔታዎች ጦሩን እንደምን ለመፈታት እንደአደረሱት ቀጥሎ እንመለከታለን።

የራስ እምሩን አጋሮ መግባት የሰማው የአማራ ሕዝብ ሴት ወንድ፣ ልጅ አዋቂ ሳይል በዙሪያቸው ተሰባሰበ። አሰባሰቡም ነፍሱን ለማዳን ስለነበረ መላቀቅ አልተቻላቸውም። ይህም የሆነበት ምክንያት አባ ጆቢር የተባለው ባላባት ለአንድ የአማራ ጭንቅላት ሠላሣ ብር እከፍላለሁ የሚል አዋጅ ጠላትን ለማስደሰት አስወጥቶ አማራውን ያስፈጅ ስለነበር ነው። በዚህ ዓይነት ያስቆረጠውን ጭንቅላት ለጣልያን እያቀረበ ገንዘብ ይቀበልበት ስለነበር፤ አንድ ነቅሳት ያለበት የአንድ ሴት ራስ አቅርቦ ጣልያን አዋጁን በሌላ አዋጅ እስኪሽርበት ቀን ድረስ የአባ ጆቢር መመሪያ ፀንቶ ተሠርቶበታል። በዚህ አዋጅ መሠረት የስንት አማራ ራስ እንደተቆረጠ ባይታወቅም፣ በብዙ ሺህ እንደሚቆጠር ግን አላጠራጠረም።

ወደ ዋናው ታሪክ ስንመለስ ይህ ሁኔታ ከ3 ሺህ የማይበልጠውን ጦር ከብዙ ጓዝ ጋር እስከ 30 ሺህ አደረሰው። በመሆኑም ቀልጣፋነቱን ቀነሰበት፤ ኃላፊነቱን ደግሞ አከበደበት።

ጉዲ ከተባለው ቦታ ከ10 ሰዓት ጀምሮ ሌሊቱን ጭምር በመጓዝና ቀን ከጫካ ውስጥ በመደበቅ ያሳልፍ የነበረው ጦር፣ አጋሮ ከተማ ሲገባ ለጠላት አይሮፕላን ጥቃት ተጋለጠ። በዚህ ጊዜ የጠላት አይሮፕላን ከትንፋሽ ጋር ገበቶ ሳንባን እያሳበጠ የሚገድል መርዝ እረጨበት። ጦሩም የተገኘውን ጨርቅ በውሃ እየነከረ አፍና አፍንጫውን እንዲይዝ ፈጣን ትዕዛዝ ለሕዝቡ በማስተላለፍ አደጋውን ተከላከለ። ይህ በመደረጉ በሰው ላይ እምብዛም ጉዳት ሳያደርስ ቀረ።

የጂማ በጠላት እጅ መውደቅ በራስ እምሩ ለሚመራው ጦር ታላቅ ጉዳት ነበር። ሁኔታው አዲስ አበባን ለማስጨነቅ፣ ብሎም ለማስለቀቅ

የነበረውን ዓላማ ሲያፈርስበት፣ የጎሬ ከተማ ከጠላት እጅ መግባት ደግሞ የባሰ ጉዳት አመጣ። የራስ እምሩንም ጦር ወደ አንድ የጠላት ከበባ አቃረበው። ከዚህ ላይ የጎሬን ዕድል ፈንታ መመልከት ያስፈልጋል።

ጎሬ ለመከላከያ ማዕከልነት መመረጥዋ በጠላት ዘንድ የታወቀ ነበር። ስለዚህ ከአዲስ አበባ በወለጋ በኩል ገስግሶ ህዳር 17 ቀን 1929 ዓ.ም ያዛት። የራስ እምሩ ጦር ወደ ወለጋ፣ የቢትወደድ ወልደ ፃድቅ ጦር ወደ ጂማ በመንቀሳቀሱ ከተማይቱ ተከላካይ አልነበራትም። በኮሎኔል ማልታ የሚመራው ጦር ከተማይቱን ለመያዝ ሲቃረብና በዚያ የነበሩ አርበኞች ተከላክለው ማዳን አለመቻላቸውን ሲረዱ፣ ጳጳሱን ይዘው ሣንቤ ወደሚባል ቦታ ሄዱ። ሐሳባቸው ከከፋ አርበኞች ጋር ለመቀላቀል ነበር። ነገር ግን ጠላት ፈጥኖ ደረሰባቸው። ጦርነት ተደርጐ ከሁለቱም ወገን ሠላሳ፣ ሠላሳ ያህል ሰው ሞተ። የተረፉት ኢትዮጵያውያን ተማረኩ። የተማረኩትን ጣልያን ወደ ጎሬ እያንገላታ መልሶ ወስዶ የኢትዮጵያውያኑን ጳጳስ አቡነ ሚካኤልን ጭምር በአደባባይ በመትረየስ ረሸናቸው።[3] ዕድል የቀናው፣ ከምርኮ ያመለጠው የኢትዮጵያ ጦር ብቻ ወደ ከፋ ተሻግሮ ትግሉን ቀጠለ።

የጅማና የጎሬ መያዝ በራስ እምሩ የሚመራውን ጦር ሌላ መንገድ እንዲቀይስ ስለአስገደደው፣ ጦሩ ምክር አደርጐ የደጃዝማች ታዬ ጉልላት ግዛት ወደ ነበረው ወደ ከፋ ለመሄድ ወሰነ። ሐሳቡም ነፍሱን በዛ ለማዳንና የተሰበሰበውን ሕዝብ ወደዚያ ወስዶ የተረጋጋ ሁኔታ በመፍጠር አዲስ የጦር እቅድ ለማውጣት ሆነ። ጉዞው አስቸጋሪ ነበር። ከችግሩ አንዱ የጓዙ መብዛት ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ሀገሩ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ የተሸፈነ፣ ለብዙ ወራት ዝናባማ፣ መንገዱ ጭቃና ማጥ የበዛበት መሆኑ ነበር። በዚህ ላይ ደግሞ የጠላት እግር በእግር መከተልና የአየር ድብደባውን ማጠናከሩ፣ ጉዳት አበዛ። ቢሆንም ጦሩ ይህንን ሁሉ አበሳ ችሎ ጉዞውን ቀጠለ። ጠላት የጦሩን እንቅስቃሴ በንቃት ይጠባበቅ ነበርና ደን ከሌለበት አውላላ ሜዳ ላይ ሲደርስ በአይሮፕላን ድብደባውን ያዘ። ነገር ግን ከስድስት የጋማ ከብቶች በስተቀር ወዲያና ወዲህ ይተረማመስ ከነበረው ከዚያ ሁሉ ሰው መግደል ቀርቶ አንድ እንኳን አላቆሰለም። በዚህም ሕዝቡ በወቅቱ እግዚአብሔርን እንደ አመሰገነ የነበሩ ተናግረዋል።

በዚህ ዓይነት ጦሩ ጥቅጥቅ ባለ ጫካ ውስጥ ተጉዞ ከአንድ ገላጣ ቦታ ደረሰ። ሕዝቡ በጉዞው ርዝመትና በረሃብ ተጉድቶ ነበር። ጥቂት ጠንቃቃ ሰዎች ከያዙት ዳቦ ቆሎ፣ ቋንጣ፣ ድርቆሽ አቃመሱት። ከሰው ድካም የተነሳ በአካባቢው የነበሩትን ከብቶች አርዶ መብላት እንኳን አልተቻለም። ነገ አርደን እንበላለን በማለት በተስፋ ተኛ። ነገር ግን በማግስቱ ጥዋት ፈጽሞ ያልተጠበቀ ጦርነት አጋጠመ። እግር በእግር ይከተል የነበረው የጠላት ጦር ጌራ ላይ ደረሰበት። ምንም ድካም ቢበዛበት የኢትዮጵያ ጦር ከመጋጠም በስተቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም። የመጣው የጠላት ጦር ከወለጋ፣ ከጂማና



ከጐሬ የተጠራቀመ ነበር። የኢትዮጵያም ጦር ጓዝ ይብዛበት እንጂ በኢትዮጵያ የውጊያ ስልት የዳበረ ልምድ ያለው ዋነኛው የራስ እምሩ ሠራዊት ሲሆን፣ ሌላው ክፍል ደግሞ በዘመናዊ የጦር ትምህርት የሠለጠነው የጥቁር አንበሳ ጦር ነበር። ይህ ስመ ጥር ጦር ሠራዊት የራስ እምሩ አመራር ጥንካሬ ሰጠው። ጠላቱን ግንባር ለግንባር ገጠመው። የኢትዮጵያ ጦር በመሬት ላይ ተኝቶ፣ በየቅርንጫፉ ላይ ተንጠልጥሎ፣ በየግንዱ ላይ ተጣብቆ በጥይት ይቆላው ጀመር። የተራብ አንጀቱን አስሮ፣ ሆዱ በጥጋብ የተቀበተተውን ጠላቱን ረፈረፈው። ውጊያው ከንጋት ጀምሮ እስከ 9 ሰዓት ቆየ። ወንዙ በኢትዮጵያውያን እጅ ገባ። የኢትዮጵያ ጦር ተግባሩን የውሃ ጥማቱን አበረደ። በአንፃሩ የጠላት የውሃ መትረየሶች ውሃ በማጣት ሥራቸውን አቆሙ። አርበኞች እንደ ሥርዓታቸው ከጠላት ጋር ተቀላቅለው የጨበጣ ውጊያ አካሄዱ። የኢትዮጵያ ጦር ይህን ከሠራ በኋላ የሚደርስበትን ጉዳት ለመቀነስ ወደ እርዱ ተመለሰ። ሕዝቡ እልል በማለት ወታደሩን አጽናና።

ጦርነቱ እንደ ጠላት አመጣጥ የከፋ ሊሆን ይችል ነበር። የጥቁር አንበሳ ታሪክ ዘጋቢ አቶ ታደሰ ሜጫ እሳቸው በዋሉበት ጉራ ከጠላት ወገን ሁለት መቶ ወታደር ሞቶ ብዙ እንደቆሰለ፣ ከአርበኞቹ ወገን የሞተውም፣ የቆሰለውም ከአንድ መቶ እንደአልበለጠ ገልጸዋል። ብዙ ሰላማዊ ሰው እንደሞተና እንደቆሰለ አስረድተዋል። በሌሎች ሁለት ጉራዎች የነበረው ሁኔታም ከዚህ እምብዛም እንደማይለይ ገምተዋል። ዋናው ነገር በዚያ ውጊያ ድሉ በማያወላውል ሁኔታ የኢትዮጵያ መሆኑ ነው።

ሠራዊቱ ከጌራ ተነስቶ ጉዞውን ቀጠለ። ቀደም ብዬ እንደገለጽሁት ጦሬ ጓዝ ከብዶበታል። አሁን ደግሞ በጦርነቱ የቆሰለውና ራሱን የማይችለውን ሰው መሸከም ተጨመረበት። ጥቂት እንደተጓዘ ለሰውም፣ ለከብትም አስቸጋሪ ከሆነ ማጥ ውስጥ ገባ። በቃሬዛ ተይዘው ይጓዙ ለነበሩ ጀግኖች የአካልና የኅሊና ቁስል ሆነባቸው። በዚህም የተነሳ ከቁስለኞች አንዱ፣ ሻምበል ለማ አባየሬ "…ተራችሁ እስኪደርስ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን…" በማለት በጥቁር አንበሳ ሠራዊት ደንብ፣ ስምንተኛ ቁጥር መሠረት የተሰጠውን የመትረየስ ሽጉጥ ነቅሎ ሕይወቱን አሳለፈ።

ሠራዊቱ ወደ ጉጀብ ወንዝ ጉዞውን ቀጠለ። በጠላት የተገዙ ባላገሮች በየጫካው እየተሸጉጡ ብዙ ሴትና ሽማግሌ፣ ልጅ ገደሉ። አንዳንዶችም ስለ ወንድ ልጅ ጨርሱን እያሉ ከስቃያቸው ለማረፍ ይለምኑ ነበር። ከደጃዝማች ታዬ ጋር ተቀላቅሎ ከረሃብ ለመዳንና ትግሉንም በተጠናከረ ሁኔታ ለመቀጠል ተስፋ አድርጐ የነበረው ይህ ሠራዊት፣ ቀደም ብሎ እንዲሠፍር ምልክት ተደርጐበት ከነበረበት አንዲት ቦታ ደረሰ። አንዳንድ ጉጆዎችና የዘይት ጣሳዎች፣ ቀዳዳ የምግብ ዕቃ መያዣ ቆርቆሮዎች ወድቀው ይታዩ ነበር። ማለትም በዚያች ቦታ የጠላት ወታደር ሳያልፍ እንዳልቀረ የማያጠራጥር ሁኔታ ተስተዋለ።

ጠላት የጐጀብን ወንዝ ተሻግሮ፣ መድፍና መትረየሱን ጠምጥሞ ይጠብቅ ኖሮአል። ጦሩ ያስተናግደናል ብሎ ተስፋ የጣለባቸው ደጃዝማች ታዬ ለጠላት ገብተው ኖሯል። ሌሊቱን ወደ ሣጃ ከተማ የሚሄደውን የኢትዮጵያ ሠራዊት ጠላት ከጫካ ውስጥ እያወጣ መሣሪያውን በመቀበል ወደ ማረፊያ ቤት ሲያስገባ ስለአደረ፣ የሠራዊቱ ኃይል ተቀንሶ ኖሯል። ነገር ግን እነዚህ ሁኔታዎች በጦሩ ዘንድ አልታወቁም። ጥዋት ሲነጋ የተደራጀ የጠላት ጦር በወንዙ ማዶ እንደሚጠብቀው ሲረዳ አርበኛው አዘነ። ጦርነትና ረሃብ የመተረውን፣ የቀንና የሌሊት ጉዞ ያንገላታውን ወታደር እንደገና መልሰህ ተዋጋ ማለት ለጦር መሪዎች ከባድ ነገር ሆነባቸው። መራር ሐዘንም ተሰማቸው።

ሠራዊቱ ከድንጋጤው ሳይነቃ ሁለት የጣልያን መኰንኖች ሙሉ የጦር ልብስ እንደለበሱ በቀኛዝማች መጅድ አቡድ መሪነት ከሠፈሩ ደረሱ። ወደ ራስ እምሩም ገብተው ተነጋገሩ። ራስ እምሩ በዶክተር ዓመለወርቅ በየነ ኃላፊነት ሦስት ኢትዮጵያውያን መኰንኖች ወደ ጣልያኖቹ ሠፈር በመላክ እንዲነጋገሩ አደረጉ። ጣልያኖቹ እጅ ከመስጠት በስተቀር አንዳች ነገር አንቀበልም አሉ። ራስ እምሩ ይህንን ሲሰሙ ከጦር ሹማምንቶቻቸው ተመካክረው የተከተላቸውን ሰላማዊ ሕዝብ ሳይቀበላቸው ከጣልያን ጦር መሪ ጋር እንደማይነጋገሩ አስታወቁ። የጣልያን የጦር መሪ ጥያቄአቸውን በመቀበል ሰላማዊዉን ሕዝብ ወሰደ። ተከትሎአቸው የነበረውን ሰላማዊ ሕዝብ ከአስረከቡ በኋላ ራስ እምሩ እጅ አልሰጥም አሉ።



ጀግናው ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ

ሁኔታው በእንዲህ እንደአለ ለጣልያኑ የጦር አዛዥ በእጅ የገቡትን ሰላማውያን ሕዝብ እንዲጨርሰና የራስ እምሩን ጦር በጋዝ መርዝ እንዲያጠፋ ከግራዚያኒ ትዕዛዝ በቴሌግራም ደረሰው። የጦር አዛዡ የደረሰውን ትዕዛዝ ገልጦ የማስጠንቀቂያ ቃል ሰጠ። ቃሉም "... ሰላማዊውን ሕዝብ መረከባችን



እናንተን ስንፈልግ እንጂ፣ ሽክማችሁን በገዛ እጃችን አቃልለን እንደገና በሙሉ ኀልበት እንድታጠቁን አይደለም። ... እምቢ ብትሉ ግን የተረከብነውን ይህንን እጅግ የበዛ ሕዝብ ...ያለርህራሄ መፍጀታችን ... አሁኑኑ እወቁት..." የሚል ነበር። አያደርጉትም ተብሎ አልተጠረጠረም። ምክንያቱም ጣልያኖች ጭካኔአቸውን ቀደም ብለው በግብር አሳይተው ነበርና።

በኢትዮጵያውያን ዘንድ ምክር ተደረገ። ጠላት ጦሩ በ24 ሰዓት እጅ እንዲሰጥ ስለአዘዘ፦

1ኛ. ለሕዝቡ ሕይወት ሲባል ጦሩ እጅ እንዲሰጥ፣

2ኛ. ከጣሊያን ከድተው ከኢትዮጵያውያን ጐን ከቆሙት፣ ከሞት የተረፉት ኤርትራውያን ከጎሬ ግምጃ ቤት የተወሰደው ገንዘብና ጥሩ ጥሩ መሣሪያ ተሰጥቶአቸው እጃቸውን በፍጥነት እንዲያወጡ ተወሰነ።

ውሣኔው ለሠራዊቱ በተገለፀለት ጊዜ ከባድ ሐዘን ሆነ። ኤርትራውያኑ እንደተወሰነው ተደርጐላቸው በሽኘ እጃቸውን አወጡ። የኢትዮጵያም ሠራዊት ሌሊቱን በእጁ የሚገኘውን ጥሩ ጥሩ መሣሪያ ከጐጀብ ወንዝ ውስጥ ለቀቀው።

ይህ ሁሉ ከተደረገ በኋላ ራስ እምሩ ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ ሾ"ርኮው ሠፈር አመሩ። ሽጉጣቸውን እንደታጠቁ በበቅሎአቸው ላይ እንደተቀመጡ ነበሩ። ቀኛዝማች ደጀኔ የተባሉት የጦር መሪ ከጣልያን የጦር መኰንን የተማረከ የደንብ ልብስ ከእነ ማዕረጉ ለብሰው በሌላ በቅሎ ተቀምጠው ጌታቸውን ተከተሉ። ሠራዊቱ በክብር ከጠላት ሠፈር ገባ። ጣልያኖቹም የወገናቸውን የክብር ልብስ የለበሰ ኢትዮጵያዊ ባዩ ጊዜ ተበሳጩ።

ጦሩ እጅ ከሰጠ በኋላ የጠላና የፈራውን ውርደት ተቀበለ። ኢጣልያኖች አንድ በአንድ መሣሪያውን ገፈፉት። ቀኛዝማች ደጀኔ ያንን የኢጣልያዊ መኰንን የክብር የጦር ልብስ ከየት እንደ አመጡት ጠየቃቸው። እሳቸውም በሞታቸው ቆርጠው በግድ የለሽነት በታላቁ የሰሜን ጦርነት ላይ እንደማረኩት ነገሩት። እሱም ሰውየውን ወዴት እንደአደረሱት መልሶ ጠየቃቸው። አጥብቆ ጠያቂ እናቱን ይረዳል እንዲሉ "...እሱን ገድዬ መሣሪያውን ገፈፍኩት። ልብሱንም ይኸው እንደምታየው ለበስኩት..." አሉት። በማናቸውም ጊዜ ቢሆን ሀገራቸውን በሚመለከት ጉዳይ ሁሉ መሥዋዕት ለመሆን ዝግጁ ነበሩና። እሱም ለጊዜው ምንም አላደረጋቸውም።

የኢትዮጵያ ጦር ከተማረከበት ከጐጀብ ወደ ቦንጋ ከተማ በትካዜና በሐዘን ጉዞውን ቀጠለ። ጀሌውን ስለነበረ፣ ከግል ዕቃው በስተቀር ሌላ ሸክም አልነበረበትም። ነገር ግን ሁኔታው ከድንጋይ የሚከብድ እንደ ነበር በሕይወት የተረፉ መሥክረዋል። አንዳንድ የጠላት ወታደሮች ወንድሞቻችንን የፈጁብን



ጀግናው ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ

እነዚህ ናቸው እያሉ በሰደፍና በአለንጋ ይመቱታል። ምርኮኛው በዚህ ዓይነት የመከራ ጉዞውን ቀጥሎ በሁለተኛው ቀን ቦንጋ ገባ።

በዛ ራስ እምሩ ከጦራቸው ተለይተው በጥንቃቄ ከሚጠበቁበት ቦታ ተቀመጡ። ጦራቸው የግዞት ቦታ ተመራና የጦር መሪውን ድንኳን ከብቦ ሠፈረ። ሠፈሩን ጠላት በመትረየስና በመድፍ ዙሪያውን አጠረው። ራስ እምሩን ወደ አዲስ አበባ የሚያወጣ አይሮፕላን የሚያርፍበት ሜዳ ዝግጅት ተካሄደ። ጣልያን አገሬውን እያስገደደ ደኑን ያስመነጥር፣ አባጣ ጉባጣውን ያስደለድል ነበር።

ሜዳው ተደልድሎ ሲያልቅ የጣልያን አይሮፕላኖች መጥተው አረፉ። በአንዲት ትንሽ ከተማ እየኖሩ እርስበርሳቸው እንዳይገናኙ ተከልክለው የቆዩት ራስ እምሩና የደጃዝማች ታየ ጉልላቴ ተገናኙ። በጣልያኖች ዘንድ ሁለቱም የቅኝ ግዛት ዜጐች ነበሩ። ልዩነታቸው አንዱ በጦር ሜዳ የተማረከ፣ ሌላው ወድዶ የገባ መሆናቸው ብቻ ነበር። ራስ እምሩንና ደጃዝማች ታዬ ጉልላቴን የያዙት አይሮፕላኖች አኮብኩበው በመነሳት ወደ አዲስ አበባ በረሩ። የኢትዮጵያ ጦርም ወደ ኋላ ተመልሶ ረጅም የምርኮኝነት ጉዞውን ወደ ጂማ፣ ከዚያም ወደ አዲስ አበባ ቀጠለ።[4]

በራስ እምሩ የሚመራው ጦር ቢማረክም፣ ጦርነቱ ግን አልቆመም። በፊታውራሪ ደበበ የሚመራ ሌላ የአርበኛ ቡድን ሦስት መዓልትና ሦስት ሌሊት ከተዋጋ በኋላ ሸዋ ጊሚራን በከፊል በቁጥጥሩ ሥር አደረገ። በየካቲት 1931 ዓ.ም የተላለፈ አንድ ሌላ ሪፖርት ደግሞ በጂማና በከፋ ብዙ መሣሪያ የታጠቁና በጣም የደረጁ አርበኞች እንደነበሩ ያስረዳል። ብዙ ነጭ ጣልያናውያን ወታደሮችም እንደሚዋጉአቸው ይገልፃል። ምርከኞቹ ከቦታው ከመነሳታቸው በፊት እንኩዋን ሦስት ጣልያናውያን ከጂማ ከተማ ወጥተው ከአርበኞቹ ጋር መቀላቀላቸውንና ያልታደሉ ሦስት ሌሎች ደግሞ ከአርበኞቹ ጋር ከመቀላቀላቸው በፊት መያዛቸውን ያረጋግጣል።[5]

በዛ አካባቢ ለጊዜው ድል የቀናው የጣልያን ጦር ወደ ከፋ ሲሻገር የጉራጌ አገርና የጂባት አርበኛ ኖኖ በተር በተባለው ቦታ ቀደም ብሎ በተደረገው ስምምነት መሠረት ተባብሮ እየተከተለ ወጋው። በሸዋና በከፋ ድንበር ላይ የምትገኘውን የእበልቲን ምሽግ አስለቀቀው። ከሞት የተረፉትን 17 ጣልያናውያን ከአርባ መትረየስና ከብዙ ጠመንጃ ጋር ማረካቸው። በአረንገማ ምሽግ የነበረውን የጠላት ጦር በመዓልትና በሌሊት ለሁለት ቀን ወግቶ ወደ ጢሮ አባረረው። ተከታትሎ ጢሮ በመድረስ ከብቦ ለሁለት ቀን እንደተዋጋ ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ መግባታቸው ተሰማ። ወዲያውም ንጉሠ ነገሥቱ ኖኖ ግሼ ድረስ ሄደው ስለጉበኙት አርበኛው ኃይል ተሰምቶት የሚሸሸውን የጣልያን ጦር ጠልጋ ኖኖ፣ ለሙ ሰቃና ለሙ ካሣ በተባሉ ቦታዎች ላይ ታላላቅ ውጊያዎች በማድረግ ደምስሶ ጂማ ደረሰ።



ጂማ፣ የኦሮሞ-ሲዳማ ክፍለ ሀገር ዋና ከተማ ስለነበረች፣ ከፍተኛ የጠላት ክምችት እዛ ነበር። በዚህ ላይ ከጉጃም በጉሐ ጽዮን፣ በገዳ በኩል ሠብሮ የገባው ጦር ብዙ ስለነበር፣ ከተማይቱ የምትያዝበትን መንገድ በልዩ ዘዴ መቀየስ አስፈለገ። መጀመሪያ ከተማይቱ ከተከበበች በኋላ ምክር ተደርጐ ከፊታውራሪ ገረሱ ዱኪና ከልጅ ጃገማ ኬሎ የተውጣጣ ቡድን ቀደም ብለው ከተማረኩት ጣልያናውያን መካከል የተወሰኑ ሰዎችን ይዞ ንግግር እንዲያደርግ ተወሰነ። ቡድኑም በስምምነቱ መሠረት ተመርጦ ጂማ ከተማ ገባ። የጂማ ሕዝብ ጣልያኖች በጦርነቱ አመካኝተው ሕዝብ ለማስጨረስ እንደ አሰቡ አውቆ ነበርና ሴት፣ ወንድ፣ ሕፃን፣ ሽማግሌ ሳይል ወጥቶ ከቡድኑ ጋር ተደባልቆ ጣልያኖች ያለአንዳች ደም መፋሰስ እጃቸውን እንዲሰጡ ጠየቀ። ጣልያኖችም እንደ ተከበቡና ሕዝብም እንደ ተነሳባቸው ስለተረዱ እና በተካሄደው የጦር ትርእይትም ስለተደናገጡ፣ እጅ ለመስጠት ተስማሙ። እንግሊዞችም ተከታትለው ስለደረሱ በምክሩ እነሱም ገብተውበት ጣልያኖችን በሙሉ ለኮሎኔል ፎክስ፣ መሣሪያውን ፊታውራሪ ገረሱ ዱኪ እንዲረከቡት ስምምነት ተደረገ። በስምምነቱ መሠረት ሰኔ 12 ቀን 1933 ዓ.ም 8000 ጣልያኖች እጅ ሰጡ። ሃምሣ መኪና መድኃኒት እንደዚሁም በርካታ የወርቅ ቡችላና የብር ነዶ ከብዙ መሣሪያ ጋር ተማረከ። ነገር ግን እንግሊዞች ቃላቸውን ባለማክበር ከምርኮው የሚበዛውን ወሰዱት። አጋሮ፣ ጌራና ጉማ የነበሩ ጣልያናውያንም ተማረኩ።[6]

ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ፣ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሸሸውን የጠላት ጦር የሚከታተል ሠራዊት ተላከ። ለዚህም ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ ፊታውራሪ ተብለው አዛዥ ሆኑ። ከጉጃም ከሸሸው የጠላት ጦር አብዛኛው ከግንደ በረትና ከጉራጌ አገር አርበኞች ጋር እየተናነቀ እኩሉ በወለጋ፣ እኩሉ በጂማ በኩል ወደ ኢሉባቡር ተጓዘ። በዚህም ላይ ከከፋ ጊሚራ፣ ከጋሞ ጐፋ፣ ከማጂ ወደ ጎሬ ዘመተ።

የኢሊባቡር አርበኞች በእነ ባላምባራስ ገዳሙ ግዛው እና ወንድሞቻቸው፣ በእነ አቶ ወዳጆ ዲሣሣ፣ በእነ አቶ ሞረዳ ጥልም መሪነትና አስተባባሪነት ያቀርበን ወንዝ እንዳይሻገር፣ ተሻግሮም ሳምቤንና የጉራይሌን ኮረብታ እንዳይዝ በብርቱ ተናነቁት። በንጉሠ ነገሥቱ ትዕዛዝ በፊታውራሪ /ራስ/ መስፍን ስለሽ የሚመራው ነፃ አውጭ ጦርም ደርሶ ጎሬን ተቆጣጠረ። ከዚያም ወደ ሣምቤና ጉራሌሌ ሄዶ ለአርበኞቹ ድጋፍ ሰጠ። የጠላትም ጦር የጉራይሌን ኮረብታ ይዞ በብረት ተከላከለ። ከዘጠኝ የመዓልትና የሌሊት ጦርነት በኋላ መሣሪያውን ከምሮ እጁን ሰጠ።[7]

ከሰኔ 12 እስከ 14 ቀን 1933 ዓ.ም ቢሎ፣ ወለጋ ከተካሄደው ጦርነት ያመለጠው የጠላት ጦር ወደ ኢሉባቡር ተሻገረ። ጦሩ በደሌ ላይ ለሻለቃ /ኰሎኔል/ ወርቁ አየለ እጅ መስጠት ሲጀምር፣ በፊታውራሪ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራውም ጦር ደርሶ ከምርኮው ተሳተፈ።

በጀነራል ጋዜራ የሚመራው የጠላት ጦር ደግሞ ወደ ጮራ ተጓዘ። እሱንም የአጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ከበደ ይርዳው ጦር ደርሶ ሰኔ 17 ቀን ኮሪ ላይ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ድል ለኢትዮጵያ ሆነና 333 ከፍተኛ የጣልያን መኰንኖች ከዘጠና ከባድ መኪናና ከሰባት አውቶሞቢል፣ ከሃያ ሁለት የመኪና መጐተቻ ጋሪ ጋር ተማረኩ። ነገር ግን ጀነራል ጋዜራ አሁንም እጁን አልሰጥም ብሎ ወደ ጎሬ ተሸጋገረ፤ የገባን ወንዝ ድልድይ ሰበረ። ከዚያ ደግሞ ወደ ወለጋ ተሻግሮ የሶረን ወንዝን ድልድይ ሰበረ።

በዚህ ጊዜ ከጂማ፣ ከማጂ፣ ከከፋ የሸሸው የጠላት ጦር ቀደም ብሎ ጎሬ ገብቶ ነበር። በፊታውራሪ ወርቅ ዓለማየሁ ፋሪስ የሚመራው ነፃ አውጭ ጦር በደረኒና፣ በሱቦ አድርጐ ጎሬ ከተማ ደረሰና ሰኔ 26 ቀን 1933 ዓ.ም የነፃነት መዓዛ የሸተተው አርበኛና ተስፋ የቆረጠው የጠላት ጦር ግንባር ለግንባር ገጠሙ። ድል የኢትዮጵያ ሆነ። ከኢትዮጵያ ወገን ከአምስት መቶ በላይ ሰው ሲሞት፣ ከጠላት ወገን ግን የሞተውና የቆሰለው በድምሩ ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሠላሣ አራት ነበር። እንደዚሁም አሥራ ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሣ መኰንንና ወታደር በሕይወት ተማረኩ። በኢሉባቡር የተካሄደው ፍልሚያ በዚህ ዓይነት ተፈፀመ። በጦርነቱ ላይ አርባ ሦስት የውሃ መትረየስ፣ አንድ መቶ ሃምሣ ድግን መትረየስ፣ እጅግ ብዙ ጠመንጃና ጥይት ተማረኩ።[8]


**ማጣቀሻ ፅሑፎች**

1. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ* ፣ገጽ 164።
2. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ *ሕይወቴና የኢትዮጵያ እርምጃ 1ኛ መጽሐፍ*፣ ገጽ 25-7።
3. "የኢሉባቡር ታሪክ"፣ የኢሠፓ ኮሚቴ ጥናት፣ ገጽ 30-1።
4. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 65-116።
5. ሕይወት አደሩ፣ *ያቺ ቀን ተረሳች*፣ ገጽ 65።
6. ታቦር ዋሚ፣ *አባ በራ፣ የደጃዝማች ገረሱ ዱኪና የሌሎች አርበኞች ታሪክ*፣ ገጽ 77-95።
7. "የኢሊባቡር ታሪክ"፣ ገጽ 30-1።
8. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 364-4።




# ምዕራፍ ሃያ አራት
# በወለጋ የተካሄደ የአርበኝነት ሥራ

ጣልያን በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ከመጀመሯ አስቀድሞ፣ ክርስትናን ትምህርት የሚያስተምሩ፣ ወንጌል የሚሰብኩ አስመስላ ሰላዮች ከአሰማራችባቸው ክፍላተ ሀገራት አንዱ ወለጋ ነበር። ከዚህም የተነሣ በዚህ ክፍለ ሀገር የአርበኝነት ሥራ ማካሄድ ቀላል አልሆነም። ያም ሆኖ መልካም የአርበኝነት እንቅስቃሴዎች ለማድረግ ተሞክሯል።

የሆለታ ጦር ትምህርት ቤት ምሩቃን ቡድን ከሆለታ በመንቀሳቀስ በአምቦ፣ በጌዶ፣ በቦኒያ አድርጐ ነቀምት ገባ። ደጃዝማች ሀብተማርያም ኩምሣ በክብር ተቀበሉት። በአቅዋሙ ስለተደሰቱ ደመወዝ ለእያንዳንዱ ሰው ተመደበለት። አደላደሉም ለወታደር በወር 3 ብር፣ለሃምሣ አለቃ በወር 5 ብር፣ለመቶ አለቃ በወር 8 ብር፣ ለሻምበል በወር 12 ብር፣ ለሻለቃ በወር 15 ብር ነበር።

ጦሩ ስሙን "ጥቁር አንበሳ" ብሎ ሰየመ። አሥር አንቀጽ ያለው የመተዳደሪያ ደንብ አወጣ። የጦር አለቆችም መረጠ። እንቅስቃሴውን በአካባቢው ሁሉ አስፋፋ።ከሀገሩም ሰዎች አንዳንዶች ተባብረው ከጐኑ ቆሙ።

ጠላት የተደራጀ ጦር መኖሩን ሲረዳ አካባቢውን በአይሮፕላን ያስመረምር ጀመር። ጦሩ ግን ስለተደበቀ፣ አንዳች ምልክት አልታየም። ስለዚህ በሁኔታው ጠላት ተደናገረ። በአየር ላይ በመነፅር ሊረዳው ያልቻለውን የአካባቢውን ውስጣዊ ሁኔታ የሚያጠና ቡድን በ3 አይሮፕላኖች ላከ። አይሮፕላኖቹም ሰኔ 18 ቀን 1928 ዓ.ም በነቀምት አየር ላይ ከአንዣበቡ በኋላ ከነቀምት በስተምሥራቅ ቦኒያ ከተባለው ቦታ የኢትዮጵያ መንግሥት አሠርቶት ከነበረው አይሮፕላን ሜዳ ላይ አረፉ። የማረፋቸውም ወሬ ከቀትር በኋላ በ10 ሰዓት በወታደሩ ዘንድ ተሰማ።

አይሮፕላኖቹ ከማረፋቸው አስቀድሞ በደጃዝማች ሃብተ ማርያም አጥር ግቢ ወረቀት ጥለው ኖሮአል። የጣሉትም ወረቀት በቦኒያ አርፈው እንደሚያድሩ ገልፆ በማግሥቱ ጥዋት ጣልያኖቹ ወደ ነቀምት መሄጃ በቅሎዎች እንዲልኩላቸው የሚጠይቅ ኖሮአል። በስልክም ተነግሮአቸው ነበር። ጥቁር አንበሳ ይህንን ሁኔታ እንደተገነዘበ አስቸኳይ ስበሰባ አድርጐ አይሮፕላኖቹ ላይ አደጋ ለመጣል ወሰነ። ይህንንም ለደጃዝማች ሀብተማርያም ገለፀላቸው። ነገር ግን እሳቸው ከጣልያኖቹ በደረሳቸው ጥያቄ ከሕዝብ ጋር ተመካክረውበት የጣልያኖቹን ጥያቄ ለመቀበል ተወስኖ ስለነበር፣ የጥቁር አንበሳን ሐሳብ ለመቀበል አዳገታቸው። ጥቁር አንበሳ ግን በውሣኔው ፀና።

ሌሊቱን ወደ ቦኒያ ሄዶ አይሮፕላን ማረፊያውን በሽምቅ ከበበ። ሲነጋ ፈጥኖ በአይሮፕላኖቹ ውስጥ በመግባት በዚያ ያገኛቸውን ጣልያኖች ፈጅቶ በውስጡ የነበረውን መሣሪያ ካወጣ በኋላ አይሮፕላኖቹን አቃጠላቸው። የጦር

ማዕረጉ መቶ አለቃ የሆነ አንድ ጣልያናዊ ቄስ ከሁለት ኢትዮጵያውያን ባንዶች ጋር ትናንትናውኑ ከአይሮፕላኑ ወጥተው ለስለሳ ወደ መንደር ሄደው ስለነበር ከሞት ሲድኑ፣ ሌሎቹ 12 ጣልያኖች ግን ተገድለው ተቃጠሉ።

በዚህ ጊዜ የጥቁር አንበሳን ለጥቃት መዘጋጀት ያዩት ደጃዝማች ሀብተማርያም ወደ ግንቢ ሄዱ። እዳሪ ለመውጣት ሄዶ የነበረ አንድ ሌላ ጣልያናዊ በጥይት ተመትቶ በጥቁር አንበሳ ሲያዝ፤ ቄስ መቶ አለቃ በሩሱ ግን በፊታውራሪ ሞሣ ደባቂነት ድኖ ወሬውን ለጣልያኖች ነገረ። ሌላ አንድ አይሮፕላን ነጂ የነበረውን መኰንን ገበሬዎች አግኝተው በጦር ስለወጉት ከጥቂት ቀን በኋላ ሞተ። በጥይት ቆስሎ የተያዘው ወታደር ግን ተሰቃይቶ በስምንተኛው ቀን በገዛ እጁ ራሱን ገደለ።

በማግስቱ እሑድ ጣልያኖች ነቀምት አካባቢ በነበረው የጥቁር አንበሳ ሠፈር ላይ በሦስት አይሮፕላን ቦምብ በመጣል፤ በሌሎች ሁለት አይሮፕላኖች የመትረየስ ተኩስ ድብደባ አካሄዱ። በጦሩ ላይ ግን አንዳች ጉዳት አላደረሱም።

ከዛ ደጃዝማች ሀብተማርያም ከግንቢ ተመልሰው ነቀምት ገቡ። ነገር ግን በእሳቸውና በጥቁር አንበሳ ሠራዊት መካከል ስምምነት ሊገኝ አልቻለም። እሳቸው ከሕዝቡ የቀረበላቸውን ሐሳብ መቀበል ግድ ሆነባቸው። ጥቁር አንበሳ ከነበረው አቅዋሙ ንቅንቅ አልልም አለ። ስለዚህ ደጃዝማቹ ጥቁር አንበሳ አካባቢያቸውን እንዲለቅላቸው ጠየቁ። ሠራዊቱም በጉዳዩ ደጋግሞ ከመከረበት በኋላ ያለሕዝቡ ፈቃድ መቆየት ውጤት እንደማያስገኝ በመገንዘብ፣ በሰልፍ ሆኖ በደጃዝማች ፊት በማለፍ ከተማውን ጥሎላቸው ወጣ። ሲወጣም

"እናት ኢትዮጵያ ውዲቱ፣ ውዲቱ፣
ላንቺ የማይረዳ ሳለ በሕይወቱ፣
በረከትሽን ይንሳው እስከ እለተ ሞቱ።"

እያለ፣ ድምፁን ከፍ አድርጐ በመዘመር ነበር።[1]

ደጃዝማች ሀብተማርያም እንደዚህ ባለ ሁኔታ ነቀምትን ለጣልያን አስረከቡ። እነሱም ይዘው በመግደል ዋጋቸውን ከፈሉአቸው። በዛ የነበሩት ሌላኛው ኢትዮጵያዊ፣ ብላታ ደሬሳ ግን በሱዳን በኩል ወጡ። ትግሉም ቀጠለ።[2]

በ1929 ዓ.ም በእነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት በወለጋ የመቀዝቀዝ መልክ አሳይቶ የነበረው የአርበኝነት ተጋድሎ በ1930 ዓ.ም እንደገና ተቀሰቀሰ። ጥቅምት 13 ቀን 1930 ዓ.ም ጉድሩ ከዋ ላይ ግጭት ተደረገ። ከዚያም ከሜጫ የተሻገረው አርበኛ ወደ ሆሮ ጭብር ከተማ በገባ ጊዜ ሕዝቡ በእልልታ ተቀበለው። የፊታውራሪ አፈሣ ልጅ አቶ ደርጉ አፈሣ፣ እንደዚሁም ደጃዝማች ደስታ እስቴና ቀኛዝማች ገሠሠ ከአርበኞቹ ጋር በመቀላቀል ድጋፍ አስገኙ።



በዚህ ጊዜ ነቀምት የሠፈረው የጠላት ጦር በሕዝቡ ላይ ተፅዕኖ አሳደረ። ከዚህ የተነሣ ከሆሮና ከአሞሩ ሕዝብ ከፊሉ አርበኞችን ሲደግፍ፣ ከፊሉ ደግሞ ለጠላት አመነ። ሊባኖስ ወንዝ ላይ አሞሩና ጊዳ ከሚባለው ቦታ ውጊያ ተካሄደ። አሥራ ሰባት ያህል ባንዶች ሞቱ። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው አርበኛ ከሆሮ ወደ ሊሙ አያና ሄደ። በግራዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው አርበኛ ደግሞ ህዳር 21 ቀን 1930 ዓ.ም አያና ገበያ አካባቢ ከደረሰበት የአየር ጥቃት አምልጦ ወደ ኢባንቱ ሄደ። በወቅቱ የኢባንቱ ሕዝብ በጠላት ተሰብኮ ነበር። ስለዚህ በዚያ የነበረውን አማራ ወደ ሆሮ በመውሰድ ለመፍጀት ያስቡ ስለነበሩ ከእልቂት አዳናቸው።

አርበኛው ከጊዳ አሞሩ ሲንቀሳቀስ ጠላት በበኩሉ ሊባኖስ ላይ ጠብቆ ታህሣሥ 2 ቀን 1930 ዓ.ም እሑድ ዕለት ጦርነት ገጠመው። በደጃዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው አርበኛ መንገዱን በጦርነት እየጠረገ ተጓዘ። ሰባት ያህል የጠላት ወታደር ገደለ።

በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን የሚመራው ጦር ከሊሙ፣ ደጃዝማች ዘውዴ ደግሞ ከኢባንቱ መጥተው ጀርቲ ከተባለው ቦታ ላይ ተገናኙ። ጠላት ይህንን ሲሰማ ስለዘመተባቸው ታህሣሥ 16 ቀን 1930 ዓ.ም ጦርነት ተደረገ። ጥር 13 ቀን 1930 ዓ.ም መንፍሬጉ ላይ መጠነኛ ውጊያ ተካሄደ። የአካባቢው ባንዳ በበኩሉ የካቲት 7 ቀን ደንጉሮ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጥሎ ነበር። አርበኞቹ እየተከላከሉ አምልጠው ወጡ።

የካቲት 11 እና 12 ቀን ጂማ ገነቲ ላይ ጦርነት ተካሄደ። ከጠላት ወገን አርባ ያህል ሰው ሳይሞት አልቀረም። የጠላት ከበባ እየጠነከረ ስለሄደ በወለጋ ይንቀሳቀስ ከነበረው አርበኛ በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን የሚመራው ቡድን ወደ ጐጃም ለመሻገር አሰበ። በሆሮ በኩል ወደ አጐል ሄዶ ከደጃዝማች ነጋሽ በዛብህ ጋር ተላላከ።[3]

በዚህ ዓይነት አርበኛው ጉዞውን ቀጥሎ ከወለጋ ወደ ጐጃም ሊሻገር ሲጓዝ አጋምሣ ላይ ጠላት የካቲት 13 ቀን 1930 ዓ.ም አደጋ ጣለበት። አደጋ የጣለው ይኸ የጠላት ጦር በውስጡ የዓረብነት ትውልድ ያላቸው እንዲሁም የሊቢያ (ጡሩምቡሌ) ወታደሮች እና የከሰላ (በተለምዶ አጠራር፦ ሻንቅላ) ወታደሮች ነበሩበት። ብዛቱም ከአርበኞቹ እስከ ሃያ እጠፌታ ይገመታል።

አርበኞቹ በብርታት ተዋጉ። ጠላት ለማደፋፈር ብሎ ወታደሩን አረቂ አጠጥቶት ስለነበር የጨበጣው ውጊያ ለኢትዮጵያውያን ሠመረ። እርስበርሱ እስከ መተላለቅ አደነጋገሩት። ጦርነቱ ከጥዋቱ 2 ሰዓት የተጀመረ እስከ 9 ሰዓት ድረስ ቆየ። አርበኛው አልበገር ስለአለ ጠላት ጥሎ ሄደ። አርበኛውም ወንዝን ተሻግሮ የካቲት 15 ቀን 1930 ዓ.ም ጐጃም፣ ቡሬ አፋፍ ወጣ።[4]

በዚህ ዓይነት ከወለጋ ወደ ጐጃም የተሻገረው ጦር ጥቂት ቆይታ ካደረገ በኋላ ምክር ተያዘ። በምክሩም አርበኛው ከሁለት ተከፈለ። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው ቋልቁ ቡድን ከንጉሠ ነገሥቱ መመሪያ

ለመቀበል በሚል ሽፋን ወደ ሱዳን መስደድን መረጠ። በግራዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው ትንሹ ቡድን ግን ወደ ባዕድ አገር አንሄድም አለ። ሚያዝያ 27 ቀን 1930 ዓ.ም ጐጃም ክፍለ አገር ቁጭ ከተባለ ቦታ ሁለቱ ቡድኖች ተሰነባብተው በሰላም ተለያዩ።

ከዚያ ወዲያ ከጐጃም ወደ ወለጋ ተመልሶ የሚሻገረውን አርበኛ ጠላት አላስገባም ብሎ ያዘ። ከጐጃምም የጠላት ጦር ገሥግሦ ደረሰ። ከዛው ከአባይ ሸለቆ ሚያዝያ 30 ቀን ታላቅ ውጊያ ተደረገ። ከወለጋ ወገን ያለውን የጐጃሙ፣ ከጐጃም ወገን ያለውን አርበኛ የወለጋው እያሸጋገረ በመድፍና በመትረየስ ደበደበው። አርበኞች በበኩላቸው በብርታት እየተዋጉ ከዓባይ ወንዝ ገብተው ውሃ ጠጡ። ከብቱም ሰውም ትንፋሽ አገኘ። ምንም ወሩ ሚያዝያ ቢሆንም የበልግ ዝናም ነበርና የዓባይ ውሃ ቀላል አልነበረም። እስከ ወገብ ይደርስ ነበር። አርበኛው የወለጋውን ወገን ካላጠቃ በስተቀር ሌላ ማምለጫ እንደሌለው ስላወቀ በርትቶ ተዋጋ። "ቆራጥና ጭስ መውጫ አያጣም" እንደሚባለው በሩን ሰብሮ፣ ጠላትን አባርሮ ወጣ።

እዚህ ላይ አንዳንዶች በአሰቃቂ ሁኔታ ከበረሃው ላይ በውሃ ጥም እየደከሙ ቀርተዋል። ሌሎች ከወንዙ ከገቡ በኋላ ደግሞ ጥቂቶቹን ውሃ ወስዷቸዋል። ሴት፣ ልጅ እና አዛውንትም ተማርከዋል። ይሁን እንጂ አርበኛው ከጥፋት ሊድን ችሏል።

አርበኛው የአሣር ጉዞውን በዚህ ዓይነት ቀጥሎ አጐል በረሃ ገባ። ይህ ቡድን ወደ ጐጃም በተሻገረ ጊዜ ይከተለው የነበረውን የጠላት ጦር ለማገድ አካባቢውን በእሳት አቃጥሎት ስለነበር፣ አሁን ተመልሶ በሚመጣበት ጊዜ ከአመድ ላይ ደረሰ። ከቃጠሎው የተረፈው ጉቶና ስንጥር፣ የበረሃው ረሞጫ እጅግ አሰቃየው። ሥፍራው በረሃ ከመሆኑ ጋር ገደላማ ስለሆነ በከብት ለመጓዝ አያመችም። የውሃ መትረየሱን የተጫነችውን በቅሎ ማጓጓዝ እጅግ ከባድ ሆነበት። ጦሩ እንደምንም ታግሎ ጨዲቲ ከተባለው ወንዝ ደርሶ ውሃ ጠጣ። ከብትም፣ ሰውም እንደገና ትንፋሽ አገኘ። አቶ አጐናፍር ብቻ በፅኑ ታመው እዚህ በረሃ ላይ በአሰቃቂ ሁኔታ ቀሩ።

አርበኛው ጉዞውን ቀጠለ። የሚበላ እህል ስለጠፋ ሰው ያብጥና ይነፋ ጀመር። ምግብ ለማምጣት የተላኩት ሰዎች ከአንድ ሣምንት በኋላ ጥቂት እህል ይዘው ተመለሱ። ሰው እሱን በመብላት ከእልቂት ድኖ በሬዳ ወደተባለው ቦታ ጉዞውን ቀጠለ።

ቡድኑ በሬዳ ሲደርስ አቶ ነገሬ ገመቹ የተባሉ አርበኛ መልካም አቀባበል አደረጉለት። የሚበላም የሚጠጣም ሰጡት። አንዱ ችግሩ የእንቅልፍ ማጣት ስለነበር አቶ ነገሬ ሰዎቻቸውን ቃፊር አቁመው የመተኛት ዕድል ሰጡት። ነገር ግን ጠላት ከጉድሩ አዲስ ጦር አንቀሳቅሶ ደረሰባቸው። አርበኞች እየተከላከሉ ከጉዳት አምልጠው ግንቦት 11 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ግንደ በረት ተሻገሩ።[5]



ከዚህ በኋላ በወለጋ ሲካሄድ የነበረው የአርበኝነት ተጋድሎ እንደገና ቀዘቀዘ። ንጉሠ ነገሥቱ ተመልሰው በመጡ ጊዜ፣ የጠላት ጦር ለራሱ መከላከያ ሊያደርገው ያሰበው የወለጋን ግዛት ነበር። በዚህም የተነሣ በርካታ የጠላት ጦር ወደዚያ ተልኮ ነበር።

ንጉሠ ነገሥቱ በበኩላቸው ሰኔ 5 ቀን 1933 ዓ.ም ለነቀምት ሕዝብ አዋጅ አስነገሩ። አዋጁም ጠላት በሕዝብ ላይ ያካሄደውን ጭፍጨፋ ከገለፀና በጐሣና በሃይማኖት እየለያየ ያደረሰውን ጥፋት ከአስገነዘበ በኋላ፣ ስለወደፊቱ አስተዳደር ፍንጭ የሚሰጥ ነበር። "...ጥረታችን የዘር ልዩነት ሳይደረግ፣ ሁሉም እንደ ችሎታው ከሕይወቱ በሚሠራው ሥራ ዋጋው እንዳይጠፋ፣ ራሱ እንዲጠቀም ነው..." ይል ነበር። ፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ አስተዳዳሪ ሆነው መሾማቸውንም ይገልፃል።

በጦር በኩል ደግሞ ሻለቃ /ራስ/ መስፍን ስለሺ ፊታውራሪ ተብለው ተልከው ነበርና፣ ቢሉ በተባለው ቦታ ከሰኔ 12 እስከ 14 ቀን 1933 ዓ.ም ጦርነት ተካሄደ። ጠላት ድል ሆኖ ወደበደሌ ሄደ። በጄነራል ጋዜራ የሚመራው የጠላት ጦር የዴዴሳን ወንዝ ድልድይ ሰብሮ ወደ ግንቢ ተሻገረ። ከዚያም ወደ ደምቢደሎ ቀጥሎ ከዛየር ለመጡ የቤልጅግ ወታደሮች እጁን ሰጠ።[6]

## ማጣቀሻ ፅሑፎች


1. ታደሰ ሜጫ፣ *ጥቁር አንበሳ*፣ ገጽ 46-60።
2. Greenfield, Ethiopia, p.245.
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 340-344
4. ሙሉሰው ምትኩ፣ *ከሸዋ እስከ ሱዳን ጠረፍ*፣ ገጽ 36-60።
5. ታደሰ ዘወልዴ፣ ገጽ 345-351።
6. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 429-432።

# ምዕራፍ ሃያ አምስት

## ግንደ በረትና ሜጫ የተካሄደው ትግል

ንጉሠ ነገሥቱ ወደ ውጭ አገር መሄዳቸው ሲረጋገጥ፣ አዲስ አበባ ውስጥ የነበረው የኢትዮጵያ ጦር እጁን ማውጣት ነበረበት። የጠላት አመጣጥ በደብረ ብርሃንና በናዝሬት በኩል መሆኑ ታውቆአል። የሲዳሞው ጦር ለብዙ ጊዜ እንደሚመክት ስለአልታወቀ የጂማ በር አላስተማመነም። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ለመውጫ የተመረጠው በር የወለጋ በር ሆነ። ጥቂቶች የዛው ተወላጆች ደግሞ ወደ ቡልጋ ገቡ።

በወለጋ በር ከወጣው ጦር በመቶ አለቃ ወልደ ዮሐንስ የሚመራው አንዱ ቡድን ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም ገፈርሣ ላይ ከባንዳ ጋር ግጭት አጋጠመው። ቢሆንም ጉዳት ሳይደርስበት ጥሎት አለፈ። የኢትዮጵያ የጦር መሪዎች ከአዲስ አበባ ወጥተው በወጨጫ፣ በመናገሻ ጫካዎች አድፍጠው መጠባበቅ ያዙ።

የጠላት ጦር ወደ ወለጋ ለመሄድ ሲጓዝ በግንቦት ወር መጀመሪያ ወልመራ ላይ በሻለቃ /ራስ/ መስፍን የሚመራው የኢትዮጵያ ጦር ግንባር ለግንባር ገጠመው። ምንም ጠንክሮ ቢዋጋ የኢትዮጵያ ሠራዊት የጠላትን ጦር ሊመልሰውና ጉዞውን ሊያስቆመው አልቻለም። አንድ ጄነራልና ብዙ ወታደሮች ግን ገደሉበት። የጄነራሉ ሐውልት እስከ 1966 ዓ.ም ድረስ ገፈርሣ በመንገድ በስተሰሜን ቆሞ ይታይ ነበር። ከማይጨው በኋላ ደፍሮ ግንባር ለግንባር የገጠማቸው ሰው አልነበረምና ጣልያኖች ይህንን ቦታ ሁለተኛ ማይጨው አሉት።

ጠላት የአካባቢውን ሕዝብ በስብከትና በትዕዛዝ ተፅዕኖ አድርጉበት ስለነበር በያለበት የባንዳ ኃይል ተንቀሳቀሰ። ሰኔ 12 ቀን አዳበርጋ፣ ሰኔ 18 ቀን ደግሞ ሜታ ዋዩ ግጭት ተደረገ። ነገር ግን በአርበኛው እምብዛም ጉዳት አልደረሰበትም።

በመቀጠል አርበኛው ሙሌ ከሣንድ ፎርድ ቤት የሠፈረውን የጣልያን ወታደር ለማጥቃት ዕቅድ አዘጋጀ። ነገር ግን እቅዳቸውን አስቀድሞ በመስማት ጠላት ወደ አዲስ አበባ ሸሸ። እነሱም ተከታትለው ሐምሌ 5 ቀን 1928 ዓ.ም ዕለተ እሑድ ወግዲ ከምትባል ቦታ ገጠሙት። ከጥዋት እስከ ምሽት የቆየ ውጊያ ተካሄደ። ብዙ ወታደር ፈጁበት፤ ምርኮም አገኙ። ከእነሱም ወገን አምስት ሰዎች ሲሞትባቸው፣ አንድ ሰው ቆሰለ።

ሐምሌ 17 ቀን 1928 ዓ.ም በሜታ ቢታ አካባቢ መስቀሌ በተባለው ቀበሌ ጠላት አርባ በሚሆኑ አርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። ቢሆንም ስድስት መትረየስ ከበቂ ጥይት ጋር እንደዚሁም በቂ የነፍስ ወከፍ መሣሪያ ስለነበራቸው ከበባውን ስብረው አመለጡ። ብዙ የጠላት ወታደሮች ሞቱ፣ ሌሎች ቆሰሉ። ከአርበኞች ወገን ሁለት ሞቱ፤ ሌሎች ጥቂቶች ቆሰሉ።



እዚህ ላይ የሚጠቀስ አስፈላጊ ጉዳይ አለ። ይኸ ጦርነት በአርበኞች ላይ ያደረሰው ጉዳት እንደተገለፀው ቁጥር የሚገባ አልነበረም። በዚህ ውጊያ ምክንያት ግን እነደጃዝማች ፍቅረማርያም በደብረ ብርሃን በር፣ እነደጃዝማች ባልቻ በጂማ በር፣ እነደጃዝማች አበራ በጉጃም በር፣ አዲስ አበባን ሲያጠቁ ከግንደ በረት በወለጋ በር ሙከራ ሳይደረግ ቀረ። እናም ተባብሮ አዲስ አበባ ለመግባት የነበረውን እቅድ አከሸፈ።

ወደ ግንደ በረትና ሜጫ ተጋድሎ ስንመለስ ጠላት መስከረም 12 ቀን 1929 ዓ.ም ወረ ጃርሶ ላይ አደጋ ጥሎ በአርበኞች ላይ መጠነኛ ጉዳት አደረሰባቸው። ከዚህ በኋላ በአርበኞች መካከል ምክር ተደረገ። ምክሩም በምን በምን ቦታና ዘዴ ጠላትን ማጥቃት እንደሚቻል ነበርና የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ። በሻለቃ /ራስ/ መስፍን የሚመራው እኩሉ ሠራዊት ወደ ምዕራብ እንሂድ ሲል፣ በባላምባራስ /ራስ/ አበበ የሚመራው ደግሞ ከማህል ሀገር እንዋጋ አለ። ሁሉም እንደፍላጎቱ እንዲያደርግ ከስምምነት ላይ ተደርሶ እንደዚሁ ተደረገ።

ጣልያን በመጠናከር ላይ የነበረውን የአርበኞች እንቅስቃሴ በእንጭጩ ለመቅጨት ከአዲስ አበባና ከአምቦ፣ ከደብረ ብረሃን፣ ከጉጃም፣ ከወሎም ጭምር ጦር አንቀሳቀሰ። የጠላት ጦር የመጣው በግንደ በረት በኩል ስለነበር አርበኞች የሙገርን ወንዝ ተሻግረው የሰላሌ ክፍል ከሆነች ውልጮ ከምትባለዋ ቦታ አድፍጠው ጠበቁት። ጦርነቱ ታህሣሥ 11 ቀን 1929 ዓ.ም ከጥዋቱ በ1 ሰዓት ተከፍቶ ታላቅ ውጊያ ተደረገ። ብዙ መሣሪያ በአርበኞች እጅ ገባ። ባላገሩ ጭምር ተከፋፈለው።

ወደ ምዕራብ የሄደው አርበኛ ወደ ወለጋ ስለተሻገረ፣ የቀረው እስከ 1929 ዓ.ም የበጋ ወራት አካባቢ ድረስ ጥቂት ፋታ አገኘ። ነገር ግን ክረምቱ ሲገባ ጦርነቱ እንደገና ተቀጣጠለ። ሐምሌ 18 ቀን 1929 ዓ.ም ቨልቢ ላይ ጦርነት ተደረገ። ውጊያውም በጠመንጃና በመትረየስ ብቻ ሳይሆን በጥንቱ የመዋጊያ መንገድ በሥለት፣ በሰይፍና በጉራዴ ጭምር ተካሄደ። ጦርነቱ ከቀኑ 7 ሰዓት ጀምሮ እስከ ሌሊቱ ድረስ ተካሄደ። በዚህ ጦርነት ላይ ከአርበኞቹ ወገን ብዙ ሰው ሞቷል። ነገር ግን ከጠላት ወገን የደረሰው ጉዳት ከዛ የሚበልጥ እንጂ የሚያንስ አልነበረም። በዚህ ጦርነት አንድ ትልቅ የጭነት ዛባኾሎል የተባለ የውሃ መትረየስ፣ ሌላ ዘጠኝ ድግን መትረየስ ተማረከ። አንድ ሺህ አልቤንና ከእቅፍ በላይ የሆነ የምንሽር ጠመንጃ እንደዚሁ ተማረከ። ሰው የተቻለውን ያህል አነሳ። ውጊያውም ከቀኑ 9 ሰዓት ተጀምሮ ሌሊቱን ሁሉ ቀጠለ። አርበኞቹ ድል አድርገው የጠላትን ጦር መሪ ጭንቅላት በመቁረጥ ባላገር ጌጤ እንዲጫወትበት አደረጉ።

ነሐሴ 28 ቀን 1929 ዓ.ም ሌላ የጠላት ጦር በዚሁ በሸኖ ኢየሱስ በኩል መጣ። አርበኞች ምቹ ቦታ ይዘው ጠብቀው ጥፋት አደረሱበት። በተነሳው ሽብር አንድ የእንጨት ድልድይ ተሰብሮ ሰባ አምስት ጣልያኖች

ውሃ ውስጥ ገብተው አለቁ። ነሐሴ 29 ቀንም ጠላት ለማጥቃት ሙከራ አድርጐ ነበር። እሱው ራሱ ተመልሶ ተጠቃ እንጂ፣ በአርበኞች ላይ ጉዳት ሊያደርስ አልቻለም።

መስከረም 6 ቀን 1930 ዓ.ም ውዴሣ ላይ ጦርነት ተካሄደ። ጦርነቱ ከጠዋቱ 4 ሰዓት ተጀምሮ እስከ 11 ሰዓት ተኩል ቆየ። የማታ ማታ ድሉ የአርበኞች ሆነ። ብዙ መሣሪያና ዕቃ ተማረከ። ጠላት ነጭና ጥቁር ወታደሮች አነባብሮ ቀብሮ ጥሎ ሸሸ። በማግስቱ ባላገሩ እየቆፈረ ቢያወጣው ብዛቱ አስገራሚ ሆነ። መስከረም 27 ቀን ደግሞ ጂማ ገነት ላይ ጦር አሠፈረ። ጦሩም 12 ሺህ የተገመተ ሲሆን የመጣውም ከአዲስ አበባና ከነቀምት ነበር። አርበኞቹም ምሽጉን ተጠግተው ከቀትር በኋላ ገጠሙት። ሁለት መዓልትና ሁለት ሌሊት ወጉት። በመጨረሻ ጠላት ሲያይልባቸው ወደቆላው አፈገፈጉ።

ነገር ግን በዚህ ጦርነት ከተገኘው ምርኮ ይልቅ ያመለጠው ሳይበልጥ አልቀረም። ሁኔታውም እንዲህ ነው። ጀነራል ማርቲኒና ራስ ኃይሉ በጦርነቱ ተሸንፈው እጃቸውን ለመስጠት ይቃረባሉ። በንግግሩ ወቅት ደጃዝማች አውራሪስ እንዲቀርቡላቸው ይጠይቃሉ። ሰው በመምረጣቸው የተበሳጩ አርበኞች የዘለፋ ቃል ይናገራሉ። ጀነራል ማርቲኒና ራስ ኃይሉ ደንግጠው መዋጋትን ይመርጣሉ። አጋጣሚ ዝናምም መጣ፤ መብረቅም ወርዶ አምስት የጣልያን መኰንኖችን ገደለ። ቀኑም መሸ። ቢዋጉም አርበኞች ቀደም ብለው ያጡትን የምርኮ ዕድል መልሰው ማግኘት የማይቻላቸው ሆነ። ራስ ኃይሉና ጀነራል ማርቲኒ አመለጡ። በኋላ ላይም አርበኞች ተስፋ ባለመቁረጥ ተከታትለው ለመማረክ ሞከሩ። ማሚቴ ወልደሰንበት የተባለችው የራስ ኃይሉ ገረድ ተማርካ ነበርና ተጠየቀች። መስኮብ ጠመንጃ እንጂ ደረቅ ብረት እንደሌላቸው ገለፀች።

ሐምሌ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ጦርነት ተጀመረ። ጀነራል ባሲኒ ኩሚ የሚባለው የጣልያን ጦር አዛዥ ሸኖ ኢየሱስ ላይ አጥብቆ ተዋጋ። አርበኛውም ታላቅ ምርኮ ሸትቶት ነበርና በኃይል ተዋጋ። ጦርነቱ እስከ ሐምሌ 4 ቀን ድረስ ቀጥሎ በአቅራቢያው የነበረውንም ያዘ። ከአርበኞቹም ከጠላትም ብዙ ሰው ሞተ። ጠላት በቴሌግራም ጠይቆ አዲስ ጦር አስመጣ። ጦርነቱ እንዲቆም በአርበኛ መሪዎች ተወሰነ።

አርበኞች ጉድሩ ሳሉ ጠላት ከወለጋ፣ ከሲዳሞ፣ ከከፋ፣ ከአምቦ በሁለት ጀነራሎች የሚመራ እስከ 30 ሺህ የሚሆን ጦር አቀረበ። አርበኞች አንዱን ጀነራል ገድለው ድል አድርገው አበረሩት። ብዙ ነጭና ከሊቢያ የመጡ አረብ ወታደሮች አለቁ።

ጠላት ወደ ጉዶ ምሽግ ሲገባ አርበኞች ከቆላው ወጥተው ከሜዳ ላይ ሠፈሩ። ጠላት ይህንን ሲያይ በአይሮፕላን ሊያጠቃቸው ሞከረ። ጥቅምት 5 ቀን 1930 ዓ.ም ጥዋት ሁለት አይሮፕላን አምጥቶ አከባቢውን አስደበደበ።



በተለይ አርበኛው በሠፈረበት ቦታ በአንድ ትልቅ በርሜል የጋዝ መርዝ ጣለ። በርሜሉ ገና በአየር ላይ እንዳለ መርዙን መርጨት ስለጀመረ ሠራዊቱ መርዝ መሆኑን ተረድቶ በመበታተኑ ጥቂት የጋማ ከብት ከመግደሉ በስተቀር በሰው ላይ ጉዳት ሳያደርስ ቀረ።

የአርበኛው ቡድን እየተጠናከረ ሲሄድ በሕዝብ ዘንድ ይበልጥ ተቀባይነት አገኘ። አርበኛው ከሚዋጋበት አገር ይልቅ ጣልያን የሠፈረበት ይበልጥ ይጐዳ ጀመር። ስለዚህ አርበኞቹን ሂዱልን ትውልድ አካባቢያችን አታስጠፉብን የሚለው ወገን እየተቀነሰ "ኑልን አድኑን" የሚለው እየበዛ ሄደ። የጨልያ ሕዝብ መክሮ ኑልን ሲል፣ በባላባቱ በፊታውራሪ በፈቃዱ መርጊያ በኩል ጋበዛቸው።[1] እነሱም በመቀበል ሄደው ሀገሩን በማረጋጋት ረዱት። እነሱም ራሳቸው ለተወሰነ ጊዜ እፎይታ አገኙ።

ጠላት አዲስ ጦር አደራጅቶ ዘመተ። አርበኞችም ግንቦት 17 ቀን 1930 ዓ. ም ከቱሴ ላይ ጦርነት ገጠሙት። ጦርነቱ በማግስቱም ቀጠለ። ከአርበኞች በስተጀርባ የነበረው አገር በረሃ ስለነበር ለመከላከል አላመቻቸውም። ስመጥር አርበኞች ሞቱ። ከጠላት ወታደሮችም ብዙዎች ወደቁ። አርበኞች የተደረገባቸውን ከበባ ሰብረው ወደ አቡና ቆላ ገቡ። ጠላት ተከታትሎ ሌላ ሁለተኛ ከበባ ሠራባቸው። የተከማቻቸውን የአርበኛ ቡድን በሰላዮች አማካኝነት ተረድቶ ፈጅቶ ለመገላገል ጥረት አደረገ። አርበኞችም ሐሳቡን አውቀው ነበርና በርትተው ተዋጉ። ቢሆንም በታተናቸው። ገሚሶቹ ወደ ሰላሌ ተሸጋገሩ፣ ሌሎች በዚያው በነበሩበት አካባቢ ትግላቸውን ቀጠሉ።

በግንደ በረት በረሃ የቀሩት አርበኞች ድካም ስለበዛባቸው እና ብዙ ሰው ስለተለያቸው ቁጥራቸው ወደ አንድ መቶ ዝቅ አለ። ከጠላት መሰወርና በሽምቅ መሥራት ግድ ሆነባቸው። በአንፃሩ ደግሞ ባንዳ እጅ እጃቸውን ይዞ ለጠላት በመስጠት ሊሸለምባቸው አሰፈሰፈ። የአርበኛው አስተባባሪ ደጃዝማች ዘውዴ አስፋው ነበሩ። ሽክሙ ስለከበደባቸው የውሃ መትረየሳቸውን አቶ ኩሪ ገመዳ ዘንድ አደራ አስቀምጠው የጉደርን ወንዝ ተሻግረው ወደ ወለጋ ሄዱ።

በግንደ በረት ሲከላከል የቆየው አርበኛ ግንቦት 25 ቀን 1930 ዓ.ም ምክር አደረገ። በዚህም ምክር እንደ ቀድሞው ሁሉ የሐሳብ መለያየት ደረሰ። በደጃዝማች ዘውዴ አስፋው የሚመራው በዚያው አካባቢ በሕቡዕ ሥራውን መቀጠልን መረጠ። ጥቂቶቹ ሰላማዊ ሕይወት የሚያገኙ መስሎአቸው ወደ ጠላት ገቡ። ግንቦት 17 ቀን 1930 ዓ.ም ከዲጉ ወደ አምቦ ወጡ። ጠላትም እየተከታተለ ወጋቸው። በተለይ ግንቦት 19 ቀን በተደረገው ውጊያ አርበኞች በጠላት ላይ ጉዳት አደረሱ።

በአገር ውስጥ ሥራውን ለመቀጠል የወሰነውን ቡድን ግን ጠላት ተከታትሎ ሳይደርስበት ከአንድ ዓመት በላይ ቆየ። ዲጉ ቆላ መሆናቸውን አውቆ ጠላት መስከረም 20 ቀን 1931 ዓ.ም አደጋ ጣለባቸው። ነገር ግን ሊያጠፋቸው ሳይችል ቀረ። ቢሆንም ክትትሉን በማጠናከር መሪውን ጠላት

በጠቋሚ ግንደበረት ውስጥ አስያዛቸው። ባላምባራስ ወልደ ፃድቅ የተባለው ሀገር ወዳድ በጠላት መሣሪያነት ሁኔታውን የሚያጣራ በመምሰል አስቀርቦ አርበኞችን አስጠነቀቀ። እንዲያመልጡ የሰጣቸውን ምክር ግን ባለመቀበል ከጠላት እጅ እንደገና ወደቁ።

ጠላት ስለመጣ ወበሪ ላይ ጥቅምት 5 ቀን 1930 ዓ.ም ጦርነት ተደርጐ ድል የአርበኞች ሆነ። ነገር ግን ለተከታታይ ሥራ መዘጋጀት ስለአስፈለገ ምክር ተያዘ። ከቡልጋ በመጡት በእነ ባላምባራስ ተሻገርና በግንደ በረት አካባቢ ሲከላከሉ በቆዩት አርበኞች መካከል የአስተያየት ልዩነት ተፈጠረ። ከቡልጋ የመጣው አርበኛ የለመደው በተራራና በሸንተረር በወንዝና በሸለቆ ውስጥ ተሰማርቶ መዋጋት ሲሆን፣ በሜዳ ላይ መዋጋት አልሆንልህ አለው። በግንደ በረት አካባቢ በሜዳ ላይ የቆየው ደግሞ በፈረስ እየጋለበ መዋጋት እንጂ፣ በእግሩ ብዙ መንገድ መጓዝ ከበደው። ስለዚህ ጥቅምት 6 ቀን 1932 ዓ.ም በዋለው ምክር ሁሉም እንደ ፍላጐቱ እንዲያደርግ ከስምምነት ላይ ተደረሰና ባላምባራስ /ፊታውራሪ/ ተሻገር ወደ ቡልጋ ለመመለስ ወደ ሰላሌ ተሻገሩ። እዛ ከሆለታ የተንቀሳቀሰ የጠላት ጦር መጣባቸው። አርበኞችም ጥቅምት 12 ቀን 1932 ዓ.ም መዳላ ከተባለው ቦታ ገጥመው በመውጋት ወደ ኋላው መለሱት። ከዚያም ወደ ሙገር ቆላ ወርደው ወደሐሮ ተሻገሩ።

ኃይል እንደተቀነሰባቸው ባወቀ ጊዜ ጠላት በግንደ በረት አካባቢ በነበሩ አርበኞች ላይ ጦርነት አጠነከረባቸው። አርበኞችም ፋታ ለማግኘትና እንደገና ለመጠናከር የሚረዳቸውን ዘዴ በማሰብ ለጠላት የእርቅ ፊት አሳዩት። በተደረገውም ድርድር ፋሽስቶች ከሆለታ ወዲያ አልፈው በልጅ ከበደ ብዙነህ ላይ ደረሱባቸው። እንዲሁም ልጅ ከበደ ከሆለታ በላይ ሳይደርሱ ህዳር 14 ቀን 1931 ዓ.ም ስምምነት ተደረገ። ከዚህ ስምምነት ላይ የተደረሰው በባላገሩ ላይ የደረሰውን ችግር ለማቃለል ታስቦ ጭምር ነበር። ከዚህም በስተቀር አዋጁ ሕዝቡ በጥቅም መጋጨቱን ትቶ አንድነቱን እንዲያጠናክር ነበር። እንዲሁም ስምምነቱ አንዱ የአንዱን ወሰን በመተላለፍ እንዳይዘራረፍ ለማስቻል እና ለመምከር ነበር። ጠላት በመጣ ጊዜ ተባብሮ ለመውጋት ሕዝባዊ ስምምነት ለማስገኘት ታስቦ ነበር።

ፋሽስቶች በቃላቸው መጽናት አይሆንላቸውም። ወር ሳይሞላቸው ስምምነቱን በመጣስ ታህሣሥ 5 ቀን አምስት መኰንኖች ደበሌ ወንዝ ወርደው ለጦር ሥራ የሚረዳ ካርታ ሲሠሩ ተገኙ። እጃቸውን ለመስጠት ፈቃደኞች ባለመሆናቸው ተገደሉ። ገብረ ማርያም የተባለ መሪአቸው ብቻ አመለጠ። ገብር ማርያም ጦር ይዞ ስለመጣ ቆላ ቱሊ ከተባለው ቦታ ታህሣሥ 7 ቀን ጦርነት ተደረገ። ሁለት የጠላት ወታደሮች ሞቱ አንድ ቆሰለ። ልጅ ከበደ ብዙነህ ራሳቸው አመለጡ። ነገር ግን አሽከራቸው ሞተ፣ እንደዚሁም ብዙ መሣሪያና ዕቃ ተማረከባቸው።



ህዳር 17 ቀን 1931 ዓ.ም የግንደበረቱ በጋጅ፣ በጀልዱ፣ በሆሶሌ በኩል እንደዚሁም የአዲስ አበባው በቀጨማ፣ በጐሮ በኩል መጣባቸው። አርበኞቹም በሦስት ረድፍ የመጣባቸውን የጠላት ጦር ተጋጥመው ህዳር 17 ቀን 1931 ዓ.ም ወጉት። የጠላት ኃይል ስለአየለ ህዳር 20 ቀን ወደ ሰላሌ ተሻገሩ። አርበኞች ባይበገሩለትም ጠላት ማጥቃቱን አልተወም። ታህሣሥ 12 ቀን አዲስ ጦር ሠርቶ መጣ። አርበኞችም ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት። አርባ ሰባት ባንዶች ማምለጥ ሲሳናቸው እየሸሹ ከአንድ ታላቅ ዋሻ ውስጥ ተደበቁ። አርበኞቹ ሦስት የእጅ ቦምብ በመጣል አቁስለው አስደንግጠው ማረኩአቸው። ነገር ግን ከማረኩአቸው በኋላ አንዳች ሳያደርጉአቸው መሣሪያቸውን ገፍፈው በነፃ ለቀቋቸው። ጥር 9 ቀን ደግሞ ከሸኖ እያሰሰ የጠላት ጦር ስለመጣ ኡላ ጉራ ከተባለው ቦታ ውጊያ ተካሄደ።

የካቲት 10 ቀን ከአምቦ፣ ከአዲስ አበባና ከሰንዳፋ የጠላት ጦር እንደገና መጣ። ታላቅ ውጊያ ተካሄደ። ላቀው ይፍሩ፣ አሰላ ተመናኘተሀና አሥማር የተባሉ ሦስት አርበኞች ተሰማ ገላን በተባለ ባንዳ ተገደሉ። ስመጥር አርበኞች ነበሩና ተሰማ ራሳቸውን ቆርጦ ለጣልያን በማቅረብ ተሸለመባቸው። የቀረውን አስከሬናቸውን አርበኛው ሊባስ ተክለሃይማኖት ወስዶ ቀበራቸው።

ጠላት በእርቅ ሰበብ የአርበኞችን ልቡና ለማላላት ያደረገው ሙከራ እርቅ መፍረሱን በዚህ አካባቢ የነበሩት አርበኞች ከራስ አበበ ጋር በመላላክ ወዲያው ሰምተው ለጦርነት ተዘጋጁ። ጠላትም ብዛታቸውንና ያሉበትን ቦታ በእርቁ ወራት አጥንቶ ነበርና በፍጥነት ደምስሶ ለመገላገል ጥረት አደረገ።

ጦርነቱ ሚያዝያ 8 ቀን ተከፍቶ እስከ 13 ቀን 1931 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። ነገር ግን ለጠላት አንዳች ውጤት አላስገኘለትም። ከግንቦት 1 እስከ 5 ቀን እንደዚሁ ጥረት አደረገ። አልተቃናለትም። ግንቦት 29 ቀን ያደረገውም ሙከራ ከሸፈበት። እንዲያውም አርበኞች እስከ ምሽጉ ድረስ ገብተው ይወጉት ጀመር። እንዲያውም የክርስትና ጠላ ለመጠጣት ከአንድ ባንዳ ቤት ገብተው የነበሩን አንድ ሻምበልና አንድ መቶ አለቃ ከስምንት ወታደሮቻቸው ጋር ፈጁበት። ይህ አድራጐት በባንዳና በጣልያን መካከል የነበረውን ግንኙነት ለመስበር ሆን ተብሎ የተደረገ መሆኑን ማጤን ይገባል።

ጠላት ከጌዶና ከነቀምት ሌላ ጦር አምጥቶ ከበባ አደረገ። አርበኞቹም ሊባስ ላይ ገጠሙት፣ በጠላትም ላይ ጉዳት አደረሱ። የካቲት 17 እና 20 ቀን ሲጋ በተባለ ቦታ በተደረገ ጦርነት ሁለት ባንዶች ሲገደሉ በድምሩ ስድስት ባንዶች ተማረኩ። የእነ ላቀው ይፍሩ በባንዶች እጅ መገደልና ራሳቸው መቆረጥ የአርበኛውን ደም አፍልቶት ነበርና እንደ ወትሮው በሰላም አልተላቀቀም። ሁሉም በሞት ተቀጡ።

ጣልያን ይህንን የአርበኛ ቡድን ከኢላማው ውስጥ አስገብቶት ነበርና በሰው እያሰለለ፣ ከአዲስ አበባና ከአካባቢው ካሉት ምሽጐች ጋር በሬዲዮ እየተነጋገረ አጥብቆ ተከታተለው። ክፀቻ ጉራንደ ምሽግ ወጥቶ ሊያጠቃቸው

መጣ። አርበኞቹም ጥቅምት 17 ቀን 1932 ዓ.ም ጦርነት ገጥመው ሠላሣ ስምንት ወታደር ገደሉበት። እሱም ይህንን ባየ ጊዜ ተመልሶ ወደ ወጣበት ምሽግ ገባ።

ጠላት አርበኞቹን ለማጥቃት መጣ። እነሱም መጋቢት 19 ቀን 1932 ዓ.ም ቡርቃ በዲሣ ከተባለ ቦታ ጠብቀው ገጠሙት። ኡርጋ ወንዝ ላይ በሚያስደንቅ የጦር ሥልት ወግተው መለሱት።

በአንድ የመቶ አለቃ የሚመራ ጦር በአካባቢው ሲዘዋወር መንዳደር ፋሉ ላይ ታየ። ሜጢ ቆላ ሲደርስ ሚያዝያ 15 ቀን ፊት ለፊት ገጠሙት። የጦር መሪውንና ብዙ ወታደር ገድለው፣ አሥራ አምስት ምንሽር ጠመንጃና አንድ አልቤን መትረየስ ማረኩ። ባላገርም በየጥሻው ውስጥ ከወደቀው የጠላት ወታደር ብዙ መሣሪያ ወሰደ። አሥራ ስድስት በቅሎዎችም ተማረኩ።

ግንቦት 6 ቀን እንጭኔ ጊዮርጊስ፣ ደንሴ ማርያም ላይ ጦርነት ተደርጐ አርበኞቹ ጠላትን አሳፍረው መለሱ። ግንቦት 16 ቀን አልጌ በተባለው ቀበሌ እንደዚሁም ሰኔ 9 ቀን ደብደሌ ወንዝ ላይ ከባንዶች ጋር ግጭት ተደርጐ ባንዶች ዋጋቸውን ተቀበሉ።

የ1932 ዓ.ም ሲጀምር ዘመኑ የነፃነት ወጋገን የታየበት ነበርና የአርበኛው መንፈስ በአዲስ ስሜት ተነሳሳ።

ጥቅምት 3 ቀን 1933 ዓ.ም አደነገዎ ላይ በተደረገው ጦርነት አርበኞች ቀናቸው። ጥቅምት 17 ቀን ደግሞ ከጐጃም የመጣ ጦር ውልሜ አዳበርጋ ላይ ገጠማቸው። በዚህም አርበኞች ቀናቸው። የመጣው የጠላት ጦር ወደ ኋላው ተመልሶ ወለንኮሜ ሠፈረ። የሚሸሸውም የሞቱትና የቆሰሉበትን ወታደሮች ከአገሬው ለመሠወር ከነመሣሪያቸው እየሰበሰበ በእሳት አቃጠለ። ይህኛው ግብር ከሌላውም የመረረ ሆነ።

ህዳር 26 ቀን ሌላ ጦር ከአዲስ አበባና ከሆለታ ቢመጣባቸውም አርበኞችም በልበ ሙሉነት ወጉት። የጦር አዝማቹ በቅሎውን አስማርኮ፣ እሱም ራሱ በሩሉ ገደል ገብቶ በአሳር በመከራ ከሞት ተረፈ።

አርበኞች የጥቂት ጊዜ እረፍት እንደ አደረጉ ልጅ ባዩ ተክለ ወልድ የንጉሠ ነገሥቱን መልዕክትና ፎቶግራፋቸውን ይዘውላቸው ደረሱ። ታላቅ ደስታ ሆነ፣ ልባቸውም ይበልጡኑ ተፅናና። ነገር ግን ልጅ ባዩ ሥራውን በመቀጠል ሲጓዝ ወጀ ዲሬ ከተባለው ቦታ አረጋ ዳዲ በተባለ ከሃዲ ተገደለ። አርበኞች አስክሬኑን አንስተው ለመቅበር ሲሞክሩ ግጭት ተፈጥሮ ብዙ ባንዶች ሞቱ። በዚህም የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ወሬ ይበልጡኑ ተዛመተ። ጥር 1 ቀንም ቀርዩ አዳበርጋ ድረስ የጠላት ጦር መጣ። ነገር ግን ደፍሮ ጦርነት አልከፈተም።

የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት በይፋ እየታወቀ ሲሄድ የአርበኛው ወኔ አየለ። የጠላት ልብ ደግሞ ተሰበረ። ከጐጃም የሸሸው የጠላት ጦር የዐባይን ወንዝ ተሻግሮ ዳገቱን በመውጣት ጐሐ ጽዮን ደረሰ። ሃሳቡ አዲስ አበባ



ከአለው ጦር ጋር ተቀላቅሎ ለመመከት ነበር። ነገር ግን እንደዚያ አልሆነም። ጠላት አዲስ አበባ ላይ ለመዋጋት አስቦት የነበረውን ዕቅድ ተወ። ምክንያቱንም ይህንኑ በሚመለከት በሌላ ምዕራፍ እናየዋለን።[2] አሁን ግን የዚህ ዕቅድ መለወጥ ያስከተለውን ችግር እንመለከታለን።

ይህ ከጐጃም የተንቀሳቀሰው የጠላት ጦር ገብረ ጉራቻ ሲደርስ ተበተነ። አንዱ ቡድን ወደ መርሐቤቴ አመራ፣ አንዱ ደግሞ ወደ ደቡብ አዘቀዘቀ። ሐሳቡ በአዲስ ዓለም በኩል አቋርጦ ተፍኪ ከሚጠብቀው ወገኑ ጋር በመቀላቀል ወደ ጂማ ከዚያም ወደ ጐሬ ለመሄድ ነበር። ነገር ግን አርበኛው እርምጃ በእርምጃ ይወጋው ጀመር። ከሰላሌ አርበኞች ጋር እየተተናነቀ የሙገርን ወንዝ ተሻግሮ ሜጫ ክልል ሲገባ፣ የዚያ አካባቢ አርበኞች በፋንታቸው ይጠዘጥዙት ጀመር።

በአንድ ኰሎኔል የሚመራ ጦር ከገብረ ጉራቻ በሐሮ በኩል አድርጐ አደሞጃ ደረሰ። አርበኞቹም የካቲት 10 ቀን ግንባር ለግንባር ገጠሙት። የማያሳልፉት ሆነ። ወደ ተፍኪ ለመጓዝ የነበረውን ሐሳብ ለውጦ ወደ አዲስ አበባ ተጓዘ። ያለቀው አልቆ የተረፈው አዲስ አበባ ገባ።

አርበኞች የካቲት 17 ቀን አድአ በርጋ የኪዳነ ምሕረትን በዓል በፈንጠዝያ ከአከበሩ በኋላ በማግስቱ የካቲት 17 ቀን ከጐጃም የመጣውን ጦር እየተከታተሉ ሲወጉት ዋሉ። የካቲት 29 ቀን ደግሞ ሌላ አዲስ ጦር ከጐጃም የካ ከተባለው ቦታ ደረሰ። ኤቢሣ ከተባለው ሥርጥ ላይ ገጥመው ወደ አድአ በርጋ እንዳይሄድ አገዱት። እፊት የቀደመውን የጠላት ጦር በማስቃየት ፈጅተው የተቻላቸውን ያህል መሣሪያ አነሱ።

የጠላት ጦር ሌላ አዲስ ጦር ስለደረሰለት ሠፍሮበት ከነበረበት ቦታ ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም ከወደፊቱ ቀድመው ምቹ ቦታ በመያዝ ጐፍላላ አደበርጋ ከተባለው ቦታ ገጠሙት። ጠላትም መንገዱን ለመቀጠል ስለአልቻለ ሠፈር አደረገ። አርበኞቹ ከየካቲት 1 ቀን እስከ 5 ቀን ድረስ ያለ ዕረፍት ወጉት። ጠላት ወደ ጂማ ለመሄድ የነበረውን ሐሳብ ለውጦ የካቲት 6 ቀን 1933 ዓ.ም በበዲና በሙሉ በኩል ወደ አዲስ አበባ አመራ።

መጋቢት 15 ቀን ከዚያው ከጐጃም ሌላ ፈረሰኛ ጦር መጣ። አርበኞቹም ሞጆ ላይ ገጥመው ብዙ ሰውም ፈጁበት። ይህንን ድርጊት የተመለከቱ ባንዶች ከጠላት ገሸሽ አሉ። ወደ ድል አጥቢያ አርበኝነት ገቡ።[3]

መጋቢት 17 ቀን በዚያው መንገድ በአንድ ኰሎኔል የሚመራ ጦር ደረሰ። አርበኛውም የአስተናጋጅነት ሥራውን ቀጠለ። ብዙ የጠላት ሠራዊት ገደሉ። ነገር ግን ኰሎኔሉ የእጅ ቦምብ እየወረወረ በመከላከል አልሞት ብሎ እንደገመሬ ዝንጀሮ እየተጐማለለ አቃተ። አንዲት ነጭ በግ ማስከተሉን አርበኞቹ አጢነው ነበርና እሱን ትተው በግዋን በቅድሚያ ገደሉአት። እሱንም ወዲያው አከታትለው በመተኮስ ገደሉት። ይህም የጠላት መኰንኖች

ከጭንቀታቸው ጽናት የተነሣ በጥንቆላ ሥራ እስከማመን ደርሰው እንደነበር ያሳያል።

ከጉጃም ሲጓዝ ያደረ ሌላ ጦር መጋቢት 26 ቀን ከዚያው ቦታ ደረሰ። አርበኞቹ መንገዱን በጥይት ስለአጠሩበት ግን ገብቶት ሠፈረ። ጦርነቱ መጋቢት 27 ቀን እና 28 ቀንም ቀጠለ። የእንግሊዝ ጦር በገፈርሣ በኩል አልፎ በዱ ከተባለው ቦታ ድረስ መጥቶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ አውለበለበ። የጠላትን የጦር መሣሪያ ከተረከበና አዛገፉን ጄነራል ከማረከ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። የእንግሊዝ መኰንን ወደ አዲስ አበባ ከመመለሱ አስቀድሞ ለአርበኞቹ ንግግር አደረገላቸው። በንግግሩም በትግላቸው ከዚያች ቀን ጀምሮ ነፃነታቸውን ማግኘታቸውን አረጋግጦ፤ የንጉሠ ነገሥታቸውን መምጣት እንዲጠባበቁ ምክር ሰጣቸው።

የድል ጠረን ሲሸታቸው የሜጫ አርበኞች በበኩላቸው የአዲስ ዓለምን ምሽግ መስበር ፈለጉ። ቀደም ብሎ በ1932 ዓ.ም የጀልዲን ምሽግ የመቱበትን ሥልት በማጠናከር ዕቅድ አወጡ። ወይዘሮ ሸዋረገድ ገድሌ የምስጢር ሥራ የማካሄድ ተግባራቸውን አጠናከሩ። ህዳር 21 ቀን የአዲስ ዓለም ማርያም ክብካብ ነው። ማታውኑ ተቃርበው ሌሊቱን በመጓዝ ከከተማው ገብተው በአቶ ዓለማየሁ ቤት ተደብቀው ዋሉ። ህዳር 22 ለ23 አጥቢያ ተዘዋውረው ሁኔታውን አጠኑ። አርበኛው በሙሉ እንዲመጣ ጥሪ ተላልፎ ህዳር 24 ቀን ገባ።

በባላምባራስ /ደጃዝማች/ ዘውዴ ጥላሁንና በልጅ /ጄነራል/ ጃገማ ኬሎ የሚመራው ይህ ቡድን ህዳር 25 ማታ ተዘጋጀ። ጠመንጃ ያለው ጠመንጃውን ፈተሸ። ጆሌው የወይራ ዱላና የክትክታ ቆመጡን አዘጋጀ። ከሁለት ተከፍለው በሁለት አቅጣጫ ተሰማርቶ ሲጠባበቅ ቆይቶ፣ ትዕዛዝ ሲደርሰው ሥራውን ቀጠለ። እሥረኞቹን ከወህኒ ቤት ያለምንም ችግር ማስወጣት ተቻለ። የጦር መሣሪያ መጋዘኑ ተከፍቶ ተዘረፈ። አንድ ኰሎኔልና ሰባ አምስት ጣልያኖች ተገደሉ። አንድ አርበኛ ቆስለው በኋላ ሞቱ። አንድ ገበሬ በጥይት ተመታ። ሌላ ችግር በአርበኞች ላይ አልደረሰም።

ጠላት ጥቂት ከአገገመ በኋላ አርበኞቹን ለመከታተል ተንቀሳቀሰ። እነሱም ነቅተው ይጠብቁት ነበርና ወለንኮሜ ቱሉበቾ ከተባለው ሥፍራ ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ብዙ ሰው ቢሞትና ቢቆስልባቸውም ድሉ የእነሱ ሆነ።

ጠላት በአዲስ ዓለም ምሽግ መሰበር የደረሰበትን ውርደት ለመክፈል በአርበኞች ላይ ተንቀሳቀሰ። እነሱም በመሸሸ ፈንታ ወደ እሱ ገስግሰው ወላንኮሜ ቱሉ በቾ ከተባለው ቦታ ወጉት ጨፈጨፉት። ወደ ማታ ድሉ የእነሱ ሆነ። ጠላትም ወደ ኋላው ተመለሰ።





ልጅ ጃገማ ኬሎ(ከመሃል) ከአርበኞች ጓደቻቸው ጋር።

ፈረስ የያዘ የፋሽስት ጦር ቀደም ብሎ ወደ አምቦ ሄዶ ነበር። በርጋ ከተባለው ወንዝ ሲገባ በባላምባራስ /ደጃዝማች/ ዘውዴ የሚመሩት አርበኞች ገጠሙት። ጦርነቱ ከመጋቢት 24 እስከ 27 ቀን 1933 ዓ.ም ድረስ ቀጠለ። በመዓልትና በሌሊት በተካሄደው ጦርነት ያለቀው አልቆ የተረፈው የጣልያን ጦር አዲስ ዓለም ገባ። ከአዲስ አበባ ለዕርዳታ የመጣውን የጦር ኃይልና ብረት ለበስ አርበኞቹ ተሽከርካሪ ጠዘጠዙት። ከአለፈው የባሰ እልቂት አደረሱበት።


ጠላት ማጣፊያው ስለአጠረበት ባልተሰባበሩት ጥቂት ብረት ለበስ መኪናዎቹ እየተንጠለጠለ ወደ አዲስ አበባ ሄደ። በባላምባራስ /ደጃዝማች/ ዘውዴ ጥላሁን የተመራው አርበኛ አዲስ ዓለምን ሚያዝያ 26 ቀን 1933 ዓ.ም ነፃ አውጥቶ የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ ተከለ።[4]

በልጅ /ጄነራል/ ጀገማ የሚመራው ሌላው የአርበኛ ቡድን ደግሞ ሆለታ ላይ የነበረውን የጠላት ምሽግ ከቦ መተናፈሻ በማሳጣት ከወጋው በኋላ በምሽጉ ውስጥ ገብቶ ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፍ ድራሹን አጠፋው።

እዚህ ላይ አንድ ነጥብ ሊታወቅ ይገባል። የዚህ አካባቢ አርበኞች የጠላትን መንገድ በማጠር ወደ አዲስ አበባ እንዲገባ ያስገደዱት፤ ወደ ጅማ በመሄድ በዛ እንዳይከማች እና በዚያ ታላቅ ጦርነት ለማካሄድ እንዳይቻለው ነው። ዕቅዳቸው አዲስ አበባ ገብቶ እንዲታጐርና በዚያው እንዲማረክ መሆኑ ሊታወቅላቸው ይገባል።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

1. ሙሉሰው ምትኩ፣ *ከሸዋ እስከ ሱዳን*፣ ገጽ 30-32።
2. አዲስ አበባ፣ የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ።
3. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 419-452።
4. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 504-514፡



ልጅ ጃገማ ኬሎ(ከመሃል) ከአርበኞች ጓደቻቸው ጋር።

# ምዕራፍ ሃያ ስድስት
# በመርሐቤቴና ሰላሌ የተካሄደ ትግል

ሚያዝያ 26 ቀን 1928 ዓ.ም የጠላት ወታደር ከደብረ ብርሃን ወደ አዲስ አበባ በሚያደርገው ረጅም ጉዞ ቢታክትም በድል አድራጊነት ስሜቱ ተበረታቶ ሳለ፣ በቀኛዝማች ኃይሉ ማርያም ማሞ የተቀሰቀሰ የተባበሩ የአርበኞች ቡድን ጫጫ ሱኪ ሣራቤ ከተባለው ቦታ ላይ አደጋ ጣለበት። አርበኞች አምስት ካሚዮኖች ሠብረው ስድስት መትረየሶች፣ ብዙ ሣጥን ጥይት፣ መድኃኒቶችና የወታደር ልብስ ነጠቁ። ይህንን በማድረጋቸው ልባቸው ደነደነ። ግንቦት 1 ቀን የተደረገባቸውን ከበባ በቀላል ጥሰው አመለጡ።

ይህ በእንዲህ እንዳለ በእንሣሮ አካባቢ ሌላ የአርበኞች እንቅስቃሴ ተጀመረ። እሱ ደግሞ የሚመራው በልጅ ሥዩም ገብረ ሕይወት ነበር። እነሱም በቆላው ተቀምጦ ጠላት እስኪመጣ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ከደጋው አገር እየወጡ ምሽጉን እየከበቡ መውጫ መግቢያ ማሳጣት እንደሚያስፈልግ አመኑ፤ እንደዚሁም አደረጉ።

በወቅቱ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዘው የጠላት ወታደር በመንገዱ ላይ ያገኘውን ቤት ማቃጠልና ሀብቱን መዝረፍ ያዘ። በባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ የሚመራው የአርበኛ ቡድን ግንቦት 24 ቀን 1928 ዓ.ም ጅሩ ዋዩ ሰከላ ግንባር ለግንባር ጦርነት ገጠመው። ጠላትም ብዙ ሰው ከአስፈጀ በኋላ ሸሸ። ከዚያ በኋላ ለአራት ወር በዚያች አካባቢ ዝር አላለም።

ሐምሌ 23 ቀን 1928 ዓ.ም አሰሌ ጅሩ ምክር ተጀመረ። በምክሩ ላይ እኩሉ ወደ ግንደ በረት ከዚያም ወደ ጠረፍ እንሂድ ሲል፣ እኩሉ ደግሞ ወደ መንዝ ተሻግረን እንዋጋለን አለ። ሁኔታው በአርበኛው መካከል ልዩነት እንዳይቀሰቅስና የርስበርስ ግጭት እንዳያስነሳ ስለአሰጋ በጥንቃቄ ተያዘ። ነገሩም ውሣኔ ሳያገኝ እየተጠና ሰነበተ። ወደ ሣህል አገር ገብቶ ለመዋጋት ያሰበው ታላቁ ቡድን ጋጂ ደምቢ ከተባለው ቦታ ሠፈረ። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው ቡድን ግን በታላቅ ቅሬታ ተሰናብቶ ከእነሱ ተለይቶ ጉዞውን ቀጠለ።

የ1928 ዓ.ም ተፈጽሞ የ1929 ዓ.ም ባተ። የአርበኞችም ኃይል ጥቂት በጥቂት መጠናከር ጀመረ። የጠላት አገባብ በአካባቢው ሕዝብ ላይ የፈጠረው ድንጋጤ ተቀነሰ።

ጣልያን መረሐቤቴ ለመግባትና መራኛ ምሽግ ለመሥራት ሞከረ። በመቶ አለቃ /በደጃዝማች/ ገለታ ቀርቾ አስተባባሪነት የሚንቀሳቀሰው የአርበኞች ቡድን አናስገባም ብሎ መከተ። ጥቅምት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥሞ ተዋጋ። ጣልያን ጦርነቱን በምድር ብቻ ለመግፋት ስለአልቻለ አካባቢውን በአይሮፕላን ደበደበ። በጠላትም በአርበኞችም ላይ ብዙ



ጉዳት ደረሰ። ቢሆንም አርበኞች ሰባት ጠመንጃ ማረኩ። ነገር ግን ጠላት ሙሉ አድሮ እንደአሰበው በዛ ቦታ ላይ ምሽግ ሠራ።

ጥቅምት 11 ቀን ደራ ዱግዳ ላይ ከፍ ያለ ጦርነት ተደረገ። በልጅ /ደጃዝማች/ አበበ ሽንቁጥ የሚመራው የአርበኛ ቡድን አሸንፎ ጠላትን እስከ ምሽጉ ድረስ አባረረው። በዚሁ ቀን ወደ ጅሩ የተሻገረውን ጦር አርበኛው እስከ ደራ ዱግዳ ወግቶ ወደ ኋላ መለሰው። ከቀናት በኋላ ግን የጠላት ጦር እየገፋ ወደ ማሕል አገርና በየገጠሩ መሠራጨት ጀመረ። የጣልያን ጦር በገጠር መሠራጨት የጠላትን ኃይል እንደሚያጠናክር በአንፃሩ ግን የአርበኞችን ኃይል እንደሚቀንስ በጠላትም በወገንም ዘንድ የታወቀ ነበር። በተለይም በየደረሰበት ምሽግ መመሸጉ አሳሳቢ ጉዳይ ሆነ። አርበኛው ይህንን የጠላት የኃይል ግንባታ ለመቋቋም አሰበ።

ስለዚህ ጠላት ዝንጀሮ ውሃ ሲደርስ አርበኛው ህዳር 25 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠመው። ስርጠሰስ ከተባለው ቦታ ቀኑን ሙሉ ጦርነት ተካሄደ። ምንም ጠንክሮ ቢዋጋ የጠላትን ኃይል ጥቂት በጥቂት መቀነስና እርምጃውን በየደረሰበት ማዘግየት እንጂ፣ አርበኛው የጠላት እርምጃ ሊያግደው አልቻለም። ጠላት ግን ከግንደ በረትና ከሜታ ሮቢ ሌላ ኃይል ደረሰለት። በዚህ ሁኔታ ጦርነቱን መቀጠል በወገን ላይ ጉዳት ማብዛት ሆኖ ስለተገኘ አርበኛው ወደ ቆላው አፈገፈገ።

በሌላ በኩል ደግሞ የሰላሌ ሕዝብ መሪ አድርጎ የተከተለው የራስ ካሣን ልጆች ደጃዝማች አበራንና ደጃዝማች አስፋ ወሰን ካሣን ነበር። ነገር ግን እነሱ ወደ ጠላት ለመግባት ማሰባቸው በአርበኛው ዘንድ ጥርጣሬ አሳደረ። ማስረጃም እየተገኘ ስለሄደ ታላላቅ አርበኞችና ሽማግሌዎች፣ ባለቤታቸው ወይዘሮ ከበደች ሥዩም ጭምር ደጃዝማች አበራ ካሣን እንዲያነጋግሩአቸው ተደረገ።

አርበኞችም ታህሣስ 10 ቀን 1929 ዓ.ም ቅዳሜ ጥዋት ደጃዝማቹን አነጋገሩአቸው። እንዲያስተባብሩአቸውም ጠየቁአቸው። እሳቸው ግን ጠላት የፍቼን ከተማ ለመያዝ የወሰነ መሆኑን ገለፁ። በከተማይቱ ላይ መዋጋት ሕዝብ ማስጨረስ መሆኑን፤ ጠላት አንዳች ምክንያት ከአገኘ ሕዝቡን ከመጨረስ ወደ ኋላ እንደማይል አስታወቁ። ከዚህ በኋላ ከተማይቱን ለቅቆ ለመውጣት በጉባኤው በድምፅ ተወሰነ። ደጃዝማች አበራ ፈቃደኞች የሆኑ አሽከሮቻቸውን አስከትለው ከፍቼ ከተማ ወደ ደገም ሄዱ። ቀራ ካራ ከተባለው ቦታ ለመዋጋት ታሰበ። እሱም ሳይሆን ቀረና ሰንበሌጥ ወደተባለው ቦታ ሄዱ። ከዚያም ታህሣሥ 11 ቀን ሰልሚ ደረሱና ጦርነቱ በመርሐቤቴ እንዲሆን በምክር ተወሰነ።

የጣልያን መንግሥት ይህንን እየተረዳ የራስ ካሣን አሽከሮችና ባለምዋሎቻቸውን ከአምስት መቶ የማያንሱ ሰዎች ይዞ አሰረ። "ደጃዝማች አበራ ካሣና ደጃዝማች አስፋወሰን ካሣ እጃቸውን ካልሰጡ እረሽናቸዋለሁ።

ሁለቱ ወንድማማቾች እጃቸውን ከሰጡ ሹሜ ሽልሜ ከአባታቸው ርስተጉልት አስቀምጣቸዋለሁ" አለ። በዚህ ጉዳይ የሕዝቡ ልብ ታወከ። ሁለቱ ወንድማማቾች እጃቸውን እንዳይሰጡ በአርበኞቹ ዘንድ ምክር ተያዘ። ወገኖቻቸው የታሠሩባቸው ደግሞ እጃቸውን እንዲሰጡ ወተወቱ።

*ታህሣሥ* 11 ለ12 አጥቢያ ከነደጃዝማች አበራ ዘንድ ታላቅ የምክር ሌሊት ነበር። ጥርጣሬው ይፋ ወጣ። ክርክሩ ከጣልያን እንግባ፣ የለም ጦርነቱን እንቀጥል የሚል ሆነ። በምክሩ ላይ የተገኙት ሻለቃ /ራስ/ *መሥፍን* ስለሺና ሌሎችም የአርበኛ *መሪዎች* ወደ ጠላት እንዳይገቡ አጥብቀው *መ*ከሩአቸው። ለራሳቸው ለደጃዝማቹ ሕይወት አስጊ *መሆኑን* በማስረጃ ገለፁላቸው። ጠላት ሁለቱ ደጃዝማቾች እጃቸውን ከአልሰጡ የሰላሌን ሕዝብ እንደሚፈጅ አስፈራርቶ ነበርና ደጃዝማቾቹ ለጣልያን እንዲገቡ የሚፈልጉ የአባታቸው አሽከሮች ጭምር ተቃውሞ አነሱ። ሁኔታው ተካርሮ የርስበርስ ግጭት እንዳይፈጠር ከሚያሰስብበት ደረጃ ደረሰ። ደጃዝማቹ ለጣልያን ለመግባት ወሰኑ። አርበኞቹ እንዲሁም ባለቤታቸው ቆራጥዋ ወይዘሮ ከበደች ሥዩም ጥለዋቸው ሄዱ።

ሁለቱ ወንድማማቾች *ታህሣሥ* 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጥዋት ጉዞአቸውን ወደፍቼ ከተማ ጀመሩ። በልበ ሙልነት የወረዱትን ቁልቁለት በተሰበረ ልብ ዳገት መውጣት ሆነባቸው። ከፍቼ ከተማ ገቡ። ጠላት በሰላም ተቀብሎ ለንስሐ ሳያበቃ ሳያውል ሳያሳድር ዕለቱን በተከበሩበት አደባባይ ሁለቱንም ወንድማማቾች በመትረየስ ረሸናቸው።[1] ግራዚያኒም "ወንድማማቾች አበራና አስፋወሰን ካሣ በጦርነት ተማርከው በሰጠሁት ትዕዛዝ መሠረት ፍቼ አደባባይ ላይ በጥይት ተደበደቡ። አገራችን የምትያዘው ስናልቅ ነው ያሉት ቃል ተፈፀመ" የሚል ቴሌግራም ወደ ሞሶሎኒ አስተላለፈ። ይህ አገዳደል ለአርበኞች ትልቅ ትምህርት ሰጠ። ጣልያን ቃሉን የማያከብር ቀጣፊ መሆኑ በይፋ ተገለፀ። የሀገር ፍቅር ከሀገር ጋር የሚኖር እንጂ ከሰው ጋር ተገድሎ የሚቀበር አይደለምና ጦርነቱ ቀጠለ።

ጣልያን ሁለቱን ወንድማማቾች ከገደለ በኋላ፣ አርበኞችን ከአካባቢው ለማጥፋት በሙሉ ኃይሉ ተንቀሳቅሶ አካባቢውን እያሰሰ ጐሐ ጽዮን ደረሰ። አርበኞችም *ታህሣሥ* 28 ቀን 1929 ዓ.ም ረቡዕ ገጠሙት። ነገር ግን አጥብቀው ቢዋጉም ውጤት ማግኘት ሳይችሉ ስለቀሩ ወደ አባይ ቆላና ወደ ሙገር ወንዝ ወረዱ።

ጣልያን በፍቼ አካባቢ እነ ደጃዝማች አበራ ካሣን አስጨንቆ በነበረበት ወቅት፣ በውልጮ ደግሞ አርበኛው ጣልያንን አስጨንቆ ነበር። ጠላት ሕዝቡን እየፈጀ፣ ቤቱን እያቃጠለ፣ ከብቱን እየዘረፈ መጣ። ይህንንም የሚያደረገው ሕዝቡን አስደንግጦ አርበኞችን እንዳይደግፍ ለማድረግ መሆኑ ግልፅ ነበር። ግንደ በረትን ጨርሶ ወደ ደጋው ሲወጣ አረሁ ላይ አርበኛው



*ታህሣሥ* 11 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠመው። በጠላት ላይ ጉዳት ደረሰበት። ስድስት የሊቢያ (ጡሩምቡሌ) ወታደሮች ከብዙ ባንዳዎች ጋር ተገደሉ። ብዙ ምርኮ ተገኘ። ውልጮ አፋፍ ላይ ምሽግ ለመሥራት የነበረውን ሃሳብ ትቶ ሽሽቱን ቀጠለ።

የፍቼው የጦር አዛዥ እንደ እነደጃዝማች አበራ ካሣ ይታለሉለት መስሎት መልዕክቱን አዥጐደጐደ። *ታህሣሥ* 16 ቀን በቀኛዝማች አሸኔ፣ *ታህሣሥ* 20 ቀን ደግሞ በአዛዥ ባህሩ እጅ ላከ። እነሱ ግን ባለማወላወል እምቢታቸወን ገለፁ። እሱም አማላጅ የላከው ጦር እያዘጋጀ ነበርና ለማጥቃት ተንቀሳቀሰ። አርበኞች በበኩላቸው ጠላት የሚገኝበትን ሁኔታ በማጥናት ሌመን ከቀኛዝማች ሣህሌ ምስጋናው ቤት ግብር ሲበላ ጥር 5 ቀን ደርሰው አደጋ በመጣል ጥቃት አደረሱበት። የተፈለገው ዋና ሰው ገደል ተንከባልሎ ቢያመልጣቸውም አስራ ሁለት መውዜር ጠመንጃ ከስምንት ሺህ ጥይት ጋር እንደዚሁም አንድ ጐራዴ ማረኩ። ይህ የአርበኞች ሥራ ከእምቢታቸው ይበልጥ አናደደው። ሌላ ጦር ሠርቶ መጣ። እነሱም እሬሬ ከተባለው ቦታ ግንባር ለግንባር ገጥመው ወግተው ድል አድርገው አባረሩት።

ጠላት እንደገና ለማጥቃት ሌላ ሙከራ አደረገ። አርበኞችም ያያ ቀጨማ ላይ ጥር 11 ቀን ቅዳሜ ከጥዋቱ በአራት ሰዓት ገጠሙት። ጀምበር እስክትጠልቅ ድረስ ወጉት። አሥር ሰዓት ገደማ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የገዛ ቤታቸውን እሳት ለኩሰው ከሰዎቻቸው ጋር ቦታ ይዘው ጠበቁት። ጠላት ቤቱን ያቃጠለው የእሱ ወታደር መስሎት ሲገሰግስ ደረሰ። እሳቸውም ለወሬ ነጋሪ ሳያስተርፉ ጨረሱት። በጠላት ወገን አዝማቾች ሆነው የመጡትም ጀነራል ትራኪያ፣ ጀነራል ፍጃና ኩሎኔል ሮሰኒ ስለነበሩ የእነሱ መገደል ውርደት ሆነበት። አርበኞችም ድል አድርገው ከዚያው ሰነበቱ።

ጠላት በዚህ ቁጭት ሌላ ፈረሰኛ ጦር አመጣ። አርበኞችም በዚሁ ያያ ቀጨማ ከተባለው ቦታ ሳይነቃነቁ ጠብቀው ጥር 21 ቀን ረቡዕ ገጠሙት። አሥራ አምስት ሰው ገድለው ድል አድርገው አባረሩት።

*ታህሣሥ* 12 ቀን ተጀምሮ የነበረው ምክር ሲብላላ ሰንብቶ ነበርና ጅሩ ላይ ቀጠለ። በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከስምምነት ተደረሰ። ዋና ዋናዎቹ ነጥቦች፣

- በቀለብና በስንቅ አርበኛው እንዳይጐዳ ማድረግ፣
- ሕዝቡን እርስበርሱ ማስማማት፣
- እንደ ልቤ ልሁን ባይን ሥርዓት ማስያዝ የሚሉ ነበሩ።

ከዚህም በስተቀር አርበኛው በየአለቃው እየተዳደረ አንዱ ሌላውን እየረዳ እንዲሠራ፣ የጦር አለቆች በበላይነት እንዲመሩ ተወሰነ። አለቆችም ተመረጡ። የተመረጡትም አለቆች ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይና ሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሽ ነበሩ።

የወታደሩ ቀለብ ጉዳይ ከሁሉም በላይ አሳሳበ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ይህንን ችግር በተመለከተ ሐሳብ አቀረቡ። ሐሳቡም የራሳቸው አባት እንደዚሁም የደጃዝማች መሸሻ ወልዴ ሀብት ለአርበኛው ይሰጥ የሚል ነበር። ሁለቱም ባለሀብቶች የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ስለነበሩ ሐሳቡ ድጋፍ አገኘ። ሃሳቡ ተቀስቅሶ የነበረውን የውስጥ ልዩነት አቀዘቀዘው።

ከዚህ ውሳኔ ላይ ከተደረሰ በኋላ አርበኛው በደጃዝማች መሸሻ ቤት ላይ ከበባ አድርጎ ጥር 22 ለ23 ቀን 1929 ዓ.ም አጥቢያ ሌሊት ተኩስ ተካሄደ። ደጃዝማች ጥዋት ተያዙና በጥበቃ ሥር ቆይተው ለፍርድ ሲቀርቡ፣ ለቀረበላቸው ጥያቄ ተገቢና ትክክለኛ መልስ አለመስጠቻው የአርበኛውን ቁጣ አባባሰ። ሥራቸው ሲመረመር ጠላትን ደስ ለማሰኘት ሲሉ ዘጠኝ የሀገር ተጋዳዮች እየያዙ በገበያ ላይ መስቀላቸው በማስረጃ ተረጋገጠባቸው። ሌሎች ሃያ ዘጠኝ ተጋዳዮች ከቤታቸው ውስጥ አስረው ተገኙ። በቤታቸው ውስጥ ብዙ ወርቅና ብር፣ ከጠላት የተቀበሉት ብዙ ሣጥን አረቄ ተገኘ። በሕይወት ይኑሩ የሚል ሰው ታጣ። ይህም ሁሉ ሆኖ አርበኛው እጁን አላነሳባቸውም። ፍርድም አልፈረደባቸውም።

ደጃዝማች መሸሻ በጥበቃ ሥር እንደአሉ ልጃቸው የጣልያን ጦር ይዞ ለዕርዳታ ደረሰ። ጦሩ ከሰላሌና ከደብረ ብርሃን ነበር። ከአርበኛው ጋር ለስድስት ሰዓት የቆየ ውጊያ አካሄደ። ጠላት እንደ አሰበው ደጃዝማች መሸሻን ማስለቀቅ ሳይችል ወደየመጣበት ተመለሰ። ነገር ግን በጦርነቱ ላይ ብዙ ሰው ሞተ፣ ሌላ ብዙ ቆሰለ። ይህ ሁኔታ የአርበኛውን ቁጣ እንደገና ቀሰቀሰው። የደጃዝማቹን ሕይወት ማዳን አልተቻለም። ገና ፍርድ ሳይሰጥ ሠራዊቱ በጉራዴ በጣጥሶ ጣላቸው።

ጠላት እንደገና ሌላ ጦር አሠናድቶ ለማጥቃት መጣ። አርበኞች የካቲት 3 ቀን 1929 ዓ.ም መረሬ ከተባለው ቦታ ገጥመው ወጉት። እሱም ተዘጋጅቶ የመጣበት ጉዳይ ነበርና አርበኞቹን ለመፍጀት ከበባ አደረገ። አርበኞቹ ሦስት መቶ ስድሣ የጠላት ወታደር ገድለው ከበባውን ሰብረው በሙውጣት ከሰላሌ ወደ አዳበርጋ መሬት ሲሻገሩ፤ የጦር መሣሪያ ምርኮ መሰብሰቡ ሥራ እስከ አሥራ አምስት ቀን ዘለቀ።

የካቲት 10 ቀን ኖሌ ከሚባለው ቦታ ጠላት አደጋ ጥሎ ብዙ ሰው ገደለ ብዙም ማረከ። ቢሆንም ዋናው አርበኛ ቡድን ከበባውን ሰብሮ አመለጠ። በማግሥቱ የካቲት 11 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ ሌላ ጦር እንደገና መጣ። አርበኞች ሙገር በቾ ጉንጋ ከተባለው ቦታ ወግተው ድል አድርገው አባረሩት። ጠላት በዚያ አካባቢ የነበረውን አርበኛ ለመደምሰስ ጥረት በማድረግ ላይ እንደአለ በግራዚያኒ ላይ የተጣለው አደጋ በሬዲዮ ተሰማ። በድንጋጤው ጽናት የተነሣ የጀመረውን ሥራ ትቶ ከአዲስ ዓለም የመጣው የጠላት ጦር በግራር በኩል አቋርጦ ወደ ፍቼ ሲሄድ፣ ከአዲስ አበባ የመጣውም ከበቾ ውጊያ ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ።



ቢሆንም ጠላት አርበኞችን አድኖ ለማጥፋት የያዘውን ሥራ ስለቀጠለ፣ አርበኞችም ትግላቸውን ቀጠሉ። የካቲት 24 ቀን 1929 ዓ.ም ጀነሌ ማርያም ጦርነት ተደርጎ ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው ሞተ ቆሰለም።

በሌላ በኩል ደባ ላይ ሠፍሮ የነበረው የኢጣልያ ጦር የኮላሽን አምባ ለመያዝ ተንቀሳቀሰ። አርበኛው ደግሞ ይህቺን አምባ ላለማስያዝ አሰበ። ይህቺ አምባ ስመጥር ስለሆነች የእርስዋ መያዝ ሀገሩን ተስፋ ከማስቆረጡም በላይ በዚያ አካባቢ የሚካሄደውንም የጦርነት ሚዛን ወደ ጠላት እንዲያዘነብል የሚያደርግ ነበር። ስለዚህ በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ ክብረ ሥላሴ የሚመራው አርበኛ ከየካቲት 16 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ለስምንት መዓልትና ሌሊት ተዋጋ። አርበኛው የጠየቀው ዕርዳታ ሳይደርስለት ጠላት ተጨማሪ ጦር ስለአገኘ ጥሶ ገባ። ኮላሽ ተያዘች። ከሁለቱም በኩል ብዙ ሰው አለቀ።

በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የሚመራው አርበኛ ደግሞ መጋቢት 18 ቀን 1929 ዓ.ም ከደብረ ብርሃን የመጣውን የጠላት ጦር ደዶቴ ላይ በድንገት ገጠመው። ጠላትም ሰባት የውሃ መትረየስ ጠምዶ፣ በከራ አባ ገሙ በኩል ደግሞ አንድ ሺህ ፈረሰኛ አስነስቶ ተዋጋ። ምንም ኃይሉ ከባድ ቢሆን አርበኞችን መቋቋም ስለአልቻለ ወደ መጣበት ተመለሰ። ነገር ግን ጠላት በዚህም አልበቃውም። በማግስቱ መጋቢት 19 ቀን እንደገና ገጠማቸው። ያንለትም ቢሆን አልቀናውም። ቢሆንም ሰው ስለተጎዳ አርበኞች ወደ ጠፊት ጋራ ተሻገሩ።

አርበኞች ሁሞ፣ ሞረት እንደአሉ የጣልያን ጦር መጣ። በእግር ጦር ብቻ መቋቋም እንደማይቻለው አውቆ አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበ። አርበኞች እግረኛውን የጠላት ጦር መጋቢት 26 ቀን 1929 ዓ.ም የደብረ ዘይት በዓል በሚከበርበት ዕለት ገጠሙት። ጦርነቱ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ጀምሮ እስከ ስምንት ሰዓት ቆየ። ጠላት የሚመረጠውን ቦታ ይዞ ነበርና ተጠቀመ። ብዙ አርበኞችንም አበላሸ። ድፍረት በመብዛቱም ምክንያት ብዙ ሰው አለቀ። የአርበኛው እንቅስቃሴ ለመድፍና ለመትረየሱ የማይሳት ዓላማ ሆነ። ጊዜው ደግሞ ፆም ስለነበር ራብና ጥማቱም የዚያኑ ያህል ጉዳው። መጋቢት 26 ቀን በእንዲህ ተውሎ በማግስቱ ደግሞ ጠላት የደባን በር አልፎ ከበሩ ላይ ተጠባባቂ ጦር አድርጎ ጠበቃቸው። ነገር ግን በጦርነት ጥሰውት አለፉ።

አርበኛው በዜና ማርቆስ እንዳለ ጣልያን በኰሎኔል ጋሬሊ እና በሻለቃ ጀርዳም መሪነት ከአሥራ አምስት ሺህ የማያንስ ሌላ ጦር ከሰላሌና ከደብረ ብርሃን ላከ። አርበኛውም ሚያዝያ 10 ቀን 1929 ዓ.ም ደረት ለደረት ገጥሞ ተዋጋው። ጦርነቱ ቀኑን ሙሉ ውሎ እስከ ሌሊቱ አምስት ሰዓት ቆየ። በጠመንጃ ብቻ አልተወሰነም፤ በጨበጣ እና በስለት ጭምር ሆነ። በአንድ ወቅት ቅልቅሎሹ ስለበትም ሳይመች ስለቀረ በሰይፍ ጭምር ከጠላት ጋር ተሞሻለቀ። ምርኮው እጅግ ብዙ ሆነ። ሁለት ትልልቅ መድፍ፣ አንድ

ፊያት ነጭ መትረየስና ሌሎች ድግን መትረየሶች፣ ብዙ አልቤን ጠመንጃና ጥይት ተማረከ። አንድ አይሮፕላን በጥይት ተጣለ። በውስጡ የነበሩት ሰባት የጠላት ወታደሮች ከተማረኩ በኋላ አርበኞችን ተንኩሰው ኖሮ እንደ አልሆነ ሆኑ። አንድ ሻለቃና አንድ መቶ አለቃ ጣልያናውያን ከብዙ ወታደሮቻቸው ጋር ተገደሉ።

በማግስቱ ሚያዝያ 12 ቀን 1929 ዓ.ም አርበኞች ጠላትን ማጥቃት ቀጠሉ። ካቢ ጥግ የነበረውን የጠላት ጦር አበረሩ። እንደዚሁም ጉናት ከተባለው ሠርጥ ላይ አርባ ባንዶች ማረኩ። አሥራ ስድስቱ ዕለቱን ጉዳያቸው ተመርምሮ ስለተፈረደባቸው በጥይት ተደበደቡ። የፍርዱ ሥራ በማግስቱም ቀጥሎ ሌሎቹ ሁሉ በጥይት ሲደበደቡ አንድ ብቻ አመለጠ።

አዳበርጋ አቤሣ ከተባለው ቦታ ከፋ ገደ ከተባለው ቀንደኛ ባንዳ ላይ ሚያዝያ 2 ቀን 1929 ዓ.ም አርበኞች አደጋ ጥለው አምሣ የመውዜር ጠመንጃና ሁለት ፍሻሌ ሽጉጥ ማረኩ። ትንሣኤንም ከዛው ሰው ቤት ዋሉ። ይህ በእንዲህ እንደአለ በሁለት የመቶ አለቆች የሚመራው የጠላት ጦር መጣ። አርበኞችም ሚያዝያ 22 ቀን ዓሊ ዲራ ከተባለ ቦታ ገጥመው በመትረየስ በማግለብለብ ወደ ኋላው መለሱት። ከጠላት ወገን ሠላሣ ወታደሮች ሲሞቱ በአርበኞች ላይ የደረሰ ጉዳት አልነበረም።

የዚህ ጦር አመጣጥ ምክንያት አርበኛውን ስለ አስገረመውና ስለ አስገነገነው፣ ጓዝ ለመጠበቅና ደጀን ለመሆን ከኋላ ቀርቶ የነበረው አርበኛ የከፋ ገዳን ቤት ፈተሸ። የጠላት ዕርዳታ እንዲደርስለት ስለመጠየቁ ማስረጃ አልተገኘም። ሌላ አስገራሚ ነገር ግን ተገኘ። እሱም ስለሀገራቸው የመቆርቆር ስሜት ያላቸውን ሰዎች ሁሉ እየተከታተሉ በስቅላት የሞት ፍርድ ለመፈፀም የሚያስችል ሥልጣን ለከፋ ገዳና ለወርዶፋ ቆርቾ ጠላት የሰጠበት ወረቀት ከቤቱ ተገኘ። በዚህ አርበኛው ተቆጥቶ የከፋ ገዳን ቤተሰብ በሙሉ ገድሎ ቤቱን አቃጠለው።

ጠላት ሌላ ከበባ አካሄደ። ጦሩ ባንዳ ቢበዛውም በሁለት ጣልያናውያን ኮሎኔሎች ስለተመራ ቀላል አልነበረም። አርበኞችም ምንም ቀኑ ማዕዶት ቢሆንና ቀደም ብለው በአካሂዱአቸው ጦርነቶች ገና ያላገገሙ ቢሆኑ፣ አይተው ሊተውት አልፈለጉም። ሚያዝያ 23 ቀን ከጥዋቱ በአምስት ሰዓት ላይ ያያ ሐሮ ከተባለው ቦታ ገጠሙት። ጠንክረው ተዋጉ። ነገር ግን ጠላት አየለና ከመካከላቸው ገብቶ በታተናቸው።

ቢሆንም የአርበኛው ጦር ከተበታተነበት ተሰብስቦ ተማከረ። ጦሩ በአንድነት መንቀሳቀሱ ጠላትን ለማጥቃት ምቹ ሆኖ ሳለ፣ ሌሎች ችግሮች ስለ መኖራቸው በምክክሩ ወቅት ላይ ተረዱ። ከእነዚህም አንዱ የማንኛውም አካባቢ ገበሬ ብዙ ሠራዊት ለብዙ ጊዜ እየቀለበ ለማኖር መቸገሩ ሲሆን፣ ሌላው ችግር ደግሞ ጠላት በአየለ ጊዜ ሁሉንም የመደምሰስ ዕድል ማግኘቱ ነበር። የርስበርስ አለመስማማትም አልታጣም። በእነዚህ ምክንያቶች



አርበኛው ወደ ልዩ ልዩ ቦታ እንዲከፋፈል ተወሰነ። አንድ ቡድን ወደ መርሐቤቴ ተሻገረ። ሌላው ደግሞ ወደ ግንደ በረት ሄደ።

ግንቦት 1 ቀን 1929 ዓ.ም ባንዶች ለእርዳታ የመጡ አርበኞች በመምሰል ቀርበው በድንገት አደጋ በመጣል በአርበኛው ላይ የሞትና የመቁሰል አደጋ አደረሱ። በመሆኑም ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ግራ አይናቸውንና ቀኝ እጃቸውን ተመቱ። ጦርነቱን መቀጠል ስለአልተቻለ አሽከሮቻቸው ወደ ሙገር ቆላ አውርደው ማስታመም ያዙ።

ጠላት የቀኛዝማች ኃይለማርያምን ሁኔታ በሰላዮች አማካኝነት ሰምቶ ጦር አሠናድቶ ወደዛው ዘመተ። አርበኞቹ ምክር አድርገው ከመዋጋት ይልቅ የአለቃቸውን ሕይወት ማዳን እንደሚብስ ስለተገነዘቡ በበቅሎ አስቀምጠው እየደገፉ ወደ ገርቢ ከዚያም ወደ አደበርጋ መዳሌ ወሰዱአቸው። ከዚያም ተበታትኖ የነበረው አርበኛ እንዲሰበሰብ ጥሪ ተላለፈና ከስምንት መቶ በላይ ሠራዊት ተሰበሰበ። እሳቸውም ማገገም ጀመሩ። የአርበኛው መንፈስም እንደገና ተጠናከረ። ቀኛዝማች ለማነጣጠር ይረዳኛል በማለት በግራ ዓይናቸው መቁሰል ቀለዱ። ነገር ግን የቀኝ እጃቸው መመታት እንደዚህ የሚያዋዛ አልነበረም።

ጠላት የኮላሽን ምሽግ በምን ዓይነት ትግል እንደያዘ ቀደም ብለን ተመልከተናል። የዚህ አምባ መያዝ እንደተፈራው የአርበኛውን ሞገስ ቀነሰ። ኃይሉንም የሚያዳክም ሆነ። ስለዚህ አርበኛው ምሽጉን ለማስለቀቅና አካባቢውን ከጠላት ቁጥጥር ነፃ ለማድረግ አሰበ። አስቦም አልቀረ ጥር 19 ቀን 1929 ዓ.ም በምሽጉ ላይ አደጋ ጣለ። ነገር ግን ሙከራው የታሰበውን ውጤት ሳያስገኝ ቀረ፤ ብዙ ሰውም ተጐዳ።

ጠላት በዚሁ ወር በግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም ሚዳ ላይ ወ/ሮ ከበደች ሥዩምን ከበበ። በመቶ አለቃ /ደጃዝማች/ ገለታ ቆርቾ የሚመራው አርበኛ ፊጥኖ በመድረስ ጋፋች ከተባለው ቦታ ከቀኑ በስድስት ሰዓት ገጠመው። ጦርነቱም እስከ አሥራ ሁለት ሰዓት ተኩል ቆየ። ብዙ ባንዳ አለቀ። በአርበኞች ላይ የደረሰው ጉዳት መጠነኛ ነበር። በዚህ ሁኔታ ወይዘሮ ከበደችን ከምርኮ ለማዳን ተቻለ። እሳቸውም ታሪኩ አበራ የተባለውን ልጃቸውን ወረግቡ ነበሩና ማጓጓዙ ቀላል አልነበረም። አርበኞች ለማጥቃት ሲቃረቡ ጠላት በአንድ ወገን ሰብሮ በመውጣት አመለጠ። አርበኞች በማግስቱም ማጥቃታቸውን ቀጥለው ቅቤና ከተባለው ቦታ ተዋጉ። በዛም ብዙ ባንዳ ሞተ። ጥቂት አርበኞች ወደቁ። ወይዘሮ ከበደችም ጠላት ለመታረቅ ያቀረበላቸውን ጥያቄ ረግጠው ከአርበኞች ጋር ሰኔ 3 ቀን ጉዞ ጀመሩ።

ይኸ በእንዲህ እንዳለ ሌላ የጠላት ጦር ቤቱንና ቤተክርስቲያኑን እያቃጠለ፤ የራያ ሠራዊት አስከትሎ ወንዱን እያሰለበና የሴቱን ጡት እያስቆረጠ መጣ። አርበኞችም ኢዲዎ ከተባለው ቦታ ግንቦት 25 ቀን 1929

ዓ.ም ግንባር ለግንባር ገጥመው ወጉት። በጦርነቱም ላይ አራት ከጠላት ወገን በኩል የዘመቱ ከነለበን ጠመንጃዎቻቸው ተማረኩ። ምርኮኞቹም በጠላት ተገድደው ከመዝመት በስተቀር ሌላ በደል ፈጽመው ስለአልተገኙ መሣሪያቸውን አስረክበውና ምክር ተቀብለው በሰላም ተለቀቁ።

በዚሁ ጊዜ የጠላት ጦር በሌላ ግንባር በባላምባራስ /ራስ/ አበባ ላይ ዘመተ። እሳቸውም እነዋሪ ላይ ገጥመው ተዋጉት። በታንክና በአይሮፕላን እየተደገፈ የሚዋጋቸውን የጠላት ጦር ስምንት ቀን ሙሉ መክተው ተዋጉት፤ ድልም አደረጉት። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ምንም ለጊዜው ድል አድርገው ቢመልሱት ሌላ ጦር ሠርቶ እንደገና እንደሚመጣባቸው በማወቅ ወደ መርሐ ቤቴ ተሻገሩ።

የቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞን መቁሰል ቀደም ብለን ተመልክተናል። ጠላት ይህንን ተረድቶ አዲስ ጦር ሠርቶ መጣባቸው። እሳቸውም ከመሸሽ ይልቅ መዋጋት መረጡ። በአልጋ እስከ ጦርነቱ ቦታ ድረስ ውሰዱኝ ብለው ግንቦት 26 ቀን 1929 ዓ.ም ዲሬ ከተባለው ቦታ ገጠሙት። ሠራዊታቸው አንድ መትረየስ አስጨብጦ አንድ ወታደር ጠባቂ ትቶላቸው ከጦርነቱ ገብቶ በኃይል ተዋጋ። ሁለት ጣልያናውያን ሻምበሎች ገድሎ፣ አንድ የወሬ ማስተላለፊያ ሬዲዮና ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ በብዛት ማረከ። የዚያ አካባቢ ሕዝብ አርበኝነቱን ማጠናከር የቻለው በዚህ ቀን በማረከው መሣሪያ ነው። ጠላትም በበኩሉ ብዙ ሰው ገደለ፤ አቆሰለ። አቶ ገብረፃድቅ ጀፈሴ የተባለውን አርበኛ ማረከ። ነገር ግን ሊገድለው ሲዘጋጅ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ ግዛው የተባሉ ጓደኛው ገስግሰው ደርሰው ሊገድለው የነበረውን ጠላት ገድለው አስለቀቁት። ጓደኛ ይሏል እንደዚህ ነው።

ወደ ዋናው ታሪክ ስንመለስ ጠላት ብዛ ጦር አስከትቶ በቁርጥ በቁርጥ ከፋፍሎ በሌላው የአርበኛ ቡድን ላይ መጣበት። በሻለቃ /ራስ/ መሥፍን ስለሺ የሚመራው አርበኛ ግንቦት 25 ቀን 1929 ዓ.ም ይድና በተባለው ቦታ ገጠመው። ከቀኑ ከስድስት ሰዓት እስከ ፀሐይ ጥልቀት ወግቶ ብዙ ጣልያኖች ፈጅቶ፣ ድል መትቶ አባረረው። የንጉሠ ነገሥቱ ባለምዋል የነበረው ቀኛዝማች ተክለ ማርቆስ ከጠላት ጉን ሆኖ ሲዋጋ ውሎ ቆስሎ አመለጠ።[2]

እዚህ ላይ አንድ የታሪክ ማስታወሻ ላክል። የአርበኞችን መልእክት ይዘው ቀጬማ ከተባለው ቦታ ተነስተው ሲጓዙ፤ ከሆለታ የዘመተ የጣልያን ጦር ግንቦት 2 ቀን ማረካቸው። በዚህ ጊዜ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ በጥርጣሬ በመከታተል ከቦታው ደርሰው በጠላት ላይ አደጋ በመጣል ምርኮኞቹን አስለቀቁ። በተካሄደው ውጊያ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላለኝ ራሳቸው ቆሰሉ። አርበኞች ጓደኞቻቸው ደርሰው የተጧጧፈ ጦርነት ተካሄደ። ጠላት ድል ሆኖ ሲሸሽ አሥራ ሁለት ወታደሮች ከነመሣሪያቸው ተማረኩ።



እንደዚሁም ሌላ አሥራ ሁለት ጣቃ ካኪ ተማረከ። ለባንዳ መስበኪያ የተጫነ ነበር። ምርኮኞቹ መሣሪያቸውን አስረክበውና ምክር ተቀብለው ተለቀቁ።

ጠላት ከመርሐ ቤቴ ወደ ግንደ በረት የሚሻገረውን አርበኛ ለመደምሰስ ገሠገሠ። በመቶ አለቃ /ደጃዝማች/ ገለታ ቆርቾ የሚመራው አርበኛ የጀማና የወንጭት ወንዞች ከሚገናኙበት ቦታ ሰኔ 1 ቀን 1929 ዓ.ም ደርሶ አደጋ በመጣል ወጋው። ከጠላትም ከአርበኞችም ብዙ ሰው ሞተ። በዚህ ውጊያ ላይ ብዙ አርበኞች በጠላት እጅ ቢማረኩም፣ ጠላት እነባላምባራስ /ራስ/ አበበን የመከታተልና የማጥፋት ዓላማውን ለማደናቀፍ ተቻለ።

ሰኔ 7 ቀን 1929 ዓ.ም ጠላት አርበኞችን ለማጥቃት ስለመጣ፣ አርበኞች ጸሎታ ከተባለው ቦታ ሊገጥሙት ተዘጋጁ። ነገር ግን ጠላት ሁኔታውን በመገምገም ተኩስ ሳይከፍት ወደ ኋላው ተመለሰ። ይህ ሁኔታ ከታሪክ ውስጥ የሚጠቀስበት ሌላ ምክንያት ስለአለ እንጂ የጠላትን ፍርሐት ለማሳየት ብቻ አይደለም። በዚሁ ቀን አርበኞች የሠፈሩት ወይዘሮ አዩ አንበሳ ቤት ነበር። ይህቺ ሴት የጠላትን መምጣት በሰማች ጊዜ "ከወንዶቹ ቤት ሲቀመጡ ያልነካቸው አሁን የሴት ቤት ነው ብሎ አገሩን ለመዝረፍ ነው የመጡት" ብላ ሰማንያ አንድ የታጠቀ ወታደር ይዛ ከሞቀ ቤትዋ በመውጣት ከአርበኞቹ ጋር ተቀላቀለች።

ከመርሐቤቴ ወደ ግንደ በረት ከዚያም ወደ ወለጋ ሊሄድ የአሰበው የአርበኞች ቡድን፤ ሰላሌ ውስጥ በየደረሰበት ግጭትና ጦርነት አጋጠመው። ሰኔ 9 ቀን 1929 ዓ.ም ጀርሶ በር ላይ፣ ሰኔ 10 ቀን ደግሞ ወቦ ከተባለው ቦታ፣ እንደዚሁም በማግስቱ ሰኔ 11 ቀን 1929 ዓ.ም በቀኝደኛ ባንዳ ቤት ላይ አደጋ ተጥሎ ከነልጆቹ ተያዘ። ከተለያዩ አርበኞች ላይ እየታለለ የገፈፈው የመውዜር ጠመንጃ፣ ሦስት በሩቅ የሚያሳዩ መነጽሮችና ሁለት አውቶማቲክ ጠመንጃዎች ተማረኩ። በርካታ አርበኞች ስለነበሩ በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የሚመራው ጦር ተጠናከረ። ዓለማየሁ ካሣ የተባለውን አርበኛ ሰላሌ ላይ ገድሎ ጠመንጃውን ቀምቶ ይኖር የነበረው ደምሴ መርሻ የተባለው ባንዳ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በተተከለበት ጉባኤ ጥፋቱ ስለተረጋገጠበት በፍርድ ተገደለ። እነ ወርደፋ ቆርቾ ግን ጠመንጃ ከመንጠቅ በስተቀር ሰው ስለአልገደሉ አልተገደሉም።

በቾ ጉረንዳ በተባለው ቦታ ሠፍሮ የነበረውን የጠላት ጦር አርበኞች ሰኔ 24 ቀን 1929 ዓ.ም አደጋ ጣሉበት። በጦርነቱ ሁለት ሻምበሎች፣ ሁለት የመቶ አለቆች፣ አንድ ሃምሣ አለቃና አንድ ወታደር ጣልያናውያን ተገደሉ፤ ብዙ ባንዳ ሞተ። ነገር ግን የባንዳው ሞት ከቁጥር አልገባም። ባንዳዎችም በፉንታቸው በሚያውቁት ቦታ ከጀርባ ዞረው በአርበኛው ላይ መጠነኛ ጉዳት አደረሱበት።

ጣልያን በዚህ ወራት ዘዴ አድርጎ የያዘው ወንዱን ብልቱን የማሰለብና ሴቷን ጡቷን ማስቆረጥ ነበር። ለዚሁ ብሎ ከራያና አዘቦ ብዙ

ባንዳ መልምሎ ጨቤ እያስታጠቀ፣ ጠመንጃ ከያዘው ወታደር ኋላ አሰልፎ ነበር። የዚህ ቡድን ተግባር ሰላማዊውን ሰው ከላይ እንደተገለጸው በመስለብ፣ አብያተ ክርስቲያናትን በማቃጠል እምነቱን መደምሰስ ነበር። ሁኔታው እጅግ መራር ሆነ። እንደዚህ ያለ እልቂት ሲካሄድ እያዩ ዝም ማለት አልተቻላቸውምና፤ የመርሐቤቴ አርበኞች ሰኔ 11 ቀን 1929 ዓ.ም ግንባር ገጠሙት። የዚህ የሰለባና የጡት ቆረጣ ፕሮግራም ኃላፊ የነበረው ሼህ ሡልጣን፣ ኩሬ ውሃ በተባለው ቦታ ተማረከ። ያካሄደው የጭካኔ ሥራ ከባድ ስለነበር ፍርዱ ቀላል ሆነ። አላከራከረም፣ ዋጋውን እለቱን አገኘ፤ ተገደለ። ዘርፎት የነበረውም ንዋየ ቅድሳት ለየባለመብቱ ቤተክርስቲያን ተመለሰ።

የሸዋው ባንዳ ከልቡ እንዲዋጋለት ሲል ጣልያን ፊታውራሪ አያሌውን ደጃዝማች ብሎ ሾመው። አያሌውም ሺህ ያህል ሰው ሰበሰበለት፤ በርትቶም ተዋጋለት። አርበኛው ደግሞ ከዚህ ከሃዲ የሚገላገልበትን መንገድ ፈለገ። ከቺሣ ከተባለው ቦታ ሰኔ 19 ቀን 1929 ዓ.ም ጦርነት ገጠመው። አያሌው ይዞት የመጣውን አንድ ሺህ ባንዳ ይዞ ተዋጋ። ነገር ግን ሊያጠቃም ሊያመልጥም አልቻለም። ተገድሎ፣ ተቆርጦ በገበያ ላይ ተሰቀለ። ብዙ ባንዳም ሞተ፣ ቆሰለ። የተረፈውም ተበተነ። ከአርበኞችም በኩል ጥቂት ሰው ሞተ፣ ቆሰለ።

ዋናው የጣልያኖች መሣሪያ ራስ ኃይሉ ነበረ። እርሱም መጠሪያውን ወልዱ ለንጉሥ ተክለ ሃይማኖት አሰኝቶ ነበር። የነጩ መኰንንና ወታደሮች ከኋላ ደጀን ሆነው፣ እርሱን ከፊት አስቀድመው ከጐጃም ዓባይን ተሻግረው መጡ። ምንም ሠራዊታቸው ቢበዛ መመከት አልቻሉም። ሙገር ላይ ግጥሚያ ተደርጎ አርበኛው አሸነፈ። በዚሁ ጊዜ በባላምባራስ /ራስ/ አበበ የሚመራው ቡድን ሜታ ላይ ተዋግቶ ተመሳሳይ ድል አገኘ።[3]

ጳጉሜን 3 ቀን 1929 ዓ.ም ጠላት ሌላ አዲስ ጦር አሠናድቶ መጣ። የነጭ ወታደር በብዛት ያለበት ነበር። የነጭ ወታደር የበዛው የባንዳ መግተልተል ምንም እንደማይፈይድ በጠላት ዘንድ እየታወቀ በመሄዱ ሳይሆን አልቀረም። አርበኛው ይህንን ጦር ጅሩ ኩሣያ ከተባለው ቦታ ገጠመው። ጠላትም እንደልማዱ ሰባት አይሮፕላን አስነስቶ አስደበደበው። ነገር ግን አርበኛው አልተበገረለትም። አሳሩን አሳይቶ አባረረው። እሱም ሬሣና ዕቃውን እያዝረከረከ ወደ ፍቼ ሄደ።

መስከረም 4 ቀን 1930 ዓ.ም የፍቼው የጠላት ጦር የደብረ ብርሃኑን ጨምሮ መጣ። አርበኞቹም ቦታ ቦታ ይዘው አንጥፈው በመጠበቅ አደጋ ጣሉበት። የደገምን ተራራ ተተግነው ጉዳት አደረሱበት። የሌመንን ወንዝ እንዳይሻገር ከለከሉት። እሱም አመጣጡ ሳያዩት አደጋ ጥሎ ለማጥቃት እንጂ ለመዋጋት አልነበረምና ሸሽቶ ወደ መጣበት ተመለሰ።



ጠላት ሌሊቱን ሲገሠግስ አድሮ መስከረም 10 ቀን ጥዋት ሚልኪ ከተባለው ቦታ ደረሰ። አሁንም የጠላት ሀሳብ በአርበኞች ላይ አደጋ ለመጣል እንጂ በእሱ በራሱ ላይ አደጋ እንደሚጣልበት አልጠረጠረም ነበርና ጥቂት ተኩስ እንደተደረገ ጥሎ ሄደ። መስከረም 11 ቀን ጎሐ ጽዮን ላይ መሽጐ ተቀምጦ የነበረው የጠላት ጦር አርበኞችን ለማጥቃት ወጣ። እነሱም ገጠሙት። የፍቼው ጦር እስኪደርስለት ወደ ኋላው ተመልሶ ሠፈረ።

የጠላት ሃሳብ በዚያ አካባቢ የነበረውን አርበኛ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመደምሰስ ነበርና መልሶ አጠቃ። መስከረም 12 ቀን 1930 ዓ.ም የፍቼና የደብረ ብርሃን የጠላት ጦር ተባብሮ በእነ ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ላይ ወረጃርሶ ያያ ያበና በተባለው ቦታ አደጋ ጣለባቸው። ቀኛዝማች ባንተ ዳኘ እና 26 አርበኞች ሞቱ፤ ሌሎችም ቆሰሉ። በዚህ ቀን ጉልጂ አፋፍ ላይ ሌላ ጦርነት ተካሂዶ ጥቂት አርበኞች ቆሰሉ፤ ሌሎችም ተማረኩ።

መስከረም 14 ቀን 1930 ዓ.ም ጠላት ዜጋ ወደም በተባለው ቦታ እንደአለ በአርበኛው ላይ አደጋ ጣለ። ከበባም አድርጐ ስለነበር ለምርኮ አቃረበው። ሦስቱ ጀግኖች የክቡን ሰንሰለት ለመስበር በቁርጠኝነት ተነሱ። በጀግንነት ተዋግተው እንደአሰቡት አደረጉ። የክበቡን ሰንሰለት ሰብረው ወገኖቻቸውን ከእልቂትና ከምርኮ አዳኑ። እነዚህም ጀግኖች ባሻ /ደጃዝማች/ ተሰማ አርጌጤ፣ ባላምባራስ /ፊታውራሪ/ ተሻገር ግዛውና ወንድማቸው አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ ግዛው ነበሩ። በእኔ አስተያዬት፣ ምስጋና ይገባቸዋል።

መስከረም 16 ቀን 1930 ዓ.ም ይህ የአርበኛ ቡድን ወደ ካቢ ለመውጣት ጉዞ ጀመረ። ውላ ገባን ከተባለው ቦታ እንደሠፈረ፣ የተኩስ ድምጽ ተሰማ። ጠላትም ኃይሉን አጠናክሮ ቢሻ ሚኮ የተባሉትን ታዋቂ አርበኛ ገደለ።

ለማስታወሻነቱ ያህል በዚህ ቀን ስለተፈፀሙ አስደናቂ ነገሮች እንድጠቅስ ይፈቀድልኝ። የጨበጣ ውጊያ ሲካሄድ አጋፋሪ /ፊታውራሪ/ ሞላልኝ አሥር የጠላት ወታደሮች በአንድ ጉርሻ መትረየስ ፈጁ። ከወደቁት የጠላት ወታደሮች አንዱ መትረየስ የያዘ ነበር። መትረየሱን ለማንሳት ልጅ የማነ ብርሃን አባኮራን ቢሄድ ወንድሙ ሆኖ አገኘው። ሁኔታው ሳያስቅቀው አልቀረም። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ደግሞ የቢሻ ሚኮን ሞት እንደ ሰሙ ስለ ተናደዱ፣ በሩጫ ከጠላት ጦር ውስጥ ገብተው ወበሪ ከተባለው ቦታ አንድ ጣልያናዊ መቶ አለቃ እና ስድስት ባንዶች ገድለው በገላጋይ ብዛት ተመለሱ።

የዕለቱ ጦርነት እንዲህ ትርምስና ግርግር የበዛበት ነበር። አርበኛው ጠላትን ማባረሩን ቀጥሎ እስከ ወበሪ ድረስ አሳደደው። ከጠላት ወገን በዚህ ቀን ጦርነት ሁለት መቶ አሥር ወታደሮች ተገደሉ። ውጊያው እንደ ኳስ ቅብብሎሽ ሆኖ ነበረና የጠላት ጦር በካራ አባገሙ በኩል መጣ። በዚያ የነበረው አርበኛ በሚያስደንቅ የጦር ሥልት ወግቶ አባረረው።

በዋዩ አካባቢ የነበረውን አርበኛ ክጥቃት ለማዳን ቀኛዝማች ቁምቢ ከምሴ የተባለውን የባንዶች መሪ ማስታገስ አስፈለገ። ይህ ሰው ከአርበኞች ጋር ሊሠራ ከማለ በኋላ ከድቶ፣ በዘወርዋራ መንገድ ብዙ አርበኞችን ያስፈጀ ነበር። መስከረም 18 ቀን 1930 ዓ.ም ተዘመተበት። እሱም ሞተ፤ ቤቱም ተቃጠለ። አሥር ያህል ጠመንጃና ሁለት በቅሎች እንደዚሁም በአንድ ቤት ሙሉ የተደረደረ ሣሙና ተገኘ። የሣሙናው ክምር እሱነቱን እንዲያፀዳለት ሳይሆን፤ ወገኖቹን ላስጠፋበት የተሠጠው ሽልማቱ መሆኑ ነው።

የአርበኛው ቡድን ጥቂት ዕረፍት ከአደረገ በኋላ መስከረም 24 ቀን ከዋዩ ወደ ታላቅ አምባ ሄደ። መስከረም 26 ቀን 1930 ዓ.ም አንድ ቡድን እስከ ደብረ ብርሃን ጥግ ተጠግቶ የጠላትን መተላለፊያ እንዲያጠና ተላከ። ቡድኑ ተልእኮውን ከአከናወነ በኋላ፣ ከነጋድራስ ቂርቆስ ቤት ሠላሣ አፈድስት መውዜር ከእነ ጥይቶቻቸው፣ እንዲሁም ሌሎችም ትጥቆች ከተቀበሩበት አውጥቶ ተመለሰ። ይህም ጀሌዎችን ለማስታጠቅ ረዳ።

መስከረም 27 ቀን አርበኛው ሳይቆይ፣ ጊዜውን (በማለዳ) ወደ ደንገዜ በማምራት የመራር ውሃን ወንዝ ተሻገረ። ቀደም ብሎ፣ ታህሳስ 12 ቀን 1929 ዓ.ም ጅሩ በምክር በተወሰነው መሠረት መንገቲ ገባ።

ጥቅምት 1 ቀን 1930 ዓ.ም ደራ ላይ መሽጐ ተቀምጦ ለነበረው የጠላት ጦር ስንቅና መሣሪያ ለማቀበል መጣ። ይህንን፣ ከወገኖቹ ይልቅ ጣልያንን ሊረዳ የተንቀሰቀሰውን የጠላት ባንዳ፣ አርበኛው ባሶ ከተባለው ወንዝ ላይ በጥይት ፈጀው። ብዙ ባንዳም ገደል እየገባ የሞተ ሲሆን፣ ብዙ ስንቅና አምስት ምንሽር ተማረከ።

አርበኞች ሚዳ ወረዳ፣ ደንጐሬ ከተባለው ቦታ መሽጐ ተቀምጦ የነበረውን ጠላት ለማጥቃት አሰቡ። በህዳር 1930 ዓ.ም አደጋ ጥለው ሙሉ ቀን ወጉት። ታህሣስ 10 ቀን 1930 ዓ.ም ደግሞ ሻለቃ ከስቲላ በሚባለው አዛዥነት የመጣባቸውን የጠላት ጦር ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት ደፈጣ አድርገው በመውጋት፣ ጠዋት ሲነጋ ወደመጣበት እንዲመለስ አደረጉ።

ጥር 19 ቀን 1930 ዓ.ም ግዛው ጭንቅሎ የተባለው ባንዳ ተገደለ። እርሱም የአርበኞችን ምሥጢር በስለላ እያጣራ ለጠላት በመንገር ብዙ ጉዳት ያደረሰ ነበር። አብረውት የነበሩት ባንዶችም ተማረኩ። አርበኛው ግን ጉዳት አላደረሰባቸውም።

በዚህ ጊዜ ወረይሉና ሚዳ የነበረው የጠላት ጦር መርሐቤቴ ለነበረው ወገኑ መሣሪያና ስንቅ ለማቀበል ተንቀሳቀሰ። አርበኞች አካሄዱን በማጥናት ወንጭት ወንዝ ላይ ገጥመው ለቁጥር ያታከተ ባንዳ ፈጁበት። ነጭ ግን ደጀን ስለነበረ ሊያገኙት አልቻሉም። ስለዚህም ባንዳውን ተገን በማድረግ ሸሽቶ ሚዳ ምሽግ ገባ። የተማረከው የጦር መሣሪያ እጅግ ብዙ ነበር። ባላገሩ ጭምር ተከፋፈለው፤ ሕዝብ በሙሉ ባለ መሣሪያ ሆነ። ይህም የአርበኞችን ክንድ አጠነከረ። ይህንን ጥቃት ለመበቀል ፌጥራ ላይ የነበረው የጠላት ጦር



ተንቀሳቀሰ። ሆኖም አርበኛው ግንባር ለግንባር ገጥሞ አሳሩን አብልቶ መለሰው።

ጠላት የማጥቃት ሥራውን ለመቀጠል እንደገና ተንቀሳቀሰ። አርበኞችም ደሃህላ ከተባለው ቦታ ወጉት። ጦሩን እየመራ የመጣውን ሀብታሙ የተባለውን ባንዳ ማረኩት። እሱም ሳያንገራግር ተማረከ። የመጣው ጦር በያለበት ፈረጠጠ። ብዙ የእጅ ቦምብና መሣሪያ ተማረከ። ነገር ግን በሀብታሙ ላይ አርበኛው አንዳች ጉዳት አላደረሰበትም። ለአመክሮ በጥበቃ ላይ እንዳለ ሌላ ጦርነት ሲያጋጥም አምልጦ ከጠላት ገባ። ጦር በመጣ ቁጥር ለጠላት ቀዳሚ በመሆን ሲያስቸግር ቆየ። ከአለመፀፀቱም ይልቅ የሚገርመው ግን፣ ነፃነት ከተመለሰም በኋላ በጦር ሠራዊት ባልደረብነት ሊቀጠር መቻሉ ነው።

በክረምቱ ወራት ወንጭትና ገሮማ የተባሉት ወንዞች ሞልተው ሰው በማያሻግሩበት ጊዜ፤ ደንጐሬ ከተባለው ቦታ መሽጐ ተቀምጦ የነበረውን የጠላት ጦር አርበኞች ከበቡት። በነሐሴ ወር 1930 ዓ.ም የተፈጠረበትን ቀን እስኪረግም ድረስ አስጨንቀው ወጉት። ይህንን ቂም ለመበቀል ጠላት ወረጎ በተባለው ቦታ በነበረው በአርበኞች ቡድን ላይ ነሐሴ 1 ቀን 1930 ዓ.ም ከንጋቱ 11:00 ሰዓት አደጋ ጣለ። አደጋ የተጣለበት ቡድን ራሱን ለማዳን በርትቶ ተከላከለ። አገሪት በተባለው ቦታ የነበረው ሌላው የአርበኛ ቡድን ፈጥኖ በመድረስ አዳነው። በአጥቂው የጠላት ጦርና በረዳቱ መካከል ጣልቃ ገብቶ በማጥቃት፤ ረዳቱን ጦር ወደመጣበት በመመለስ አስለቀቀው።

ሌላው የአርበኛ ቡድን ደግሞ ነሐሴ 1 ቀን 1931 ዓ.ም ፌጥራ ላይ የነበረውን ምሽግ አልፎ ቡዮና እረመሽት ከሚባለው ቦታ የጠላትን ወታደሮች ገድሎ፣ የተረፉትን በማባረር አካባቢውን ከጠላት ነፃ አደረገ።

በመርሃቤቴ አውራጃ ወረሞ በተባለ ቦታ በነበረ ደምሴ ስሜ በተባለ የባንዶች መሪ ላይ እርምጃ መውሰድ አስፈለገ። እርምጃ እንዲወሰድ ያስፈለገው የመርሃ ቤቴንና የሚዳን ሕዝብ በሙሉ እየዘረፈ፣ ለጠላት መሪ በመሆን በአርበኞች ላይ ጉዳት እያደረሰ ስለአስቸገረ ነበር። እሱም ጥፋቱን ተረድቶት ከሕዝብ ተለይቶ ምሽግ ሠርቶ ይቀመጥ ነበር። መስከረም 3 ቀን 1931 ዓ.ም ከንጋቱ 12:00 ሰዓት ላይ አደጋ ተጣለበት። እሱም የቻለውን ያህል ተከላክሎ አለውጤት የዘመን መለወጫ ዕለት ተገደለ። ከወረይሉ የመጣለትም የጠላት ጦር አሣሩን አይቶ ተመለሰ። ብዙ መሣሪያም በአርበኞች ተማረከ።

የመረሃቤቴ አርበኞች ክረምቱ ሳይወጣ፣ የወንዞቹ ውሃ ሳይጐድልና መሬቱ ሳይደርቅ፤ ሚዳ መራኛ ከተባለው ቦታ መሽጐ ተቀምጦ የነበረውን ጠላት ለማጥቃት አሰቡ። ዓላማቸው ምሽጉን ሰብረው ለማስለቀቅ ነበር። በመስከረም ወር ከንጋቱ በ11:00 ሰዓት የማጥቃት ተግባራቸውን ቀጠሉ። ጠላትም አጥብቆ ተከላከለ። ሊመልሳቸው እንደአልቻለ ሲረዳ በአይሮፕላን

አስደበደበ። እነሱ ደግሞ ወደኂላ አፈግፍገው ቦታ ይዘው ቆዩ። ከዚያም አይሮፕላኑ ሲመለስ ወደቦታቸው ሄዱ።

በዚሁ ዓመት ጀራ ወረዳ፣ ሀሮ በተባለው ቦታ መሽጉ ተቀምጦ የነበረውን ጠላት ደጋግመው በመውጋት አብርረው፣ ጉንዶ መስቀል በተባለው ቦታ መሽጉ ከነበረው ጋር አቀላቅለውታል።

የመርሃቤቴ አርበኞች ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ ጋር ለመመካከር ከመርሃ ቤቴ ተንቀሳቀሱ። ጥቅምት 27 ቀን 1931 ዓ.ም ጭምብሬ ላይ ተገናኝተው ተነጋገሩ። ዋናው ሐሳብ አርበኞች በያሉበት ሆነው ጠላትን በተቀነባበረ ሁኔታ ለመውጋት፣ እርስበርሳቸው ለመረዳዳት የሚችሉበትን መንገድ መቀየስ ነበር። ይህ ምክር መልካም ውጤት አስገኝቶአል።

ጠላት በበኩሉ በዚህ አጋጣሚ በመጠቀም ቀደም ብለው አስለቅቀውት የነበረውን የኮላሽ አምባ መልሶ ለመያዝ ሞከረ። አርበኞቹም ጠንክረው ተከላከሉ። ነገር ግን ሠራዊታቸው በከፊል እንጂ ሙሉ በሙሉ አልተከታተላቸውም ነበርና ጠላትን መመለስ አልቻሉም። እንደ አሰበው የኮላሽን አምባ መልሶ ያዘ። ሌላው የአርበኛ ቡድን ደግሞ ጥቅምት 27 ቀን 1931 ዓ.ም ከጠላት ጋር መጠነኛ ውጊያ አካሄደ።

ጠላት አርበኞችን ለማደን ተንቀሳቀሰ። ባላገሮቹ ሁኔታውን ነግረው አስጠነቀቁ። አርበኞችም ላምዋሻ ከተባለው ቦታ ጥቅምት 19 ቀን 1931 ዓ.ም ገጠሙት። ውጊያው ከቀኑ ስድስት ሰዓት ጀምሮ እስከ አሥር ሰዓት ቆየ። በዚህ ጊዜ ብዙ የጠላት ወታደር ወደቀ። አዝማቹ ጣልያናዊ መኰንንም ቆሰለ። ተሸክመውት ሲሸሹ መኰንኑን ለመንጠቅ በተደረገው ሙከራ ውጊያው ቀጥሎ፣ ጠላት ጋሬት የተባለውን ምሽግ ለቆ ዞማ ምሽግ ከሌሊቱ በአምስት ሰዓት ባሳር ገባ። የአልቤንና የምንሽር ጠመንጃ በብዛት ተማረከ።

ጠላት አርበኞችን ለማጥፋት በአደረገው ሙከራ ታህሣሥ 18 ቀን 1931 ዓ.ም በልበሊት ላይ ጦርነት ተካሂዶ ብዙ አርበኞች ሞቱ። ጠላት በዚህ በአገኘው ድል ተደፋፍሮ በአራት ማዕዘን ከበባ አደረገ። ከበባውም በበልበሊት፣ በሰሌ፣ በመርሐ ቤቴ ምዕራብና በፌጥራ ነበር። ጥቂት ሰው ቢሞትና ቢቆስልባቸውም አርበኞቹ ከበባውን ሰብረው ወጡ። ከበባውን ለመስበር የቻሉትም በረድፍ በረድፍ ሆነው በመዋጋትና ሰብሮ የወጣው ገና ያልወጣውን ለማስለቀቅ የሚያስችል የጀርባ ውጊያ በማካሄዱ ነው። እንደዚሁም ለእርዳታ የመጣው የጠላት ጦር ያልፍበት የነበረውን ጫካ በእሳት በማቃጠል እርስበርሱ እንዳይረዳዳ በማድረግና መሪውን በመግደል ነበር።

በሚያዝያ ወር 1931 ዓ.ም ጠላት እረመሽት ከተባለው ቦታ የነበረውን አርበኛ ለማጥቃት ሙከራ አደረገ። አርበኞቹ አጥብቀው ተከላከሉ፤ የእርዳታ ጥሪም አስተላለፉ። ቀደም ብሎ በተደረገው ስምምነት መሠረት



ጭምብሬ፣ ዘሪት ከተባሉት ቦታዎች አርበኞች ፈጥነው በመድረስ ጠላትን ከጀርባው እየወጉ የተከበበውን አርበኛ አዳኑ።

ሰኔ 26 ቀን 1931 ዓ.ም ጠላት መርሐቤቴ ቁምአምባ ከተባለው ቦታ መጣ። አርበኞቹም ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ወጊያው ከሌሊቱ 11 ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ 9 ሰዓት ድረስ ቆየ። ሁለት ጣልያናውያን የጦር መኮንኖች ቆስለው በቃሬዛ ተወሰዱ። ሃምሣ ሦስት ባንዳ ሞተ፤ ሌላ አርባ ሦስት ባንዳ ቆሰለ። አርባ ሰባት ጠመንጃ ተነሳ። ጥቂት አርበኞች ሞቱ፣ ሌሎችም ቆሰሉ።

የ1931 ዓ.ም ዘመን በዚህ ዓይነት ተፈጽሞ የ1932 ዓ.ም ትግል ቀጠለ። ጦርነቱ ውሎም ሳያድር በመስከረም ወር ተጀመረ። ከፌጥራ ምሽግ ውስጥ የነበረው የጠላት ጦር ከምሽጉ ወጥቶ ወደ እንሣሮ ይጓዝ በነበረው አርበኛ ላይ ተኩስ ከፈተ። አርበኛውም መክቶ ግንባር ለግንባር ገጠመው፤ ተጨፋጨፉ። ብዙ የጠላት ወታደር ወደቀ። የተረፈው ከወጣበት ምሽግ ተመልሶ ተከተተ።

ከአዲስ አበባ ዕለት ዕለት የሚደርሰው ትዕዛዝ ጨና ነስቶት ነበርና፣ ጠላት አርበኞች የሄዱበትን ዱካ እየተከታተለ አካባቢውን ያሰስ ጀመር። ከአርበኝነት ሥልት አንዱ ጠላትን ከቦታ ቦታ በማዞር ማድከም ስለነበር ብዙ አንከራተቱት። ሞረት ቆላ፣ ዝግብ ከሚባለው በረሃ ላይ ሲደርስ ጥቅምት 1 ቀን 1932 ዓ.ም ገጠሙት። የጠላት ጦር ሥፍር ቁጥር አልነበረውም፤ የሚመራውም በአንድ ጀነራል ነበር። ቦምብና ጥይት እንደ ነጐድጓድ ወረደ። በመንከራተት የደከመው የጠላት ወታደር ሬሣ ተረፈረፈ፤ ብዙ አርበኞችም ወደቁ። ይህኛው ጦር ሲገባደድ ሌላ አዲስ የጠላት ጦር ደረሰ። እሱንም ደርሶ መዋጋት ሞኝነት ስለሆነ፤ አርበኞቹ መንገድ በመስበር ወደ መርሐቤቴ አፋፍ ወጡ።

ጠላት የማጥቃት ዘመቻውን ቀጠለ። ከምብ በምትባል የእንሣሮ ወረዳ፣ ሙጢ ከሚባለው ቦታ ጥቅምት 10 ቀን 1932 ዓ.ም ብዙ አርበኞች በጀግንነት እየተዋጉ ወደቁ። የጠላትም ጦር በአጋጠመው ዕድል ተጠቅሞ በርትቶ ተዋጋ፤ ከበባም አደረገ። ይህ ቀን በዚያ አካባቢ ለነበሩ አርበኞች ከባድ ነበር። በአቅማቸው ሙሉ ተከላከሉ። አጥብቀው በመከላከላቸውም ከማለቅና ከመማረክ ዳኑ። ነገር ግን ከግንቦት 10 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምረው ጠላትን ሲያርበደብዱት የቆዩት ጀግናው ልጅ ሥዩም ገብረሕይወት ሞቱ። አሽከሮቻቸውም ሬሣቸውንና መሣሪያቸውን ለጠላት ሳያስነኩ ሞረት፣ ሰገድ ሚካኤል ቤተክርስቲያን ወስደው በክብር ቀበሩአቸው።[4]

በወቅቱ ከጉጃም በኩል የሚነፍሰው ወሬ ለአርበኛው የልብ ልብ ይሰጠው ጀመር። ክረምቱ በአርበኛው ላይ የኑሮ ችግር እንጂ የጠላት ጥቃት አላመጣበትም። ለአዲስ ትግል መዘጋጃ ሆነ። የ1933 ዓ.ም የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራትም በዚህ አካባቢ ለነበረው አርበኛ ብዙ ፈተና አላስከተለበትም።

ህዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም ለሸዋ ሕዝብ የተነገረው አዋጅ ከጐጃም ተላከ።[5] ይህም የንጉሠ ነገሥቱን መምጣት አበሠረ።

በእዛ አካባቢ የማሚጠጫው፣ ዋናው ጦርነት በታህሣሥ ወር 1933 ዓ.ም መርሐቤቴ፣ አደሬ ከተባለው ቦታ ላይ ተካሄደ። እኩሉ አርበኛ በአደሬ፣ እኩሉ ደግሞ በስንደዶ በኩል ሆኖ ጠላቱን ቀጠቀጠው። ጦርነቱ ሁለት መዓልት ወሰደ። ጣልያን አርበኞቹን ማሸነፍ ቢያቅተው በአንድ በኩል ጦር ልኮ ጉብል ከተባለው በረሃ የነበረውን ሴትና ልጅ፣ ጓዝ አስማረከ። አርበኞቹ ከዚያም ገስግሰው ደርሰው ተዋጉ። ጠላትም ወደኋላው ተመለሰ። ነገር ግን ምርኮኞቹን ማስለቀቅ አልተቻለም።

ከጐጃም የሸሸው እስከ ስድሣ ሺህ የሚገመት የጣልያን ጦር የዓባይን ወንዝ ተሻግሮ ጎሐ ጽዮንን አልፎ ገርባ ጉራቻ ሲደርስ፣ ከሁለት እንደተከፈለ እና አንዱ ወደ ደቡብ ተቀልብሶ ወደ አዲስ ዓለም እንደሄደ፣ ሌላው ደግሞ ወደ ሰሜን ታጥፎ ወደ መርሐቤቴ እንደገባ ቀደም ብለን ተመልክተናል። በመሆኑም በእነሱ ላይ የመጣውን የጠላት ጦር ማስተናገድ የመርሐቤቴ አርበኞች ዕድል ፈንታ ሆነ።

ወደ ሰሜን የወጣው የጠላት ጦር ሐሳብ ዠማ የተባለውን ወንዝ ተሻግሮ በደራ፣ ካራምችግ አደርጐ ወደ ወረይሉ ተሻግሮ ደሴ ለመግባት ነበር። ደሴ መያዙን ሲረዳ ደግሞ እኩሉ ወደ ጐንደር፣ ገሚሱ ወደ አምባላጌ ጉዞውን ቀጠለ። ኢትዮጵያን ለመውረር የመጣበትን አቅጣጫ ይዞ ወደ ሰሜን አቀና። ይህ እንደታወቀ ከንጉሠ ነገሥቱ ለአርበኛው ትዕዛዝ ተላለፈ።

ይህንን የአርበኞች ጥቃት ለማስታገስ ጠላት መጋቢት 23 ቀን 1933 ዓ.ም እረመሽት በተባለው ቦታ በአርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። አርበኞችም ሸሽቶ ከምሽጉ እስኪገባ ድረስ እያባረሩ ወጉት። በዚሁ በመጋቢት ወር 1933 ዓ.ም የስቅለት ዕለት አርበኞች መራኛ የተባለውን ምሽግ ለማስለቀቅ ጥቃት አካሄዱ። ውጊያው የተካሄደው ቀደም ብሎ ለቅቆት ወደ ወረይሉ ሄዶ የነበረው የጠላት ጦር ተመልሶ መጥቶ ምሽጉን እንደገና በመያዙ ነበር። አርበኞቹ በርትተው በመዋጋት ድል አድርገው መልሰው አባረሩት።

የንጉሠ ነገሥቱ ጐጃም መግባት እንደታወቀ፣ ባንዳው ከጠላት እየከዳ ከአርበኛው ጋር ተቀላቀለ። ብዙ የቀድሞ ባንዶች አሁን ደግሞ ከአርበኞች ጐን በመቆም፤ ጌታቸውን ጣልያንን መልሰው በመውጋት ደማቸውን ለሀገራቸው ለማፍሰስ ተሠለፉ። በሁለት ወገን ሞቱ ማለት ነው።



# ምዕራፍ ሃያ ሰባት
# የመገናኛ መሥመርን መቆጣጠር

የጣልያንን የጦር እንቅስቃሴ መጉዳት ከሚቻልበት መንገድ አንዱ ከአዲስ አበባ እስከ ጂቡቲ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ መሥበር ሆነ። ስለዚህ ከአዲስ አበባ ከተማ ወጥተው በአካባቢው የተሰማሩ፣ የቴክኒክ እውቀት የነበራቸው ወጣቶች በዚህ ሥራ ላይ ተሰለፉ። ሕዝብ ተባበራቸው፤ መጠለያ ሰጣቸው። እንግዳ የሆኑበትን አንዳንድ የቴክኒክ ሥልቶች ከእነሱ እያጠና እሱም ራሱ የበኩሉን አደረገ።

ቡድኑ የባቡር ሐዲዱን በመንቀልና የስልክ መሥመሩን በመቁረጥ የጥቃት ሥራውን ጀመረ። በሥራው ገበሬውም ተባበረ። የራሱን ዘዴ ጨመረበት። ከሰዋራ ቦታ ታላላቅ ድንጋይ በሐዲድ ላይ በመጋረጥ፣ የስልኩን ሽቦ በጥሶ ከሰል በተቀባ ገመድ በማሠር፣ ገበሬው ሊያደርሰው የሚችለው ጥቃት ሆኖ ተገኘ። ጥቂት ሽፍቶች በአካባቢው እንዲታዩ በማድረግ በእነሱ እያመካኘ ውስጥ ውስጡን ሥራውን ቀጠለ።

በዚህ ዓይነት ከአዲስ አበባ ወጥቶ ሕዝቡን ተገን በማድረግ የተንቀሳቀሰው ቡድን፤ ከአዲስ አበባ እስከ ጅቡቲ የተዘረጋውን የባቡር ሐዲድ ማጥቃት ጀመረ። ጥቃቱ የሚካሄደው ከአዲስ አበባ ቅርብ በሆኑ ቦታዎች ስለነበር፣ ጠላት እጅግ አስቸገረው። ከማጥቃቱ ሥራ የመጀመሪያው በተጠቀሰው ቀላል ዘዴ የስልክ መሥመሩን መበጣጠስ ሆነ። ድልድይ መስበር፣ ከገደላማ ቦታ ላይ ትልቅ ድንጋይ በእልህ እያንከባለሉ ከሃዲድ ላይ ማስቀመጥ፣ ወዘተ...፣ ሌሎቹ ዘዴዎች ነበሩ።

በባቡር ላይ አደጋ መጣል፣ ሰኔ 29 ቀን 1929 ዓ.ም ተጀመረ። ቦታው በአቃቂና በሞጆ መካከል ነበር። ባቡር የመምታቱ፣ ሀዲድ የመስበሩ፣ ስልክ የመበጣጠሱ ሥራ የሚካሄደው በቡልጋና በሸንኮራ ገበሬ ድጋፍ እንጂ በራሱ አልነበረም። እንደጠቀስኩት ሥራውን የሚያካሂዱት ከአዲስ አበባ ወጥተው በአርበኝነት ሥራ በተሠማሩ የተማሪ ወጣቶች ነበር። ሥራውም የሚካሄደው በዘመናዊ ሥልት ነበር።

ስለዚህ ከሐምሌ 1 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ የሐዲዱን ጥበቃ ጀነራል ግራዚያኒ ራሱ ያዘ። ነገር ግን ከአርበኞች የሚሰነዘረውን ጥቃት ሊገታው አልቻለም። ሐምሌ 2 ቀን 1928 ዓ.ም አዳማ ከተማ፣ ሐምሌ 4 ቀን እና 5 ደግሞ ከአዲስ አበባ 439 ኪሎ ሜትር ከሚርቅ ቦታ በባቡር ላይ አደጋ ጥለው፣ በሁለት ጎታቾች፣ እንዲሁም በስምንት ሃላፊዎች ላይ ጉዳት አደረሱ። በዚሁ በዓ.ም፣ ሐምሌ 4 ቀን ከምሽቱ ሦስት ሰዓት ሞጆ አካባቢ በሌላ ባቡር ላይ አደጋ ጣሉ፤ ስልኩንም በጣጠሱ። ሐምሌ 9 ቀን 1928 ዓ.ም ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ የሚጓዘውን ባቡር ዱከም ላይ አርበኞች አደጋ

ጥለው ጉዞውን አቋረጡበት። በዚሁ ቀን አንድ ሌላ የአርበኛ ቡድን ከቀኑ በ11፡ 30 ሰዓት ሞጆ አካባቢ በሌላ ባቡር ላይ አደጋ ጥሎ ጉዳት አደረሰበት።

አርበኞች አዋሽ አርባ /ቦርደዲ/ በተባለው ቦታ በባቡር ላይ አደጋ ጥለው በዚያ ከነበረው የጠላት ጦር ጋር ተዋጉ። ነሐሴ 7 ቀን 1928 ዓ.ም ደግሞ አዋሽ ባቡር ጣቢያ በሠፈረው በአንድ ጄነራል በሚመራ ጦር ላይ አደጋ ጣሉበት። ነሐሴ 9 ቀን ደግሞ አርበኞቹ መተሐራ ባቡር ጣቢያ ላይ አደጋ ጥለው ጣልያናውያን ወታደሮች ገድለው ተመለሱ። በማግስቱ ነሐሴ 10 ቀን ደግሞ አልከጂሉ በተባለው ቦታ በነበረው ባቡር ላይ አደጋ ጣሉ።

አርበኛው ሞጆን በመያዝ የባቡርን መሥመር ከነጭራሹ ለመዝጋት ተዘጋጀ። ነሐሴ 21 ቀን 1928 ዓ.ም ታላቅ ውጊያ አካሄደ። የቡልጋ፣ የሸንኮራ፣ የምንጃርና የደቡብ ጐጃም ሰው ተባበረ። በጠላቱ ላይ የየአቅሙን ያህል ተራውን ተወጣ። ጊዜው ዝናም፣ መሬቱ ጭቃ፣ ሰማዩ ደመና ነበር። ጠላት በአይሮፕላን ለማጥቃት አልተመቸውም። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ነገር ግን የጠላት ኃይል ስለአመዘነ አርበኞቹ እንደ አሰቡት ሞጆን ለመያዝ ሳይችሉ ቀሩ። ቢሆንም ሙከራው ራሱ ጠላትን አስደነገጠው።

የአርበኞችን ጥቃት ለመከላከል ሲል ጣልያን ብዙ እግረኛ ወታደር ያሰማራል። አካባቢውን በአይሮፕላን ይደበድባል። ጫካውን በእሳት ያቃጥላል። ለባቡር ሐዲድ ጥበቃው ሥራ ጄነራል ግራዚያኒ 72 ከፍተኛ መኮንኖች፣ 113 ዝቅተኛ መኮንኖች፣ 1136 ወታደሮች መደበ። ነገር ግን ከንቱ ሆነበት። አርበኞች ማጥቃታቸውን ቀጠሉ። ነሐሴ 22 ቀን 1928 ዓ.ም ለዕረፍት ወታደሮች ጭኖ በሚጓዘው ባቡር ላይ፤ ከአዲስ አበባ 205 ኪሎ ሜትር ርቀት አደጋ ጥለው ከባድ ጉዳት አደረሱበት።

ሁኔታው በእንዲህ እንደአለ የጣልያን የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ኢትዮጵያን፣ ማለትም በዚያን ጊዜው አሠራራቸው የኢጣልያን የምሥራቅ አፍሪካ ቅኝ ግዛት እንዲጐበኝ በሮም ታሰበ። ጉብኙቱ እንዲደረግ የታሰበው በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ የተቀሰቀሰውን የአርበኝነት ሥራ ለማብረድ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሰላም የተመሠረተ አስመስሎ በማሳየት የዓለምን ህብረተሰብ ለማወናበድ ነበር። አልተሳካላቸውም እንጂ ይህንን እንደተገነዘቡ አርበኞች ጥሩ እርምጃ ወሰዱ። መስከረም 29 ቀን ከምሽቱ 3 ሰዓት ላይ ከድሬዳዋ ሦስት ባቡሮች ተከታትለው ተነሱ። ግን የቅኝ ግዛት ሚኒስትሩ ሲኖር ሌሶና የተሳፈረው በየትኛው ውስጥ እንደነበር በአርበኞች ዘንድ አልታወቀም ነበር።

ባቡሮቹ ጉዞአቸውን ቀጥለው መስከረም 30 ቀን 1929 ዓ.ም ዱከም ደረሱ። ከዱከም አራት ኪሎ ሜትር ያህል እንደወጡ በመጀመሪያው ባቡር ላይ ከቀኑ በ7:45 ደቂቃ አደጋ ተጣለ። አዲስ አበባ ሲገባ ለሚደረግለት አቀባበል እንዲመች ሲባል ከመጀመሪያው ላይ ሣይሣፈር አይቀርም በሚል መላምት ሳይሆን አልቀረም። ነገር ግን ሌሶና ከዚያ ውስጥ አልነበረም።



በአቃቂና በዱከም መካከል በነበረው ሐዲድ ላይ ሁለተኛ አደጋ ተጣለ። እሱ ደግሞ ሌሶና የነበረበት ባቡር ከመድረሱ ጥቂት ቀደም ብሎ ሆነ። ስምንት ኢጣለያውያንን ቢገድሉም ሌሶናና አብሮት የመጣው ከቦሊ ጂሲ ጉዳት ሳያገኛቸው ቀረ። ትርፉ "ዋይ ነዶ" ሆነ። ቢሆንም ሌሶና የአርበኞቹን ጥንካሬ ሳይገነዘብ አልቀረም።

ጥቅምት 5 ቀን 1929 ዓ.ም ጣልያን የኤረርን ተራራ ሲያስስ፣ አርበኞቹ ናዝሬት ከተማ አጠገብ አደጋ ጥለው ጉዳት በማድረስ የሚደክመው በከንቱ መሆኑን ለጠላት በግብር ገለፁለት። ጄነራል ግራዚያኒ በአርበኞች የጦር ሥልት መበለጡን አመነ። አምኖም የባቡርና ሐዲዱን ጥበቃ ለጄነራል ጋሊና ለቀቀ።

ጄነራል ጋሊና በዚያው እሱ በተሾመበት በጥቅምት 5 ቀን 1929 ዓ.ም ከጠዋቱ በአንድ ሰዓት አርበኞች በአንድ ባቡር ላይ አደጋ ጥለው ጉዳት ማድረሳቸውን የሚገልፅ ሪፖርት በማንበብ ሥራውን ጀመረ። የአቅሙን ያህልም ተፍጨረጨረ። ቢሆንም በሐዲዱ ላይ የሚደርሰውን አደጋ ማቆም አልሆነለትም። ጥቅምት 6 ቀን 1929 ዓ.ም በአዋሽና በወልንጭቲ መካከል አደጋ ተጥሎ ባቡር ተጐዳ። አርበኞቹ የካቲት 7 ቀን በወልንጪቲና በበርጭታ መካከል 399 ኪሎ ሜትር ላይ ሐዲዱን ስለሠበሩት ባቡር መተላለፍ አቋረጠ። በዚሁ በጥቅምት 7 ቀን 1929 ዓ.ም ሌላ ባቡር በአዲስ አበባና በደብረ ዘይት መካከል ተመታ። የተመታው ደግሞ በመድፍ መሆኑ ጣልያኖችን አስደነገጠ።[1]

ይህ ቡድን ፈጥኖ ቢዳከምም፣ በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት አድርሶአል። ጦርነቱ እንደተጀመረ እንጂ እንዳላለቀ አውሮፓ ሲረዳው በሚችል መልክ አስረድቶታል።

<u>ማጣቀሻ ፅሑፎች</u>

[1] ጳውሎስ ኞኞ፣ *የኢትዮጵያና የኢጣልያ ጦርነት*፣ ገጽ 173-178።

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት
## በቡልጋና ሸንኮራ የተካሄደ ትግል

የቡልጋ ሕዝብ የኢትዮጵያን መሸነፍ ሲሰማ ደንግጦ፣ የንጉሠ ነገሥቱን ወደ አውሮፓ መሄድ ሲሰማ ደግሞ ተገረመ። የአንድ ጥቁር ሕዝብ ጉዳይ በነጭ አደባባይ ተሰምቶ ትክክለኛ ፍርድ ይገኛል ብሎ አላመነም። የንጉሠ ነገሥቱንም ጉዞ ከሽሽት ለይቶ አላየውም። ጠላት አንዳች ተቃውሞ ሳያጋጥመው አዲስ አበባን መያዙ አስቆጣው። ስለዚህ የበኩሉን ትግል ጀመረ።

ንጉሠ ነገሥቱ ከአዲስ አበባ በወጡበት ቀን ማግስት፤ ማለትም ሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ቅዳሜ ዕለት፤ የሀገር ሽማግሌዎቹ ሕዝቡን በጥሩምባ በመቀስቀስ ኰረማሽ ዋሻ ውስጥ ተደብቆ የነበረውን የጦር መሣሪያ አስነሱ። የማሣሪያ ማንሳቱ ሥራ ከአጼ ምኒልክ አደራ በተቀበሉ ሽማግሌዎች ኃላፊነት ተካሄደ። እነሱም ግራና ቀኝ ቆመው ሕዝቡን በተራ እያስገቡ፣ የየመስክህን የሚል ምክር እየሰጡ በሥነ ሥርዓት መሣሪያ እንዲያነሳ አደረጉ። ሥራው ቅዳሜ ቀንና ሌሊት፣ እንደዚሁም እሑድ ቀንና ሌሊት በሰላም ተካሄደ። ሚያዝያ 27 ቀን ሰኞ ወደማታ ዋሻው ተቃጠለ። በቃጠሎው የዋሻው በር ስለተደረበ በየዋሻው የነበረው ሰው አብሮ ተቃጠለ። አንድ ቄስ ከሣጥን ላይ ለጥፎት የሄደው ጧፍ ሳይታይ ሣጥኑን እሳት በማቀጣጠሉ ነበር። እሳቱን ለማጥፋት ያልተቻለው ደግሞ ሣጥኑ ዲናሚት ተቀምጦበት ስለነበር በመፈንዳቱ ነው። ብዙ ሰው አለቀ። መሣሪያውን ያስነሱ የነበሩ ሽማግሌዎች ጭምር ገና ካልተነሳው መሣሪያ ጋር አብረው ተቃጠሉ።

የዚህን መሣሪያ ምሥጢር መመርመር ይገባል። አጼ ምኒልክ በአውሮፓ በኩል ስለ አድዋው ጦርነት የነበረውን ስሜት ያውቁ ነበርና፣ ኢጣልያ የእጅዋን ውርደት አሜን ብላ፣ ከመቀበል አርፋ እንደማትቀመጥ ገመቱ። ተከታታይ ጥቃት እንደምታመጣ በማወቅ፣ በመከላከያ ረገድ እርምጃ ወሰዱ። ለነበሩአችው ጠመንጃዎች በየዓይነታቸው ጥይት የሚያሰሩበት ፋብሪካ አዲስ አበባ ላይ አቋቋሙ።[1] ይህ ብቻ አልነበረም የአጼ ምኒልክ ጥንቃቄ። ብዙ መሣሪያ ገዝተው ከአውሮፖ አስመጡ። የመጣውም በታጁራ ወደብ በኩል በምሥጢር ሲሆን፣ በረሃውን በግመል፣ ደጋውን በአጋሰስና በአህያ እየተጫነ ነበር። አስመጥተውም ኰረማሽ አስቀመጡት። ለማስቀመጫው አሥራ ሁለት፣ ለጥበቃው ኃላፊዎች አንድ፣ በድምሩ አሥራ ሦስት ቤት ከዋሻው አሠርተው ከዚያ በመልክ በመልኩ አስቀመጡ። እስከ ቦታው ድረስ ራሳቸው ሄደው አይተው ለሀገሩ ባላባቶች አደራ ሰጡ። አደራው መሣሪያው ለውጪ ጠላት መከላከያ እንጂ ለእርስበርስ ጦርነት እንዳይውል ነበር።



ከዚህ ላይ መነሣት ያለበት ጥያቄ፦ «መሣሪያው ለምን በማይጨው ጦርነት አልተሠራበትም?» የሚል ነው። ምክንያቱ በሌላ በኩል፣ በትክክል ባይታወቀም፣ የሀገር ሽማግሌዎች እንደሚሉት ግን መሣሪያው በዚህ ዓይነት፣ በዋሻ እንደአለ የሰገሌ ጦርነት ደረሰ። በወቅቱ ባለሙሉ ሥልጣን አልጋ ወራሽ የነበሩት ልዑል ራስ ተፈሪ፣ መሣሪያው ለጦርነቱ እንዲውል አዘዙ። ከአጼ ምኒልክ አደራ ተቀብለው የነበሩ ሽማግሌዎች ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ለንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ ስለ ተሠጣቸው የአደራ ቃል ነገሩ። ንግሥቲቱ የአባታቸውን የአጼ ምኒልክን ውሣኔ ያፀናሉ። በዚህ ልዑል ራስ ተፈሪ ይቀየማሉ። ሆኖም በንግሥቲቱ ውሣኔ መሠረት መሣሪያው በጦርነቱ ጊዜ ሳይሠራበት ቀረ።

የንግሥቲቱ ኃይል እየቀነሰ፣ የአልጋ ወራሹ የፖለቲካ ኃይል እያየለ ሲሄድ፣ ከአጼ ምኒልክ አደራ የተቀበሉት ሽማግሌዎች መሣሪያውን ከኰረማሽ ከተማ በስተደቡብ ምዕራብ ሦስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ከሚገኝ ዋሻ ሌሊት ሌሊት በምሥጢር አግዘው ደበቁት። የዋሻውንም በር በግንብ አሠርተው፣ መዝጊያ አስገጠሙለት። የማይጨው ጦርነት ጊዜ መሣሪያው እንዲነሳ ሽማግሌዎች ማስታወሳቸው አልቀረም። ነገር ግን አልተነሳም፤ በጦርነትም ጊዜ አልተሠራበትም።

እንደ ተገለፀው የኰረማሽ መሣሪያ ጥቂቱ ከተነሣ በኋላ የሀገር መከላከሉ ሥራ ቀጠለ። ቡልጋ ከኰረማሽ ያገኘውን መሣሪያ መፈተሽ፣ መጠራረግ ያዘ። በየመልከኛው እሁድና በበዓላት ቀን እየተሰበሰበ ይመክር ጀመር። የመጀመሪያው ጉዳይ የጐበዝ አለቃ መምረጥ ሆነ። የጐበዝ አለቃ በመምረጥ ላይ ብዙ ውጣ ውረድ አለ። አንዳንዱ ለምን አልተመረጥኩም በሚል ቅር ሲለው ሲችል፣ ሌላው ደግሞ እኔ አልችልም፣ ሌላ ሰው ምረጡ እያለ ያስቸግራል።

በእኔ አካባቢ የተፈፀመውንና እኔ ራሴ ያየሁትን እንደማስረጃ ባቀርበው ይቀለኛል። ምንም በዚያን ጊዜ ልጅ ብሆን ዛሬም ሁኔታው በትክክል ይታወሰኛል። ቦታው ቡልጋ ተድላ ማርያም፣ ሙገሬ ዛለ ሚጢ ይባላል። በዚያ የነበረው ሕዝብ መከረ። የአሰቤ አገር ሚካኤልና የሚጢ ማርያም ሕዝብ በሕብረት አንድ የጎበዝ አለቃ መረጠ። በዚህ ብዙ አልተቸገረም። ነገር ግን ምን ሊደረግ እንደሚገባ ንግግር ሲጀመር የሀሳብ ልዩነት ተፈጠረ። አንዱ ወገን እንሸፍት፣ ሌላው ወገን እንመን አለ።[2] ከብዙ ቀን ምክርና ክርክር በኋላ "እንሸፍት" በሚለው ሀሳብ ፀና። ነገር ግን አንድ አቶ ሀብተኢየሱስ የተባለው ሰው አልሸፍትም ብሎ እምቢ አለ። ሕዝቡ አደመበት። ከንጉሥ መንገድ እንዳይወጣ፣ እሣት እንዳይጭር፣ ከቤቱ ሰው ቢሞት ከቤተክርስቲያን እንዳይቀበር ተከለከለ ተወገዘ። ሚስቱ ጥላው ከሰው ተቀላቀለች። እሑድ ይህ ተወሰኖበት በሦስተኛው ቀኑ ማክሰኞ ደወል ደውሎ ከሀገር ታረቀ። የዚያ

አካባቢ ሕዝብ ለአርበኝነት ተንቀሳቀሰ። ሆኖም ሕዝቡ በሙሉ ወዲያው አንድ ልብ ሆነ ማለት አይቻልም።

በዚህ ዓይነት የተንቀሳቀሰው ሕዝብ ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴን በበረከት፣ ቀኝ አዝማች ታቺን በድንጋይጥራ፣ ግራዝማች አብርሃምን በቡርቃ፣ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዱን በሙገሬ ዛለ፣ ፊታውራሪ መኩሪያን በሸላኪ የጣር አለቃ አደረገ። ሌላውም ሁሉ በየአካባቢው እንደዚሁ አደረገ። ወደ ሸንኮራ ወደ ምንጃር የትብብር ደብዳቤ /ጥሪ/ ተላለፈ። ሸንኮራ በሙሉ ተባበረ፤ ምንጃርም በመጠኑ። በቡልጋ የመጀመሪያዋ የአርበኝነት ጥይት ጦስኝ በተባለው ቦታ በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ሰኔ 9 ቀን 1928 ዓ.ም ተተኮሰች። ጠላት እስከተባረረበት ዕለት ድረስ አልበረደችም።

ወዲያው በፊታውራሪ መኩሪያ የሚመራው አርበኛ፣ ሸለጌ የፈጠን ጥግ ተንተርሶ፣ በሸምብራ ምድር በኩል ከመጣው የጣልያን ወታደር ጋር ተዋጋ። ከደብረ ብርሃን አዲስ አበባ የሚጓዘውን ሰውና ዕቃ በመንገድ ላይ እያደፈጠ በመውጋት ብዙ ጉዳት አደረሰበት። ጠላትም በበኩሉ ይህንን አርበኛ ቡድን በእንጭጩ ለመቅጨት ሞከረ። በኃይል እንደዛ ለማድረግ ግን አልተቻለውም። ሁለት ጊዜ ጦርነት አካሂዶ ሁለት ጊዜም ከተሸነፈ በኋላ ዘዴውን ለውጦ ዕርቅ ጠየቀ። አርበኞች በሰላም እጃቸውን ከሰጡ ምንም ዓይነት ጉዳት እንደማይደርስባቸው ማረጋገጫ ሰጠ። በአስታራቂነቱ ካህናትም ገቡበት። በዚህ ዓይነት አርበኛው ተታሎ በሐምሌ ወር 1928 ዓ.ም እጁን ለጠላቱ ሰጠ። ጠላትም ደብረ ብርሃን ወስዶ ፊታውራሪ መኩሪያን ከአርባ አንድ ባልደረቦቻቸው ጋር በመትረየስ ረሸናቸው።

ጦርነቱ በሌላውም የቡልጋ አካባቢ ተጀመረ። ጥቅምት 14 ቀን 1929 ዓ.ም አሰቤ አገር፣ ወህኒ በተባለው ቦታ ጠላት በአርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው አርበኛ ተኩሱን በተኩስ ተከላክሎ ራሱን ከጉዳት አዳነ። አለቃ ወልደፃድቅ በሕይወታቸው ለመጀመሪያም፣ ለመጨረሻም ጊዜ ጥይት ከሽፋሽፍታቸው ላይ ጨረፈቻቸው።

በሸንኮራም እንደዚሁ እንቅስቃሴ የተጀመረው በዛው በ1929 የመጀመሪያዎቹ ወራት ነበር። ጣልያን በሸንኮራ በኩል አልፎ የያዘውን የአርበኛ ሠራዊት ከአልበተነ የባቡሩ መሥመር ጤና እንደማያገኝለት ተረዳ። አማካሪ ባንዶችም አላጣም። ስለዚህም የማጥቃት እርምጃ ወሰደ። የጠላት ጦር ብዙ የነጭ ወታደር፣ የአፍሪካ ቅኝ ግዛት ወታደሮች[3] እና ብዙ ባንዳ ነበረበት። ከአርበኞች ወገን በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመራው ሠራዊት መጠነኛ ብዛት ነበረው። እነፊታውራሪ /ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተሚካኤልና እነ ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያም ተባብረውት ነበር።

አርበኞች ጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም ገጠሙት። ቦታው ከባልጭ ከተማ በስተደቡብ ራምቡቲ የተባለው ነበር። ጦርነቱ ከጥዋት ጀምሮ ሲካሄድ ዋለ። ከጠላትም ከአርበኞችም ብዙ ሰው ሞተ፣ ቆሰለ። ጠላት አየለ።



የተረፈው አርበኛ ተበታተነ። በፊታውራሪ /ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተገብርኤል የሚመራው፣ ከአርሲ የመጣው ቡድን ተመልሶ ወደ አሩሲ ሸሸ። ደረቅ ጦር ስለነበረ በደጃዝማች ፍቅረማርያም የሚመራው ቡድን ወደ ምንጃር ወረደ።[4] ጉዞው በዝናም፣ መሬቱም ጭቃ ነበርና፣ ሊያመልጥ አልቻለም። ከፊሉ ሞተ፣ ከፊሉ ቆስሎ ወደቀ፣ ከፊሉ ተማረከ። ጠላትም የተማረከውን አርበኛ ኤጀሬ ወስዶ በ30 እና በ40 እየከፈለ በቤት ውስጥ እጅ፣ እጁን የፊጥኝ በማሠር እያጉረ መርዝ ረጨበት። ቶሎ ያልሞቱት እያንቋረሩ ስለአቃቱ፣ ጥቅምት 21 ቀን በእሳት አቃጠላቸው።[5]

ጀግናው ደጃዝማች ፍቅረማርያም ይናዱ በዚህ ጦርነት ላይ ወደቁ። እንዳልሞቱ ግን ተነገረ።[6] ከጦርነቱ ድነው እንደወጡና ወደ ሣማ ሰንበት ዋሻ እንደገቡ ለቤት አሽከሮቻቸው መነገሩን በዕለቱ የሰሙ ሰውም አሉ።[7] የጣልያኖቹም ማስታወሻ የሚያመለክተው እንደዚሁ የተዘበራረቀ ነገር ነው። ጋዜጠኛው ቹሮ ማጂሊ ጥቅምት 19 ቀን 1929 ዓ.ም በፃፈው ማስታወሻ "ፍቅረማርያም በሐዲዱ አካባቢ ተገደሉ..."ይላል። እንደገና ጥቅምት 23 ቀን በፃፈው ማስታወሻው ደግሞ አንዱ አስካሪ /የቅኝ ግዛት ወታደር/ ጭንቅላታቸውን ቆርጦ አዲስ አበባ እንደአመጣ፣ የሚያውቁአቸው ሰዎች የእሳቸው ራስ መሆኑን ስለአረጋገጡ ለወታደሩ ገንዘብ እንደተከፈለው ገልፆአል። የተገደሉበት ቦረ ኤረር ተራራ አጠገብ ከምትገኝ ሌቸ ከተባለች ቦታ እንደሆነም ይነገራል። ውሎ አድሮ መጋቢት 30 ቀን 1929 ዓ.ም በተፃፈ ሌላ ማስታወሻው ደግሞ አርሲ ውስጥ እንደሞቱ አድርጐ ያመለክታል። መንደሩንም የጣልያን ሹማምንት እስከ ቦታው ደረስ ሄደው እንደ አዩ ይገልፃል።[8] ዋናው ነገር ደጃዝማች ፍቅረማርያም በአንድ ልብ ፀንተው በጠላት እጅ መውደቃቸው ነው። ይህንን ጠላትም፣ ወገንም አምኖበታል።

እንዲሁም፣ እንደተገለፀው ጦርነቱ ላይ እነ ፊታውራሪ /ደጃዝማች/ በቀለ ሀብተሚካኤል እና እነ ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ፣ እንደዚሁም የቡልጋ ወጣቶች የተሳተፉበት ታላቅ ጦርነት ነበር። ደጃች ፍቅረማርያም ራሳቸው ውጊያ ከጀመሩበት ቦታ ማፈግፈግ የማይፈልጉ፣ የንጉሠ ነገሥቱን ወደ አውሮፓ መሄድ እንኳን አጥብቀው የተቃወሙ ሰው ነበሩ። አዲስ አበባን ባጠቁ ጊዜ እንኳን፣ በጣቢያው ቆይቶ ሌላ ጊዜና ቦታ ቢፈለግ እንደሚሻል ሀሳብ ቢቀርብላቸው "ማይጨውም የተሸነፍነው እንዲሁ ተብሎ ነው..." ብለው በእልህ ጦርነቱን እንደከፈቱ በታሪክ ተመዝግቧል።[9] ስለዚህ በጦርነቱ ላይ መሞታቸው ይበልጥ አስተማማኝ ነው። ከጦርነቱ ተመልሰው ወደ ሳማ ሰንበት ዋሻ ሄዱ የሚለው እውነትነት ያለው አይመስልም። ሠራዊቱ እንዳይደነግጥ የተፈጠረ ማደናገሪያ ሳይሆን አልቀረም።

ያም ሆነ ይኽ፣ የአርበኞችን እንቅስቃሴ የደጃዝማች ፍቅረማርያም ሞት አላቀዘቀዘውም፤ እንዲያውም ይበልጡኑ ተጋጋመ። መጋጋሙ ጠላትን አስነገነው። ከአካባቢው ባንዳ እየመረጠ፣ መሣሪያ እየሰጠ ማዘጋጀት ጀመረ።

በቡልጋ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ፣ በምንጃር ፊታውራሪ አስፋው ሀብተማርያም፣ በበረከት ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖት /በኋላ ተፀዕተው በአርበኝነት የሞቱ/ ጉዳይ አስፈፃሚዎች ሆኑለት። ሥራውም በመጠኑ ተቃናለት። ይህ ሁኔታ በሕዝብ መካከል የሐሳብ ልዩነት ቀሰቀሰ። ጉዳዩ በምክር የሚፈታ አልሆነም። ባንዳነት ካልገባውም አብዛኛው ደገኛ ለጠላት አመኖ አደረ። አብዛኛው ቆለኛው ሸፈተ። ስለዚህ አርበኛ ለመሆን የወሠነው ደገኛ ቆላ ወረደ። ለጠላት ያመነ ቆለኛ በበኩሉ ደጋ ወጣ። በዚህ ዓይነት ማናቸውም ወገን፣ ውሳኔዉን ለመፈፀም የሚያመችውን የተግባር ቦታውን ያዘ።

ጠላት በበኩሉ አካባቢውን የመቆጣጠር አዝማሚያ አሳየ። አርበኞች ይህንን ሁኔታ የማይታገሱ ሆኑ። በመሆኑም ህዳር 10 ቀን 1929 ዓ.ም ጦርነት ተከፈተ። እንደ ሽፍቶች ይታዩ የነበሩት አርበኞች በዚህ ቀን ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ተኩሱ የተከፈተው ወደ አይገብር ከተባለው ተራራ ላይ ነበር። ይህ ቦታ የተመረጠው ታስቦበት እንጂ፣ እንዲያው በአጋጣሚ የሆነ አልነበረም። ቡልጋ እንደማይገብር፣ ጣልያን ቁርጡን እንዲያውቀው ነበር። ጦርነቱ በማግሥቱ ቀጥሎ ዋለ። ጠላትም እንደ አልሆነለት አውቆ ወደ መጣበት ተመለሰ። አርበኞችም የቅዱስ ሚካኤልን በዓል አስቤ አገር አከበሩ።

ጣልያን ደጃዝማች ፍቅረማርያምን ከአጠና፣ ሠራዊታቸውን ከበተነ በኋላ፣ አረርቲ ላይ ምሽግ ቆረቆረ። ወደ ተድላ ማርያም ለመሻገርም ከጀለ። በዚሁ በህዳር ወር መጨረሻም ሰበርና ዮሐንስ ላይ ጦርነት ተደረገ። ከሁለቱም ወገን ሰው ሞተ። በዚሁ ወር በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ላይ፣ ጋይ ሜዳ ከተባለው ቦታ ጠላት ድጋሚ አደጋ ጣለ። ተከላክለው ስለመለሱት ጉዳት ማድረስ አልቻለም።

እንዲህ እያለ የአርበኞቹ ኃይል ጠነከረ። ጣልያን ይህንን በማየት በረከትንና አካባቢውን በአይሮፕላን አስደበደበ። ድብደባውን በታህሣስ ወር 1929 ዓ.ም በመጀመሪያው ሣምንት ድንጋይ ጥራ በተባለው ቦታ ጀመረ። በየቀኑ አራት አራት አይሮፕላን እየላከ የቦምብ መአት አወረደ። በመጀመሪያው ቀን በሕዝብ ላይ ታላቅ ድንጋጤ ወደቀ። ነገር ግን ጠላት በዚያ ሁሉ ድብደባ ያደረሰው ጉዳት አንድ ላምና ሦስት አህዮች መግደል ብቻ ሆኖ ስለተገኘ፣ ሕዝቡ ከደረሰበት ድንጋጤ ፈጥኖ አንሰራራ። ለአይሮፕላን መሸበሩም ቀረ።

ይህ የአይሮፕላን ድብደባ ግን አርበኞችን አስገነገነ። ያስገነገነበት ምክንያትም ድብደባው የተካሄደው በዋናው የአርበኞች አስተባባሪ፣ በፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ቤት ላይ ሳይሆን፣ በአንዱ ቡድን መሪ በቀኛዝማች ታቺ ቤት ላይ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ፊታውራሪ ኃይለሥላሴ ከጠላት ጋር የውስጥ ግንኙነት እንደሌላቸው በግብር ማረጋገጥ ግድ ሆነባቸው። ጠላት ይህንን ድብደባ ያካሄደው በማን ጠቋሚነት እንደ ሆነ ለማወቅ ጥናት ተደረገ።



በተገኘው ፍንጭ መሠረት እርምጃ ተወሰደ። የድብደባው አቀነባባሪ የነበረው ባሻ በላይነህ ባንዳ ታህሣሥ 19 ቀን 1929 ዓ.ም ሙገሬ ዛላ፣ እለእሴ ከነበረው ቤቱ ተከበበ። እጁን እንዲሰጥ ቢጠየቅ ፈቃደኛ ባለመሆኑ ተገደለ።

የዚህ ሰው መገደል ጠላትን አስቆጣ፤ በተለይም ፊታውራሪ ተሰማ ከተማን። ጠላትም አዲስ ጦር ሠርቶ ታህሣሥ 25 ቀን ሙገሬ ዛላ ገባ። አርበኞችም በየአሉበት በሕዝብ በጥሪ ተሰብስበው በማግስቱ ታህሣስ 26 ቀን 1929 ዓ.ም እመይት አገር ግንባር ለግንባር ገጠሙት። ጦርነቱ ከንጋት እስከ ምሽት ዋለ። አርበኞቹ የጀግንነት ተግባር ሠሩ። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ጠላትም የሕዝቡን ቤት በማቃጠልና ከብቱን በመዝረፍ አፀፋውን ተበቀለ። ከአርበኞችም ጥቂቶቹ ሞቱ። የደጃዝማች ፍቅረማርያምን አሟሟት ወሬ ከአመጡት ሦስት ሰዎች ሁለቱ በዚህ ጦርነት ወደቁ። ጠላት ወደ መጣበት ወደ አንኮበር ሸሸ፤ አርበኞችም ወደበረከት ወረዱ።

ጠላት ሳይውል ሳያድር በአርበኞች ላይ ሌላ አዲስ ጦርነት ከፈተ። ይህኛው ደግሞ በበረከት በኩል ነበር። ጠላት አዲስ ጦር ነው ያቀረበው። አርበኞቹ ግን እነዚያው በእመይት አገር ጦርነት የደከሙት ብቻ ነበሩ። ቢሆንም በቆራጥነት በረከት ላይ ገጠሙት። ታህሣሥ 28 ምና 29 ዓ.ም ሙሉ ቀን ተዋጉ። ከሁለቱም ወገን ብዙ ሰው አለቀ። ጦርነቱ ከእመይት አገርም የከፋ ነበር። ስለዚህ አርበኞቹ አካባቢውን ለቅቀው ወደ ወይናደጋው ወጡ። ጠላትም ወደ ቦታው ተመለሰ። በሁሉም ላይ ድካም ጠንክሮ ነበርና አንዱ ሌላውን ለማባረር አልሞከረም።

አርበኞች እንደዴ በተባለው ቦታ ሠፍረው ጥቂት ዕረፍት ከአደረጉ በኋላ ምክር ተጀመረ። የሐሳብ ልዩነት ተፈጠረ። አንዱ ወገን "ስግደድ ብለን ከደረሰብን ጉዳት እናገግም፣ በየአለበት ከሚገኙ አርበኞች ጋርም እንላላክ" ሲል፣ ሌላው ወገን ደግሞ "ጊዜው ፋታ የሚሰጥ አይደለም በርትተን እንከላከል፣ ካልቻልን አካባቢውን ለቅቀን እንውጣ" አለ። አስታራቂ ሐሳብ ጠፋ። ምክንያቱም ሳይታወቅ የምክሩ አቀነባባሪና አማካሪ በሻህ የተባለ ሰው ሆነ። እሱም እስከ ሦስት ቀን ድረስ ከቤቱ እንዲቆዩ አበክሮ አሳሰበ። የሚበዛው ሰው በዚህ አጉል ምክር አመነ። የበሻህ ውትወታ በሞገደኛው በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራውን ቡድን አስገነገነ። ቡድኑ በዚህ ነገር አልስማማም ብሎ በሰላም ተሰናብቶ ጥር 1 ቀን 1929 ዓ.ም ተለይቶ ወደ ሙገሬ ዛላ ሄደ። በፊታውራሪ ኃይለሥላሴና በባላምባራስ ይልማ ወልደኢየሱስ የሚመራው የአርበኞች ቡድን ከዚያው ከበሻሁ ቤት ቀረ።

ይህ በሻህ የተባለው ጠንቋይ፣ ከጣልያን ጋር በምሥጢር ተላልኮ ኖሮ፣ በእሱ ምክር አምነው ከቤቱ ውስጥ የተቀመጡትን አርበኞች ጥር 2 ቀን 1929 ዓ. ም አስያዛቸው። ጣልያንም ሹማምንቱን በሰንሰለት፣ ሠራዊቱን በገመድ የፊጥኝ እንደታሠሩ ወደ አንኮበር ወሰዳቸው። የአንኮበሩ ገዥ ጥር 10 ቀን የጥምቀት ዕለት በአደባባይ በመትረየስ ፈጃቸው። ከአሥር ያልበለጡ

አባላት የነበሩት በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው ቡድን ግን የአርበኝነት ሥራውን ቀጠለ። በተደጋጋሚ ወና፣ እመይት አገር፣ በረከት ላይ የተካሄዱት ጦርነቶችና የእነ ፊታውራሪ ኃይለ ሥላሴ በጠላት እጅ ተይዞ መገደል፣ በሕዝበ ልቡና የነበረውን ፍርሃት እንደገና እንዲያገረሽ ስለአደረገው የአርበኞች ሥራ እንደሸፍትነት ተቆጠረ። አርበኞች ግን ትግላቸውን ቀጠሉ።

ከዚህ ላይ እኔ ራሴ ስለማውቀው፣ ጠቅሼው ስለነበረው፣ በግል ፈቃዱ አርበኝነት ስለገባው አንድ ጀግና አብራርቼ ልገልጽ ይገባኛል። ስሙ በየነ ወልደገብርኤል ሲባል፣ የትውልድና የአርበኝነት ቦታው በረከት፣ ዋጨ ነበር። ጓደኞቹ በዚህ ጦርነት ሲያልቁና ሲበታተኑ፣ እሱ ብቻውን ተጋድሎውን ቀጠለ። በእመይት አገሩ ጦርነት ጊዜ አንድ ለበን ጠመንጃ ማርኮ ናስ ጠመንጃውን ለወጠ። ነገር ግን ከለበኑ ጋር ያገኘው፣ በውስጡ የጐረሰውን አሥር ጥይት ብቻ ነበር። ዝናሩ፣ የጠላት ወታደር እንደታጠቀው አምልጦታል። ጠላት በየነ የነበረበትን ቦታና ሁኔታ አውቆ ከበበው። በየነም የካቲት 13 እና 14 ቀን 1929 ዓ.ም ሁለት ቀን ሙሉ በአንዲት ዋሻ ውስጥ ሆኖ በጀግንነት ብቻውን ተዋጋ። ስምንት ሰው እንደገደለ ሸለላውን አቆመ። ቦታው ርጭ ጭጭ አለ። ጠላት ገብቶ ቢያይ አርበኛው ዘጠነኛዋን ጥይት ጠጥቶ ሞቶ ተገኘ። ታዲያ አንድዋን ጥይት ለምን ተዋት? ብሎ ለሚጠይቅ፡- ዘጠነኛዋ ብትከሽፍ፣ ለመጠባበቂያ እንድትሆነው ብሎ መሆኑ ነው።

ወደ ዋናው ጉዳይ ልመልሳችሁ። በዚህ ጊዜ ላይ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ሰው ማስተባበራቸውን ቀጠሉ። ጠላት ይህንን ሰምቶ አካባቢውን መበርበር፣ መፈተሽ ያዘ። በቅዱስ ሚካኤል ላይ የነበራቸውን ተአምኖ በማወቅ፣ የአሰቤ አገር ሚካኤልን መንበር ጭምር አስገልጦ አየ። ነገር ግን ሕዝቡ አጥብቆ ስለደበቃቸው አላገኛቸውም።

ከዚህ ላይ ደግሞ የአንድ ሌላ ካህንን ብልሀት መጥቀስ ያስፈልገኛል። ደብተራ ወልደማርያም ይባላሉ። ቦታቸው በረከት ቡርቃ ከተባለው አገር ነው። አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅን ደብቀዋል ተብሎ በጠላት ትእዛዝ ሜጢ፣ አቶ ደጀኔ ወልዴ ቤት ይታሠራሉ። የታሠሩበትን እግር ብረት ሰብረው አወጧቸው። ናዝሬት (አዳማ) በመሄድ፣ ፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በሕዝብ ላይ የሚያካሄዱትን ጭፍጨፋ በማስረዳት ከሥልጣናቸው ተሽረው፣ ሸኖ ከተማ በግዞት እንዲቀመጡ አስደረጉ። በተጨማሪ አሥራ ሦስት አገር ያምሱ የነበሩ ሌሎች ባንዶች፣ ቆስጤ አገር ተወስደው መቃብራቸውን ራሳቸው ቆፍረው በጥይት እንዲደበደቡ በማድረግ ለአካባቢው አርበኞች ሁሉ አብነት ያለው ሥራ ሠሩ። በአርበኞች ላይ የነበረው ውጥረት ተቀነሰ።

ትግሉ በገለፅኩት ሁሉ መልክ የቀጠለ ቢሆንም፣ ከጥር 1 እስከ ሐምሌ 20 ቀን 1929 ዓ.ም የነበረው ጊዜ፣ በዚያ አካባቢ ለነበሩ አርበኞች እጅግ ከባድ ነበር። በመሆኑም ለጠላት ያላመኑ ወገኖች በሙሉ፤ ሴት፣ ወንድ፣ ልጅ፣ አዋቂ፣ ካህን፣ መሃይምን ሳይሉ፤ በሀሳብና በሥራ መተባበር



ነበረባቸው። እኔም እንኳን በሕፃንነት አቅሜ የሥራ ድርሻ ነበረኝ። ሥራዬም ለገበሬዎች የምወስድ እያስመሰልኩ ለአጐቴ ለአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ስንቅ ማቀበል ነበር። የሚያስደንቀው ነገር ይህንን ሥራ ለማካሄድ እናቴን ወ/ሮ ፀዳለ አባ በለውን ከባለቤቻው ከአቶ ደጀኔ ተክሌ፣ አባቴን አለቃ ዘዮሐንስ ዘውዴን ከባለቤታቸው ከወይዘሮ ዘነበች ተክለሃይማኖት አፋትቼ ማንም ሰው ሳይሰማ ለማስታረቅ መቻሌ ነው። ይህንን ማድረግ የተገደድኩት የእንጀራ አባቴ ከጐኑ፣ የእንጀራ እናቴ ከጠቃ አገር የወረዱ ደገኞች ስለነበሩ፣ ወሬ እያፈተለከ ስለአቃተ ነበር። በዚህም የስንቅ ማቀበሌ ሥራ ተቃና።

የስንቁ ማቀበል ሥራ ቢቃናም፣ በእኔ ላይ ግን ሌላ ችግር ተከተለ። መጀመሪያ የእንጀራ አባቴ፣ ቀጥሎም የእንጀራ እናቴ ንብረቶቻቸውን በማጣታቸው ባደረባቸው ቁጭት፣ ምስጢሩን በፊታውራሪ ተሰማ ከተማ በኩል ለጣልያን አደረሱ። ጣልያንም በበኩሉ እኔን እንዲያስረክቡት አቶ ተክሌ ቢረሴ የተባሉት ሽማግሌ፣ ቅድም አያቴን ያዘ። ቅድም አያቴ ግን እኔን ለጠላት ማስረከብ ስላልፈቀዱ፣ ዳዊት አገር የተባለ መልከኝነታቸውን ነጥቆ ታደሰ ለተባለ ባንዳ በመስጠት አዘረፋቸው። እሳቸውም በዚህ ብስጭት ሞቱ።

አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የጀመሩት ሰው የማስተባበሩ ሥራቸው ተቃናላቸው። እነ ግራዝዝማች/ፊታውራሪ/ አጐናፍር ባዩ፣ እነ አቶ/ቀኛዝማች/ ስንቅነህ፣ እነ አቶ /ፊታውራሪ/ ኃይሌ/ኃይለ ራጉኤል/ ወልደፃድቅ፣ ሌሎችም በብዛት ተባበሩአቸው። የጠላት ክትትል ስለጠነከረ በሰኔ ወር አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ እንደሞቱ አድርጐ ማውራት አስፈልጐ እንደዛው ተደርጎ ነበርና፣ አለመሞታቸውን ሲረዳ ጠላት ከፍተኛ ጦር አዘመተ።

ይህ ጦርነት ወሳኝነት ስለነበረው ዝርዝሩን ማየት አስፈላጊ ነው። አርበኞች በዝያን ሰዓት የነበሩት ሀገረ ማርያም ጭቁ ቀላ ነበር። ጠላት ሲመጣ ጥቂት ሰዎች እየተኮሱ እንዲሸሹ አደረጉ። ጠላትም ለማባረር ወደደቡብ የሚፈስሰው ወንዝ እንደደጋን ተጠምዝዞ ወደ ምሥራቅ ከሚዞርበት ጉባ ውስጥ እንዲገባ አደረጉት። በአንፃሩ አርበኞች ገዥ ምድር የሆነውን የደብረ ብርሃን ጥግ ያዙ። የጣልያን ወታደር እዚያ ላይ ሲደርስ አደጋ ጣሉበት። በየጫካው ውስጥ ሆነው በጥይት ጠዘጠዙት፤ መውጫ መግቢያ አሳጥተው ፈጁት። አገሬው በጐራዴ፣ በጦር፣ በአንካሴ፣ በጩቤ፣ በዱላና በመጥረቢያ ሳይቀር የጠላትን ወታደር፣ በተለይም ባንዳውን ከተከተው። ከጠላት ወታደር ከሦስት መቶ በላይ ሞተ፣ ሌላም ብዙ ቆሰለ። የቀረውም መሣሪያውን እየወረወረ፣ ዝናሩን እና ጀበርናውን ከወገቡ እየፈታ እየጣለ ሸሸ። አገሩን ከድቶ፣ ከአርበኝነት ወደ ባንዳነት ገብቶ፣ በአውቃለሁ ባይነት ጠላትን እየመራ ያመጣው ጨፈቃ ይገዙ የተባለው ባንዳ ተገደለ። ከወገንም ጥቂት ሰው ሞተ። ከስድስት መቶ በላይ እንደ ማውዜር፣ ለበን፣ ቤልጅግ ያለ ደረቅ ብረትና አንድ አውቶማቲክ ከነጥይቱ ተማረከ። ቡልጌ ከአረማዝ

የዘረፈውንና ከአባቱ የወረሰውን እንደ መስኮብ፣ ወጂግራ፣ ሰናድር፣ ናስ ማሥር የመሳሰሉትን ብረቶችን ጣለ። የማረከውን ደረቅ ብረት ጨበጠ።

አርበኞች የቆላውን ሀገረ ማርያምን፣ የተድላ ማርያምን፣ የክትበወይራን፣ የሙገሬ ዘለን፣ የበረከትን ሕዝብ አስተባበሩ። ከጠላት ጐን ሆኖ የወጋቸውን ከትንቢት እስከ ገርም ገብርኤል ድረስ ያለውን አገር አቃጠሉት። ከዚያም ወደ ቆላው ወደ በረከት ወረዱ።

በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን እዳንዴ ገባ። አውፋ አቤኮ በሻህ ቤት ሲበላ፣ ሲጠጣ አደረ። በሻህም የሆነለት መስሎት ፍሪዳ አርዶ እየጠበሰ፣ እየቀቀለ አስተናገደ። ጥዋት ቁርስ ከተበላ በኋላ ፍርድ ተያዘ። በሻህ እንደምን ከጠላት ጋር እንደተሳሳከና ግንኙነቱ በእነማን አማካይነት እንደነበረ ተናዘዘ። አንድ ሰው የሚራራለት ጠፋ። ነሐሴ 17 ቀን እሱም በተራው በፍርድ በጥይት ተደበደበ።

እንግዳ እሸት የተባለ የልጅ ኢያሱ ልጅ በአብዬ ገዳም መድኃኒዓለም አለቃ በአባ ይርዳው እጅ እንደአለ ያውቁ ነበርና፤ አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የበሻህን ፍርድ ካስፈፀሙ በኋላ ወደ ገዳሙ አመሩ። ከዚያም መነኩሴውን አባ ይርዳውን በማሳመን፣ ወጣቱን መሥፍን እንግዳ እሸትን ነሐሴ 19 ቀን 1929 ዓ.ም ወደ ጦር ሠፈራቸው ወደ መክፈሌ ወሰዱት። አባ ይርዳውም ማታውኑ እስከ ጦር ሠፈር ደረስ መጥተው ወጣቱ የልጅ ኢያሱ ልጅ መሆኑን ለአርበኞቹ አረጋገጡ። ያሰበው ሀሳብ እንደማይቃና ያላቸውንም ሥጋት ሕልማቸውን በማዘር ገለፁ።

ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በተጣለባቸው አደራ ምክንያት ጥቂት ቢያቅማሙም የሀገር ጉዳይ መሆኑን በማየት በወጣቱ መሥፍን መንገሥ ተስማሙ። አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ወጣቱን መሥፍን እጅ ከአደረጉ በኋላ በአካባቢው ለነበሩ አርበኞች ጥሪ አስተላለፉ።

አርበኛው ወከረሴ ከተባለው ቦታ ነሐሴ 20 ቀን 1929 ዓ.ም ተሰብስቦ ምክር ተያዘ። ጥያቄው የአርበኝነትን ሥራ ለማጠናከር በሚችልበት ጉዳይ ላይ አተኮረ። አርበኝነትን ለማጠናከር አንድ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል መሪ መምረጥ ማስፈለጉ ታመነበት። በአለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው ቡድን ያቀረበው ሀሳብ የልጅ ኢያሱን ልጅ ማንገሥ ሆነ። ተቃውሞ ተነሳ። ተቃዋሚውም ደግሞ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከዓለም መንግሥታት ማህበር ዕርዳታ ለመጠየቅ ወደ አውሮፓ ሄደው ሳለ፣ የእሳቸው ቁርጥ ሳይታወቅ ሌላ ንጉሥ ማንገሡ እንደምን ይቻላል? የሚል ሆነ። ጠንካራ ክርክር ተካሄደ። ንጉሥ እናንግሥ የሚለው ሀሳብ አመንጭና አራማጅ የነበሩት አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ የዚህን ጉዳይ አስፈላጊነት አጥብቀው አስረዱ። ክርክሩ እየጠነነ በሄደ ጊዜ "አንድ ሰው ሸሽቶ ስለሄደ ሁላችን እናልቃለንን?" ብለው ጠየቁ። እናንግሥ የሚለው ሀሳብ ተደገፈ። ከምክር በኋላ አዲስ ንጉሥ እንዲነግሥ ተወሰነ።



ንጉሥ እናንግሥ የሚለው ሀሳብ ያሸነፈባቸው ምክንያቶች፤

1ኛ. በፊታውራሪ ኃይለሥላሴ የሚመራው ቡድን ጥር 2 ቀን 1929 ዓ.ም በጣልያን እጅ ወድቆ ለእልቂት የተዳረገው በሕዝብ ዘንድ ድጋፍ ያለው መሪ ባለመያዙ እንደሆነ ከልምድ በመታየቱ።

2ኛ. ጣሊያን ኃይልዋን አጠናክራ ሕዝብ በገሐድ መፍጀትዋ። ከየካቲት 12-14 ቀን 1929 ዓ.ም አዲስ አበባ፤ ከዚያም እንደ ደብረ ሊባኖስ፣ ዝቋላ ገዳም፣ ደብረ ብርሃን ላይ የታየው እልቂት።

3ኛ. ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወደ ስደት ከሄዱበት ከሚያዝያ 25 ቀን 1928 ዓ.ም ጀምሮ ምንም ወሬ አለመሰማቱ።

4ኛ. የጣልያንን በኢትዮጵያ ላይ ገዥነት ብዙ የውጭ አገር መንግሥታት ማወቃቸው ነበሩ።

በኋላ ላይ ግን፣ የንጉሠ ነገሥቱ ለመንግሥታት ማህበር ሰኔ 23 ቀን 1929 ዓ.ም አቤቱታ ማቅረባቸው እየተሰማ በሄደ ጊዜ ፣ አዲሱ ንጉሥ ተሰበቀስ ደጋፊ እያጣ መጣ። የአርበኛውም ጆሮ ወደ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እያቆበቆበ፣ ልቦናውም ቀስበቀስ ወደ እሳቸው እየተመለሰ ሄደ። የአዲሱ ንጉሥ ጉራ እየቀዘቀዘ ሀዶ በመጨረሻው ላይ እንዴት እንደፈረሰ ወደፊት እናያለን።

የንግሡ ዝግጅት ተካሄደ። የደጃዝማች ወልደገብርኤል የክብር ልብስ ወጣ። የአካባቢው ካህናት በወክፈሌ ሚካኤል ተሰብስበው በአንድ ወገን ሰዓታት በሌላ ወገን ማህሌት ተቆመ። በሦስተኛ ወገን የሥርዓተ ንግሡ በሎት ተደረሰ። እንግዳ እሸት የተባለው የአሥራ አምስት ዓመት ወጣት፣ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ተብሎ፤ እሑድ ነሐሴ 24 ቀን 1929 ዓ.ም፤ እንደ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት፣ ሥርዓተ መሐላ ፈጽሞ ሥጋ ኢየሱስ ተቀበለ። ቅብአ መንግሥት ተቀብቶ ከነገሠ በኋላ ሥርዓተ ቅዳሴ ተካሄደ።

የቤተክርስቲያኑ ሥነ ሥርዓት እንደተፈፀመ፣ ነጋሪት እየተጐሸመ የአርበኛ ሠራዊት እየተመመ ወደ ሀገሩ መልከኛ ቤት ጉዞ ሆነ። ከቁርስ በኋላ የመጀመሪያው ሹመት በነጋሪት ተሰጠ። ቀኛዝማች ኃይሉ ወልደመድህን የደጃዝማች ተብለው የወጣቱ ንጉሥ ሞግዚት ሆኑ። ግራዝማች አጐናፍር ፊታውራሪ፣ አለቃ ወልደ ፃድቅ ቀኛዝማች፣ አቶ ስንቅነህ ቀኛዝማች፣ አቶ ኃይሉ ወልደፃድቅ ግራዝማች ተባሉ። በሣምንቱ ነሐሴ 28 ቀን 1929 ዓ.ም ደግሞ ለሁለተኛ ጊዜ የማረሚያና የማጠናከሪያ ሹመት ተሰጠ። ቀኛዝማች ወልደፃድቅ ፊታውራሪ ተባሉ። ሌሎችም አርበኞች ተሾሙ።[10]

በሸዋ ለነበሩ አርበኞች የትብብር መጠየቂያና እንዲመጡ የመጥሪያ ደብዳቤ ከአዲሱ ንጉሥ ተላለፈ። ለባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ የተፃፈውን ደብዳቤ አቶ ኪዳኔ አደረሱ ይባላል። እኔ የማውቀው ግን አቶ ይፍሩ አየለ የተባለ የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ባልደረባ መውሰዱን ነበር። ባላምባራስ

/ራስ/አበበም መንዝ ሣጋ ከተባለ ቦታ ተነስተው በጦጦሲ በጠራ አድርገው ከደጃዝማች ዘውዴ አባኮራን ጋር በመምጣት፣ አሣግርት ፍንጥርጌ ከተባለው ቦታ ጥቅምት 8 ቀን 1930 ዓ.ም ለንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ምኒልክ ገቡ፡፡ የመልአከ ፀሐይ መንግሥት በልጅ ኢያሱ ላይ ሴራ ለሠሩ ወገኖች ጭንቅ ሆነ፡፡

ሸንኮራ፣ ምንጃር፣ ቅንብቢት እስከ አንኮበር ድረስ የአርበኝነት ሥራ ያዘ፡፡ ከአርሲም ፊታውራሪ መኰንን ወልደጊዮርጊስና ፊታውራሪ ከበደ ወልደጊዮርጊስ መጡ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ደግሞ ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ መጡ፡፡ /ፊታውራሪ/ ወልደ ፃድቅ ዘውዴ ከጥቂት ግብረ አበሮቻቸው ጋር በታጋይነት መልክ የጀመሩትን ሥራ በሰቃ ዋጩ ጦርነት አማክኝነት ዳብሮ ወደ ሽፍትነት የደረሰው፣ ከዚያም ሀገር የመከላከሉ ሥራ ንጉሥ መልአከ ፀሐይን አንግሦ ወደ ከፍተኛው የአርበኝነት ሥራ ተሸጋገረ፡፡ ማንም አራሙቻ ቢጥልበት፣ የማይጠፋ ታሪካዊ ሥራ ተካሄደ፡፡

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተብሎ በወቅቱ ነግሦ በነበረው ንጉሥ የተሾሙ እና በእሱ የተሰጣቸው የማዕረግ ዓይነት ከብዙ በጥቂቱ፡-

ባላምባራስ አበበ አረጋይ የራስ ማዕረግ፤
ቀኛዝማች ኃይሉ ወልደመድህን የደጃዝማች ማዕረግ፤
ፊታውራሪ ዘውዱ አባ ኮራን የደጃዝማች ማዕረግ፤
ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የደጃዝማችነት ማዕረግ /አልተቀበሉም/
ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴ የደጃዝማችነት ማዕረግ፤
ለአለቃ ወልደፃድቅ ዘውዴ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለባሻ ደባልቄ ተክሌ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ መኰንን ወልደጊዮርጊስ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ከበደ ወልደጊዮርጊስ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ከበደ ካሣ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ አጕናፍር ባዩ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ አበበ ወልዴ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሀብቴ ሥላሴ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ኪዳኔ ወ/ጊዮርጊስ የፀሐፊ ትዕዛዝነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሉሌ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ በለጠ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ ተሰማ ጉርጂ የፊታውራሪነት ማዕረግ፤
ለአቶ መኩሪያ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ወዳጆ ጉርሙ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ለማ ሽቀጣ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ታፈሰ አባናዳ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ወንድምሲያምረኝ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤



ለአቶ መኰንን አበረቱኝ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ገብረመስቀል ኃይሌ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ልኬለህ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ መኰንን የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ገላግሌ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ፍቅሬ ወልደሰማያት የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሺፈራ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ፈጠነ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ አባይነህ አፍራሳ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ኃይሌ ወልደኪዳን የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሐጐስ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ጋሾ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤
ለአቶ ሺፈራው ዱባለ የቀኛዝማችነት ማዕረግ፤

የኢቲሣ ተክለ ሃይማኖት ገዳም አበምኔት የነበሩት መምህር በላይ፣ ለእጨጌነት በአርበኛው ተመረጡ፡፡ እሳቸው እጨጌ ገብረጊዮርጊስ ተብለው የመንፈሳዊውን ሥራ ማካሄድና ካህናቱን የማስተባበር ሥራ ቀጠሉ፡፡ አዲስ አበባ የደብረ ሰላም እስጢፋኖስ የመጽሐፍ አስተማሪ የነበሩት መምህር ጽጌ የንጉሥ መልአከ ፀሐይ ፍትሐ ነገሥት አውጭ ሆኑ፡፡ የአኮርሚቱ /ኰሎኔል/ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ ለፀሐፊ ትእዛዝነቱ ሥራ ተመረጡ፡፡

የአርበኞች በዚህ ዓይነት መጠናከርና በአዲስ ኃይል መንቀሳቀስ ጣልያንን አስገነገነ፡፡ ወደ አውሮፓ የሄዱትን ቀዳማዊ ኃይለሥላሴን አስደነገጠ፡፡ ኢየሩሳሌም የነበሩትን እጭጌ ገብረ ጊዮርጊስንም አሰጋ፡፡ ዝርዝሩ ወደፊት በየረድፉ ይገልፃል፡፡

ጣልያን በኃይል ተንቀሳቀሰ፡፡ እንደልማዱ የነጩን መኮንንና ወታደር ከኋላ ደጀን አድርጎ፣ ባንዳውን አስቀደመው፡፡ ከባንዳው በኋላ ከኤርትራ፣ ከሊብያና ከሶማልያ ያመጣቸውን የቅኝ ግዛት ወታደሮች ከአዘቦ ከተመለመለ ራያ ጋር አቀላቅሎ ምድሩን እያሰሰ፣ አካባቢውን ከአይሮፕላን እያደባየ መጣ፡፡ ወንዱን እያሰለበ፣ የሴቱን ጡት እየቆረጠ፣ ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ ሰው እየፈጀ፤ ቤተክርስቲያኑን፣ ቤቱን፣ የእሕልና የገለባ፣ የሣር ክምር ሳይቀር እያቃጠለ መጣ፡፡ ታላቅ እልቂት በሕዝብ ላይ ደረሰ፡፡ የጣልያን ሐሳብ ኢትዮጵያን ከምድር ገጽ ማጥፋት መሆኑ በግልጽ ታወቀ፡፡

ጣልያን ጦር ያመጣው ከሞጆ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከሰላሌ፣ ከሸዋ፣ ከደብረ ብርሃንና ከደሴ ነበር፡፡ ሁሉንም በየቦታው አዘመተ፡፡ ዋናው ጦር ከደብረ ብርሃንና ከደሴ የመጣው ነበር፡፡ እሱም በቀንበሩ፣ በጠራ፣ በአሣግርት፣ በቅንብቢት፣ በመጠዱስ አድርጐ በደብር በኩል ሀገረ ማርያም ገባ፡፡ ከዚያም በደንሴ፣ በመከኒሣ አልፎ በጉርጌ ፀኩል ወደበረከት ተሻገረ፡፡ አርበኞች በየጕራቸው ተዋጉ፡፡ ሲመጣ ከፊት፣ ሲጓዝ ከግራና ቀኝ፣ ሲያልፍ

ከኋላው እየተኮሱ ብዙ ወታደር ጨረሱበት። አርበኞች በዚያን ሰሞን ከተዋጉባቸው ቦታዎች ዋና ዋናዎቹ ደጃት፣ ቀምበሬ፣ መሰቢት ደብር፣ ሰቃዋጩ፣ ድንጋይ መዝጊያ፣ ከትም ወይራ፣ ቀሬ ወንዝ ናቸው።

ህዳር 1 ቀን 1920 ዓ.ም ቡርቃ ከተባለው ቦታ ታላቅ ጦርነት ተደርጐ፣ ፊታውራሪ መኰንን ወልደጊዮርጊስ ከብዙ ጀግኖች ጋር ወደቁ። ጣልያንም የፊታውራሪ መኰንንን ራስ ቆርጦ ደብረ ብርሃን በመውሰድ ጌጤ ተጫወተበት። ራስ መቁረጥ፣ በቡልጋ፣ በእሳቸው ተጀመረ። ከጠላትም ብዙ ወታደሮችና ጥቂት መኰንኖች ሞቱ።

ህዳር 7 ቀን 1930 ዓ.ም ከስድስቶ፣ ከአዲስ አበባና ከአራቱ ማዕዘናት፣ ቁጥሩ እጅግ በርከት ያለ የጣልያን ጦር መጣ። አርበኞችም ደፈጣ አድርገው ለእነሱ አመች ከሆነ ቀለበት ውስጥ እስኪገባላቸው ድረስ ጠበቁት። በሽ ዱባለ የተባሉ ጀግና በመጀመሪያይቱ ጥይታቸው አዛገፉን ኰሎኔል ከተቀመጠበት በቅሎ ዘነጠፉት፤ ሌሎችም አርበኞች ሌሎችን ነጮች እየለዩ በመምታት ጨረሱአቸው። ብቻውን ሲቀር፣ ባንዳው ትርምስምሱ ወጣ። በዚያ ላይ ኃይለኛ ዝናም ዘንሞ መሬቱን አጨቀየው፤ ወንዞችን በውሃ ሞላቸው። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ብዙ መሣሪያም ተማረከ። ይህንን የጀግንነት ሥራ የሠራው፣ በቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የሚመራው አርበኛ ነበር።

ኩርፎ በተባለው አካባቢ ከጥቅምት 9 ቀን እስከ ህዳር አጋማሽ 1930 ዓ.ም ድረስ ብዙ ከባድ ውጊያዎች ተካሄዱ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ከሠራዊታቸው ተለይተው ጠፍተው ስለሰነበቱ፣ በባልደረቦቻቸው ዘንድ ከባድ ድንጋጤ ወድቆ ነበር። ቀደም ብሎ በተደረገ ጦርነት ቀኝ እጃቸውን ቆስለው ነበርና ችግሩ ቀላል አልነበረም። ነገር ግን ህዳር 12 ቀን 1930 ዓ.ም ስለተገኙ ደስታ ሆነ።

ባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ በጠፉበት ጊዜ ሠራዊታቸው ይፈልጋቸው ነበር። ሠራዊቱ እሳቸውን ይፈልግ በነበረ ጊዜ ወደዳማ ከተባለ ቦታ ከቀኛዝማች ዘውዴ ተክለጊዮርጊስ ቤት አንድ ባለወርቅ መርገፍ የኢትዮጵያ ሠንደቅ ዓላማ ህዳር 11 ቀን አገኙ። በዚህም ታላቅ ደስታ ሆነ። ያም የሰንደቅ ዓላማ በጦርነት ጊዜ ሁሉ የአርበኛው አርማ ሆኖ ኖረ። አሁንም አዲስ አበባ በጥንታዊ ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር ጽ/ቤት ለታሪክ መዘክርነት ተቀምጦ ይገኛል።

ባላምባራስ /ራስ/ አበበ ከሠራዊታቸው ጋር በተለዩበት ጊዜ ከበሻ አሳየ ጋር መስጊዳ አቶ ተሰማ የተባለ ገበሬ ደብቆ አቆያቸው። እሳቸው ከሠራዊታቸው ጋር ተመልሰው እንደተቀላቀሉ ጦርነቱ ቀጠለ። በተለይ ፊሣ በተባለው ቦታ ላይ ያካሄዱት ጦርነት፣ በቡልጋ ሕዝብ ዘንድ ሲታወስላቸው የሚኖር ነው። በሀገር ላይ የጨፈረውን የጣልያን ጦር በዚያ ቦታ ፊሣ በፊሣ አደረጉት። የአዘቦም አሮሞ የሽዋን ቁላ እንደተሸከመ በየጫካው ተራገፈ።



በዚህ ወቅት ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ጌልጌላ ነበሩ። ከዚያም ወደ ሙገሬ ዛላ መጥተው ጭንቂት ማርያም አቶ ተክለ ወልድ ቤት ሠፈሩ። ባላምባራስ /ራስ/ አበበም መጥተው እንደገና በተገናኙ ጊዜ ደስታ ሆነ። ትግሉ በተጠናከረ ሁኔታ ቀጠለ። ከጦርነቱ ክብደት የተነሳ በያለበት ተበትኖ የነበረው አርበኛ እንደገና ተሰበሰበ። ቁስለኛው በተቻለ መጠን አገገመ። ደጃዝማች አውራሪስ ከእነልጆቻቸው ከመንዝ መጡ። ልጅ ደስታ ሸዋ አርካብህና ባሻ ተሰማ እርገጤ ከይፋት መጥተው ለንጉሡ እጅ ነስተው ሁለቱም ፊታውራሪ ተባሉ። ከጉራጌ አገርም ሻለቃ /ደጃዝማች/ በቀለ ወያ መጥተው ሳይቆዩ ወደ ሥፍራቸው ተመለሱ።

በታህሣሥ ወር 1930 ዓ.ም የአርበኛ መሪዎች ተማከሩ። ምክሩ ጦርነቱን ለመመለስና የጠላትን ኃይል ለመቀነስ ስለሚቻልበት መንገድ ነበር። የአርበኛውም በአንድ ቦታ መከማቸት የፈጠረው ችግርና የሰጠው ጥቅም ከተመዛዘነ በኋላ፣ ሁሉም በየአለቃው እየተመራ በየአገሩ ቢዋጋ፣ ትግሉንም በተባበረና በተቀነባበረ መንገድ እንዲያካሂድ ማድረግ የተሻለ ሆኖ ተገኘ። ከባላምባራስ /ራስ/ አበበ አረጋይ በስተቀር የመጣው ጦር ሁሉ ወደየመጣበት አገር ተመለሰ።

በዚሁ በታህሣሥ ወር 1930 ዓ.ም በፊታውራሪ ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን ተድላ ማርያም፣ ቁንጩ አገረ ገብርኤል ላይ ከጣልያን ጋር ተዋጋ። ጦርነቱ የተከፈተው ሞላሎ ከተባለው የከሰም ወንዝ መልካ ላይ ነበር። ጣልያን ከብቱን ውሃ ሊያጠጣና ለራሱም ውሃ ሊቀዳ ከአረርቲ ውስጥ ወረደ። አወራረዱ በአርበኞች ዘንድ በደንብ የተጠና ነበር። ጠላት መትረየሶች ደጁን አስጠምዶ፣ ጥቂት ወታደሮች ደጀን ሆነው እንዲጠብቁ አድርጎ፣ ሠራዊቱ በሰላም ከወንዙ እንዲገባ አደረገ። አርበኞቹ ከተድላ ማርያም ወገን ያለውን ተዳፋት ይዘው በዝምታ ጠበቁና ጠላት ከውሃው ላይ ሲወድቅ አደጋ ጣሉበት። የመጀመሪያው ተኩስ ደጀን የነበረውን የጠላት ወታደር በመጨረስ መትረየሶቹን ዝም አሰኘ። ሁሉም ተዘረረ። በተጋጋመ ሁኔታ ከጥዋቱ 4:00 ሰዓት እስከ ቀኑ 9:00 ሰዓት በቆየው ጦርነት ብዙ አርበኞች ወደቁ። ነገር ግን ከጠላት ወገን የወደቀው ብዙ አጠፌታ ነበር። ድል የአርበኞቹ ሆነ። አንድ አልቤን መትረየስ፣ ብዙ ምንሽርና አልቤን ጠመንጃ ከእነጥይቱ፣ ከብዙ አጋሰስ ጋር ተማረከ።

የአርበኞቹ እንቅስቃሴ የጣልያንን መንግሥት አስገነገነው። ባዶሊዮ እንዲሻርና በምትኩ የአስተዳደር ችሎታ ያለው አንድ መሥፍን እንዲሾም ሞሶሎኒ ለንጉሡ፣ ለሣልሣዊ ኢማኑኤል ሀሳብ አቀረበ። ከሁኔታው አስፈሪነት የተነሳ የጣልያንን ዘውድ የሚያረክስ እንዳይሆንበት ቢሰጋም፤ ንጉሡ ከጳጉሜ 4 ቀን 1929 ዓ.ም ጀምሮ ሲያውጠነጥን የቆየውን ሀሳብ ስለተቀበለው፣ ዱክ አሚዲዮ ደአዎስታ ተሹሞ ታህሣሥ 17 ቀን 1930 ዓ.ም አዲስ አበባ ገባ። ከሞሶሎኒ የተሰጠው መመሪያ፡-

1ኛ.ጣልያኖች ከቅኝ ግዛት ህዝቦች መቀላቀላቸው ውርደት ስለሆነ፣ ለጣልያን ንፁህ ዘር ጥበቃ እንዲያደርግ፤

2ኛ.ስለጦርነቱ ሮም የሚደርሰው ሪፖርት የተጋነነ ስለሚመስል እርግጠኛውን እንዲያስታውቅ፤

3ኛ.የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት በገንዘብ ረገድ ራሱን እንዲችል እንጂ ከጣልያን ሀገር ገንዘብ እንዳይጠይቅ፤

4ኛ.በሃይማኖቶች ምክንያት የሚታየውን ችግር እንዲያቃልል፤

5ኛ. አገረ ገዥዎች ሙሉ ሥልጣን እንዲኖራቸው እንዲያደርግ ነበር።

የባዶሊዮ ተሸሮ የዱክ ደ አዎስታ መሾም ግን፣ በአርበኞች ስሜት ላይ እንዳች ልዩነት አልፈጠረም። ታህሣሥ 23 ቀን የማጠቃለያ ጦርነት ተደርጐ አንድ ኢጣልያዊ መኰንንና ብዙ ወታደር ተገደለ። መከኒሣ፣ በዳንሳ ደግሞ ሌላ ጦርነት ተደርጐ፣ የአርበኞች ቡድን በጠላት ላይ ጉዳት አደረሰ። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን ሱንበ፣ አራግቻ ከተባለው ቦታ በመኪና በሚተላለፉ ጣልያኖች ላይ አደጋ ጥሎ ዘጠኝ ካሚዮን ሰባበረ። ብዙ ጣልያኖች ገደለ።

ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ (ገፅ 183 ይመልከቱ) የአንዱን ጣልያን ጭንቅላት ቆርጠው ዘቅዝቀው በማንጠልጠል ፎቶግራፍ ተነሱበት።[11] ነገር ግን ዘዴው ሳይታወቅ ስለቀረ በካሚዮኖቹ ላይ በሸራ ተሸፍኖ ተጭኖ የነበረው መሣሪያና ስንቅ ሳይዘረፍ ቀረ። ምሥጢሩ በታወቀ ጊዜ በአርበኞች ዘንድ ታላቅ ቁጭት ሆነ። የፊታውራሪ መኰንን ወልደጊዮርጊስን ደም እንደተበቀሉላቸው እንዲረዳው ፎቶግራፉን ለደብረ ብርሃኑ ገዥ ላኩለት። ጣልያንም በዚያ አካባቢ የአርበኛ ጭንቅላት ዳግመኛ መቁረጡን ተወ።

የካቲት 1 ቀን 1930 ዓ.ም ተድላ ማርያም፣ ስድአሳ አገር አርበኞች ምክር አደረጉ። ምክሩም ወደ ጨኖ ወርዶ በዚያ የነበረውን ጠላትና ግብረአበሮቹን ማሳፈር ነበር። በሃሳቡ ስምምነት ስለተደረገ አርበኞቹ በገና መምቻ በኩል አድርገው በጠቋሚ ሺህ ዓሊዎ ከተባለው የባንዳች መሪ ቤት ደርሰው ከበቡ። ያለብዙም ችግር ከቤቱ ገቡ። በተጠቆሙት መሠረት፣ በቤቱ ውስጥ ሃያ ዘጠኝ መውዜር፣ አንድ ምንሽር፣ አንድ ባለካርታ ለበን ጠመንጃና አንድ ተገንጣይ ቤል ሽጉጥ ከእነ ጥይቶቻቸው፤ እንዲሁም ብዙ ሣጥን ብርና ልብስ ተገኘ። የታረዘ አርበኛ የወገቡን ዝናር በጥይት ገጠገጠ። ኪሱንም ሞላ፣ አገሩንም አሣመነ፣ ጠላትን አሣፈረ።

በዚህ ጊዜ ንጉሥ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ከሙገሬ ዛላ ወደ ሰቆቃው ሄደው ነበርና፤ ራስ አበበና ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ከእነ ሠራዊታቸው ወደዚያው ሄዱ። ሁኔታውን በንቃት ይከታተል ስለነበረ፣ ጣልያን ቶሎ ብሎ ከአዳማና ከሞጆ ጦር አንቀሳቀሰ። ሀሳቡ ወደ ቡልጋ ተሻግሮ አርበኞችን ማጥቃት ነበር። አርበኞቹም ተዘጋጅተው ጠበቁት። ወንዙን አናሻግርም ብሎ



ከመተናነቅ ይልቅ፣ ከሰምን ከተሻገረ በኋላ ማጥቃት የተሻለ ሆኖ አገኙት። እንዲሁም አደረጉ። በፊታውራሪ ሽበሽ ዓለማየሁና በፊታውራሪ አማረ የሚመራው አርበኛ የካቲት 11 ቀን 1930 ዓ.ም ገጠመው። ውጊያው ለሦስት ቀን ቀጠለ። በመጨረሻም ከቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ሠራዊት አንድ ክፍል ለእርዳታ ስለደረሰ ድል የአርበኞች ሆነ። አንድ የጣልያን ባንዲራና ልዩ ልዩ መሣሪያ ተማረከ። ሰንደቅ ዓላማው በአደባባይ ተቃጠለ።

በፊታውራሪ አጐናፍር ባዩ የሚመሩ አርበኞች መጋቢት 6 ቀን 1930 ዓ.ም የጨፌ ደንሳን ምሽግ አጠቁ። የምሽጉ ኃላፊ የነበረውን አንድ የመቶ አለቃ ጣልያን ገድለው ራሱን በመቁረጥ ለሕዝብ መሳለቂያ አምቡር ገበያ ከኮሶ ግንድ ላይ ሰቀሉት። ሦስት መውዜር ጠመንጃ ገፈው ወደ ሠፈራቸው ተመለሱ።

አርበኛው በየፊናው ጠላትን በማጥቃት ሙያውን ማሳየት አመጣ። አንዳንዴ በተናጠል፣ ልላ ጊዜ ብቻ ለብቻ፣ ወይም ከሚያምናቸው ጓደኞቹ ጋር እየሆነ ጠላትን ማጥቃት ያዘ። አንዳንዱ ከምሽግ ተሾልኮ እየገባ ሲያጠቃ፣ ሌላው ከድቶ የመጣ እየመሰለ ሙያውን ማሳየት አመጣ። ሌሎች ሥልቶች እያቀላቀለም ቀጠለ፦ በመንገድ ላይ እያደፈጠ እንዲሁም በጉዞ ላይ እየተቀላቀለ ቦታና ጊዜ በመምረጥ እያጠቃ፣ እየገደለ፣ መሣሪያ እየገፈፈ ይመለስ አመጣ። መጥቶም በአለቃው ፊት ግዳይ እየጣለ ይፎክራል። አለቃውም በክብር እየተቀበለ፣ ለንጉሡ እያቀረበ የማዕረግ ስም ያሰጠዋል። ሥልቱም ከሰው ሰው፣ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ እየተራቀቀ ሄደ። ለእነዚህ ሥራዎች ማስረጃ ያስፈልጋችዋል።

ሙገሬ ዛላ አለከሴን መንገሻ ወልደፃድቅ የተባለ ወጣት ነበር። ጠላት በገባ ጊዜ ገና የአሥራ አምስት ዓመት ማርተጋሻ ነበር። በአርበኝነት ጊዜ ሰው ብሎ መሣሪያ የሚሰጠው ዘመድ ስለአጣ፣ እንደሚከተለው አደረገ። አዲስ አበባ ገብቶ አክስቱን ተለማመጠ። እሳቸውም አንድ እሩቅ የሚያሳይ መነጥር፣ የጠላት ወታደሮች የሚያደርጉአቸውን ሦስት የአንገት ፋሻዎች፣ አንድ የጨርቅ የቅልጥም ገንባሌ፣ ሁለት የእጅ ቦምቦች ከጠላት ወታደሮች ሰርቀው ሰጡት። እነዚያን ይዞ አገሩ በመግባት በእነሱ እየተጠቀመ በጉዞ ከደከመ የጠላት ወታደር ጋር ወደ ማታ እየተቀላቀለ፣ በድምሩ አሥራ ስምንት ምንሽር ከብዙ እጅ ቦምብና ጥይት ጋር በመቀማት በፊታውራሪ ወልደፃድቅ የሚመራው አንድ ቡድን አባል ሆነ። ባላምባራስ ተባለ። ይህ ሰው በጠላት ላይ የመጀመሪያውን አደጋ የጣለው ገበያ ነበር።

ታደሰ አበበ የተባለ ሌላ ወጣት በበኩሉ አንድ አሮጌ ውጂግራ ይዞ ጊና አገር ለጠላት የከዳ መስሎ ገባ። ጣልያንም አምኖ አዲስ ምንሽር ጠመንጃ ሰጠው። ስድስት መሣሪያ ገፎ በማምለጥ ከፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ ጋር ተቀላቀለ።

አባቱ ኦጋዴን ዘምተው የሞቱበት አቶ ደመና ከተማ የተባለ ሌላ ወጣት፣ አርሲ ከነበሩ አርበኞች ጋር ተንቀሳቅሶ በዚያ የነበረው አርበኛ ወደ ዳር አገር ሲሄድ አብሮ መሄድ ደስ ሳይለው ቀረ። ናዝሬት መጥቶ ለጣልያን ባንድነት ገብቶ ጥቂት ረገጠ። ቋንቋም ትንሽ አጥንቶ አንድ ምንሽር ጠመንጃ ተቀበለ። መተሐራ አጠገብ የነበራቸውን ምሽግ እንዲጠብቅ ከተመደበው ጦር አባል እንዲሆን ተደረገ። ስድስት ሰዎች አስከድቶ፣ ሁለት ጣልያኖች ገድሎ በረከት በመሻገር ከአጐቱ ከፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ጋር ተቀላቅሎ አርበኝነቱን ቀጠለ።

በዚህ ዓይነት በተናጠል፣ በግለሰብ የሚካሄደው የማጥቃት ዘዴ በጠላት ላይ ቀጥሎ እያለ በቡድን፣ በቡድን እየሆኑ ግንባር፣ ለግንባር በመግጠም የመውጋቱ ሥራ ተጋጋመ። አንዱ ሥልት ለሌላው ሥልት ደጋፊ፣ ጦር ከፋች እየሆነ ሄደ። ለምሣሌ አንድ የአርበኞች ቡድን መጋቢት 8 ቀን 1930 ዓ.ም እቲሣ፣ ጥጥ አምባ በጠላት ላይ አደጋ ጥሎ ደህና ሥራ ሠራ። ሌላው ቡድን ደግሞ መጋቢት 12 ቀን ጨመሪ በነበረ ጠላት ላይ አደጋ ጣለ።

ይህ ተደጋጋሚና ተደራራቢ ጥቃት ጠላትን ቆጠቆጠው፤ አዲስ ጦር አዘጋጅቶ መጣ። እንደ ሥርዓቱ ብዙ ባንዳ አስቀድሞ፣ ነጩ ከኋላ ሆኖ ነበር። አርበኞች ትንሽ ተኳኩሰው ስለሸሹለት፣ የአሸነፈ መሰለው። ሊጨርሳቸው ማባረር ያዘ። አርበኞች የሸሹለት ለእነሱ ከሚመች ወጥመድ ቦታ ለማስገባት ነበር። ዘዴአቸው ያዛቸው። ከቀለበት ውስጥ አስገብተው በጥይት ቆሉት። ፈረሰኛውን ከፈረሱ ላይ አወረዱት፤ እግረኛውን ማሳ ለማሳ በጥይት እያባረሩ ለቀሙት። ፎክሮ የመጣው ጀነራል፣ እንደ ዋለ ቀረ። ከአርበኞች ወገን የሞተው እጅግ ጥቂት ነበር። አንጀት የሚያርስ ሥራ ሠሩ። በተገኘው ድል የተደሰቱ ሦስት የኮርማሽ ባላገሮች ሦስት ሺህ ጥይት አምጥተው በራሳቸው ፈቃድ ለአርበኞች በነፃ ሰጡ። ሽልማትና የግራዝማችነት ስም አገኙ።

ንጉሥ መልአከ ፀሐይ የትንሣኤን በዓል ሚያዝያ 12 ቀን ክትም ወይራ፣ ጀሎ አገረ ማርያም ጨፋ አከበሩ። ግብር ሲበላ ሰነበተ። የዳግም ትንሳኤ ሌሊት ከጀሎ አገረ ማርያም ሙሉ ሥርዓተ ፀሎት ተደርሶ ንጉሠ ነገሥት ተባሉ። በእጨጌው ገበሬ ሠናይነት ቆረቡ። ከዚያ መልስ ሠፍረውበት ወደ ነበረው ወደ ባሻ ደምሴ ተክሌ ቤት ሄዱ። ከዚያም ሰነበቱ።

አርበኛው እንዲሰበሰብ ተጠርቶ ነበርና፣ ከቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ሠራዊት በስተቀር ሌላው ተሰበሰበ። ከሚያዝያ 20 ቀን 1930 ዓ.ም ጀምሮ ምክር ተያዘ። ምክሩ ስለጦር አመራርና ስለአስተዳደር ሳይሆን አልቀረም። ስብሰባው ጨፌ በባሻ ደምሴ ተክሌ ቤት ነበር። ዋናው ስብሰባ በአዳራሹ፣ የውስጥ ስብሰባዎች ደግሞ በእልፍኙ ውስጥ እንደ ነበረ እኛ ማቲዎቹ ከቅጥር ግቢው ውስጥ ሆነን አይተናል። ነገር ግን ንግግሩ



በምስጢር በመሆኑ እንደሌላው ጊዜ ዝርዝሩን የማወቅና ክርክሩን የመስማት ዕድል አልነበረንም።

ሚያዝያ 20 ቀን ሰኞ ለንጉሡ እጅ ከመንሳት በስተቀር ሌላ ጉዳይ የተካሄደ አልመሰለም። ዋናው ንግግር ሚያዝያ 21 ቀን ማክሰኞ ተጀመረ። በምክሩ ላይ የነበሩ፤

ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ፣
ደጃዝማች ኃይሌ ወልደመድህን ሞግዚት፣
ፊታውራሪ ዘውዴ አባኮራን፣
ባላምባራስ አበበ አረጋይ፣
ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴ፣

የፊታውራሪነት ማዕረግ ያላቸው የጦር መሪዎችም ነበሩ። የምክሩ ሁኔታ የተገለፀው ሚያዝያ 28 ቀን 1930 ዓ.ም በተሰጠው ሹመት ብቻ ነው። ሹመቱም ከዚህ እንደሚከተለው ነበር።

1ኛ.ባላምባራስ አበበ አረጋይ ራስ ተብለው ጠቅላይ የጦር አዛዥ፤
2ኛ.ፊታውራሪ ዘውዴ አባኮራን ደጃዝማች ተብለው የጎላ አገር ጦር መሪ፤
3ኛ.ቀኛዝማች ከበረ ኃይለሥላሴ ከንቲባ /የቤተ መንግሥት ኃላፊ/፤
4ኛ.ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የፊታውራሪ ዝቅ አርጌንና የፊታውራሪ ሞገቢን ጨምረው የቡልጋ ጦር አስተባባሪ ሆነው ነጋሪት እየተጎሰመ በአዋጅ ተሾሙ።

ራስ አበበ አረጋይ ባለወርቅ ቀይ ካባ፣ ደጃዝማች ዘዉዴ የወርቅ ዝምዝም ያለበት ጥቁር ካባ፣ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ከደረቱ ላይ የወርቅ ፊርጥ ያለበት ሰማያዊ ካባ ለብሰው ከግቢው ወጡ። የከንቲባ ከበረ አለባበስ በውል አይታወሰኝም። ወታደሩ በረጅሙ ተሰልፎ ነበርና በዚያ መካከል አልፈው እዚያው ጨፋ ወደ ሠፈሩባቸው ቤቶች በአጀብ ገቡ። ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ራስ አበበን ከሠፈሩበት ቤት አድርሰው ሰበርን በረት አቶ አሻግሬ ቤት ነበሩና ወደዚያው ሄዱ። ፊታውራሪ ዝቅ አርጌ በማግስቱ ጥዋት በረት ድረስ መጥተው በድልድሉ ማስማማታቸውን በመግለጽ፤ ምሣ በልተው ከፊታውራሪ ወልደፃድቅ ተሰናብተው ወደቡልጋ ዞሩ። የፊታውራሪ ሞገሴን መምጣት አላስታውስም። የጨፋ ሹመት የተሰጠው ሚያዝያ 21 ቀን ጀምሮ በተደረገው ምክር ብቻ አይመስልም። ለብዙ ጊዜ ሳይታይበት አልቀረም። የሹመቱ መሰጠት የአርበኞችን አቅዋም ያጠናከረም ያዳከመበትም ሁኔታ አለ። አጠናካሪ ገፅታው ግልፅ ነው። ብዙም አያከራክርም። አርበኛው ልቡ ተጽናና፣ ገበሬውም አመነ፤ ተባበረ። ከተሿሚዎቹም በተለይ ራስ አበበ፣ ደጃዝማች ዘውዴና ከንቲባ አበራ ደስ አላቸው።

ነገር ግን ሹመቱ የፈጠረው የደስታ ስሜት ብቻ አልነበረም። ቅሬታም አንጃ። ምንም የቡልጋን አርበኛ እንዲምሩና የፊታውራሪ ዝቅ አርጌንና

የፊታውራሪ ሞገሴን ሠራዊት እንዲያስተባብሩ ቢፈቅድላቸው፣ ደጃዝማች አለመባላቸው ፊታውራሪ ወልደፃድቅን ቅር አሰኛቸው። ቢሆንም ቅሬታቸውን ትተው ሥራቸውን ቀጠሉ። ለራስ አበበም ትብብራቸውን አላጉደሉባቸውም። ነገር ግን የቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ አቋም የተለየ ነበር። ከስብሰባው ላይ አልተገኙም። የእንኮበርን፣ የዳውሌንና የበረከትን ጦር ይዘው የደጃዝማችነት ማዕረግ አሉበት ደብረ ከብድ ድረስ ቢላክላቸው እንኳን አልተቀበሉም። ለሰዎቻቸውም የማዕረግ ስም እንዲሰጥ ዝርዝር ማቅረብ አልፈቀዱም። እኛ የተነሳነው ለሀገራችን ነፃነት ለመከላከል እንጂ እርስበርሳችን ለመሿሿም አይደለም አሉ ተባለ። ይህ አባባል እውነት ነበረው። ለሀገሩ በነፃ የሚያገለግለውን አርበኛ የአገሌ ታዛዥ ጭፍራ ሁን ማለት አግባብ አልነበረም። ይህ ስሜት የአርበኛውን ልብ ለመከፋፈል ለተነሱ ኃይሎች በር ሳይከፍት አልቀረም።

የሹመቱ አሰጣጥ ደግሞ የራሱ የሆነ ችግር ነበረበት። የአርበኝነቱ ሥራ የሚንቀሳቀሰው ሀገር ወዳድ በሆኑ ተራ ሰዎች ነበር። ብዙዎቹ ጀግኖች ከሥራቸው በስተቀር የሚመኩበት የዘር ሀረግ አልነበራቸውም። የሚከፈላቸው ደመወዝ፣ የሚሰጣቸው ድጋፍ አልነበረም። ጠመንጃዎቹ እንኳን ከጣልያን የማረኩአቸው እንጂ ከመንግሥት የተሰጡአቸው አልነበሩም። ሹመቱ ግን በዘር ሆነ። ምንም በተለይ በራስ አበበ ጀግንነትና ብልህነት ቅር የተሰኘ ባይኖር፣ ሠራዊቱ በሙሉ ልብ አልተደሰተም።



የአርበኞች አውራ ራስ አበበ አረጋይ።

ብዙም ሳይቆይ የአስተዳደር ችግር ተፈጠረ። ለምሣሌ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የተወለዱበትና አርበኝነቱን የቀረቀሩበት፣ ቤተሰቦቻቸው የሚኖሩበት ሜጢ የተባለው ሀገር ለፊታውራሪ ደባልቄ ተሰጠ። ሁለቱን ፊታውራሪዎች ለማጋጨት ሆን ተብሎ የተጠነሰሰ ሴራ ነበር። እውነትም እነዚህ ሁለት ወንድማማቾች ሌላ ምንም የሚያገናኛቸው ነገር ሳይኖር



እርስበርሳቸው ለጦር ተሰላልፈው እስከ መዋጋት ደረሱ። ሌላውንም በዚህ ሹመት ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ወደፊት እናያለን።

ከዚህም በስተቀር በስደት ላይ የነበረውን መኳንንት ሳያሳስብና ቀዳማዊ ኃይለሥላሴንም ሳያሰጋ አልቀረም። ኢየሩሳሌም የነበሩትን እጨጌ ገብረጊዮርጊስን ጭምር። የውስጥ አርበኞች በኃይል ተንቀሳቀሱ። የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ደጋፊዎች እዚያው እጨጌ ውስጥ እየጻፉ፣ በሣሙና ላይ ተቀርፆ በተሠራ ማሕተም እያተሙ፣ ከንጉሠ ነገሥቱ ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የተላከ እያስመሰሉ ለአርበኛው የሚያስነብቡም ነበሩ። እንዲሁም ለራስ አበበ፣ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የሚደርሱ መልዕክቶች እየበረከቱ ሄዱ። ዋናው ጥያቄ "በአንድ አገር ሁለት ንጉሠ ነገሥት እንደምን ይሆናል?" የሚል ነበር። ለዚህ ከባድ ጥያቄ የጭምቱ የራስ አበበ ምላሽ "ይታሰብበታል" ሆነ።[11] ሁኔታው ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የውጭ አገር ዕርዳታ ማግኘት ጋር በቀጥታ የተያያዘ ሆነ።

ሹመቱ ያስከተለው ችግር ይህ ብቻ አልነበረም። የጣልያንን መንግሥት አስደነገጠው። ለመጀመሪያ ጊዜ የእርቅ ሐሳብ በማቅረብ የሰላም እጁን ዘረጋ። ሙሴ ቀስተኛን በአማላጅነት ላከ። ሙሴ ቀስተኛ የሥራ ሚኒስቴርና ባልደረባ በመሆን ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ጊዜ የቆየና፣ በየመኳንንቱ ቤት እየዞረ ሲበላና ወግ ሲያጠና አርባ ዓመት የኖረ የስዊስ ተወላጅ ነበር። እሱም ከአዲስ አበባ ተነስቶ በሸንኮራ፣ በሰቃ ዋጪ፣ በተድላ ማርያም ዞሮ ሹመቱ ከተሰጠበት አካባቢ በአንድ ሣምንት ጊዜ ደረሰ። እሱ ተድላ ማርያም ሲደርስ፣ ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ወደ ቀይ አፈር ሄደው ነበር። እሱም እግረ መንገዱን ሀገሩን እያጠናና እየሰለለ ተጉዞ ንጉሠ ነገሥቱ ከአሉበት ደረሰ።

ገሊላ ደርሶ፣ በወቅቱ ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነግሠው ከነበሩት መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተገናኘ። መልዕክቱንም አስረዳ። እስከ ሦስት ቀን ድረስ በባላምባራስ ሞላልኝ ግዛው እጅ ሰንብቶ፣ የተቆረጠ መልስ ሳያገኝ ሚያዝያ 30 ቀን 1930 ዓ.ም ወደ ደብረ ብርሃን ሄደ። ለደብረ ብርሃኑ ገዥ ከሰጠው ምክር ዋናው ምሽግን ማብዛትና ማጠናከር እንደሆነ ወዲያው ከአርበኞች ዘንድ ተሰማ።

ጣልያን የአቀረበው የእርቅ ሀሳብ በአርበኞች ዘንድ ሌላ የሀሳብ ልዩነት ፈጠረ። ብዙው ሰው ድካም ተሰምቶት ነበርና፣ በተገኘው ዕድል በመጠቀም መታረቅና የወደፊቱን ሁኔታ ማጥናት ይሻላል የሚል አስተሳሰብ ያዘ። ሌላው ወገን ደግሞ የዕርቁ ሀሳብ አዘናጊና ትጥቅ አስፈች ሊሆን እንደሚችል ሰጋ። በዕርጋታ እንዲታሰብበት ስለአስፈለገ በቶሎ ከውሣኔ ላይ ሳይደረስ ቀረ። ለሙሴ ቀስተኛም የተቆረጠ ምላሽ ሳይሰጠው የቀረው በዚህ ምክንያት ነበር።



የአርበኞች አውራ ራስ አበበ አረጋይ።

ጠላት ሃሳቡ እንደአልሰመረለት ሲረዳ ከጐንደር፣ ከጐጃም፣ ከወሎ፣ ከትግሬ፣ ከሐረር ጦር ሰብስቦ አዲስ አበባ፣ ደብረ ብርሃንን እና ናዝሬትን (አዳማን) ዋና፣ ዋና የጦር ሠፈር በማድረግ አዘመተ። ከደብረ ብርሃን የተንቀሳቀሰው የጠላት ጦር በጫጫ፣ በደጀን ጥጌ መጣ። አርበኛውም ግንቦት 12 ቀን 1930 ዓ.ም አሰበር አጠገብ ገጠመው። ጦርነቱ ከጥዋቱ አምስት ሰዓት ጀምሮ እስከ ምሽቱ አንድ ሰዓት ድረስ ቆየ። አርበኛው ብዙ የጠላት ወታደር ፈጀ። ሁለት መትረየስና ሌላም መሣሪያ ማረከ። ከእሱም ወገን ፊታውራሪ ተወንድ በላይነህን እና ሌሎችም ብዙ ጀግኖች ሞቱ፤ ሌሎች በርካቶችም ቆሰሉ።

አርበኞቹ ጠላት እስከ አለበት ድረስ ሄደው ግንቦት 13 ቀን 1930 ዓ.ም ውጊያውን ቀጠሉ። ድል አድርገው በመመለስ ወደ ኋላ ሲገፉት፣ ይዞት የነበረውን ሰውን የመጨረስ፣ ቤትና ቤተክርስቲያን የማቃጠል ሥራውን ለጊዜው አስጥለውት ወደ ገሊላ ወረዱ። እሱም በማግስቱ ግንቦት 14 ቀን አፋፍ ላይ ጠምዶ የቀይ አፈር ላይ ሆኖ ቆላውን በመድፍ ሲደበድብ ዋለ። ድብደባው ስለአሰለቻቸው አርበኞቹ ወደ ቆላ ወረዱ። ከዚያም በአጡራ ጨባቃ አድርገው አይራራ ወንዝ ላይ ሠፍረው እስከ ግንቦት 28 ቀን ድረስ ዕረፍት አደረጉ። ከብቱም ሰውም ውሃ ጠገበ።

ራስ አበበ ከአይራራ ተነስተው በዳውሌ በኩል አድርገው ወደ ቡልጋ ለመሄድ ታሞ ከተባለው ቦታ ገቡ። ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ ደግሞ ከገሊላ ተነስተው ወደ ቡልጋ ለመዞር ጉዞ ቀጠሉ። እሳቸውም ገሊላ በነበሩበት ጊዜ ለሠራዊታቸው ግብር ሲያበሉ መሰንበታቸውን የሚያስታውሱ አሉ። ነገር ግን ከጠራ በሮች በኩል የሚጓዝ የጠላት ጦር ሰቃ ከተባለው ቦታ አጋጠማቸውና ግንቦት 25 ቀን በተካሄደው ውጊያ እግራቸውን በጨረፍታ ተመቱ።

ግንቦት 26 ቀን 1930 ዓ.ም ጊና አገር አጠገብ፣ ወልዶ ለሞት ከተባለው ቦታ ታላቅ ጦርነት ተደረገ። ይህ ወልዶ ለሞት የተባለው ቦታ በደጋውና በቆላው አገር መካከል እንደግድግዳ የቆመ ገደል ነው። አርበኞች የገደሉን ጫፍ ይዘው በአሣግርት ሜዳ ላይ የሚርመሰመሰውን የጠላት ወታደር በጥይት ጨፈጨፉት። ፊታውራሪ ሸበሽ ዓለማየሁን ጨምሮ ብዙ ጀግኖች እዛ ወደቁ። አርበኞች የሞቱትን ቀብረው፣ በድንጋይ ጥራ በኩል አድርገው የቁሲሎን ተራራ በመጠጋት መርቆሬ አገር ሠፈሩ።

ጠላት አርበኞች በቆላው የሚያደርጉትን ጉዞ ለማደናቀፍ ለውጋ በደጋው በሙጥማየስ ዞሮ፣ በቁንጥሴ ሰብሮ ግንቦት 28 ቀን 1930 ዓ.ም ሙገሬ ዛላ ገባ። በአርበኞች በኩል ላለማስገባት የተደረገው ሙከራ ውጤት ሳያስገኝ ቀረ። በማግስቱ ግንቦት 29 ቀን 1930 ቤትና ቤተክርስቲያን ሲያቃጥል፣ ሰው ሲፈጅ ዋለ። አቶ አበሬ የተባለ የምስለኔ አገር ሰው አንድ ካርታ የቤልጅግ ጥይት በኪሱ ውስጥ ስለተገኘበት፣ እሱን ጠላት ከግንድ ጋር



የፊጥኝ አስሮ፣ በላዩ እንጨት አስቆልሎ፣ በእሳት አቃጠለው። በዋዜማው አንድ መምሬ አባት የተባሉ ቄስ ከአማኑኤል ቤተክርስቲያን ጋር አቃጥሎ ነበርና፦ «አርከ /ጣልያን/ አብሬ መምሬ አይልም፣ አያውቅም።» ተባለ።

በዚህ ወር የተካሄደው የጣልያን ዘመቻ ባለብዙ ፈርጅ፣ ከባድ እንዲሁም ጭካኔ የተሞላበት ነበር። የበረከት ሽማግሌዎች እንዲያነጋግሩት ጥሪ አደረገ። እነሱም አስቀድሞ በሙሴ ቀስተኛ የተደረገውን ሙከራ ሰምተው ነበርና ለዕርቅ ጉዳይ ይሆናል በማለት ቀረቡ። እሱ ግን ኡመር አሊ ከሚባል ሰው የቀረበለትን ሰብቅ በመስማት ብቻ እርስበርሳቸው በገመድ አስተሳስሮ ሦስት ቀን ሙሉ በረሃብና በውሃ ጥም ከአሰቃያቸው በኋላ፣ ግንቦት 28 ቀን 1930 ዓ.ም በመትረየስ ጨረሳቸው። ሬሣቸውም እንዳይታይ ጋዝ አርከፍክፎ በእሳት አቃጠላቸው። ጠላት ከተባረረ በኋላ ከእነኚሁ መካከል ስማቸው ታውቆ ሊመዘገብ የቻለው የሦስት መቶ ሰማንያ ሦስቱ ብቻ ነው።[12]

እነዚህ ሰዎች ያለቁት በታላቅ የክህደት ሥራ ስለሆነ ሊጤን ይገባል። ጣልያን ሽማግሌዎችን የጠራው እርግጥም ሀገሩን እንዲያረጋጉለት ነበር። ነገር ግን ከላይ ስሙ የተጠቀሰው ኡመር አሊ የተባለው ከሐዲ፣ ቀደም ሲል ፊታውራሪ ከበደ ወልደጊዮርጊስ፣ የወንድማቸውን የፊታውራሪ መኮንን ወልደጊዮርጊስን ደም ለመበቀል ሲሉ፣ ገድሎ ጭንቅላታቸውን አስቆርጦ ደብረ ብርሃን በመውጣት የተጫወተበትን ጣልያን ገድለው፣ ጭንቅላቱን ቆርጠው፣ ሦስት ቀን ሙሉ ጊጤ ሲጫወቱበት ሰንብተው፣ ስድስቶ ከተባለው ቦታ ከትንጭብ ግንድ ላይ፣ በዓይኑ ጉድጓድ ተክለውት ሄደው ነበርና፤ እሱን አንስቶ ከድብኝቱ ውስጥ በመደበቅ አቆይቶ አዲስ ለመጣው ጣልያን በምሥጢር አስረከበ። አስረክቦም ይህንን ሥራ የሠሩት የእነዚህ አሁን ለእስታራቂነት የቀረቡት ሽማግሌዎች ልጆች መሆናቸውን አሳበቀ። ጣልያኑም ራሱን የተቆረጠው ወንድሙ ነበርና ነገሩን ሳያጣራ፣ ሽማግሌዎችን ከላይ በተነገረው ዓይነት ረበረባቸው። ሆኖም ሬሳውን ማቃጠል ሲጀምር ዘጠኝ ሰዎች ከጥይቱ ድብደባ ድነው ኖሮ ሮጠው አመለጡ። ምሽቱም አገዛቸው።[13] የጣልያኑም መኰንን የወሰደው እርምጃ ጭካኔ የተሞላበት ቢሆንም በእሱ ፍርድ የለም። ክህደቱን ባካሄደው በኡመር አሊ እንጂ። የሚያስቆጨው ነገር ደግሞ ጠላት ከተባረረ በኋላ ከሃዲው ኡመር አሊ ማንም ሳይነካው እንደተጀነነ መኖሩ ነው።

የጠላት አመጣጥ ከባድ ነበርና፣ ደግሞም ፋታ የሚገኝበት የክረምቱ ወራት ለመግባት ገና አንድ ወር ቀርቶት ነበርና፣ አርበኞች ጋደራ ላይ ስብሰባ አድርገው ተማከሩ። ሙሴ ቀስተኛ ለጠላት የሰጠው ሪፖርትና የጠላት አመጣጥ ተገመገመ። ከወሎ፣ ከትግሬ፣ ከጐንደር፣ ከጐጃም ሰባ ሁለት ሺህ ወታደር አስመጥቶ ደብረ ብርሃን ላይ ማስፈሩ ታወቀ። ከዚህም በስተቀር ከሐረር ሌላ ጦር አምጥቶ ናዝሬት ላይ አስፍሮ ነበር። ይህ ሁሉ ከታየ በኋላ ጦሩ በየበሩ ተደለደለ። ራስ አበበና ደጃዝማች ዘውዴ በቁስ አገር፣ ቀኛዝማች

ኃይለማርያም ማሞ በወልዴ አገር በኩል ተመደቡ። የጠላት ጦር በብዛት መጣ።

ቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ የነበሩበትን ከጠቋሚ በመረዳት ሌላውን ትቶ ወደ እሳቸው አመራ። ቀኛዝማች ኃይለማርያምም የጠላትን አመጣጥ ከገበሬ ሰምተው ተዘጋጁ።[14] ግንቦት 29 ቀን 1930 ዓ.ም ሾላ ገበያ ደብር ከተባለው ቦታ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ ከቀትር እስከ አሥራ አንድ ሰዓት ቆየ። አርበኞቹ ጠመንጃና መትረየሶቻቸው ሲግሉ በውሃ እያቀዘቀዙ የጠላትን ወታደር ረፈረፉት። ጠላትም በመትረየስና በጠመንጃ በመድፍ አጥብቆ ተዋጋ። ግንቦት 12 ቀን ተማርኮ ከአርበኞች ጋር ቆይቶ የነበረ የጠላት ወታደር እንደገና ተመልሶ ከወገኖቹ ተቀላቀሎ ሁኔታውን አስረዳ። ጠላት ማፈግፈግ በጀመረ ጊዜ ቀኛዝማች ኃይለ ማርያም ማሞ በደረታቸው ተኝተው ይዋጉ ከነበረበት ቦታ ቀና ሲሉ ግንባራቸውን ስለተመቱ በቅጽበት ሞቱ። ሙሉ ቀን ተኝተው ሲዋጉ ከዋሉበት ቦታ ቀና ያሉት አንድ የጠላት መትረየስ ተኳሽ ሞቶ ሊማረክ ተጋልጦ ነበርና፣ እሱን ለማንሳት የአርበኞችን ዓይን ለማዳለጥ ነጭ መሐረብ እያረገበ የመጣውን ጣልያን የገደለውን አቶ ኃይለሥላሴ ዓለሙ የተባለ አርበኛ ለማመስገን ነበር። የሞቱትም 370 ጥይት ከተኮሱ በኋላ መሆኑ በታሪክ ተመዝግቦአል። ሌሎችም ብዙ አርበኞች ሞቱ፤ ቆሰሉም። የተነሱብትን ዕድል ፈንታ ተቀበሉ። ሙሉቀን በዋለው ጦርነት፣ ራስ አበበና የደጃዝማች ዘውዴ አንዳችም ዕርዳታ አለማድረጋቸው የቀኛዝማች ኃይለ ማርያምን ሰዎች አሳዘነ። ተለይተው ወደ ግንደ በረት ለመዞራቸውም ምክንያት ነበር። ለጠላት ግን አንድ እፎይታ ሆነ።

ግንቦት 30 ቀን 1930 ዓ.ም በዚሁ በሾላ ገበያ አካባቢ አልፎ አምባ ፈላ ጦርነት ተደረገ። ጦርነቱ በሁለት ገጽ የተከፈለ ነበር። የደብረ ብርሃኑ የጠላት ጦር በኮቱ አድርጐ በሾላ ገበያ፤ የከረሣሹ ደግሞ ከሰምን ተሻግሮ በመስኖ ማርያም መጣ። አርበኞቹ በሁለቱም ወገን በርትተው ተዋጉ። ቀን ሲመሽ በሰቻት በኩል አድርገው ወደ ጭቃያስ ሄዱ።

ሁለት መቶ ያህል ባንዶች፣ በሁለት አዝማቾች እየተመሩ ሰኔ 4 ቀን 1930 ዓ.ም መጡ። ሐሳባቸው አጥቅተው ለጌ ታቸው ለጣልያን ግደይ በመጣል ለመፎከር ነበር። ብዙ ባንዳ በየጊዜውና በየቦታው መጥቶ እንደ ሁኔታው ተመልሶአል። በአርበኝነት ሥራ ላይ የተለየ ውጤት ከአሳየው በስተቀር አብዛኛው የባንዳ ዘመቻ አላስፈላጊ እንደ መሆኑ በዚህ መፅሐፍም አልተነገረም። ይኼኛው የባንዳ ዘመቻ ግን ሊጠቀስ የሚያስፈልግበት ምክንያት አለ። ስለዚህ እንደሚከተለው፣ በአጭሩ እጠቅሰዋለሁ።

አርበኛው በፍጥነት ከበባቸው። ተኩስ አልከፈቱምና፣ መከበባቸውን እንዲያውቁት አደረገ እንጂ አልነካቸውም ነበር። ነገር ግን ጉዳዩ በዚሁ አላበቃም። ባንዶቹ መልእክት ወደ ጌታቸው በሬዲዮ አስተላልፈው ኖሮ አይሮፕላን መጥቶ አካባቢውን ይማትር ጀመር። አቶ መኩንን ሸፈራው



የተባለው ሰው ቀደም ብሎ ከጠላት ከድቶ ከአርበኞች ጋር ተቀላቅሎ ነበርና፣ ዘዴውን በማወቅ ነጭ ሸማ መስቀያ አንጥፎ አሳየው። አይሮፕላኑም ምልክቱን አይቶ ለባንዶች የመጣውን እርዳታ አርበኛው ሠፈር ላይ አራገፈ። አራግፎ ሲጨርስ ቀኛዝማች አበበ በዛ የተባለ ጀግና በመውዜር ጠመንጃ አይሮፕላኑን መታው። ነጂው ከነአይሮፕላኑ እንደ ምንም አዲስ አበባ ደርሶ ሌላ አይሮፕላን በማምጣት አካባቢውን በቦምብ ደበደበው። ሆኖም አጣጣሉ በብስጭትና በፍርሃት ስለነበረ ቦምቡ የትም ተበተነ። በአርበኞች ላይ አንዳች ጉዳት አላደረሰም።

ባንዶቹ ይህም አልበቃ ብሎአቸው ሌላ ቴሌግራም ስለአስተላለፉ፤ ጠላት በአይሮፕላን መልእክት በተነላቸው። መልእክቱም፣ "...ከቦታው አደገኛነት የተነሳ መጥተን ልንረዳችሁ አንችልም። ጦር ይቀርባል። በሦስት ቦታ መድፍ ይተኮሳል። በዚያን ጊዜ ክቡን ሰብራችሁ ውጡ" የሚል ነበር። መልእክቱን አርበኞቹ አግኝተውት ነበርና፣ ባንዶቹ መውጣት አልቻሉም። ለወሬ ነጋሪ ሳይተርፉ፣ የውሃ ሽታ ሆነው ቀሩ። ከዚህም በስተቀር አሥራ ስድስት ሺህ ጥይትና ብዙ ፍርኖ፣ ሻይ ቅጠል፣ ዱቄት አገኙ። ምሥጢር ያለባቸው ፅሑፎችም ተገኙ። ፈንጠዚያ ሆነ።

ከታች በሀገረ ማርያም፣ ከላይ በፋሪ በኩል የጣልያን ጦር መጣ። አርበኞቹም በሁለቱም ወገን ገጠሙት። በሁለቱም ወገን ድል እየመቱ ወደየመጣበት መለሱት። ብዙ በቅሎች፣ አረቄና ስንቅ እንደ ተጫኑ ተማረኩ።

አርበኞች ወደ በረከት ሄዱ። ጠላትም ታቹን በሣርአምባ፣ ላዩን በወና መጣ። አርበኛው በሦስት ወገን ንጉሡን ይዞ ወደ ቡልጋ ተመለሰ። ሁለተኛው ወደ መስጊድ ሄደ። ሦስተኛው እንዶዲ ሠፈረ። እንዶዲ የሠፈረው ቡድን ሰኔ 12 ቀን 1930 ዓ.ም ኮካ ከተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ተዋጋ። ጥሩ ጦርነት ነበር። ሴት ወይዘሮዎች ሳይቀሩ በጠመንጃና በመትረየስ ሲዋጉ ዋሉ። የትልቁ የውሃ መትረየስ እግር ሳይደርስ ቢቀር፣ አርበኞች መትረየሱን ከወይራ ግንድ ባላ ላይ አስደግፈው ሲሰሩበት ዋሉ። ጠላትም ወደ መጣበት ተመለሰ።

ራስ አበበን ጠላት አይሎባቸው ነበርና ሌሊቱን ምክር ተደርጐ ሠራዊቱ እሳቸውን ለመቀበል ወደ ወክፈሌ ሄደ። ይህ በመሆኑ ጠላት የሌባ መስቀያን ተራራ ሰኔ 13 ቀን ያዘ። ራስ አበበ ወደ ቡልጋ ሲጓዙ ቡርቃ ከተባለው ቦታ ከጠላት ጋር ተገናኝተው ውጊያ ተካሄደ። ሌላው ቡድን ደግሞ ገባሮች ከሌላ አምባ ተዋግቶ አሸነፈ። አንድ አልቤን መትረየስና ስንቅ ማረከ። ሀገሩ በመጎዳቱ ምክንያት ምግብ እንደልብ አይገኝም ነበርና ስንቅና ከብት መማረኩ ረዳው።

በጉንቢንሣ በኩል አንድ በጄነራል የሚመራ የጠላት ጦር መጣ። አርበኛውም በጠነከረ መንፈስ ሰኔ 15 ቀን 1930 ዓ.ም ገጥመውት ወጉት። የጠላት ጦር በሶማሌና በሊቢያ ወታደር የተሞላ ነበር። እሱንም ድል አድርገው የጄነራሉን የማዕረግ ልብሷ አስጥለው አባረሩት። የጠላት ጦር

ማሣሪያውን ከማሽላ ጉድጓድ እየጨመረ፣ ሬሣውን እያቃጠለ፣ ሸሽቶ በጮባ በኩል ወደ ምንጃር ተሻገረ።

በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራው አርበኛ ከሙገሬ በመንቀሳቀስ ሾላ ገበያ ጉርፍ ሐምሌ 19 ቀን 1930 ዓ.ም ከጠላት ጋር ጦርነት አደረገ። አንድ መድፍ ከነጥይቱ ጋር ማረከ። የዚህ መድፍ ጉዳይ ምስጢር እንደሆነ ቀረ። መድፉ መማረኩ መማረክ ነው። የተማረከውም በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ መሆኑ እርግጥ ነው።[15] ነገር ግን በዚህ ምርኮ ምክንያት የተካሄዱት ወሬዎች አስገራሚ ናቸው።

በመድፉ ምርኮ ሲፈክር አደረ። ጠባዩን የሚያውቅ ስለአልነበር አባላቱ አልተመረመረም። በማግስቱ ጥዋት ሲታይ ቁላው ወልቆ ባዶውን ተገኘ። ማታ አይተነዋል የሚሉ ብዙዎች ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ መድፍ ከመማረኩ በፊት ጣልያኑ የሚያብለጨልጭ ነገር ሲወረውር ታይቶአል የሚሉ ተነሱ። ሲወረውር ታይቶአል የተባለው ቦታ አንድም ሳይቀር ተበረበረ፣ አልተገኘም። ሲሉ ሰማሁ እንጂ አየሁ የሚል ስለጠፋ ወሬውም ራስ አባት የሌለው ሆነ። መድፉም ባዶ ስለሆነ ሳያገለግል ቀረ። ስለዚህ ተፈታቶ የሰው ሬሣ በመምሰል በሣጥን በብርሃን ዮሐንስ ተቀብሮ ቀረ። ጠላትን ለማስደንገጥ ሲባል ሌላ የመድፍ አፈሙዝ ከጥቁር እንጨት በምስጢር ተፈለፈለ። የፈለፈሉትም የሙገሬው አናጢ ግራዝማች ሸንቁጤ ወርውሬ ነበሩ። የተፈለፈለው የእንጨት አፈሙዝ ጆሉ አገሬ ማርያም ከቤተክርስቲያኑ ሥር ከግንድ ጋር ታስሮ የመድፍ ጥይት ተቆረቆረበት። ጥይቱ ካከምሱር ላይ በቤልጅግ ጥይት በባላምባራስ መስካይ ሥዩም ተመታ። የመድፉ ጥይት ተተኮሰ። ድምፁም ልክ የመድፍ ድምፅ ነበር። እስከ ጉና አገርና ሰደስት ከተማ ድረስ ተሰማ። ጥይቱም ሰለሎ፣ ዋዲያት ከተባለ ቦታ መታ። ሐቁ ይህ ሆኖ ሳለ፣ ከጠላት መባረር በኋላ ደግሞ መድፉን የማረኩት የቀኛዝማች ኃይለማርያም ማሞ ሰዎች እንደነበሩ ተደርጐ ተነገረ። ያሳዝናል።

አንዱ ጦር ሲሸነፍበት ሌላ ማቅረብ የጣልያን ሥርዓት ስለሆነ፣ ሌላ ጦር አመጣ። ዓላማው አርበኞችን ለመጨረስ፣ ካልተቻለም አታክቶ ለመበተን ነበር። ጦሩም ከሐረር፣ ከሞጆና ከደብረ ብርሃን የተንቀሳቀሰ ነበር። የደብረ ብርሃኑ በሾላ ገበያና በደብር በኩል፣ የሞጆው በዶፋ፣ የሐረርጌው በዶይታ መጣ። አርበኞቹም ቦታ ቦታቸውን ተከፋፈሉ። ከማሾ የመጣው ለፊታውራሪ አርጋው ቁንጬና ለፊታውራሪ አጉናፍር ተሰጠ። የሐረርጌው ለራስ አበበ ሆነ። በዚህ ዓይነት ሰኔ 21 ቀን 1930 ዓ.ም በሦስቱም ግንባር በአንድ ጊዜ ገጠሙት። አንዱ የጠላት ጦር ሌላውን እንዲረዳ ስለተደረገ በሦስቱም ግንባር ጠላት ድል ሆነ። ጥሩ ሥራ ተሠራ። ቀኛዝማች ገብረኪዳን ጉም የተባለ ጀግና አንዱን አዝማች በትግል ጥሎ፣ በሽጉጥ ገድሎ ተቀባበት።



ሐምሌ 19 ቀን 1930 ዓ.ም አርበኞች ከምሽጉ አጠገብ ሄደው ጣልያንን ገጠሙት። ወደምሽጉም እንዳይገባ፣ ገሚሶቹ በአቋራጭ በሩን በመያዝ እስጨንቀው ስድስት ጣልያኖች ገደሉ። ባንዳ ከቁጥር አልገባም። ልዩ ልዩ የጦር መሣሪያ ተማረከ።[16]

ከቡልጋ መልስ ሆነ። ንጉሠ ነገሥት መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ሰበርንኻ፣ አኮፎ አገር፣ አቶ ታሪኩ ቤት ሠፈሩ። ከዚያም ፍርድ ተሰጠ። የጦር ምክርም ተደረገ። የፍርዱ ጉዳይ እሱን በሚመለከተው ክፍል ይነገራል። አሁን የጦር ምክሩን ሂደትና ውጤት እናያለን። ወሣኝነት ያለው ውጤት ያስከተለ ምክር ነውና፣ በጥልቅ ሊመረመር ይገባል።

ጠላት አርበኞችን ከአጠቃባቸው ስልቶች አንዱ፣ ቁልፍ በሆኑ ቦታዎች ምሽግ በመመሸግ ጦር ማስቀመጥ ነበር። በዚህ ሥልት መሠረት ጠላት በደጋው ሸኖ፣ ኮርማች፣ ጫጫ፣ ደጃት፣ መሰቢት፣ ጊና አገር፣ ሾላ ገበያና ወጨብያ መሽጎ ነበር። በሸንኮራ በኩል ጨፌ ደንሳ፣ ባልሥ፣ በምንጃር ደግሞ አረርቲ፣ ጮባ መሸጣ ላይ ምሽግ ሠራ። ይህ አልበቃው ብሎ ከቆላው ውስጥ ገባ። ገብቶም በረከት ላይ ስድስቶ፣ ማህሙድና ጂፋር ከተባሉ ቦታዎች፣ እንደዚሁም ጉቤንሣ ላይ መሸገ።

የአኩፎ አገሩ ምክር፣ ይህንን ገምግሞ ምን ይሻላል በሚል ጥያቄ ላይ ያተኮረ ነበር። በረከት የነበሩትን ሦስት ምሽጐች ለማጥቃትና ለመደምሰስ ተወሰነ። የጦር ዝግጅት፣ የወታደር ድልድል ተደረገ። ሦስቱ ምሽጐች አንድ መደዳ ላይ ናቸው። እርስበርሳቸው መደጋገፍም ይችላሉ። ከዚህም በስተቀር ቦታው ለአይሮፕላን ድብደባ አመች ነበረ። ድልድሉ የተሠራው ይህ ሁሉ እየታወቀ ነው።

በድልድሉ ዋናው ምሽግ ስድስት ነበር። በዚህ ግንባር የተሰለፉት የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞግዚት ደጃዝማች ኃይሉ ወልደ መድህን ነበሩ። የጂፋር ምሽግ ለፊታውራሪ ወልደፃድቅ ተሰጠ። እሱም በጥንካሬ ሁለተኛው ነበር። ራስ አበበ የመሐመድን ምሽግ ያዙ።

ወታደሩ ሚጢ ገርማን በእርጋታ ተሻግሮ ቁሊሉ ከተባለው ተራራ ሥራ መርቆሬ አገር ተሰበሰበ። ጣልያን ከምሽጉ ውስጥ ሆኖ ይጠባበቅ ነበር። የአርበኞቹን የማጥቃት ዘመቻ ማወቅ አለማወቁ አልተረጋገጠም። አውቆ ቢሆን ኖሮ የአይሮፕላን ሽፋን ቀደም ብሎ ያዘጋጅ ነበር። ቢሰማም እጅግ ዘግይቶ መሆን አለበት።

ጦርነቱ ከሌሊቱ በ11 ሰዓት በአርበኞች ተከፈተ። የጠላት ጦርም ምሽጉን ለመከላከልና ከቻለም አርበኞቹን ለማባረር ከምሽጉ ወጥቶ ተዋጋ። ታላቅ ውጊያ ተካሄደ። አርበኞች ምሽጉችን ለመያዝ ተቃረቡ። በተለይም ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የጂፋርን ምሽግ ለመስበር ተቃርበው ሳለ ወደ አሥር ሰዓት ገደማ አምስት አይሮፕላኖች መጥተው በቦምብና በመትረየስ ድብደባ አካሄዱ። ጠላት እየሸሸ ከምሽጎቹ ተሸጉጠ። በሜዳው ላይ ውጊያ

አርበኞች ብዙ የጠላት ወታደር ፈጅተው ነበር። አሁንም ደግሞ አርበኛው ወደ ምሽጉ ሲጠጋ እነሱ በተራቸው ፈጁት። ምንም አንዱ በጥይት ተመትቶ ቢመለስ፤ አራቱ አይሮፕላኖች ድብደባቸውን ቀጥለው ብዙ ጉዳት አደረሱ። አርበኛው ቁስለኛውን እየያዘ ተመለሰ። አብዛኛው ሬሳ ከዚያው ከወደቀበት ቀረ። በከንቱ የፈሰሰ ደም ሆነ። ቢሆንም አምስት ጣሊያኖች ተገደሉ። ሁለት መትረየስ ተማረከ። ከፍ ሲል የተጠቀሱት ንጉሠ ነገሥትም ሠራዊታቸውን አስከትለው ወደ ዲቤና ዞማ ሄዱ።[17]

ውጤቱ ሲታይ የአኩፎ አገር ምክር ጤናማ አልነበረም። እነዚህ ሦስት ምሽጎች ጠንካሮች ነበሩ። እነሱን ለማጥቃት ከመሞከር ይልቅ መታገሡ በቀለለ ነበር። ከዚህ አንፃር ሲታይ ምክሩ ጀግና የቆመበት እንጂ፤ ሽማግሌ የተቀመጠበት አይመስልም። የጦር ድልድሉም ትክክል አልነበረም። በዋናው በስድስት ምሽግ መሰለፍ የነበረባቸው ዋናው የጦር አዛዥ ራስ አበበ እንጂ ደጃዝማች ኃይሉ አለነበሩም። ለእሳቸው በሞግዚትነታቸው ወጣቱን ንጉሥ መጠበቅ ይበቃቸው ነበር። አርበኛው ሊያገግምና ለተከታዩ ዘመን ትግል ሊዘጋጅ ይችልበት በነበረው በክረምቱ ወራት፣ ለዚህ ዓይነት ለጉስቁልና ተዳረገ። ጦርነቱንም የድንጋይ ውቅር አድርጉ ገመተው፤ እንደዛውም አለው።

ለሁሉም የሠራዊቱን ልቡና እንደገና መልሶ ለመገንባት ጥረት ተደረገ። መጠነኛ ሹመትም ተሰጠና መስከረም 16 ቀን 1931 ዓ.ም ዞማ በተባለው ቦታ ታላቅ ሰልፍ ተደረገ። ከሠራዊቱ ብዛት የተነሣ ሰልፉ ከ8 እስከ 12 ሰዓት ቆየ። በወቅቱ ንጉሠ ነገሥት መልዐከ ፀሐይ በመባል ነግሠው ለነበሩት፣ ከአዲስ አበባ ተሰፍቶ የመጣ ነው ተብሎ አዲስ የማዕረግ ልብስ ለብሰው በዓሉን አከበሩ። ሌሊቱን ግን ባልታወቀ ምክንያት ታመው አደሩ፡

ይኸ በእንዲህ እንዳለ፣ ጣልያን ከመስከረም 18 ቀን 1931 ዓ.ም ጀምሮ በዲቤ አካባቢ ታላቅ ጦርነት አካሄደ። የወጣቱን ንጉሠ ነገሥት መታመም ሰምቶ ሳይሆን አልቀረም። አርበኞች የታመሙትን ንጉሠ ነገሥት በቃሬዛ፣ በምሥጢር ከቦታ ወደ ቦታ እያዘዋወሩ በርትተው ተዋጉ። ዕድሜአቸው ይቀራረብ መልካቸውም ይመሳሰል ነበርና፣ አቶ /ደጃዝማች/ አሉላ በቀለ፣ በሊቀ መኳስነት ከንጉሡ በቅሎ ላይ ተቀምጠው ለሕዝብ ይታዩ ነበር።[18]

ወጣቱ ንጉሥ በዚህ ዓይነት ሲሰቃዩ ሰንብተው፣ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም ሌሊት ወደ ገና መምቻ ሲወስዱአቸው አረፉ። ጠላት አውጥቶ እንዳይጫወትባቸው በመስጋት፣ አርበኞች እና መኳንንቶቻቸው በቃሬዛ ወስደው በታላቅ ክብር በሥውር ቀበሩአቸው።[19] ለወጣቱ ንጉሠ ነገሥትም፣ በነገሡበት በወክፊሌ ሚካኤል፣ መስከረም 30 ቀን 1931 ዓ.ም ውሎ ተዋለላቸው፤ ፀሎተ ፍትሐትም ተደረገላቸው። «በአንድ ሀገር ሁለት ንጉሥ እንደምን ይሆናል?» የሚለው ጥያቄ መፍትሔ አገኘ።



የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞት በአርበኛው ላይ ታላቅ ድንጋጤ ሲያደርስ፣ ለጣልያን ደግሞ አንድ እፎይታ ሆነ። በወቅቱ ለንደን ለነበሩት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴና በሀገር ውስጥ በነበሩ ደጋፊዎቻቸው ዘንድ እንደዚሁ እፎይታ እንደሆነ መናገር አያስፈልግም። ምንም ያህል ሳይቆይ፣ ሞግዚታቸው ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድህንና የገንዘብ ኃላፊያቸው የነበሩት በጅሮንድ ወልደ ዮሐንስ ሞቱ። ዝርዝሩን ወደፊት እንደርስበታለን። ቀድሞ የእቲሣ ገዳም አበምኔት የነበሩት፣ እጨጌ የነበሩት መምህር በላይ መነኑ። መጨረሻ የታዩት የረር አካባቢ አንዲት ዋሻ ውስጥ ነው።

የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ወዳጅና ጉዳይ አራማጅ የነበሩት ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ በበኩላቸው ደብረ ብርሃን ሄደው ለጠላት ገቡ። የሚገርመው የልጅ ኢያሱ ወዳጅ የነበሩት የደጃዝማች መኮንን ወሰኔ ልጅ፣ ገብረክርስቶስም አብረው መሄዳቸው ነው። ሌሎች አሽከሮቻቸው ተበታተኑ፤ በጦርነቱ አለቁ። አንዳንድ የተረፉትም ስካራሞች ሆነው ቀሩ። የቤተ መንግሥት ኃላፊ የነበሩት ከንቲባ /ደጃዝማች/ ኃይለሥላሴና ፀሐፊ ትዕዛዝ የነበሩት ፊታውራሪ /ኰሎኔል/ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ ግን ተረፈው በህይወት ኖሩ። እንዲያውም በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መንግሥት ሞገስ ሳያጡ፣ ሹመት ጭምር አገኙ።

ከዚህ ላይ ስለ ንጉሠ ነገሥት መልአከ ፀሐይ ጥቂት መናገር ይገባል። አልነገሡም የሚሉ አሉ። ይህ አባባል እዚህ አዲስ አበባ ከተገባ በኋላ የተሰማ ነው። እውነት አይደለም፤ ነግሠዋል። በቅድሚያ በረከት፣ ወክፊሌ ሚካኤል ነሐሴ 21 ቀን 1924 ዓ.ም በካህናቱ እጅ ቅብአ መንግሥት ተደርጐላቸው፣ መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተብለው በንጉሥነት ደረጃ ነግሠዋል። ንጉሥ የተባሉትም ንጉሠ ነገሥትነቱን ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ለመጠበቅ ታስቦ ሳይሆን አልቀረም። ደግሞም ሚያዝያ 1930 ዓ.ም ክስም ወይራ፣ ጀሎ አገረ ማርያም በእጨጌ ገብረጊዮርጊስ እጅ ተቀብተው ንጉሠ ነገሥት ተብለው ነግሠዋል። ይህም አርበኛው በአመራራቸው ስለአመነበት መሆኑን መገመት ይቻላል። መንገሣቸውን መላው አርበኛ በዓይኑ ያየው፣ በጆሮው በወቅቱ የሰማው ነገር ነው። ልጅ መልአከ ፀሐይ እየተባለ የተፃፈው ከፍርሐት የተነሣ ነው። ስለዚህ አልነገሡም የሚለው የአዲስ አበባ ከንቱ ወሬ መሆኑን ያሳያል።

ሌሎች ደግሞ መንገሳቸውን ያምኑና የልጅ እያሱ ልጅ አልነበሩም ብለው ይጠራጠራሉ። ይህም እውነት አይደለም። ልጅ እያሱ በአንድ ጋብቻ የፀኑ ስለአልነበሩ፣ ይህ ሃሜት በልጆቻቸው ሁሉ ያለ ነው። ነገር ግን መልአከ ፀሐይን በተመለከተ የተወራው ትክክል አይደለም። የተወራውም ጠላት ከተባረረ በኋላ እዚህ አዲስ አበባ ነው። ልጅ መሆናቸውን በወቅቱ ሠራዊቱም ሕዝቡም አምኖበታል፤ ስላመነበትም በወቅቱ አንግሷቸው ነበር።

መልአከ ፀሐይ ኢያሱ ተብሎ የነገሠው ወጣት እንግዳ እሸት ኃይሌ የተባለው ልጅ ነው። በዚህ ጥያቄ አልተነሣም። የተገኘውም አብዬ ገዳም

መድኃኒአለም፣ አበ ምኔት አባ ደርበው እጅ ነው። ጥያቄው እንግዳ እሸት ማነው? የሚል ነው። ከሀገር ሽማግሌዎች የተገኘው ቃል እንዲህ የሚል ነው። ልጅ እያሱ ከሥልጣን በወረዱ ጊዜ፤ በ1909 ዓ.ም ሐረር ከተማ ነበሩ። ወሬውን እንደሰሙ ከአዳል ባላባቶች የአንዱን ሴት ልጅ ይዘው ወደ አባታቸው ወደ ንጉሥ ሚካኤል ሄዱ። ተይዘው ሰላሌ፣ ፍቼ በቆዩበት ጊዜ ይህች ልጅ ከእሳቸው ፀነሰች። እርግዝናዋ እንደታወቀ ወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ዳርጌ ወሰድዋት። በታመነ ሰው ወደ ቡልጋ ከትም ወይራ፤ ጨፋ ርስታቸው ላኩአት። የተላከውም ሰው ከፍቼ እስከ ቅየ ከቢቶ ወስዷት ከደጃዝማች መኰንን ወሰኔ ቤት ለጥቂት ቀን እረፍት ከአደረገች በኋላ ሜጢ ወረዳ፣ ከወይዘሮ ተመናኙ ተክሌ ቤት አረፈች። የወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ሹም የነበሩት አቶ ኃይሌ ሜጢ ድረስ በመውጣት ተረክበው ወደ ቤታቸው ወሰዱአት። ያደረሳትም ሰው ወደ አዲስ አበባ ተመለሰ። ያች አዳል ልጅ ብዙም ሳትቆይ ወንድ ልጅ ወለደች። በ1916 ዓ.ም አካባቢ ስሙም እንግዳ እሸት ተባለ። እሱም የአቶ ኃይሌ ልጅ እንዲመስል ተደርጎ፤ የሚስታቸውን ጡት እየጠባ አደገ። ጀሎ አገረ ማርያም ክርስትና ተነሣ። እናቱም እንደተጠናከረች በሸኚ፣ በበረከት በኩል ወደ ዘመድዎቿ ሄደች። ዘመድዎቿም መልአከ ፀሐይ በነገሡ ጊዜ ገልፀዋል። አርበኞችንም ደግፈዋል።

ወይዘሮ ፀሐይ ወርቅ ደርቤ በተያዙ ጊዜ እንግዳ እሸት ኃይሌ ማን እንደሆነ በልዑል ራስ ተፈሪ መኰንን ዘንድ ታወቀ። የአብዬ ገዳም መድኃኔዓለም አለቃ ሆነው አዲስ ለተሾሙት ለአባ ይርዳው ተሰጠ። ጨፌ የነበረው ፀሐይ ወርቅ ሁዳድ፣ በቀድሞው ሥሪት ከነበረበት ከጀሎ አገረ ማርያም ተነቅሎ፣ ከአሥር አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ከማያንስ ርቀት ላይ ለነበረው ለአብዬ ገዳም መድኃኔዓለም፣ በራስ ተፈሪ ትዕዛዝ ተሰጠ። አባ ይርዳው የኋላ እሸትን በመጠበቅ ለሚሰጡት ውለታ መክፈያ መሆኑ ነው። የጀሎ አገረ ማርያም አለቃ የነበሩት ለአለቃ ውሂበም ምሥጢሩን በመደበቅ ለፈፀሙት በደል፤ ወይም መርምረው ባለማወቅ ላሳዩት ቸልተኝነት ቅጣት እንደነበር ማጤን ይገባል። መልአከ ፀሐይ በነገሡ ጊዜ ሁዳድ እንደቀድሞው በጀሎ አገረ ማርያም ተመለሰ።

መልአከ ፀሐይ እያሱ የመንገሣቸውና የልጅ እያሱ ልጅ የመሆናቸው ጉዳይ ከተረጋገጠ በኋላ ቀጥሎ የሚነሣው ጥያቄ "ምን ምን ሠሩ?" የሚለው መሆን አለበት። የመልአከ ፀሐይ ኢያሱ መንግሥ የአርበኝነትን ሥራ በሸዋ ላይ በእጅጉ እንደ አጠናከረ ጥርጥር የለውም።መልከ ቀና፣ ደመ በራድ፣ እርጋታ ያላቸውና ከሰው ጋር ተባብረው የሚሠሩ እንጂ እኔ ባልኩ የማይሉ፣ በሥጋ ወደሙ የፀኑ ነበሩ።[20] በአባታቸው ዘመን ሰውን ያሰለቸው የመንቀዥቀዥ፣ የጭካኔ ጠባይ አልታየባቸውም። ዕድሜአቸውን ያሳጠረባቸውም ይኸው የሀገሩ ባህልና ሥርዓት፣ እንዲሁም የጦርነት ጊዜ ላይ መሆናቸው፣ ወቅቱ ከሚፈቅደው በላይ ነገርን አለዝበው የሚይዙ



መሆናቸው፤ በዙሪያቸው የተተበተበባቸውን የነገር አሽክላ መፍታት አቅቶአቸው ሳይሆን አልቀረም።

ወደሠሩት ሥራ ስንመለስ ብዙ ሹመቶች ሰጥተዋል። ከቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ባለምዋሎች መካከል በሀገር መከላከል የቆመ ሰው በወቅቱ እምብዛም ያለመገኘቱን ያህል፣ መልአከ ፀሐይ ከሾሙት መካከል አቋሙን ለውጦ ከጠላት ጎን የቆመ አልታየም። ራስ አበበ በቡልጋ አርበኛ ዘንድ ሙሉ ተቀባይነት ያገኙት በመልአከ ፀሐይ እያሱ ራስ ተብለው ከተሾሙ በኋላ ነው። በመሆኑም ዕድሜአቸው እና ጊዜው ይፈቅድ የነበረውን ያህል መልካም ሥራ ሠርተዋል።

ስለ አሠራሩ ከተነሳ፣ የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት የሥራ አመራር የቤተ መንግሥት ሥነ ሥርዓትን የተከተለ ነበር። የሥራ ድልድል የሚደረገውም እየተጠናና እየታሰበበት እንጂ በጅምላ፣ በአንድ ጊዜ አልነበረም። ምንም አንዳንዱ ቀደም ብሎ የተጠቀሰ ቢሆን፤ በሞቱበት በመስከረም ወር 1931 ዓ.ም የነበረውን የሥራ ድልድል እንደገና ማየት ጠቅላላ ሁኔታውን ለመገንዘብ ይረዳል።

- ቀኛዝማች ኃይሉ ወልደ መድህን ደጃዝማች ተብለው የንጉሡ ሞግዚትና ባለሙሉ ሥልጣን እንደራሴ
- በፊት ፊታውራሪ አማረ አየለ፤ በኋላ ደግሞ ራስ አበበ አረጋይ የጦር ሚኒስትር
- ቀኛዝማች ስንቅነህ ሊጋባ
- ቀኛዝማች ሺመላሽ የልፍኝ አስከልካይ
- ፊታውራሪ ታደሰ ጌታብቻህ የግቢ ሚኒስትር
- አዛዥ መኰንን ተክለአብ ዋና አዛዥ
- ፊታውራሪ ኪዳኔ ወልደጊዮርጊስ ፀሐፊ ትዕዛዝ
- ግራዝማች አሉላ መርጌ የልፍኝ አሽከሮች ሹም
- ባላምባራስ ገብረፃድቅ ተክለአብ አልባሽ
- ግራዝማች ይትባረክ ፋንታ የንጉሡ የክብር ልብስ አዘጋጅ
- ቀኛዝማች በቀለ ወልደመድህን የአንጋቾች ሹም
- መምህር ቀፀላ የፍትሕ ነገሥት አውጭ
- አቶ ወልደማርያም የንግሥት ዘውዲቱ በገና ደርዳሪ አጫዋች ነበሩ።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር የወጣቱን ንጉሥ መዝግቦላቸዋል። አመዘጋገቡም መሥፍኑን እስከ ጠላት ወረራ ድረስ አባ ደርበው በእንክብካቤ እንደ አሳደጉአቸው፤ ነገር ግን የተገኙት አህያ ሲያግዱ ነው በማለት ነው። ይህንን ነገር አለቃ /ፊታውራሪ/ ወልደፃድቅ ዘውዴ ያውቁ ስለነበር፤ መልአከ ፀሐይ እያሱ የንጉሥነት ሥልጣን ቢይዙ ኢትዮጵያን ነፃ

ለማውጣት ቆርጠው ለተነሱ አርበኞች እንደሚረዳ እንደ አሳመኑና ወጣቱ መሥፍን መልአክ ፀሐይ ተብለው በወክፌሌ ሚካኤል ካህናት ነሐሴ 21 ቀን 1929 ዓ.ም ሥርዓተ ንግሣቸው እንደተፈፀመ ያረጋግጣል። ማኅበሩ በመዘገበው የህይወት ታሪካቸው ላይ፦ በቡልጋ አርበኞች ምርጫ ወቅቱን እየጠበቀ ሹመት ወይም የማዕረግ እድገት እየተሰጠ በጠቅላላው የሸዋን አርበኞች እየመሩ ከቆዩ በኋላ መስከረም 27 ቀን 1931 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ ይገልፃል።

ቀጥሎ የሚነሳው ጥያቄ መልአክ ፀሐይ ኢያሱ ባይሞቱ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? የሚል ሳይሆን አይቀርም። ጥያቄው መልካም ሆኖ ሳለ፣ ለዚህ ጥያቄ አንድ ብቻ መልስ ያለ አይመስልም። አንባቢ የራሱን ሀሳብ የመደርደር ሥልጣን ይኖረዋል። በብዙዎች አመለካከት መልአክ ፀሐይ እያሱ እስከ ሰኔ 1932 ዓ.ም ቆይተው ቢሆን ኖሮ ፣ ሞሶሎኒ ከሂትለር ጐን በቆመ ጊዜ እንግሊዞች የሚደግፉት መልአክ ፀሐይን ሊሆን ይችል ነበር። ይህ ቢሆን ኖሮ ደግሞ በኋላ ላይ አርበኛ አይንገላታም፣ አይወድቅም ነበር። ሥርወ መንግሥቱም ወደ ምኒልክ ቤት ይመለስ ነበር። መንግሥቱም የበለጠ ሕዝባዊና ሀገር ውስጥ በቀል ይሆን ነበር።

የመልአክ ፀሐይ እያሱን ነገር እንዲህ ከአጠነፈፍን በኋላ፣ ወደ ጦርነቱ ጉዳይ እንመለሳለን። የቡልጋን ሕዝብ የሀገር ፍቅር ስሜት የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መሄድ እንዳላቀዘቀዘው፣ የመልአክ ፀሐይ እያሱ ሞትም አላበረደውም። ሕዝቡ ትግሉን ቀጠለ። ጣልያንም በበኩሉ ጊዜ ያጋጠመው መስሎት አርበኞችን የማውደም ዘመቻውን አፋፋመ።

ጠላት ከቆቦ እስከ መስጫ ያለውን ቦታ ያስስ ጀመረ። አርበኞችም በተቻላቸው መጠን ተከላከሉ። ብዙዎች ሞቱ፤ ተመለሱ። በዚህ ወራት በአርበኞች ዘንድ የነበረው ችግር አሰቃቂ ሆነ። ጦርነቱ ከመቼውም ይልቅ ከበደ። ጠላት የንጉሠ ነገሥቱን መሞት አውቆ ነበርና። ገበሬው አልቆና ተበትኖ ነበርና ረሃብ ሆነ። በዚህ ሁሉ ላይ እንቅጥቅጥ የተባለ የወባ ወረርሽኝ ተነስቶ ሕዝቡን ፈጀው። የተረፈውንም አደከመው።

ራስ አበበ የተረፈውን ጥቂት ሠራዊት ይዘው ፍቅሬ ግንብ ወጡ። እዚያም ጠላት ደረሰና መስከረም 28 ቀን 1931 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። እስከ መስከረም 29 ቀን ድረስ በመዓልትና በሌሊት ተዋጉ። ጠላት ገደሉን ሲጠጋ አርበኞች ከላይ ሆነው ናዳ እየሰደዱ፣ መርግ እየለቀቁ፣ የእጅ ቦምብ እየወረወሩ ፈጁት። ናዳና መርግ ጠላትን አሸዋ የተሞላበት እያስመሰለ፣ አፍረት እያወረደ፣ አንዱን ባንዱ ላይ ቆለለው። ጠላት ሰባት አይሮፕላኖች አስመጥቶ አስደበደበ። እንደ አልሆነለት ባየ ጊዜ አዲስ ጦር አመጣ።

ጣልያን በአባ ማስያስ አማካኝነት በተካሄደ ጥናት መሠረትና መነሻነት ስለፍቅሬ ግንብ ብዙ ነገር ያውቅ ነበር።[21] ስለዚህ ራስ አበበ ከዚች ተራራ ላይ በወጡ ጊዜ ከወጥመዱ እንደገቡለት አድርጐ ሳይገምት አልቀረም። በዚህ



ምክንያት ጦርነቱ ከባድ እንደነበር ማወቅ ይቻላል። ለርዳታ የመጣው የጠላት ጦር የቀረበው በውቢር፣ በቁንዴ፣ በቅጣው፣ ቆላውን ደግሞ በአዋሽ ነበር። ጠላት ያካሄደው፣ አርበኞችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ለመፍጀት ሙሉ ከበባ ነበር። በወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞት የተደናገጠው አርበኛ ራስ አበበን ደግሞ እንዳያጣ እርስ በርሱ እየተረዳዳ ተዋጋ። በልጅ አየለ ኃይሌና በልጅ ይበርታ ጣዲቁ የሚመራው አርበኛ ከደብረ ብርሃን መሥመር የወጣውንና እመምሕረት የነበረውን ገጠመው። በመስጫ የመጣውን በልጅ ደስታ ሸዋ እርካብህ የሚመሩት ያዙት። የቀረውን ከራስ አበበ ጋር የተከበበው አርበኛ ተጋጠመው።[22]

ከዚህ ላይ መጠቀስ የአለበት አንድ ራስ አበበ የተናገሩት አነጋገርና የሰጡት አመራር አለ። ፍቅሬ ግንብ ዙሪያውን በገደል የታጠረና ላዩ ሜዳ የሆነ፣ መሶብ የሚመስል ቦታ ነው። ራስ አበበ ለመከላከል የተዘጋጁት በዚያ ላይ ነው። መከበባቸውን ነገሩአቸው። የአምባው መግቢያ ዋና በር በጥብቅ እንደ ተያዘ፣ በእግር መተላለፊያ የሆነውም በር እንዲሁ እየተጠበቀ መሆኑን፣ በመንጠላጠል አንድ ሰው የሚወርድባትም ሥርጥ እንኳን ሳትቀር በጠላት ታውቃ እየተጠበቀች መሆንዋን አስረዷቸው። በማንኛውም በር አብሮ ለመውጣት እንደማይቻልም ነገሩአቸው። እጅ እንስጥ ለማለት ሳይሆን አልቀረም። ጀግናው ራስ አበበ "...ታዲያ ሞትን እንጠብቀው..." ብለው በዋናው በር ሠብሮ እንዲወጣ ለሠራዊቱ ትዕዛዝ ሰጡ። ጠላት ሠፈር ያደረጉ እንዲመስለው፣ እሳት በብዛት አስነድደው ከብቱን ዙሪያውን፣ ሰዉን ከመካከል አድርገው ወጡ። ከጥቂት ከብትና ከሦስት ሰው በስተቀር ሌላ ሳይሞት አመለጡ።

ከፍቅሬ ግንብ ጦርነት በኋላ ቡልጋ፣ ጋፍራ ላይ ስብሰባ ተደረገ። በስብሰባው ላይ የቡልጋን ጦር የቆረቆሩት ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴና ሌሎችም የጦር መሪዎች ተገኝተው ነበር። የወጣቱ ንጉሠ ነገሥት ሞት የፈጠረው ሁኔታ፣ የጣሊያን ጦር መጠናከርና አርበኞች እርስበርሳቸው አለመስማማታቸው አሳሳቢ ከነበሩት ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ሳይሆኑ አልቀሩም። ከመንዝ፣ ከተጉለትና ከመርሐ ቤቴ አርበኞች ጋር መመካከርም አስፈላጊ ሆነ። በሌላው በኩል ቡልጋን በተጠናከረ ሁኔታ መከላከል አስፈለገ። ስለዚህ የቡልጋ አርበኞች በሀገራቸው ላይ ትግላቸውን እንዲቀጥሉ፣ ራስ አበበ ወደ መንዝ ሄደው በዚያ ያለውን አርበኛ እንዲያስተባብሩ ተወስኖ፣ ጥቅምት 6 ቀን 1931 ዓ.ም ተነሱ። በጠራ በኩል አድርገው የመኪና መንገዱን በሸኖና በመርቆሪምስ መካከል አቋርጠው ኘአ ደረሱ። ከዚያም ወደ ደነባ ተሻግረው በሸደማ፣ በሱጣ ለገድ አድርገው ተጉለት ገቡ። ከዚያም ወደ ቡልጋ ዞሩ።

ጠላት አርበኞችን ለማጥፋት የሞከረው የተጠቀሱት ንጉሠ ነገሥቱ በሞቱባት አካባቢ ብቻ አልነበረም፤ በሁሉም አካባቢ ጥቃት አካሂዶ ነበር። ጥቅምት 3 ቀን 1931 ዓ.ም ሰፀርንሃ ጦርነት ተደረገ። በፊታውራሪ

ወልደፃድቅ የሚመራው ቡድን ሌላ ሁለተኛ መድፍ ለመማረክ ተቃርቦ ለትንሽ አመለጠው። ሌላው ጦርነት ደግሞ ጉርግ አገር ነበር። ጣልያንን ቀለበት ከሆነች ቦታ እስኪገባላቸው ጠብቀው ዙሪያውን በመከበብ በጥይት ጠዘጠዙት። የጦር አዝማቹ መኰንን ቆስሎ አመለጠ።

የጨፌ ሹመት በአርበኞች መካከል የፈጠረው ቅሬታ ያኔም ስላልበረደ በአንድ ወገን መስቀል እየቆመ በሸማግሌ እርቅ ሲካሄድ፣ በሌላ ወገን ጠቡን የሚያጋግሙ የውስጥ አርበኞች በፊታውራሪ ዝቅ አርጋቸውና በፊታውራሪ ሞገሴ መኩሪያ መካከል ጠብ ፈጠሩ። የአንዱ ወታደር ጠመንጃ ይዞ ሌላው በማደሩ ነው የሚሉ አሉ፤ የአንዱን ሚስት ሌላው በመቀማቱ ነው የሚሉም አሉ። ብቻ በማይረባ ነገር መሆኑ ነው። ጠቡ እንደ ተሰማ ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ ከሰበርንሃ በፍጥነት ተንቀሳቀሱ። ሙጣማያስ ሲደርሱ የፊታውራሪ ዝቅ አርጋቸው ሞት ተሰማ። ህዳር 12 ቀን 1931 ዓ.ም መሆኑ ነው። አንድ ሣምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ፊታውራሪ ሞገሴ መኩሪያ ሞቱ። የፊታውራሪ ዝቅ አርጋቸው አሽከር ገደላቸው ተባለ። ዋናው ነገር በምናምንቴ ነገር እነዚያን የመሰሉ ጀግኖች እርስበርሳቸው ማለቃቸው ነው።[23]

ወደ ጦርነቱ ሁኔታ ስንመለስ፣ የስድስቶን ምሽግ ለመስበር የተደረገው ሙከራ አለመቃናት፣ አርበኛውን አስመረረው እንጂ ተስፋ አላስቆረጠውም። ጠላትን ለማስደንገጥና ስንቅ ለማግኘት፤ የሕዝቡን ልቡና ለማጠናከር፤ ባንዳውን ለመበተን ይረዳል በሚል ምሽግ መስበር አስፈላጊ እየመሰለ ታየ። ከተቻለም በውስጡ የነበረውን ጠላት ደምስሶ ምሽጉን መያዝ ታላቅ ቁም ነገር ሆነ። ፊቱንም ቢሆን የስድስቶን ሦስት ምሽግ ከማጥቃት፣ የጊና አገር ምሽግ እንዲመታ የታሰበው በዚህ ምክንያት አልነበረም። ምሽጉ እንዲመታ የታሰበው ብዙ መሣሪያ መኖሩ በጠቋሚ ስለተደረሰበት ነበር። ከመሣሪያው መጋዘን የሚያደርስ መሪም ቀደም ብሎ ከምሽጉ በመውጣት እስከ ጭብጦ ማርገፊያ መጥቶ ከአርበኞቹ ጋር ተቀላቅሎ ነበር። ይህም ሁሉ ሆኖ አርበኛውን ከድንጋይ እየከሰከሱ ለማስጨረስ ሆን ተብሎ የተሠራ ሥውር ደባ አለ ብሎ የሚያጣራ ክፍል ነበር። በመጨረሻው ግን ምሽጉን ለመስበር ተወሰነ። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ አስተባባሪነት፣ የፊታውራሪ አርጋው ቁንጬ እና የፊታውራሪ ዳርጌ ሰዎች ተነሱ። ፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌም ለመተባበር ተስማሙ።

የጊና አገር ምሽግ ከመገዘዝ ተራራ በስተ ሰሜን ምሥራቅ፣ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ ከገደል አፋፍ ላይ የሚገኝ ነው። የመሶቢት አነስተኛ ምሽግ ደግሞ ከእሱ በስተሰሜን፣ አሥር ኪሎ ሜትር ያህል ርቃ ትገኛለች። ከዘበጠ ቦታ ስለሆነች፣ ለጊና አገር ዕርዳታ የመስጠት አቅምዋ ውስን ነው። ስለዚህ ከቁጥር አልገባችም። ዝግጅቱ ተጠናቅቆ ለማጥቃቱ እንቅስቃሴ በታህሣሥ ወር 1931 ዓ.ም ተካሄደ። ፊታውራሪ ዳርጌ ቀደም ብለው ሞተው ስለነበር፣ ሠራዊታቸው የሚመራው ቀኛዝማች ቱፋ እና ቀኛዝማች ቱሉ



በተባሉ እንደራሴዎች ነበር። ጦርነቱ ሲከፈት ቀኛዝማች ቱሉ የተባሉት፣ በእርሱ ይታዘዝ የነበረውን ሠራዊት ይዞ፣ ስተት ብሎ ከጊና አገር ምሽግ ገብቶ ከጣልያን ጋር በሰላም ተቀላቀለ። ማለትም:- አስቀድሞ የተሠራ የውስጥ ግንኙነት ኖሮታል። ፊታውራሪ ደባልቄ በታሰበው ጊዜ፣ ከተወሰነላቸው ቦታ ሳይደርሱ ዘገዩ። ጠርጣራው ፊታውራሪ ወልደፃድቅ ይህንን ሁኔታ ካጤኑ በኋላ ጥሩምባ በማስነፋት፣ ከጦር ግንባር ተጋፍጦ የነበረውን ሠራዊት ተኩስ አቁሞ ወደ ኋላ እንዲመለስ በማዘዝ ከእልቂት አዳኑት።[24] ፊታውራሪ ቱፋ የተባሉት ግን እሰፋ የተባለውን የፊታውራሪ ዳርጌን ልጅ ይዘው ወደ ጠላት ሳይገቡ የአርበኝነት ሥራቸውን ቀጠሉ።

ከመካኒሣ የተንቀሳቀሱት የአርበኞች ቡድን ሽንኩራ ተሻግረው ታህሣሥ 25 ቀን 1931 ዓ.ም የራሪቲን ምሽግ አጠቁ። በምሽጉ ውስጥ ታፍገው ከነበሩት የጠላት ወታደሮች፣ በተለይም ባንዶች ብዙ ገደሉ። መሣሪያ በመጠኑ፣ ከብትም በብዛት ማረኩ። ነገር ግን የምሽጉ አዛዥ የነበረው ሌሲት ተሽልኮ በማምለጥ ባልድ ምሽግ ገባ። ጥቂት ባንዶችም አምልጠው ከአሲልቱ ምሽግ ሄዱ። አርበኞቹም ምርኮአቸውን ይዘው ወደ ፀደታ ተሻገሩ።

የራሪቲን ጥቃት ለመበቀል ጠላት ከሞጆ አዲስ ጦር አንቀሳቀሰ። የጠላትን አመጣጥ ሲመለከት ይይታ ለነበረው ዕርዳታ ደረሰለት። ጣልያንም ይህንን ሲያይ ወደመጣበት ተመለሰ።[25]

በመጋቢት ወር 1931 ዓ.ም ራስ አበበ ከመንዝና ከተጉለት እንደገና ወደ ቡልጋ መጡ። ከመጋቢት 12 ቀን 1931 ዓ.ም ጀምሮ ሮርቹ ጊዮርጊስ ምክር ተካሄደ። የምክሩ ዓላማ የወቅቱን የጠላትንም፣ የወገንንም ሁኔታ ገምግሞ አዲስ የጦር ዕቅድ ለመንደፍ ነበር። በተጉለት የተጀመረው የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማህበር መቋቋም ጉዳይም አንዱ ሆነ። ራስ አበበ ይህንን ማህበር ያቋቋሙት ቀደም ብለው በሞቱት በመልአከ ፀሐይ እያሱ ምትክ አንግሱኝ ለማለት ነው ብሎ የተጐሻመጠ አልጠፋም። ስምምነቱ የሚገለፀው ልዩ ልዩ መሣሪያ ተቀምጦ «ይህ ቢስት፣ ይህ አይሳተኝ።» እያሉ በመራመድ እንዲሆን ተደርጐ ነበርና፣ በማህበሩ መቋቋም ስምምነት ተደረገ።[26]

የካቲት 23 ቀን 1931 ዓ.ም የአድዋን በዓል በጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ለማክበር አርበኞች ተሰባስበው ስለ ነበር፣ ጠላት በአርበኞች ላይ አደጋ ለመጣል ከጅሎ ነበር። አርበኞቹ ጠርጥረው ነበርና ከወጥመዱ አመለጡ፤ ሳይሳካለት ቀረ።

ጣልያን አርበኞችን በጥቃቅን ነገር ሸንግሎ ከእጁ ለማስገባት ሲያደባ ነበርና፣ በሚያዝያ ወር 1931 ዓ.ም ሽማግሌዎች ላከ። ሐሳቡ ሙሴ ቀስተኛ ጀምሮት የነበረውን ለመቀጠል ነበር። ንግግሩ ማህበረ በኩር ላይ ተደረገ። መልእክተኞች ሆነው ከመጡት ውስጥ ደጃዝማች ዋኰንን ወሰኔና ነጋድራስ

ተሰማ እሸቴ ተገኝተውበታል። እነሱም በንግግሩ እምብዛም እንደ አልተጫኑ በኋላ ተሰማ። ተመልሰው ሄዱ። አርበኞቹም ወደ ጌልጌላ ወረዱ።

ራስ አበበ በጌልጌላ ቆይታቸው ጊዜ ከአካሄዱት ሥራ አንዱ የወታደራዊ ሥልጠና እንዲካሄድ ማድረግ ነበር። ከየሠራዊቱ ለተውጣጡ ሦስት መቶ ለሚያህሉ ወጣቶች የአጭር ጊዜ ሥልጠና ተሰጠ። ሥልጠናውም ተከላክሎ ራስን ስለማዳን፣ ጠላትን ስለማጥቃት፣ ስለስለላ ሥራና መረጃ አሰባሰብ፣ ለጠላት የተሳሳተ መረጃ መስጠት ስለሚቻልባቸው ዘዴዎችና ልዩ ልዩ መሣሪያዎች እየፈቱና እየጠረጉ ስለመገጠም፣ የጐደለ የመሣሪያ አካልን ከሌላ መሣሪያ አዛውሮ ስለመግጠም ነበር። ሰልፍና እርግጫም ይጨምር ነበር። አሠልጣኞች፣ ቀደም ብሎ ከሠለጠኑት፣ በሕይወት የቆዩት ነበሩ።[27]

ጠላት በግንቦት ወር 1931 ዓ.ም ሙገሬ ዛላ፣ ቅጭንፍር ከተባለው ቦታ በነበሩት ፊታውራሪ ወልደፃድቅ በሚመሩት አርበኞች ላይ ጠንካራ ከበባ አደረገ። አመጣጡ በልዩ አቅጣጫ፣ የደረሰውም ሳያስቡት በድንገት ነበር። ዓላማው አርበኞቹን ከብቦ ለመፍጀት ሲሆን፣ ሊቃናለት ምንም ያህል አልቀረውም። ሆኖም አርበኞች በርትተው ተከላከሉ፤ በልዩ ልዩ ሥልት ተጠቀሙ። ከፋሪ ተራራ የሚወርደውን አንድ ቡድን፣ አርበኛው ከታች ሆኖ በጥይት ሰግጦ ያዘው። ሌላው ቡድን ከሜጢ፣ በምስለኔ አገር በመጣውና ከጀሎ አገር መጥቶ ጉርባ አገር በደረሰው መካከል ጣልቃ ገብቶ ለጥቂት ጊዜ ፊትና ኋላ በመተኮስ ውጊያ ከከፈተ በኋላ ተሾልኮ ሜጢ ገሮማ በመግባት፣ የጠላትን ጦር እርስበርሱ አዋጋው። የተራራውንም እሱ ራሱ ተመልሶ ጨረሰው። ሦስተኛው ከቁንጥሎ በልግ የወረደውን ግንባር ለግንባር ገጥሞ በመውጋት ወደ መጣበት መለሰው። አርበኞቹ እንደዚህ አድርገው ጣልያን በስንት ብልሀት የሠራውን ከበባ አፈራረሱበት።

ከወጣቱ ንጉሥ ነገሥት ከመልአከ ፀሐይ እያሱ ሞት በኋላ፣ በእሳቸው ባለሚሎችና በደጋፊዎቻቸው ላይ ችግር እንደተፈጠረ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ። ከፍ ሲል ከጠቀስኳቸው ደጋፊዎቻቸውና ባለሙዋሎቻቸው ሌላው ደጃዝማች ኃይሉ ወልደመድህን ዋናው ነበሩ። በጅሮንድ ወልደዮሐንስም ቀረቤታ ነበራቸው። እነኚህ ከራስ አበበ ጋር ስምምነት ስለአጡ፣ ተለይተው ጉዞ ጀመሩ። ሐሳባቸው ወደ ጉራጌ ሀገር ሄደው እዚያ ከነበሩ አርበኞች ጋር በመቀላቀል የአርበኝነት ሥራቸውን ለመቀጠል ነበር። የመንገድ መሪ ይዘው ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ደቦ ጐጆ ሲደርሱ መሪአቸው ሰኔ 15 ቀን 1931 ዓ.ም ከአንድ ከተቃጠለ ግንብ ቤት ውስጥ አስገብቶ አካባቢውን ልሰልል በሚል ምክንያት ተለያቸው። ሌሊቱን የጠላት ጦር መጥቶ ጨረሳቸው። ሰባ ሰው ሞተ። ንጋቱ ወልደ ዮሐንስ ከተባለ ልጅ በስተቀር የተረፈ የለም። ሀገሬው ቀበራቸው።[28]

ሰኔ 22 ቀን 1931 ዓ.ም ሰጠን ላይ ጠላት ብዙ ጦር አቅርቦ ከባድ ጦርነት ተደረገ። የሚመራውም ጂቦ በተባለ ሻለቃ ነበር። ይህ ጂቦ የተባለው



ጣልያን ቀደም ብሎ ቡልጋ ውስጥ ወንድሙ ተገድሎበት ስለነበር ደሙን የመወጣት ፍላጐት ነበረው። በአርበኞች ወገን ራስ አበበ ራሳቸውና ደጃዝማች አውራሪስ ዱሉ ከነልጆቻቸው መከቱ። ግሩም ጦርነት ተካሄደ። ብዙ የጠላት ወታደር አለቀ። ዝቶ የመጣው ጂቦም እሱ ራሱ ሞቶ ከቡልጉች ንዝንዝ ተገላገለ። ብዙ ወንድሞቻቸው ቢሞቱም፣ ብዙ መሣሪያ አርበኞች ማረኩ።

በሰኔ ወር መጨረሻ 1931 ዓ.ም ጌልጌላ ላይ ጦርነት ተደረገ። ጠላት ብዙ ጦር አምጥቶ ነበርና ጨፋና ወሴንሶ ላይ የጦፈ ውጊያ ተካሄደ። አርበኞች ሰው ቢጐዳባቸውም መልካም ሥራ ሠሩ። ብዙ የጠላት ወታደር ጨረሱ፤ መሣሪያና ስንቅም ማረኩ።

ይህ ሁኔታ ጠላትን ስለአስቆጣው፣ ለመበቀልና ሃፍረቱን ለመሸፈን ሞከረ። እንደ ገና አዲስ ጦር አመጣ። አርበኞችም አብራም አራዳ ጠብቀው እንደ ፊት ወቁት። በሐምሌ ወር 1931 ዓ.ም ያገኙት ምርኮ ለክረምቱ ወራት ስንቅ ሆናቸው።[29]

በቡልጋ የ1931 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተጠናቅቆ የ1932 ዓ.ምቱ ቀጠለ። በጠላት ዘንድ የተገመተው አርበኞች የ1931 ዓ.ምን እንደማያልፉ ነበር። ጠላት ደጋግሞ አዳዲስ ጦር በማምጣት በርትቶ የተዋጋውም ለዚህ ነበር። በአውሮፓ የፖለቲካ ተፅዕኖ ጠንክሮበት ነበርና፣ ደግሞም ለጦርነቱ ማካሄጃ የሚያወጣው ወጭ ከብዶት ነበርና፣ የጦርነቱ ማለቅ ለሞሶሎኒ መንግሥት እጅግ አስፈላጊ ነበር። አርበኞቹን በመጨረስ ጦርነቱን መፈፀም እንደአልቻለ ከጊዜ ብዛት ገባው። ስለዚህ የ1932 ዓ.ም ዋና ፕሮግራም የዕርቅና ማፈጋጋት ጉዳይ ሆነ።

ነሐሴ 21 ቀን 1931 ዓ.ም ተጀምሮ የነበረው የእርቅ ንግግር መስከረም 7፣ ከዚያም ጥቅምት 30 ቀን 1932 ዓ.ም ማህበረ በኩር ቀጠለ። በንግግሩ ላይ ከጣልያን ወገን በአስታራቂነት የቀረቡት ሽማግሌዎች በየጊዜ ይለዋወጡ ነበር። ደጋግመው የመጡት፣

ሀ. ኢጣልያውያን፤

ጄነራል ናዚ ጥቂት ጊዜ

ጄነራል ፍራንክ

ሻለቃ ለኰቲ

ሌሎች ብዙ የጦር መኰንኖችና የሲቪል ሹማምንቶች ነበሩ። ወደ መጨረሻው ላይ ጠቅላላ ቁጥራቸው ወደ ሃምሣ ተገምቶአል። የሚመጡትም በመኪና ነበር።

ለ. ኢትዮጵያውያን ደግሞ፤

ራስ ስዩም መንገሻ

ደጃዝማች መኰንን ወሰኔ

ፊታውራሪ ኃይለሚካኤል ዘውዴ ነበሩ።

በእያንዳንዱ ስብሰባ አባላቱ ከሰባት ከሰባት ቦታ ይፈተሹ ነበር። ለጥንቃቄ ብቻ ሳይሆን ለማዋረድና ለማበሳጨት፣ ለማሰልቸት ጭምር። ከሁሉም የሚያሳዝነው በዚህ መናኛ ሥራ የኢትዮጵያውያኑ መተባበር ነበር።

በአርበኛው ወገን በንግግሩ ላይ የሚቀመጡት ራስ አበበና ፊታደኞች የሆኑ የጦር መሪዎች ነበሩ። በሐሳቡ ያልተስማሙት አብዛኛውን ጊዜ ከንግግሩ አልገቡም፤ አርበኛው ለብቻው እርስበርሱ በሚነጋገርበት ጊዜ እንጂ።

ከጣልያን ወገን የሚቀርቡት ሐሳባች እንደ መልእክተኞቹ ሁሉ በየጊዜው ይለዋወጡ ነበር። በጥቅምት 30 ቀን 1932 ዓ.ም የቀረቡት፣

- ለአርበኛው ጠቅላላ ምሕረት እናደርጋለን፣
- ቀለብና ልብስ እንሰጣለን፣
- ለአርበኛው ያለበትን አካባቢ የማስተዳደር ሥልጣን እንሰጣለን፣
- ቁስለኞችን እናክማለን፣
- ሀገር እናለማለን፣

የሚሉ ሲሆኑ፣ ከአርበኛው ወገን የቀረቡት ደግሞ፣

1ኛ. እሥረኞች ይለቀቁ ወደሞቃድሾ፣ ኤርትራና ሮማ የተወሰዱት ጭምር፣

2ኛ. የዳኝነት ሥራ የሚካሄደው በኢትዮጵያውያን ይሁን፣

3ኛ. አርበኞች ከአሉባቸው አካባቢዎች የነበሩ ምሽጎችን እንዲያነሳ፣

4ኛ. ሕዝብ ከጣልያን ባለሥልጣኖች ፈቃድ /በርሜስ/ ሳያስፈልገው እንደ ፈለገ እንዲንቀሳቀስ፣

5ኛ. የሰው ንብረትና ሀብት ያለ ሕግ እንዳይወረስ፣

6ኛ. ከእርቅ በኋላ በጅሩ አውራጃ፣ ጫሳ ቀኛዝማች አድማሴ መንገሻንና ባላምባራስ ተምትምን ያለአንዳች ጥፋት ያለሕግ ከእነሰዎቻቸው ያስፈጃቸው ኩሎኔል ሎሬንሲኒ፣ በኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት፣ በሞት እንዲቀጣልን የሚሉ ነበሩ።

እነዚህም የጣልያን መንግሥት አቅርቦአቸው ከነበሩት ሐሳቦች በተጨማሪ መሆናቸው ነው።[30]

ነገር ግን በእነዚህ ነጥቦች ንግግር ተደረገ እንጂ ከስምምነት አልተደረሰም። ሁለቱም ወገኖች ስምምነቱን ራሱን አልፈለጉትም። አርበኛው በእርቁ ጉዳይ አንድ ልብ አልነበረም። ጠንካራ ተቃውሞ ነበር። ስምምነት ማድረግ ማለት ጦርነቱን ትቶ እጅ መስጠት ማለት ነው። ጣልያኖችም ቢሆኑ ጦርነቱን ማቀዝቀዝ እንጂ፣ ሽፍቶች ብለው ከሚገምቱአቸው ጋር ውል መዋዋል አልፈለጉም። ከቡልጋ አርበኞች ጋር ተተዋዋሉ በመንዝ፣ በአንኮበር፣ በመርሐ ቤቴ፣ በግንደበረትና በጉራጌ አገር ላለው አርበኛ ሁሉ የሚፀና ይሆናል። ደግሞም በጐንደር፣ በጐጃም፣ በትግሬና በወሎም ያለው ተመሳሳይ ጥያቄ ያቀርባል። ይህ ብቻም አይሆን። በዓለም ህብረተሰብ ዘንድ የአርበኛው ሕልውና በይፋ ታወቀ ማለት ነው።



በሁለቱም ወገን የተያዘው ፊሊጥ ጦርነቱን እያቀዘቀዙ ጊዜ መውሰድ ሆነ። ይህ ዘዴ ለሁለቱም ወገን ጠቃሚም፣ አስፈላጊም ነበር። አርበኛው ፋታ በማግኘቱ ለአራት ዓመት ከደረሰበት ያላሰለሰ ቅጥቃጤ ያንሠራራል። የንጉሠ ነገሥቱን የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን ሐሳብና የዓለምን ፖለቲካ ይገመግማል። አሮይታ የሚያስገኝ ሁኔታ በንግግሩ ውስጥ በማስገባት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ የማግኘት እድሉን ያጠናክራል። ጣልያን ደግሞ ከአንዳችም ግዴታ ሳይገባ ለዓለም ህብረተሰብ ጦርነቱ እንደ አለቀ አድርጐ የማቅረብ ዕድል ይኖረዋል።

ለማንኛውም ነገር ድርድር በተካሄደባቸው ነጥቦች ዙሪያ አንዳንድ እርምጃ መውሰድ ግድ ነበር። በአርበኞች ወገን ተኩስ ቆመ። ጣላትም በአርበኞች ወደ ተያዙ አካባቢዎች አዲስ ጦር ማጋዙን ተወ። ቁስለኞችን ተረክቦ አከመ። እርቅ ከከፈተ በኋላ አቶ ኃይለ ገብርኤል በላይነህ የተባለውን የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ አሽከር አሥመራ ድረስ ወሰደ፣ የተጐዳ ቁስሉን አክሞ፣ አድኖ፣ መልሶ አምጥቶ ጊና አገር አድርሶ ከጓደኞቹ እንዲቀላቀል ፈቅዶ ለቀቀው። በስንቅ ረገድ የፍሮኖ ዱቄት፣ ሻይ ቅጠል፣ ሱካር በገፍ ሰጠ። ልብስም በመጠኑ። መሣሪያ ለጨበጠ አርበኛ ከመስከረም እስከ መጋቢት ወር 1932 ዓ.ም ደመወዝ ከፈለ። ድልድሉም፡- ለወታደር በወር አሥራ ሁለት፣ ለሹማምንቶቹ በወር እስከ ሦስት መቶ ሊሬ ነበር። እሥረኞች ከሀገር ውስጥም ለይናሪም ተፈቱ። ዳኝነት በኢትዮጵያዊያን እንዲካሄድ ተደረገ። በአስተዳደሩም ሥራ ኢትዮጵያውያን የተሻለ ተሰሚነት አገኙ። አዲስ በተቋቋመው የመርካቶ ከተማ ፀሐፊ ትዕዛዝ ወልደመስቀል ኃላፊ ሆኑ።

በማህበረ በኩር ማርያም በኩል የዕርቅ ንግግር ከተደረገ በኋላ አንድ የአርበኞች ቡድን በእርዳታ አውቶሞቢል ከእነጀነራል ፍራንክ ጋር እስከ አዲስ አበባ ድረስ መጣ። የቡድኑ መሪ ፊታውራሪ ደምሴ ወልደአማኑኤል ሲሆኑ፣ ከንቲባ /ደጃዝማች/ አበራ ኃይለሥላሴ፣ ቀኛዝማች /ፊታውራሪ/ በቀለ ዘውዱ ነበሩበት።[31] የቡድኑ ተልእኮ በኢትዮጵያ ተወራሪነቱና በጣልያን ወራሪነት ላይ የዓለም መንግሥታት ማህበር የነበረውን አቅዋምና የአውሮፓ ኃያላን መንግሥታት የያዙትን አመለካከት ማጥናት፤ ወደ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ መልእክት ማስተላለፍ፤ የጣልያንን ጦር ጥንካሬ መገምገም፤ የሕዝብን አስተሳሰብ መሰብሰብ ነበር። ያመጡት ወሬ የተጠናቀቀ ባይሆንም ተስፋ የሚሰጥ ነበር።

በተከታታይ የሚነፍሰው ወሬ የጣልያንን መንግሥት ውድቀት፣ የኢትዮጵያን ነፃነት የሚያመለክት እየሆነ በመሄዱ፣ የአርበኛው ልብ

ተጠናከረ፡፡ የውስጥ አርበኞችም ተንቀሳቀሱ፡፡ ምክርም ይለግሱ ጀመር፡፡ ሁኔታው በአንዴ ተለውጦ፣ አብዛኛው እጅ አትስጡ ባይ ሆነ፡፡ በደመወዝ ከተቆጠረው ባንዳ በስተቀር፣ ሌላው ለጠላት መሣሪያ መሆኑን ተወ፡፡

በዕርቅ ላይ አርበኛው የነበረው አመለካከት ሲብላላ፣ የተቃዋሚው ክፍል እያየለ ሄደ፡፡ ሐሳቡ ስብጥርጥር ያለ እና እልህ የተቀላቀለበት ነበር፡፡ አብዛኛው የሚለው እንሞታለን ሆነ፡፡ በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ አካባቢ የነበረውን ሐሳብ ብንመለከት ስለጠቅላላው አስተሳሰብ ፍንጭ እናገኛለን፡፡ የእሳቸውና ከእሳቸው ጋር የነበረው ቡድን አመለካከት «እርቅ አዘናጊና ትጥቅ አስፈቺ ነው፡፡ ሰው ወደ ግል ኑሮው ከገባ ምቾት፣ ከቀመሰ እንደገና ወደ አርበኝነት አይመለስም፡፡ የጣልያኖች ዓላማ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ይዘው ሕዝባቸውን ማስፈር ነው፡፡ ስለዚህ እርቁ አይከበርም፡፡ ዕርቁ በማይከብርበት ጊዜ ደግሞ ዳኛ አይገኝም፡፡ ስለዚህ እርቅ አይጠቅምም፡፡» የሚል ነበር፡፡ ይህ ሐሳብ ቀስ በቀስ ድጋፍ እያገኘ፣ ስለእውነትነቱም ማስረጃ እየተገኘ ሄደ፡፡ ለምሣሌ ጣልያኖች ሕዝቡን እየፈጁና እያባረሩ በአርሲና በጨርጨር ሠፈር፣ እርሻ መጀመራቸው ተሰማ፡፡

ከዚህም በስተቀር የጠላት ጦር ዕርቁን ምክንያት በማድረግ ከየምሽጉ እየወጣ በየቦታው ይዘዋወር ጀመር፡፡ ጠላት ይህንን የሚያደርገው ለስለላ ጭምር እንጂ፣ ከአንዱ ምሽግ ወደ ሌላው ምሽግ ለመሄድ ብቻ አልነበረም፡፡ ዕርቁን ሳልተቀበሉት ወገኖች ይህ ሁኔታ ችግር ፈጠረባቸው አልዋጥላቸው አለ ገደብ አጣ፡፡ ማብቂያም ጠፋበት፡፡ ሲከለክሉአቸው ክስ ያቀርቡ ጀመር፡፡ ጣልያን የሚለው ይሰማል፤አርበኛው የሚለው አይደመጥም፡፡ ስለዚህም ግጭት ይፈጠር ጀመር፡፡ ከስድስቱ ምሽግ እየወጣ እስከ ድንጋይ ይንከዋረር የነበረውን የጠላት ወታደር ፊታውራሪ ደባልቄ ተክሌ ቢከለክሉ ሻለቃ ለኩቲ ለራስ አበበ አረጋይ ስሞታ አቀረበባቸው፡፡ በእሱ በኩል ግን ሥራ አልፈታም፡፡ ፊታውራሪ ዳርጌን ጉርጁ ጠራ ላይ ጥር 5 ቀን 1932 ዓ.ም ገደለ፡፡

ከዚህም አልፎ በጅሩ ወረዳ ጫሶ ላይ ቀኛዝማች አድማሴ ማገኛ የተባሉትን አርበኛ ያለበደል፣ ያለፍርድ፣ በግፍ ሃያ አንድ ራሳቸውን ገደላቸው፡፡ እንደዚሁም ባላምባራስ ተምትም የተባሉት ሌላ አርበኛ ከአሥራ ስደስት ሰዎቻቸው ጋር አይነበር ከተባለው ቦታ ያለአንዳች በደል ገደላቸው፡፡ በራስ አበበ ጥያቄ የሰዎች አምዋምዋት ቢጣራም፤ በገዳዮቹ ጣልያኖች ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ሳይወሰድ ቀረ፡፡[32]

ከጊና አገር ምሽግ ወጥቶ እስከ ሜጢ በመውረድ ያለአንዳች ምክንያት ሀገር የሚያስሰውን አንድ የጣልያን ጦር የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ቡድን ምስለኔ አገር ከተባለው ቦታ በጦርነት ማረከው፡፡ የጣልያን ጦር የተመራው በአንድ ሻለቃና በአንድ መቶ አለቃ ነበር፡፡ የጣልያኖቹ ጥያቄ እኛ የመጣነው በሰላም ሲሆን ለምን ተኩስ ተከፈተብን ነበር፡፡ አርበኛውን ሳትጠይቁንና ሳንፈቅድላችሁ እኛ ግዛት ምን አመጣችሁ ሆነ፡፡ ጣልያኖች መልስ



አልነበራቸውም፡፡ ተኩስ በተከፈተባቸው ጊዜ እጃቸውን ከመስጠት በስተቀር ለመዋጋት አልተወላዱም ነበርና፣ በሰላም ከነመሣሪያቸው ተለቀቁ፡፡ እነሱም ስሞታ ሳያቀርቡ ዝም ብለው ቀሩ፤ ከምሽግ መውጣታቸውንም ተዉ፡፡

የእርቁ ነገር በዚህ ዓይነት ሲሞቅ፣ ሲቀዘቅዝ ቆየና የደብዳቤ መለዋወጡ ጉዳይ ቀጠለ፡፡ ጄነራል ናዚ የካቲት 4 ቀን፣ ሻለቃ ለኩቲ የካቲት 5 ቀን፣ ሻምበል ጋሎቺ የካቲት 6 ቀን፣ ዶክተር ብሩዛ ማስም የካቲት 15 ቀን 1932 ዓ.ም ለራስ አበበ ፃፉላቸው፡፡ ሁሉም "እጅግ የተከበሩ" እንጂ እንኳን "ራስ"፣ ባላምባራስም አላልዋቸውም፡፡ ይህም የጣልያን መንግሥት ራስነታቸው ላለማወቅ ያደረገው ጥንቃቄ እንደነበረ ሊታወቅ ይገባል፡፡

በዚሁ ዓይነት የእርቁ ንግግር ሳይቋረጥ፤ በእሱ መሠረት የተወሰደውም እርምጃ ሳይሰናከል እስከ መጋቢት ወር ድረስ ቀጠለ፡፡ ነገር ግን የማመንታቱ ነገር ከዚህ የበለጠ መቀጠል አልቻለም፡፡ በጣልያን በኩል በአውሮፓ የነበረው የፖለቲካ አቀዋም ስለተበላሸበትና በአርበኞች በኩል ተቃውሞው እየጠነከረ ስለሄደ፣ ከአንድ ውሳኔ ላይ መድረስ ግድ ሆነ፡፡ መጋቢት 3 ቀን 1932 ዓ.ም አርበኞች እርስበርሳቸው በአካሄዱት ምክር ጄነራል ናዚን ጠልፈን በማገቻነት እንያዝ የሚል ሐሳብ ከፊታውራሪ ወልደፃድቅ ቀረበ፡፡ ውሣኔ ሳይሰጥበት ሰነበተ፡፡ ንግግሩን በአርበኞች በኩል ራስ አበበ፣ በጣልያን በኩል የሸዋው ገዥ ጄነራል ናዚ ሆነው እንዲጨርሱ ተወሰነ፡፡ ቀጠሮውም ለየካቲት 19 ቀን እንዲሆን ተቆረጠ፡፡ የሚፈፀመውም በሥጋ ኢየሱስ እንዲሆን ታሰበ፤ ጳጳሳትም ቀረቡ፡፡ ነገር ግን የጄነራል ናዚና የራስ አበቤ እምነት የተለያየ በመሆኑ ሥጋ ወደሙ ቀረና በመሐላ ብቻ እንዲሆን ስምምነት ተደረገ፡፡

በአርበኞች ዘንድ የእርቅ ጉዳይ ሲገመገም፣ እንዲሁም ከውጫሌ ጀምሮ የተደረጉ ውሎች ሲጤኑ፣ የጣልያኖቹ አያያዝ ቢታይ፣ የዓለም መንግሥት ማህበር አቀዋም ቢገመት፣ የአውሮፓ መንግሥታት ስሜት ቢታሰብ፣ ጣልያኖች የነበራቸው የኃይል ሚዛን ቢገመት፣ የሕዝብ አስተያየት ቢገመገም፣ የውስጥ አርበኞች ምክር ቢሰማ፦ የእርቅን ጉዳይ የማይደግፉ ሆነው ተገኙ፡፡ በመሆኑም እርቅ ይቅር ከሚል ድምዳሜ ላይ ተደረሰ፡፡

ሌላ ሐሳብ ቀረበ፡፡ ጄነራል ናዚ ለእርቅ ሲቀርብ ጠልፈን በመያዝ እናስቅበት የሚል ነበር፡፡ የሚያስከትለው ድብደባ ቢፈራም፣ ቀደም ብለው ከተካሄዱት እንደማይብስ ተገመተ፡፡ ሐሳቡ ውሳኔ ሳያገኝ የታሰበው ቀን፤ ማለትም፦ የካቲት 19 ቀን 1932 ዓ.ም፤ ደረሰና ጄነራል ናዚ ወሬውን ሰምቶ ቀረ፡፡ ሥራ አለብኝ ብሎ በማመካኘትም በእሱ ምትክ እንዲምልለት ጄነራል ፍራንክን ላከ፡፡ ጄነራል ፍራንክም በጄነራል ናዚ ምትክ ለመማል ቀረበ፡፡ ራስ አበበም ስለ እኔ ሆኖ የሚምለው በሚል አበበ የተባለውን የቀድሞ ጊዜ ባሪያቸው እንዲማማለው አዘዙ፡፡ ፍራንክ በዚህ ተናደደና ጥሎ ሄደ፤ እርቁም ፈረሰ፡፡[33]

ከዚህ ላይ ሲደረስ ሁለቱም ወገኖች በደፈጣ መተያየታቸውን ትተው፣ ነገሩን ወደ ሽኩቻ አዞሩት። ሜጀር ለኮቲ ለራስ አበበ፣ ራስ አበበ ደግሞ ለጄነራል ናዚ በአንድ ቀን፤ ማለትም፡- መጋቢት 5 ቀን 1932 ዓ.ም፤ ተመሳሳይ ሐሳብ የያዙ ደብዳቤዎች ፃፉ። ራስ አበበ ለጄነራል ናዚ የፃፉት ደብዳቤ በሞረት፣ በጅሩ፣ በተጉለትም በኩል በደረሰው አደጋ የተነሳሳውን ሕዝብ ለማብረድ ተጨማሪ ጊዜ እንደሚያስፈልግ ገልፆ፣ የመሐላው ቀጠሮ እንዲተላለፍ የሚጠይቅ ነበር። እሱም በበኩሉ የቅኝ ግዛት ሚኒስትር ችሩዚ ወደ አዲስ አበባ እንደጠሩት ይገልፅና፣ እመጨረሻው ድረስ በሰላም እንዲጠብቁት የሚጠይቅ ነበር። ነገር ግን እሱ እንዳለው አልሆነም። እርቁ ፈረሰ። ራስ አበበም በየቀኑ ይወተውታቸው ለነበረው ለሻለቃ ዶሚኮ ለኮቲ ቁርጠኛ መልስ ሰጡት። ለአርበኞቹም መመሪያ አስተላለፉ።

ለሻለቃ ለኮቲ በቁጥር 200 በፃፉለት የእርቅ ማፍረሻ ደብዳቤ፣ እሱ ቀደም ብሎ የካቲት 12 ቀን የፃፈላቸውን ደብዳቤ ይጠቅስና፣ በቀጥታ ወደ ጉዳዩ ይገባል። እንደ ወትሮው ሰላምታ አያቀርብም። ስለእርቁ መፍረስ ሲያብራራ "...በከንቱ የፈሰሰው የወንድሞቻችን ደም ተመርምሮ እውነተኛውን ነገር ከተረዳችሁት በኋላ ስለሞቱት /ስለተጐዱት/ ሰዎች ገንዘብ ተቀበሉ ብላችሁ የፃፋችሁልን ቃል በጣም ያሳዝናል። ስለዚህ ደማችንን ለገንዘብ የማንለውጥ መሆናችንን እንገልፃለን..." ካለ በኋላ ጥንቱንም የተፈራው ትክክለኛ ፍርድ እንዳይጐድል እንደነበር ገለፁ። በመጨረሻም መልእክታቸው "...የእነዚህ ወንድሞቻችን ሞት ፍርድ በሚገባ እስኪፈፀም ድረስ...ጄነራል ናዚ እንዳይመጡ" በማለት አስታውቀው፣ ነገሩን ራሱ ጣልያን ላይ ደፈደፉት። እነዚህ ወንድሞቻችን የሚሉት በጠላት ተይዘው ከነሰዎቻቸው በጥይት የሞቱት ቀኛዝማች አድማሴ ማገጃንና ባላምባራስ ተምትምን ነበር። ምንም ፊታውራሪ ዳርጌ ጐርጂ የሞቱት በእርቁ ወራት ቢሆንና፣ ጦርነቱም የተቀሰቀሰው የጠላት ጦር ያለፈቃድ በአርበኞች ክልል ሲዘዋወር በተነሳ ግጭት ቢሆን፤ የሞቱት በጦር ሜዳ ላይ ስለነበር ክርክር አልቀረበበትም። "ጄነራል ናዚ እንዳይመጡ" ያሉት ደግሞ ጠልፈን መሳቂያ እናድርገው እያሉ ከሚጐተጉቱአቸው ለመገላገል፣ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኋላ መጥቶ አንዳች ነገር ቢደርስበት ጥፋቱ የሱ ራሱ እንደሚሆን ለማብሰር ሳይሆን አልቀረም። ይህ ደብዳቤ እንደደረሰ ጳጳሳቱና ካህናቱ ጽላታቸውን አንስተው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

የእርቅን ጉዳይ በዚህ ከጨረሱ በኋላ ለአርበኞች ከባድ ማስጠንቀቂያ ሰጡ። የማስጠንቀቂያውም ቃል "ይህ የፖለቲካ ትግል ሲፈርስ ከባድ ጦርነት እንደሚሆን አምናለሁና ለመሥዋዕትነት ዝግጁ ለመሆን መሣሪያችሁ ከእጃችሁ ሳይለይ ታጥቃችሁ ጠብቁ" የሚል ነበር።[34]

እሳቸውም እርቁ ይካሄድበት የነበረውን ማህበረ በኩርን ትተው ወደ ጌልጌላ ወረዱ። አርበኞችም የቅርቡ እየተመካከረ፣ የሩቁ እየተላላከ ዝግጅቱን



ቀጠለ። ከምስሌ አገር ምርኮ በሰላም በመለቀቁ የምሥጢር ግንኙነት መሥርቶ የነበረው መቶ አለቃ ክርያ የተባለው ጊና አገር የነበረ ኢጣልያዊ መኰንን መጋቢት 6 ቀን 1932 ዓ.ም እርቅ መፍረሱን የሚገልፅ መልዕክት ላከ። በዚያው ቀን ማታ እሱ ራሱ ጭብጦ ማርጊፊያ ድረስ መጥቶ በአንድ ሰዓት ላይ አንድ ካርታ የመትረየስ ጥይት በሦስት ትንፋሽ በመተኮስ ርችት አሰምቶ ጊና አገር ገባ። የመልእክተኛው ቃልና የመትረየሱ ምልክት አንድ ሆነ። የእርቁ መፍረስ በአርበኛው ዘንድ ታመነ። እርቅን ተጠይፎ የነበረው ወገን ደስ አለው።

ጣልያኖች ሰላም በመፍጠር ሊያገኙት አቆብቁበውበት የነበረው ጥቅም በእርቁ መፍረስ ምክንያት ቀረባቸው። እርቁ ቢፀና ኖሮ፤

1ኛ. ሰላም መሥርተናል በማለት በአውሮፖ ለሚያናፍሱት የሀሰት ወሬ ማረጋገጫ ያገኙ ነበር።

2ኛ. ወታደሮችን በማሰናበት ለጦርነቱ ያወጡት የነበረውን ከፍተኛ ገንዘብ ከልማት ሥራ ላይ ለማዋል ይችሉ ነበር።

3ኛ. ከኢትዮጵያ የእርሻና የማዕድን ሀብት ወደ ሀገራቸው የማጋዝ ዕድላቸው ጠንካራ ይሆን ነበር።

ይህና ሌላውም ከሰላም ጋር ለእነሱ በኩል ይገኝ የነበረው ጥቅም ሁሉ ቀረ።

ከዛ በኋላ ጄነራል ናዚ አርበኞቹን እንዲያወድሙለት ጥሩ ትጥቅ ያላቸው የጣልያን ወታደሮች አሰማራ። ለወታደሮቹም መጋቢት 6 ቀን 1932 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጠ። ከጣልያን መንግሥት የቅኝ ግዛት ምክትል ሚኒስትር ከጄነራል ቲሩሲ የተቀበለውን ጥብቅ ትዕዛዝ አሳትሞ በአይሮፕላን በተነ። ማስታወቂያውም የጣልያን ኃይል ሁሉንም ለመልቀም የሚችል አስመስሎ፤ ተገዥነታቸውን ለገለጡ ሰዎች ሁሉ የሕይወት፣ የነፃነት፣ የሀብት ጥበቃ ስለሚደረግላቸው በፍጥነት ለጣልያን እንዲገቡ የሚመክርና ከግንቦት 7 ቀን በኋላ በጦርነቱ እየበረታና እየተጫነ እንደሚሄድ የሚያስረዳ ነበር። ፈሪ ተንደርድሮ ከምሽግ ገባ።

በአርበኞች ዘንድ ምክር ተደረገ። ፉከራና ቀረርቶ፣ ድንፋታ የበዛበት፣ እልህ ያየለበት ምክር ነበር። ሠራዊቱ የሀገሩን ጥፋት፣ የወገኑን ውርደት ከማየት ሞቱን የመረጠ መሆኑን በአዲስ መንፈስ እንደገና አረጋገጠ። የጦር ሥልትን በተመለከተ ፊት ለፊት መግጠም ሳይሆን ሠራዊቱ እየተከፋፈለ በሚያውቅ በሚያውቀው ቦታ ዳዋ እየለበሰ፣ ቋጥኙን መከታ እያደረገ፣ በየወንዙ በየተራራው ሊዋጋ ተስማማ።

የጠላት ጦር በምድር፣ በሰማይ እያስገመገመ መጣ። ብዙ ፎክሮ ነበርና ጠንካራ ጡንቻ ማሳየት ነበረበት። ከአንኮበር እስከ ኮረማሽ፣ ከዚያም እስከ ምንጃር አፋፍ አሥራ ሦስት ክፍለ ጦር አሰለፈ። ጦሩም በጠቅላላው ከሁለት መቶ ሺህ ያላነሰ ሲሆን ግማሹ ከሊቢያ፣ ከሶማልያና ከኤርትራ ቅኝ

ግዛቶች ተመልምሎ የሠለጠነና ከኢጣልያን አገር የመጣ ደንበኛ ወታደር ነበር። ሌላው ግማሽ ከኢትዮጵያ ውስጥ ተመልምሎ የሠለጠነ ባንዳ ነበር። ጦሩ የተሰበሰበው ከሐረር፣ ከጂማ፣ ከወለጋ፣ ከጐጃም፣ ከምንጃር፣ ከትግሬ፣ ከወሎና ከሸዋ ልዩ ልዩ ክፍል ነበር። በብዙ ጣልያናውያን ጄነራሎች፣ ኰሎኔሎችና መኰንኖች የሚመራ ነበር። ዓላማው ክረምቱ ከመግባቱ በፊት አርበኞቹን ጨርሶ ሀገር ሰላም ማድረግ ነበር። ጦርነቱ መጋቢት 10 ቀን 1932 ዓ.ም ተከፈተ። የጠላት ወታደር በረድፍ ፣ በረድፍ ቡልጋ ገብቶ ይርመሰመስ ጀመር። ሠላሳ አይሮፕላኖች በየተራ ሀገሩን እየዞሩ ደበደቡ።

አንድ ክፍለ ጦር ብዙ ባንዳ አስከትሎ በኰሎኔል ሎሬንሲኒ እየተመራ በራስ አበበ የሚመራውን ጦር ለማጥቃት ወደ ጌልጌላ ወረደ። እሳቸውም የወሰልን ጉራ ይዘው ተዘጋጅተው ጠበቁት። በመጋቢት ወር መጨረሻ አካባቢ 1932 ዓ.ም ታላቅ ጦርነት ተደረገ። የጠላት ጦር የተሰለፈው በአራት አቅጣጫ ከበባ አድርጐ ነበር። ውጊያው ከጥዋቱ አራት ሰዓት እስከ ምሽቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ተካሄደ። የጠላት ጦር እንደቅጠል ረገፈ። አርበኞች ጉዳት አልደረሰባቸውም፤ አንድ ሰው ብቻ ቆሰለባቸው። የሐረርጌው የጠላት ጦር፣ የሶማሌን ወታደር ይዞ በተሰለፈበት ወገን እሩምታ በመተኰስ አርበኞች ከበባውን ሰብረው ወጡ። የአዋሽን ወንዝ በመከተል አርባ ወደሚባለው ቦታ ተዛወሩ። የአፋር ሕዝብ ስንቅ ሰጣቸው። መክርም ለገሳቸው።[35]

በሙገሬ ዛላ የነበሩትን አርበኞች ለማጥቃት የመጣው ጦር፣ ቦምባርድ የተባለውን መሣሪያ ቁንጥሎ በልባ ከተባለው ተራራ ላይ ጠምዶ ከአለከሴ ጀምሮ ያለውን አገር፤ ማለትም:- ጭንቂትን፣ ሥላሴ ገዳምን፣ ጉርባ አገርን፣ ምስሌ አገርን፣ ሜጢንና አሰቤ አገር፣ ሰለሎን፤ ደበደበ። እግረኛም አከታትሎ ላከ። አርበኛው የቁሊሎን ተራራ ይዞ ተከላከለ። በምባርድ የተባለው መሣሪያ ወደ ሰማይ እየተተኰሰ ተራራውን ዞሮ (በስውር ኢላማ) የሚመታ በመሆኑ፣ የቁሊሎን ተራራ ምሥራቃዊ ገፅ ክፉኛ ደበደበው። አልተለመደም ነበርና ይህ አመታት አርበኛውን ለጊዜው አስደነገጠው። ነገር ግን እምብዛም ጉዳት አላደረሰም። አንድ ክፍለ ጦር ሜጢና ሰለሎ ገብቶ ሠፈረ። በዚህ ጊዜ አርበኞቹ ደጋ ወጥተው የገደሉን አፋፍ ዙሪያውን ከበው ይዘውበት ነበርና ከጭንቅ ውስጥ ገባ። ከአንድ ሣምንት ጭንቅ በኋላ በሦስት ረድፍ ተከፍሎ አንዱ ቀድሞውኑ በገባበት በሙገሬ ዛላ፣ ሁለተኛው በአሞሌ ገደል፣ ሦስተኛው በማይግደጊት ተንቃነቀ። አርበኞች በየቦታው በጥይት በመደብደብ ብዙ ምርኮ አገኙ።

ከደብረ ብርሃን፣ በሾላ ገበያ በኩል ጭቃ ቆላ የወረደው፣ ከናዝሬት (ከአዳማ) በምንጃር በኩል አድርጐ ተድላ ማርያም የተሻገረው የጠላት ጦር፣ በዚያ በነበሩ አርበኞች ላይ ጥቃት ለማካሄድ ሞከረ። ነገር ግን በከንቱ እየተደበደበ ምንም ፋይዳ ሳያገኝ፣ ያለቀው አልቆ፣ የተረፈው አገሩን አይቶ ተመለሰ።



በራስ አበበ መሪነት አዳል አገር የወረደው አርበኛ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴን መምጣት አልፎ መሐመድ ከተባለ የአዳል ባላባት ሰሙ። ምንም የአዳል ሕዝብ እርዳታ ቢያደርግላቸው ከሰው ብዛት የተነሣ ችግሩ ሊቃለል ስለአልቻለ ወደ ደጋው አገር፣ ወደ አንኮበር መውጣት አስፈለገ። ከልዩ አምባ አካባቢ ሲቃረቡ ጓዝ ከዚያ እንዳይቀር፣ ደረቅ ጦር አንኮበር ወጥቶ ምሽጉን በመምታት ስንቅ እንዲያመጣ ታሰበ። ራስ አበበ መሪ ሆነው ወደ አንኮበር ወጡ። ይህንን ሁኔታ ጠላት በስለላ ስለደረሰበት፣ በጓዝ ላይ አደጋ ጣለ። ከጥዋቱ አሥራ ሁለት ሰዓት ለጥቂት ሰዓት እንደተዋጋ፣ አመጣጡ ያለብዙ ተቃውሞ ጓዝ ለመማረክ ስለነበር ተኩሱን አቁሞ እየበረረ ሄደ።

ጓዝ ይጠብቅ ከነበረው አርበኛ የሸሸው የጠላት ጦር ሌላ የአርበኛ ሠራዊት ከአለበት ቦታ ደረሰ። ተኩስ ሲካሄድ ፊታውራሪ ደስታ ሸዋርካብህ ጦር ይዘው ደረሱና ወደ አንኮበር ዘልቆ፣ ወደዚያ በዘመተው ሠራዊት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ አገዱት። እውቅ አርበኞች ቢወድቁም፣ እዚያው እነበሩበት ቦታ አሳደሩት። በዚህ ጦርነት ወይዘሮ አስካለ ጐበና፣ የራስ አበበ እናት ከጥቂት ጓዝ ጋር ሲማረኩ፣ ምራቲቱ ወይዘሮ ቆንጂት በጀግንነት በመከላከል በአጠገባቸው የነበሩትን አራት ከባድ የውሃ መትረየሶች በጠላት ከመማረክ አዳኑ።

ራስ አበበ ደግሞ በጓዛቸው ላይ የተካሄደውን ጦርነት ሰምተው በግስጋሴ ሲመለሱ ከመንገድ ላይ ሌላ ጦር አገኙ። እሱንም አሳሩን አሳይተው ጓዝ ከነበረበት ቦታ ደረሱ። በአደጋው ምክንያት የተበታተነውም ሠራዊት እንደገና ተሰብስቦ ትግሉን ቀጠለ። ለጥቆም የምግብ ጉዳይ ችግር ፈጠረ። ስንቅ ለመፈለግ ወደ ዲቤ ተሻገሩ። ከዚያም ጌታ ገደል ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ጠላት ከበባ አደረባቸው። አርበኞቹም ግንባር ለግንባር ገጥመው በመዋጋት ከበባውን ሰብረው ወጡ።

የደብረ ብርሃንና የአንኮበርን ባንዳ ያስቀደመ የጠላት ጦር ዱቤ በተባለው ጋራ በኩል ተጠግቶ ሌሊት በአርበኞች ላይ አደጋ ጣለ። ጦርነት ተከፍቶ ከሌሊቱ አራት ሰዓት ሲሆን የጨበጣ ውጊያ ተገባ። እሱም በከባድ ሁኔታ ከተካሄደ በኋላ አርበኞች ወደ ከሰም በረሃ ወረዱ።

በዚህ ጊዜ ላይ ጠላት ሌሊት አደጋ የመጣል ዘዴ አመጣ። ጉዳትም ያደርስ ጀመር። አርበኛው በበኩሉ መክሮ ለዚህ ዓይነቱ የጦር ሥልት ማፍረሻ የሚሆን ዘዴ ሠራ። ሌሊት እንደወትሮው ሁሉ መተኛቱ ቀርቶ ገሚሱ ለመዋጋት የሚያስችለው መሣሪያ ታጥቆ ቃፊር እየሆነ በደፈጣ ተበታትኖ እንዲጠብቅ፣ ጠላት በመጣ ጊዜ በየቦታው እንዲፈጀው፤ ተኩስ በተሰማ ጊዜ ዋናው ሠራዊት በፍጥነት ተነስቶ በተበታተነ መንገድ ከጦርነቱ ቦታ ደርሶ ቃፊሩን ተክቶና ረድቶ እንዲዋጋ ተወሰነ። ውሎ፣ አድሮ ደግሞ አርበኛው ሠፈር አስመስሎ አንድ ቦታ እሳት እያነደደ ከዚያ እንደተኛ

በማድረግ ጠላትን ከቀለበት ውስጥ እያስገባ ቀጠቀጠው። ባንዳው በዚህ ሥልት ልቡ ቀለጠ። ጠላትም ብዙ ጉዳት ስለደረሰበት የቀኑንም፣ የሌሊቱንም ጦርነት ትቶ እየምሽጉ እየገባ ተከተተ።

ጣልያን ይህ አላዋጣ ሲለው፣ ጦርነቱን በአይሮፕላን ለማካሄድ አሰበ። አርበኞች ያሉበትን ቦታ በእግረኛ እያሰለለና በአይሮፕላንም እያስመረመረ ከረመ። በነሐሴ ወር 1932 ዓ.ም ከቀኑ 10 ሰዓት ሁለት የጠላት አይሮፕላኖች መጥተው ዝቅ ብለው በማንዣበብ ከመረመሩ በኋላ ወሌንሶ ከተባለው ቦታ ሁለት በርሜል መርዝ ጥለው ተመለሱ። መርዙም ሁለት ሰዎች ገደለ፣ አንድ ሌላ ሰው አቃጠለ። [36]

እርቅ ሲፈርስ ወዲያው የአርበኞችን ኃይል ለመደምሰስ ጣልያን የወሰደው እርምጃ ከንቱ ሆነ። ከዚህ ላይ ለወደፊት ተመራማሪዎች መነሻ እንዲሆን አንድ የተሰማ ወሬ መጥቀስ እወዳለሁ። በዚሁ ከተሰጡ ሪፖርቶች የተጠናቀረ ሪፖርት በዋናው አዛዥ በኩል ለሞሶሎኒ ይቀርባል። ይህ ሪፖርት ጦርነቱ እንደምን እንደተካሄደ፣ በእነማን እንደተመራ፣ ምን ያህል ጦር እንደተሰማራ፣ ምን እንደተሠራ፣ ምን ያህል ጊዜ እንደወሰደ፣ ምን ዓይነት መሣሪያ በሥራ ላይ እንደዋለ ከአስረዳ በኋላ ምክር ይለግሳል። ምክሩም ሽፍቶቹ ያሉበት አካባቢ የመሬቱ አቀማመጥ ወጣ ገባ በመሆኑ ለሽፍቶቹ የተመቸ መሆኑን አሳይቶ፤ ሽፍቶቹ ጥቂት መሆናቸውንና ቁጥራቸውም ከሃያ ሺህ እንደማይበልጥ ግምት ያቀርባል። እነሱም እየተዳከሙ በመሄድ ላይ መሆናቸውንና ከጊዜ በኋላ እንደሚጠፉ አስረድቶ፣ የኢጣልያን መንግሥት እነሱን ታግሦ በልማቱ ሥራ ላይ ቢያተኩር እንደሚሻለው ይጠቁማል። ነገር ግን ይህ ሐሳብ በሞሶሎኒ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝ፤ ሽፍቶቹን ለመጨረስ አስቀድሞ መሬቱን መደልደል ያስፈልጋል በማለት ሪፖርቱ አስተያየቱን ይደመድማል።

ሞሶሎኒ ይህንን ሐሳብ ከተመለከተ በኋላ በጉዳዩ “ለምን አትደለድሉትም ታዲያ” ብሎ ፃፈበት ይባላል። ምንም ወሬው ገና በማስረጃ ባይረጋገጥ፣ ሊናቅ አይገባውም። ለቀልድ የተነገረም እንኳን ቢሆን ሊጤን ይገባዋል። የኢጣልያ ሹማምንት ስለጦርነቱ ምን ያህል እንደተጨነቁና በሐሳብም እንደተለያዩ፤ በሞሶሎኒ ዘንድ ግን የአርበኞች ማለቅ የተቆረጠ ነገር እንደነበር ያሳያልና።

የ1932 ዓ.ም ትግል በዚህ ዓይነት ተከናወነ። መስከረም ጠባ። የ1933 ዓ.ም የማጥቃት ፕሮግራም ውሎ፣ ሳያድር ተጀመረ። የ1932 ዓ.ም ክረምት ለአርበኞች ችነፈር የተነሳበት፣ ረሀብ የፀናበት እና የሰውም ኃይል የተቀነሰበት፣ ፅኑ የመከራ ጊዜ ነበር። የሚቀጥለው ዘመን የእልቂት እንደሚሆን በማሰብ አንዳንዶች ቤተሰባቸውን በድብቅ ወደ አዲስ አበባና ወደ ሌሎች ከተሞች ላኩ። ይህም ተቀባይ ዘመድ፣ የኢጣልያን ባለ ሥልጣኖች ፈቃድ ስለሚያስፈልግ ቀላል አልነበረም።



በ1933 ዓ.ም የመጀመሪያው ጦርነት ሙገሬ ዛላ ላይ ተካሄደ። በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ የሚመራውን አርበኛ ለማውደም የታለመ ነበር። የጠላት ጦር በአንድ ጣልያናዊ መቶ አለቃ የሚመራ፣ በኤርትራ ተወላጅ ወታደሮች ያሉበትና ከአባባቢው በተመለመሉ ባንዶች የተሞላ ነበር። ከጊና አገር ምሽግ ሌሊት በመነሳት በቁንጥሎ፣ በልማ፣ በአለከሴ ወርዳ፣ ጭንቂት በነበረው አርበኛ ላይ በድንገት ደርሶ አደጋ ጣለበት። የሩረን አፋፍ የያዘው አሽቆልቁሎ በመተኮስ በመትረየስ አጠቃ። በጭብጦ ማርገፊያ የወረደው ደርሶ፣ የጀሎ አገርን በር ለመዝጋት አለመ። አርበኞች በብርታት ተከላክለው የፋሪ ተራራን የያዘውን ባላምባራስ /ግራዝማች/ ኃይሌ ዳርጌና ባልደረቦቹ በጥይት አባረሩት። በሰሉ የመጣውን የአቶ ደመና ከተማ ባልደረቦች ዳቦ ማርገፊያን ይዘው በጥይት አገዱት። ነገር ግን በጭንቂት የመጣው አጠቃ። ሰውንም እስከ ጉሣገር ፈረስ ማሻ ድረስ አባረረው። ከአርበኞቹ ወገን አንድ ሰው ሞተ፤ ጥቂቶች ቆሰሉ። የፊታውራሪ ወልደፃድቅ ባለቤት ወይዘሮ በልዩ ብሩ ከሁለት ልጆቻቸው ጋር ተማረኩ። ከጠላትም ጥቂት ወታደር ሞተ፤ ቆሰለም። ነገር ግን እምብዛም አልተጐዳም።

ጣልያን ወዲያው አከታትሎ ለፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ መልእክት ላከ። መልእክቱም እጅህን ካልሰጠህ ልጆችህንና ሚስትህን እጨርሳቸዋለሁ የሚል ነበር። ሞገደኛው ፊታውራሪ ወልደፃድቅ አላደርገውም አሉ። የሽማግሌ ምክር፣ የቄስ ግዝት የማይመልሳቸው ሆነ። ጠላት እንደአወቀ በምርኮኞቹ ላይ እሥር አፀና። ሰው እንዳያነጋግራቸው አድርጐ በአርበኞች ላይ የማጥቃት እርምጃ በተደጋጋሚ ወሰደ። ከቀን፣ ቀን ውጤት አገኛለሁ በማለት መስከረም 15፣ 23 እና 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተከታታይና ተመሳሳይ ጥቃት አካሄደ። ሰው በወረርሽኝ በሽታና በረሃብ ተዳክሞ ነበርና፣ ብዙ ጉዳት አደረሰ። ቢሆንም የአርበኛውን ኃይል ሊሠብረው አልቻለም።

ጠላት ጥቅምት 9 እና 22 ቀን 1933 ዓ.ም በዚሁ በሙገሬ ዛላ በሚገኘው የአርበኞች ቡድን ላይ የከፈተው የማጥቃቱ ሥራ በጣልያናውያን የሚመራ ቢሆንም፣ የሀገር ውስጥ ፖለቲካ ጎረስ ሆነ። ሁሉም ጠላቱን በዚያች ቀውጢ ቀን ለመገላገል ሞከረ። ሂደቱም በከፍተኛ ደረጃ የተቀነባበረ ነበር።

የስንቅ ጉዳይ አሳሳቢ ሆነ፤ ነገር ግን የጊና አገርን ምሽግ ለመምታት የአርበኛው አቅም አልፈቀደም። ስለዚህ ጫሬ ላይ መሽጐ የነበረውን የባንዳ ቡድን እየመታ ስንቅ ደጋግሞ አገኘ። ይህም ሆኖ በቂ ስንቅ ማግኘት አልተቻለም። ዝም ማለት ደግሞ የአርበኛውን አቅም የሚቀንስ ሆነ። በጉዳዩ ተመከረ፤ እናም የአርበኞች አቅም የተቀነሰ መስሎት የተዘናጋውን የጫጫን ምሽግ ለመምታትና ለመዝረፍ ተወሰነ።

አንድ ቡድን ተመርጦ ከሙገሬ ዛላ በመንቀሳቀስ በሙጣማያስ፣ በገርም አድርጐ በህዳር በመጀመሪያው ሣምንት 1933 ዓ.ም ከጫጫ ምሽግ

በመግባት አተራመሰው። ብዙ የጠላት ወታደር ገድሎ፣ ብዙ ስንቅ ማርኮ ከብት ነድቶ መጣ። ገበሬው ተከታትሎ እህልና ገንዘብ ስለአቀረበ አርበኛው በዚያ አገገመ። ይኽ በምሽጎች ላይ የተጣለው አደጋ፣ ጥቂት ጣልያኖችን እና ሀማሴኖችን እየተከተለ የሚያረተርተውን ባንዳ አስቀመጠው።

ጠላትም በበኩሉ እርምጃ ወሰደ። በዚሁ ሙገሬ ዛላ በነበረው አርበኛ ላይ ህዳር 8 እና 23 ቀን 1933 ዓ.መ ዘመተ። ነገር ግን በሱ በራሱ ባሰው፤ ብዙ ወታደር አለቀበት እንጂ አርበኞች አልተጎዱም።

ከዚህ በኋላ የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት በይፋ እየታወቀ ሄደ። ነገር ግን የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ታወቀም ጣልያን አርበኞችን ለማውደም ከሚያካሂደው እርምጃ አልተገታም። ታህሣሥ 9 ቀን 1933 ዓ.ም በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ዘውዴ በሚመራው አርበኛ ላይ ከጊና አገር በመንቀሳቀስ ዘመተ። በዚህ ወራት የያዘው ፊሊፕ የውሎ ገባ ዘመቻ ማካሄድ ነበር። ቢሆንም በዚህ ዘመቻው ምንም ያህል ውጤት አላገኘበትም። ጥቂቶችን ገደለ፣ ሌሎችን አቆሰለ። ነገር ግን ከእሱ በኩል የወደቁት የወታደሮቹ ቁጥር ይበዛል።

ሁኔታው በእንዲህ እንዳለ ታህሣሥ 10 ቀን 1933 ዓ.ም ቡልጋ፣ በረከት በአርበኞች መካከል በተነሣ የርስበርስ ግጭት ጉደት ደረሰ። ረሀብ ፀንቶ ነበርና አርበኞች በአካባቢው የተገኘውን አንድ በሬ ለማረድ ፈለጉ። ባለቤቱ አቶ ዝናዬ በሬው እንዳይታረድበት ተከራከረ። የበሬው መታረድ አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ፣ ለእሱና ለቤተሰቡ ድርሻ እንዲኖራቸው ተወስኖ እንዲታረድ ተስማማ። ነገር ግን ድርሻውን ሳይሰጡት ስለቀሩ በተነሣው ጠብ ፊታውራሪ አጐናፍርን፣ ፊታውራሪ ተክለ ሃይማኖትንና ባሻ ባዩን ከሌሎች ስደስት አርበኞች ጋር ፈጃቸው። በአንድ ሽንጥ ሥጋ ምክንያት ዘጠኝ ጀግኖች መውደቃቸው ያሳዝን ወይም ያሳፍር ይሆናል፤ ግን የተፈፀመ ነውና መፃፍ አለበት።

ለሌላው አገር ሕዝብ እንደተደረገው ሁሉ፣ ለሸዋም ሕዝብ ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ህዳር 9 ቀን 1933 ዓ.ም አዋጅ መጣለት። ለጠርጣራው ለሸዋ ሕዝብ የወጣው አዋጅ ለሌሎች ክፍላተ ሀገር ከተነገረው ለየት ያለ ነበር። ለሌሎች ክፍላተ ሀገር እንደተሰጡት አዋጆች ሁሉ ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች በማለት ይጀምርና "... ቢዘገይም... የእንግሊዝ መንግሥት" የሚያደርግልን ዕርዳታ ሲፈፀም ታያላችሁ። ስለዚህ ጥርጥር ሳታገቡ በትዕግስት ጠብቁ..." ይላል። ይህ ብቻ አይደለም። በሸዋ አእምሮ ሲንከባለሉ የኖሩ ሌሎች ጥያቄዎችንም ያወሳል። በመቀጠል "...ከእንግሊዞች ጋር በመሆን በሃይማኖቴም ፀረ ማርያም የሆንኩ አይምሰላችሁ። የእኔ ሃይማኖት የተዋህዶ ሃይማኖት ነው..." ይልና ወደ ፖለቲካ ጉዳይ ይሻገራል። አዋጁ ለበቀል ስለሚያገለግሉ ከሀድያንም ይናገራል። "...ስለኢትዮጵያ ጥቅም ነው እያሉ ለባዕድ የሚያገለግሉት..." ይልና ስም ከዘረዘረ በኋላ "...ያለ



አንዳች ርህራሄ የተገባቸውን ቅጣት እንሰጣቸዋለን" ይላል። ይህ ብቻ አይደለም፤ ንጉሠ ነገሥቱ ስለራሳቸውም ጭምር ይናገራሉ። "...ስለኢትዮጵያ ጥቅም ነው የሚሉትስ ንጉሥዋን ከአጣች በኋላ ኢትዮጵያ ምን ጥቅም ለማግኘት ልትችል ነው?" ብሎ ይጠይቃል።

አዋጁ በአይሮፕላን ስለተጣለ ውሎም ሳያድር ከአርበኛው እጅ ገባ። ይህንን ያህልም ተብሎ፣ ሸዋ በአዋጁ የተነገረውን አላመነም። ከጥቂት የንጉሠ ነገሥቱ የቀድሞ ባለምዋሎች በስተቀር ዋናው አርበኛ ለብዙ ጊዜ ምላሽ አልሰጠም። ይህም ንጉሠ ነገሥቱ የካቲት 7 ቀን 1933 ዓ.ም ከቢልያ የጦር ሠፈራቸው ለአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ከፃፉት ደብዳቤ ለመረዳት ይቻላል። ደብዳቤውም "...የራስ አበበ ደብዳቤ ብቻ ሳይደርሰን በመቅረቱ ለልባችን እንቅፋት ሳይሆን አልቀረም..." ይላል።[37]

በንጉሠ ነገሥቱና በራስ አበበ አረጋይ መካከል የነበረውንም ሁኔታ ማጤን ይገባል። አርበኞቹን በመወከል ሦስት ሹማምንት ለንጉሠ ነገሥቱ ታህሣሥ 20 ቀን 1931 ዓ.ም ደብዳቤ ፃፉ። ሁኔታዎችን ከገለፁና ለእሳቸው ያላቸውን ታማኝነት "አርበኞች" በማለት ከአረጋገጡላቸው በኋላ ፀሐፊዎቹ ስማቸውን ሲዘረዝሩ፣

አርበኞችም ራስ አበበ አረጋይ

ደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ

ፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራን ብለው ፈርመዋል። ንጉሠ ነገሥቱ ከለንደን ታህሣሥ 27 ቀን 1931 ዓ.ም በፃፉት መልስ የሰጡአቸው ማዕረግና ተራ፣

ይድረስ ከደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ

ከፊታውራሪ ዘውዱ አባኮራን

ከባላምባራስ አበበ አረጋይ የሚል ነበር። የሥራ ፕሮግራም የተሰጠው ለነደጃዝማች መንገሻ ወሰኔ የተላከ ተብሎ ነበር። ሌሎች ከቁጥር አልገቡም። ንጉሠ ነገሥቱ ይህንን ሁኔታ ያስተካከሉት ሰኔ 20 ቀን 1931 ዓ.ም በፃፉት ሌላ ደብዳቤ ነው። ከዚያ መጤን የሚገባው ዘውዱ አባኮራን በታህሣሥ 20ው ደብዳቤ ከንጉሠ ነገሥት መልእክ ፀሐይ እያሉ ተቀብለውት የነበረውን የደጃዝማችነት ማዕረግ በፈቃዳቸው ለቀው ራሳቸውን እንደገና ወደ ፊታውራሪነት ማውረዳቸው ነው።[38]

በራስ አበበ የሚመራው አርበኛ እንደገና ወደ በረከት፣ ከዚያም ወደ ሰጠን ሄደ። ጠላት ታህሣሥ 3 ቀን 1933 ዓ.ም አብራም አረዳ ከተባለው ሥፍራ ከበባ አድርጎ ሊያጠቃው ሞከረ። አርበኛው ያለብዙ ችግር ከበባውን ሰብሮ አመለጠ።

ታህሣሥ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ሠላሳ የሚያህሉ ወታደሮች ከጠላት ከድተው ከራስ አበበ ሠራዊት ጋር ተቀላቀሉ። የጠላት ጦር እየተዳከመና እየተረታ መሆኑን ነገሩ። መሐመድ ጁባር የተባለውን ቀንደኛ ባንዳ አሥረው

ወደ ጭሣ ወሰዱት። ጠላት በአይሮፕላን ያካሄደው ድብደባ፣ በእግርም ያካሄደው ጦርነት አላገዳቸውም። ጭሣ ጀሎሌ እስከተባለው ቦታ ድረስ ቢመጣ አርበኞቹ ታህሣሥ 21 ቀን 1933 ዓ.ም ወጉት። ብዙ ጉዳት አደረሱበት። በእነሱ ላይ ግን እምብዛም ጉዳት ሳይደርስባቸው የሠራውን ከበባ ሠበሩበት።[39]

በዚሁ በታህሣሥ ወር 1933 ዓ.ም ሙገሬ ዛላ የነበረው አርበኛ የወጨብያን ምሽግ ሁለት ጊዜ መታ። የመጀመሪያው ዘመቻ ጥሩ ውጤት ሰጠ። ስንቅ በብዛት ተገኘ። ሁለተኛው ግን እንደ መጀመሪያው ቀላል አልነበረም። ጠላት በጥንቃቄ ጠብቆ ኖሮ በአርበኞች ላይ መጠነኛ ጉዳት አደረሰ። ቢሆንም ስንቅ ተገኘ። የተፈለገውም እሱ ነበር። ቅጥቃጤ ስለበዛበት አርበኛው ሙገሬ ዛለን ትቶ ፋሪ ዳዊት አገር አፋፍ ወጥቶ ሠፈረ። ከዚያ እንዳለ ንጉሠ ነገሥቱን እንዲቀበል ትዕዛዝ ስለደረሰው ወደ ደብረ ብርሃን ሄደ ከዚያም ወደ ሰላሌ ተጓዘ። አርበኞችን የማጥፋት ሙከራው ባልተቃናለት ጊዜ ጣልያን ሕዝቡን በአርበኞች ላይ ሊያስነሳባቸው ሞከረ። በጥር ወር 1933 ዓ.ም በሙገሬ ዛለ አካባቢ ወረቀት በተነ። ወረቀቱም ታዋቂ አርበኞችን ማርኮ ላመጣ፣ ወይም ጭንቅላታቸውን ቆርጣ ላቀረበ ምን ያህል ገንዘብ እንደሚከፈል የሚያመለክት ነበር። ነገር ግን ሕዝቡ አልተቀበለውም። ስለዚህ ያንኑ ጦርነት ቀጠለ።

በራስ አበበ የሚመራው ቡድን ጥር 16 ቀን 1933 ዓ.ም ሳለ ጻናጭሬ ከተባለው ቦታ ከጣላት ጋር ተዋጋ። ከዚያም በኋላ ጥር 25 ቀን 1933 ዓ.ም እምቡር ማጭዶ ላይ ጠላት በሦስት አቅጣጫ ከበባ አድርጐ ለማጥቃት ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ወታደሩን ከማስጨረስ በስተቀር አንዳችም ውጤት አላገኘበትም።[40]

በሙገሬ ዛላ ግንባርም እንደዚሁ ጥቃት አካሄደ። ጥር 8 እና ጥር 23 ቀን 1933 ዓ.ም ከጊና አገር እየተነሣ የውሎ ገባ ዘመቻዎች አካሄደ። በዚህ ጊዜ አርበኛው ከወረርሽኙ በሽታ አገግሞ፣ ምግብም አግኝቶ ነበርና ጠንክሮ ተዋጋ። እሱ በጠላት ላይ እንጂ፣ ጠላት በእሱ ላይ ጉዳት አላደረሰበትም።

ራስ አበበ ወደ አገር ተመልሰው ሳለ በጥር ወር 1933 ዓ.ም ስለ ንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ከአዛዥ /ደጃዝማች/ ከበደ ተሰማ ለራስ አበበ የተፃፈ ደብዳቤ ደረሰ። ደብዳቤውም ቀደም ብለው ከኢየሩሳሌም ፅፈውላቸው የነበረውን ይጠቅስና "...አሁን ግን ይህንን ቃል የምፅፍልህ ግርማዊ ጃንሆይ ተሰደው ሲደክሙበት የነበረው ጉዳይ ስለተፈፀመላቸውና አገራቸው ድንበር ስለደረሱ ለኢትዮጵያ አርበኞቹ ሁሉ...የአዋጅ ቃል ለመናገር ተልኬ ስለመጣሁ ጉጃም መሬት ላይ ሆኜ ነው..." የሚል ነበር።[41] በአርበኛው ዘንድ ደስታ ሆነ። ሁሉም የደስታ ተኩስ ሲተኩስ ዋለ።

የንጉሠ ነገሥቱ መምጣት ሲሰማ፣ የጣልያን ጦር ከየተሠራጨበት ወደ ጠንካራ ምሽጐች መሰብሰብ ጀመረ። በረከት ያለው ማሕሙድና ጂፋር



በተባሉት ታናናሽ ምሽጐች ተሰብስቦ ወደ ዋናው ወደ ሳይሰች ምሽግ ገባ። ወሊብያና የነበረው፣ ሾላ ገበያ ተከተተ። ከስድስትና ከሾላ ገበያ ደግሞ ጊና አገር ተጠራቀመ። የመሶቢቱም እንደዚሁ ከአደረገ በኋላ፣ በሕዝብ ዘንድ ተሰሚነት የነበራቸውን ሰዎች በካቴና እጆቻቸውን ከርችሞ አሥሮ በቁልፍ በመቆለፍ፣ መሣሪያ ከተቀመጠበት መጋዘን ውስጥ ዘግቶ እሳት ለቅቆባቸው ከጊና አገር ወጥቶ መጋቢት 28 ቀን 1933 ዓ.ም ወደ ደብረ ብርሃን ሄደ።

በዚህ ወቅት ጠላት ዘዴ ብሎ የያዘው የከበባ ጦርነት ነበር። በራስ አበበ አረጋይ ከሚመራው የአርበኛ ሠራዊት ጋር የካቲት 4 ቀን 1933 ዓ.ም ዱቤ ላይ፣ የካቲት 29 ቀን 1933 ዓ.ም እምቡር ሥላሴ ላይ ጦርነት ተደርጐ በጠላት ላይ ጉዳት ደረሰ። አርበኞች እምብዛም ሳይጎዱ ወደ በረከት መሲል ሄዱ።

ሙገሬ አካባቢ ባሉት አርበኞች ላይ የካቲት 5 እና 13 ቀን 1933 ዓ.ም ጠላት ዘመቻ አደረገ። በተለይ የየካቲት 13 ቀኑ ውጊያ ከባድ ነበር። አርበኞች በጉርባ አገር፣ በምስለኔ አገር፣ በቅጭንፍር፣ በጭንቂት፣ በአለከሴ በጥይትና በእጅ ቦምብ ደበደቡት። ጠላት ቢሸሽም አላመለጠ። በየቀኑ የጦርነት ንዝንዝ ያሰለቸውና የነፃነት አየር የሸተተው የአርበኛ ሠራዊት ሴት ወንዱ፣ ልጅ አዋቂው ወጥቶ ቀጠቀጠው። በዚህ ግንባር ይህ ጦርነት የመጨረሻው ሆነ። ከመስከረም 7 ቀን 1933 ዓ.ም ጀምሮ 13 ጊዜ የዘመተው የጠላት ጦር ሌላ እንቅስቃሴ አላደረገም። እግዚአብሔር ይክበር ይመስገንና፣ በፊታውራሪ ወልደፃድቅ ለምንመራው አርበኞች፣ እንደ ሕማማተ መስቀል የሆነብን፣ በዘመኑ 13ኛው ጦርነት፣ የካቲት 13 ቀን 1933 ዓ.ም አከተመ፤ እኛም ዳንን።

በራስ አበበ የሚመራው ቡድን መጋቢት 12 ቀን 1933 ዓ.ም እምቡር ሥላሴ ከጠላት ጋር ተዋጋ። ጠላት በሁሉም በኩል ከቦ ስለነበር ጦርነቱ ወሳኝ ነበር። አርበኛው ቀኑን ሙሉ ሲዋጋ ውሎ ከሌሊቱ በአንድ ሰዓት ሰብሮ ወጣ። ስምንት አርበኞቹ ሞቱ፤ አምስት ቆሰሉ፤ ሌሎች ሰባቱ ተማረኩ። ከዚያም አርበኞች ወደ ደቤ ተሻገሩ። በጠላት ላይ ብዙ ጉዳት ደረሰ። ለመቁጠር ጊዜ አልነበረም። ከዚህ በኋላ ለመዋጋቱ ማስረጃ አልተገኘምና፣ ይህ ጦርነት በራስ አበበ ለሚመራው ቡድን የመጨረሻው ሳይሆን አልቀረም። በቡልጋ የአምስት ዓመት ትግል በእንዲህ ተጠቃለለ።

ዋናው የቡልጋ አርበኛ በሸንኮራ፣ በጨፌ ደንሣ አድርጐ ንጉሠ ነገሥቱን ለመቀበል ወደ ሰላሌ ሄደ። ሌላውም በየአቅጣጫው ወደዚያው አመራ። በፊታውራሪ /ኮሎኔል/ ተረፈ የሚመራው ቡድን ሰንዳፋን ከጠላት አስለቅቆ ያዘ። ሁሉም ንጉሠ ነገሥቱ አዲስ አበባ በገቡበት ቀን በሚያዝያ 27 ቀን 1933 ዓ.ም በተደረገው ሰልፍ በታላቅ ግርማ ተሳተፈ።

# ማጣቀሻ ፅሑፎች

1. ጳውሎስ ኞኞ፣ *አጤ ምኒልክ*፣ ገጽ 355፡፡
2. እንሸፍት ማለት ለሀገር እንክላከል፣ እንመን ማለት ደግሞ ለጣልያን እንግባ ማለት ነበር፡፡
3. ከኤርትራ፣ ከሊብያና ከሱማልያ የመጣ ነበር፡፡ የቅኝ ግዛት ወታደሮች የሚለውን ምዕራፍ ይመልከቱ፡፡
4. ከሃምሣ አለቃ የላቀ ጌታነህ የተነገረኝ፡፡
5. ከቀኛዝማች ምስካይ ሥዩም ተክሌ በወቅቱ በአርበኞች የተነገረኝ፡፡
6. ከአቶ ሞላ ገዝሙ የተነገረኝ፡፡
7. ጳውሎስ ኞኞ፣ ገጽ 173-179፡፡
8. Greenfield, P.222-238.
9. ዝርዝሩን በገጽ ላይ ይመለከቱታል፡፡
10. ፎቶግራፍን ይመልከቱ፡፡
11. ከመምሬ ደምሴ፣ አብዩ ሆይ ቁርሉስ የተነገረኝ፡፡
12. ከሀገሬ ሽማግሌዎች በ1963 ዓ.ም የተነገረኝ፡፡
13. አንዱ መምሬ ነሰበ የሚባሉ የድንጋይ ጥራ ጊዮርጊስ፣ ሌላው መምሬ አማረ የተባሉ የደመቆ ጊዮርጊስ ቄሶች ነበሩ፡፡ የቀሩትን የሰባቱን ስም ማግኘት አልቻልኩም፡፡
14. ከአቶ /ሻለቃ/ አሰፋ ወልደፃድቅ የተነገረኝ፡፡
15. ከባላምባራስ /ግራዝማች/ ኃይሌ ዳርጌ የተነገረኝ፡፡
16. ታደሰ ዘውልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 97-113 እና 125-128፡፡
17. ዝኒ ከማሁ፤ ገጽ 143-47፡፡
18. ከልሣን ወርቅ ተሰፋዬ የተነገረኝ፡፡
19. ታደሰ ዘወልዴ፣ገጽ 146፡፡
20. ከዲያቆን /አቶ/ ቀፀላ የተነገሩኝ፡፡
21. ታደሰ ዘወልዴ፤ *የአባላሽኝ ዘመን*፣ ገጽ 28-33፡፡
22. ታደሰ ዘወልዴ፤ *ቀሪን ገረመው*፤ ገጽ 146-8፡፡
23. ከሃምሣ አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ የተገኘ፡፡
24. ከቀኛአዝማች ገብረመስቀል ኃይሌ የተነገረኝ፡፡
25. ከፊታውራሪ ኃይሌ /ኃይለራጉኤል/ ወልደፃድቅ የተነገረኝ፡፡
26. ከአቶ ወልደፃድቅ ሽንቁጤ የተነገረኝ፡፡
27. ከወጣት /አቶ/ ንጋቱ ወልደዮሐንስ የተገኘ፡፡
28. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 133-135፡፡
29. ከመምሬ /አባ/ ደምሴ አብየ ወልደ ቁርሎስ የተነገረኝ፡፡
30. ከወጣት /ሻለቃ/ መልአኩ በቀለ የተነገረኝ፡፡
31. ፊለቀ ዳኜ፣ *አምስቱን የመከራ ዓመትና ፍፃሜውን አጭር ማስታወሻ*፣ ገጽ 25-36 እና ገጽ 46፡፡
32. ከመምሬ /አባ/ ደምሴ አብየ ወልደ ቁርሎስ የተነገረኝ፡፡
33. ፊለቀ ዳኜ፣ *5ቱ የመከራ ሰዓትና ፍፃሜውን አጭር ማስታወሻ*፣ ገጽ 45-51፡፡
34. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 182-188፡፡
35. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 189-193፡፡
36. ከበደ ተሰማ፣ *የታሪክ ማስታወሻ*፣ ገጽ 337-338 እና 362፡፡
37. ፊለቀ ዳኜ ፣ ገጽ 20-25፡፡
38. ታደሰ ዘወልዴ፣ *ቀሪን ገረመው*፣ ገጽ 300-301፡፡
39. ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 301፡፡
40. ዝኒ ከማሁ፡፡
41. ዝኒ ከማሁ፡፡